# በ

**በ** ከ “ቀ” ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**በ[1]___** 1.በስም መነሻ ላይ እየተቀጠለ ማድረጊያነትን የሚያመለክት ምእላድ:: *ተማሪው በብእር ይፅፋል::* 2. ተውሳከ ግሳዊ አገልግሎት የሚሰጥ ወይም የድርጊት ሁኔታን ለማመልከት የሚያገለግል ምእላድ:: *በኣስቸኳይ /በዝግታ/ ቀስ በቀስ*: 3. ቦታን፥ አቅጣጫን፥ ጊዜን፥... ከሚያመለክቱ ቃላት ጋር እየተጣመረ መስተዋድዳዊ ሃረግን የሚመሰርት ምእላድ:: *በጠረጴዛው ላይ /በወንዙ አጠገብ/ በቀኝ በኩል/ በዛሬው እለት::*

**በ[2]___**"ብ___"ን ተመ.

**በ[3]___**"ከ___"ን ተመ.

**በሃ** "ቡሃ"ን ተመ.

**በሃ በግ** "ቡሃ" ስር "ቡሃ በግ"ን ታመ.

**በሃ (ብሃ)ድንጋይ** ስ በቀላሉ ፍርክስክስ የሚል ነጣ ያለ የድንጋይ አይነት፤ ብክካ እየተባለም ይጠራል::

**በሀረ ሎሚ** "*በከረ" ስር "በኩረ ሎሚ"ን ተመ.

**በሀር** "*በከረ" ስር "በኩር"ን ተመ.

**በለለ** ግ 1. ተበላሸ፥ ጠፋ፥ መና ቀረ:: 2. ተሞላቀቀ፥ ቀበጠ፥ ጠባየ ብልሹ ሆነ:: 3. በነነ፥ በረረ::

**ብሉል** ቅ ከንቱ፥ መና፥ ብልሹ::

**በለሴ** ስ በወፍራሙ የተፈተለ፥ ሻካራና ዘክዛካ የሆነ የሸማ አይነት::

**በለስ** ስ 1. ኣዳምና ሄዋን በገነት ሳሉ የፈጣሪን ትእዛዝ ጥሰው ፍሬዋን ስለበሉ የተረገሙባት ዛፍ እንደሆነች የሚነገርላት በገነት የምትገኝ ዛፍ ስም:: 2. ቅጠሉ ነጣ ብሎ ሰፋ ያለ፥ ነጭ ፈሳሽ የሚወጣው የእፅዋት አይነት፤ ከዚህ እፅዋት የሚገኘው ፍሬም በለስ ይባላል::

**በለስ ቀናው / ኣገኘ** 1.ኣደን ሄዶ የሚፈልገውን ገድሉ ተመለሰ:: 2.ተሳካለት፥ ሆነለት፥ ጥሩ እድል አጋጠመው::

***በለሸ**

**ብላሽ** ቅ 1. የማይረባ፥ ከንቱ፥ ለቁም ነገር የማይሆን:: 2. ነፃ:: *ይህን ልብስ በብላሽ ሰጠኝ::*

**ብልሹ** ቅ የማይረባ፥ ከንቱ፥ ለቁም ነገር የማይሆን::

**ብልሽት** ስ እክል፥ ሳንካ፥ ጉድለት:: *ጺቃው ብልሽት ኣለው::*

**ብልሽት ኣለ** ግ ተበላሸ::

**ብልሽትሽት ኣለ** ግ 1.ፈፅሞ የተበላሸ፥ ጥቅም የማይሰጥ ሆነ::2. ኣመሉ፥ ጠባዩ መጥፎ ሆነ::

**ተበላሸ** ግ 1. ኣደፈ፥ ቆሸሸ:: 2. ተሰናከለ፥ እክል ኣጋጠመው:: *መኪናው ተበላሸ*: 3. ጠባዩ መጥፎ ሆነ:: 4. ከንቱ፥ የማይረባ፥ የማይጠቅም ሆነ:: 5.ያለጊዜው፥ ያለኣግባብ ሞተ:: *ያንን የመሰለ ጀግና ተበላሸ::*

**ኣበላሸ** ግ 1. ኣጎደፈ፥ ኣቆሸሸ:: 2. ኣሰናከለ፥ የማይሰራ እንዲሆን ኣደረገ:: 3. ጠባየ መጥፎ ኣደረገ:: 4.ከንቱ፥ የማይረባ፥ የማይጠቅም ኣደረገ::5.ያለጊዜውና ያለኣግባብ ገደለ፥ ኣጠፋ::

**በለቀጠ** ግ ሙሉ በሙሉ ከፈተ፥ በረገደ::

**በልቃጣ** ቅ (ነውር፥ ስድብ) 1. ሃፍረተ ስጋዋ እንዳይታይባት ጥንቃቄ የማታደርግ፤ በርጋዳ:: 2. ስነስርኣት የሌላት፥ የሰው አይን የማትፈራ፤ መንቃራ::

**ተበለቀጠ** ግ ተከፈተ፥ ተበረገደ::

**ተበላቀጠ** ግ ስነ ስርኣት ኣጣ፥ ተመናቀረ::

***በለበለ**

**ነበልባል** ስ 1.የነዲድ እሳት ጫፍ፥ ላንቃ፥ ልሳን:: 2. (ዘይ.) ለፍላፊ፥ ምላሰኛ::

**ተንበለበለ** ግ 1.በሃይል ነደደ፥ ተንቀለቀለ፥ ተንቦገቦገ:: 2.(ዘይ.) በፍጥነት ተናገረ፥ ለፈለፈ::

**ኣንበለበለ** ግ 1. በሃይል ኣነደደ፥ ኣንቀለቀለ፥ ኣንቦገቦገ:: 2. (ዘይ.) ያለ ምንም ችግር በፍጥነት ኣነበበ::

**በለተ** ግ ታርዶ ቆዳው የተገፈፈን እንስሳ አካል በመልክ በመልኩ እየለየ ቆረጠ፥ ገነጠለ፥ ከፈለ፤ ብልት ኣወጣ::

**መበለቻ** ስ ብልት ለማውጣት የሚያገለግል ቢላዋ፥ ካራ::

**በላች** ቅ ከብት አርዶ፥ ቆዳውን ገፎ፥ ብልቱን በየመልኩ እየለየና እየቆረጠ የማውጣት ሙያ ያለው፤ ኣራጅ፤ ብልት ኣውጪ::

**ብልት** ስ 1. እንደ ሽንጥ፥ እግር፥...ያለና ከዋናው ኣካል ተለይቶ ሊታወቅና ለብቻው ተነጥሎ ወይም ተቆርጦ ሊወጣ የሚችል ክፍለ ስጋ፥ ኣካል:: 2.ሃፍረተ ስጋ:: 3.(ዘይ.) ስልት:: *የነገር ብልት ማወቅ ጠቃሚ ነው::*

**ብልት ኣወጣ** የታረደ እንስሳን ኣካል በየብልቱ እየለየ ቆረጠ፤ እግሩን፥ ሽንጡን፥...እየቆራረጠ ለየብቻ ኣደረገ::

**ብልት ኣውጪ** ስ የታራጅ የእንስሳን ኣካል በየክፍሉ ለያይቶ የመቁረጥ ችሎታ ያለው፤ በላች::

**በለተተ** ግ አረጀ፤ ሸመገለ።

**ባልቴት** ቅ 1. አሮጊት። ስ 2. ልባም፥ ባለሙያ ሴት።

**በለዘ** ግ 1. በአደጋ ወይም በሌላ ምክንያት የቀድሞ መልኩ ተለወጠ፥ ጠቆረ፥ ዘገነ። 2. ቸከ፥ አደፈ፥ ልማም ያዘ(ጥርስ)።

**ብልዝ** ቅ 1. የጠቆረ፥ የበለዘ። 2. የቸከ፥ ልማም የያዘ (ጥርስ)።

**በለገ** ግ 1. በበልግ ወራት ለበልግ የሚበቃ ዝናም ዘነመ። 2. የበልጉ አዝመራ ሰመረ፥ አማረ።

**በልግ(ብላጊ)** ስ ለአዝመራና ለግጦሽ ሳር በቂ የሚሆን የበጋ ዝናም የሚገኝበት ወቅት (በአብዛኛው ከየካቲት እስከ ሚያዝያ ያሉት ወራት)።

**በልግ ሰጠ** በለገ፤ በልግ ሆነ።

**የበልግ እህል** ስ በበልግ ወቅት ተዘርቶ የሚሰበሰብ አዝመራ።

**የበልግ ዝናም** ስ በበልግ ወቅት የሚጥል ዝናብ።

**አበለገ** ግ የበልግ ዝናም ጣለ፥ በልግ ሆነ።

**በለጠ**[1] ግ 1. (በርዝመት፥ በክብደት፥...) ከሌላው ላቀ፥ ከፍ አለ። 2. ከሌላው ተሻለ።

**በበለጠ(በይበልጥ)** በተሻለ፥ በአብዛኛው።

**ብልጫ** ስ ከፍታ፥ ትልቅነት።

**ተበለጠ** ግ 1. ከሌላው አነሰ፥ የበታች ሆነ። 2. ተሸነፈ። 3. ተሞኘ፥ ተታለለ።

**ተባለጠ** ግ እኩል አልሆን አለ፥ አንዱ ከሌላው አነሰ ወይም ላቀ፤ ተዛነፈ።

**ተባለጥ** ስ እኩል አለመሆን፤ ተዛነፍ።

**ተበላለጠ** ግ 1. አልመጣጠን ወይም እኩል አልሆን አለ፤ ተዛነፈ። 2. አንዱ ከሌላው ጋር በቁመት ተለካከ፥ ተወዳደረ።

**አበለጠ** ግ አላቀ፥ ከፍ አደረገ።

**አበላለጠ** ግ 1. አዛነፈ፥ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ አደረገ። 2. አወዳደረ፥ አንዱን ከሌላው ጋር አነፃፀረ (የሚልቀውን፥ የተሻለውን ለማወቅ)። 3. አዳላ።

**አባለጠ** ግ አበላለጠ።

**አስበለጠ** ግ 1. ከሌላው አላቀ፥ ከፍ አደረገ። 2. በሌላው እንዲበለጥ አደረገ።

**በለጠ**[2] ግ በአስተሳሰብ፥ በእውቀት፥...ከሌላው ላቀ፥ ከፍ አለ።

**ብልጥ** ቅ 1.ብልህ፥ አዋቂ። 2. ጮሌ፥ አራዳ።

**ብልጣብልጥ** ቅ ጮሌነት የሚያበዛ።

**ብልጠት** ስ 1. ብልሃት፥ ዘዴ። 2.ጮሌነት።

**ተብለጠለጠ** ግ 1.ተቅበረበረ፥ ተጋ፥ ተጣጠረ። 2. ብልጠት፥ ጮሌነት አበዛ።

**ተብለጥላጭ** ቅ 1. ትጉህ፥ ታታሪ። 2. ጮሌ።

**አብለጠለጠ** ግ 1. አተጋ፥ አትቅረበረ። 2. ብልጣብልጥ አደረገ።

**በለጠገ "በለፀገ"** ን ተመ.

**በለጠጠ** ግ ያለወጉ፥ ያለቅጥ በጣም አድርጎ ከፈተ፥ ገለጠ (አይንን፥ መዝጊያን፥...)።

**በልጣጣ(በለጠጥ)** ቅ (ዘይ) 1.ሃፍረተቢስ፥ የሰው አይን የማይፈራ። 2. ቀበጥ፥ ሞልፋጣ፥ አዩኝ አዩኝ ባይ።

**ብልጥጥ አለ** ግ ተበለጠጠ።

**ተበለጠጠ** ግ ያለወጉ፥ ያለአግባቡ በጣም ተገለጠ፥ ተከፈተ (አይን፥ መዝጊያ፥...)።

**ተንበላጠጠ** ግ 1. በማስፈራራት መልክ አይኑን አፍጥጦ ወዲያና ወዲህ መላልሶ ተመለከተ። 2. አዩኝ አዩኝ የሚል አይነት አድራጎት አሳየ። 3. (ዘይ.) ቀበጠ፥ ተሞላፈጠ።

**አንበላጠጠ** ግ በማስፈራራት መልክ አይኑን ያለ ቅጥ ገልጦ ወይም አፍጥጦ ወዲያ ወዲህ አየ፥ ተመለከተ።

***በለጨ**

**በለጭ** ስ ብልጭልጭነት ያለው የድንጋይ አይነት፤ በረቦጭ።

**በለጭማ** ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ የሆነ (እንስሳ)።

**ብልጭታ** ስ በግታ፥ ድንገት ታይቶ የሚጠፋ የብርሃን ነፀብራቅ።

**ብልጭልጭ** ቅ 1. የሚያብረቀርቅ፥ የሚያንፀባርቅ፥ በግበግ የሚል። 2. (ዘይ.) ሲያዩት ለጊዜው አይን የሚስብ፥ ደስ የሚል ግን በጣም ጊዜያዊና ተራ የሆነ፥ መናኛ (እቃ፥ ጌጥ፥...)።

**ብልጭልጭታ** ስ ነፀብራቅ፥ ብርቅርቅታ (የመብረቅ፥ የመስታወት፥...)።

**ብልጭልጭ አለ** ግ አብለጨለጨ።

**ብልጭ አለ** ግ ድንገት በግ አለ፤ በራ።

**ብልጭ አለለት** ድንገት ታየው፥ ትዝ አለው፥ ተከሰተለት(ሃሳብ)።

**ብልጭ አለበት** የሚያናድድ፥ የሚያስቆጣ ነገር ድንገት ተሰማው።

**ብልጭ ድርግም አለ** ብርት፥ ጥፍት፥ ጥርኘ ብርኘ አለ።

**ብልጭ አደረገ** ግ 1. አበራ፥ አነደደ

(በጥቂቱ)። 2. ጥቂት ፍንጭ ሰጠ (ለሃሳብ)።

**ተብለጨለጨ** ግ 1.ተንፀባረቀ፥ ተብረቀረቀ። 2. ተጊያጊያጠ፥ ተሽቀረቀረ፥ አሸበረቀ።

**አብለጨለጨ** ግ አንፀባረቀ፥ አብረቀረቀ። 2. ተጊያጊያጠ፥ ተሽቀረቀረ፥ አሸበረቀ።

**በለፀገ(በለጠገ)** ግ ከበረ፥ ሃብት አገኘ።

**ባለፀጋ(ባለጠጋ)** ስ ሃብታም፥ ከበርቴ፥ ባለገንዘብ።

**ብልፅግና** ስ ሃብታምነት፥ የኢኮኖሚ እድገት።

**አበለፀገ** ግ 1. ባለፀጋ፥ ሃብታም አደረገ። 2. አዳበረ፥ አሳደገ።

**በላ** ግ 1. ተመገበ። 2. አላመጠ፥ አኘከ። 3.ነከሰ። *ውሻ እንዳይበላህ ተጠንቀቅ*። 4. አሳከከ፥ ቆጠቆጠ። 5.አሸነፈ፥ ረታ፥ ገቢ አገኘ (በቁማር)። 6. ጨረሰ፥ ፈጀ። *መኪናዋ ቤንዚን ትበላለች*።7.ተቀበለ፥ወሰደ። *ካሳ በላ*፡ 8.አቃጠለ፥ ፈጀ። *እሳት በላው።*

**ሲበሉ የላኩት** 1. የተላከውን መልእክት (ቃል) የሚረሳ፥ የሚዘነጋ። 2. ችኩል፥ ወደመጣበት ለመመለስ የሚጣደፍ።

**እበላ ባይ** የግል ጥቅም ለማግኘት ሲል ሌላውን ለመምሰል የሚሞክር፥ ለጥቅም ሲል ከሌላው ጋር የሚተባበር፥ አስመሳይ፥ አጎብዳጅ።

**የበላበትን ወጪት ሰባሪ** ውለታቒስ፥ መልካም ላደረገለት ክፉ የሚመልስ።

**የብላ ተባላ ዘመን** መተሳሰብ፥ መተዛዘን የሌለበት፥ የግል ጥቅም፥ ፍላጎት ሰውን እርስበርሱ የሚያናቁርበት፦...ጊዜ።

**ይብላኝ (ይብላኝለት)** ሃዘንን፥ ትዝብትን የሚገልፅ ቃል። *ይብላኝ ይህንን የመሰለ ልጅ የሚያስጠጋው አጥቶ ከበረንዳ ያድራል / ለእርሱ ይብላኝ እንጂ እኔስ እንዳጣሁ አልቀርም።*

**መብል** ስ ምግብ፥ የሚበላ ነገር።

**በሊታ** ቅ ያገኘውን ሁሉ የሚበላ፥ ሆዳም።

**በላተኛ** ስ 1. በአንድ የቤተሰብ ሃላፊ ስር የሚተዳደር ሰው፤ ተቀላቢ። 2. ተመጋቢ፥ ምግብ ፈላጊ። ቅ 3. ብዙ የሚበላ፥ ሆዳም።

**-በል(-በላ፥ -በሌ)** 1.(በቦዝ አንቀፅ ከሚነገር ግስ ጋር የሚጣመር ከፊል ቃል) ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ስራ እያካሄደ የሚኖር፥ የሚተዳደር። *አርሶ በል*። 2. (ከስም ጋር የሚጣመር ከፊል ቃል) ቀደም ሲል የተጠቀሰውን ነገር የሚበላ ወይም ዘወትር የሚመገብ። *ሳር በል እንስሳ።*

**ብላቶ** ስ 1.ፍሬው ከተበላ በሗላ የሚቀረው የእህል ገለባ፥ የፍሬው ሽፋን፥ ጥርጣሪ፥ ትርፍራፊ። 2. የአገዳ ምጣጭ። 3. አውሬ ያስተረፈው ቅንጥብጣቢ ስጋና ቆዳ። 4. በፈንጣጣ፥ በቂጥኝ፥... ቁስል ምክንያት ከሰውነት ላይ የሚቀር ጠባሳ።

**ብሎት(ብልት)** ስ የፍስክ ቀን።

**በላ በላ አደረገ** ቶሎ ቶሎ ተመገበ፥ ፈጠን ፈጠን እያለ በላ።

**ተበላ** ግ 1. አለቀ፥ ሳሳ። *ሱሪው ጉልበቱ ላይ ተበልቷል*። 2. ተረታ፥ ተሸነፈ። 3. ተገደለ።

**ተባላ** ግ 1.እርስ በርስ በነገር ተናቆረ፥ ተራኮተ፥ ተጋጨ፥ ተጣላ፥ስምምነት አጣ። 2.በጣም አዘነ፥ አነባ፥ ተላቀሰ (ብዙ ሰው)። 3.ተገዳደለ፥ ተጨራረሰ፥ ተበላላ።

**ተብላላ** ግ 1.ተዋሃደ፥ ተሟሟቀ፥ ፈላ (ድፍድፍ)። 2. ተውጠነጠነ፥ ታሰበበት፥ ተመከረበት(ሃሳብ)። 3. የ"**ተባላ**"ን ሶስተኛ ፍቺ ተመ.

**አበላ** ግ 1.መገበ። 2.ሰጠ። *ጉቦ አብልቶ ጉዳዩን አስፈፀመ።*

**አበል** ስ ድርሻ፥ ክፍያ (በአይነት ወይም በገንዘብ የሚሰጥ)።

**አባላ** ግ እርስ በርስ አጣላ፥አናቆረ፥ አጋጨ።

**አባላሽኝ** ስ የፅኑ ረሃብ ወቅት ወይም ጊዜ።

**ማባያ(መበያ)** ስ ከእንጀራ፥ ከዳቦ፥...ጋር የሚበላ፥ ወጥ፥ በርበሬ፥...።

**አብላላ** ግ አሰላሰለ፥ አውጠነጠነ፥ አበሰለ (ሃሳብን)።

**አስበላ** ግ አሳጣ፥ አጋለጠ፥ ለክፉ ነገር (ለጠላት) አሳልፎ ሰጠ።

**በላች** "**በለተ**" ስር ተመ.

**-ብል** "**በላ**" ስር ተመ.

**በልቃጣ** "**በለቀጠ**" ስር ተመ.

**በልግ** "**በለገ**" ስር ተመ.

**በልጣጣ** "**በለጠጠ**" ስር ተመ.

**በሎታ** ስ ከወደ ቂጡ ድቡልቡልነት ያለው አጭር ዱላ ፤ ከንተሮ ።

**በረሃ** ስ 1.አየሩ በጣም ሞቃታማ፥ አፈሩ አሸዋማ፥ የሚያገኘው የዝናም መጠን እጅግ ዝቀተኛ የሆነ አካባቢ። 2. ጫካ፥ ውድማ፥ ሰው ያልሰፈረበት ቦታ ወይም አካባቢ።

**በረሃ ገባ** 1. ሸፈተ። 2. መነነ።

**በረሀኛ** ቅ በበረሃ የሚኖር።

**በረሃማ** ቅ የአየር ንብረቱ እንደ በረሃ ያለ ቦታ ወይም አካባቢ።

**በረረ** ግ 1. በአየር ላይ በክንፍ ሄደ፥ ከነፈ (አሞራ፥ ወፍ፥...)። 2.ሮጠ። 3. በአውሮፕላን

ሄደ፥ ተጓዘ::

**በረራ** ስ ጉዞ (የአውሮፕላን)::

**በረር** ስ በጎችን የኩልኩልት በሽታ የሚያሲዝ ትል ወይም ጀርም::

**በረሮ** ስ ቀለሙ እንደ ትሏን የቀይ ቡኒ የሆነ መጠኑ ከጥንዚዛ አነስ ብሎ ጠፍጠፍ ያለ፥ ብዙውን ጊዜ ሙቀት ያለባቸውን ጥጋጥግ አካባቢዎች (የማቀዝቀዣ ሞተር ፥ቴፕ፥ ሬድዮ፥ቴሌቭዥን፥ሳጥን፥ልብስ፥...)የሚያዘወትር ሲሄድ ፍጥነት ያለው የቤተ ውስጥ ነፍሳት::



በረሮ

**በራሪ** ቅ 1. ክንፍ ያለው፥ በክንፍ የሚሄድ (ትንኝ፥ ዝንብ፥...):: 2. ሯጭ:: 3. እንደ መደበኛዎቹ (ተረኞቹ) ተራ ወይም የመነሻ ሰአት ሳይጠብቅ ያገኘውን ሰው ብቻ ጭኖ ከተረኞቹ እየቀደመ የሚጓዝ የህዝብ ማመላለሻ መኪና:: 4. አውሮፕላን ላይ የሚሰራ የእለቱ ተረኛ ተጓዥ:: 5. ከአንድ በላይ ቅጂ(ኮፒ) እንዲኖራቸው ሲባል ተመሳሳይ የገፅ ቁጥር ከሚሰጣቸው የካርኒ ወረቀቶች ውስጥ የመጀመሪያው ቅጠል ወይም ወረቀት::

**ብራሪ** ቅ 1. ፍንጣሪ:: 2. መጤ፥ ባይተዋር፥ አድራሻው ወይም የመጣበት ከየት እንደሆነ በውል የማይታወቅ (ሰው)::

**ብራሮ** ስ ሲቆላ ከምጣድ ላይ እየተፈናጠረ የሚወድቅ የእህል ቅንጣት::

**ብር ብር አለ** ግ በችኮላ፥ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ፥ ተዘዋወረ፥ ወዲያ ወዲህ ሄደ:: 2. ተርገበገበ፥ በፍጥነት ተንቀሳቀሰ(አይን፥ ልብ)::

**ተባረረ** ግ 1.(በስራ ምክንያት) በጥድፊያ ወዲያ ወዲህ አለ፥ ተዋከበ:: *እረፍት የለውም ተባር ነው የሚኖረው*:: 2. ተወገደ፥ ተገለለ:: 3. ተሰደደ::

**ተባራሪ** ቅ 1. በሽሽት ላይ ያለ (ሰው):: 2. ቋሚ መኖሪያውን ትቶ ወደሌላ አካባቢ እንዲሰደድ የተደረገ::

**ተባራሪ ወሬ** ስ እርግጠኛነቱ የማይታወቅ፥ ተዛማች ወሬ::

**ተባራሪ ጥይት** ስ ኢላማውን ስቶ ወደ ሌላ አቅጣጫ የሄደ ጥይት::

**አበረረ** ግ 1. አሮጠ፥ አጣደፈ:: 2. አስወገደ:: 3. ከስራ አሰናበተ:: 4. በሃይል፥ በፍጥነት ነዳ፥ አሽከረከረ::

**አብራሪ** ቅ አውሮፕላን ነጂ::

**አባረረ** ግ 1.አሮጠ:: 2. አሳደደ:: 3. አስወገደ:: 4. ተከታተለ::

**መስተባርር** ስ የተደገመበትን ሰው ከሚኖርበት ቤት፥ ቦታ የማባረር ሃይል አለው ተብሎ የሚነገርለት አስማት ወይም ድግምት::

**አባራሪ** ቅ 1.አሳዳጅ:: 2. አንድን ነገር ስራዬ ብሎ የሚከታተል::

**በረሰ** ግ 1.ተሻረ፥ ረከሰ (መድሃኒት፥አስማት):: 2. ተበረዘ፥ በረደ፥ ቀዘቀዘ::

**ማብረሻ** ስ የመድሃኒት መሻሪያ፥ ማርከሻ::

**በረቀ** ግ ቦግ፥ ብልጭ፥ ፍልቅ አለ፤ ተብለጨለጨ::

**መብረቅ(ብራቅ)** ስ 1.የሰማይ ብልጭታን ተከትሎ የሚሰማ ከፍተኛ የፍንዳታ ድምፅ፤ ነጎድጓድ 2. ከፍተኛ ሙቀትና ሃይል ያለው፥ እጅግ በጣም ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት ተምዘግዝጎና በሰውም ሆነ በንብረት ላይ አንዳንድ ጊዜ ጉዳት አድርሶ በቅፅበት ከእይታ ውጪ መሆን የሚችል የሰማይ ብልጭታ::

**በረቅ** ስ 1.መብረቅ:: 2. ነጭ የሆነ የማእድን አይነት (አፈር፥ ድንጋይ)::

**ብርቅርቅ** ቅ ብልጭልጭ::

**ብርቅርቅታ** ስ ብልጭልጭታ::

**ብርቅርቅ አለ** ግ አብረቀረቀ::

**ተብረቀረቀ** ግ ተብለጨለጨ፥ ተፍለቀለቀ::

**አበረቀ** ግ ብልጭ አለ ወይም ብልጭ አደረገ (ሰማይ)::

**አብረቀረቀ** ግ አብለጨለጨ፥ አፍለቀለቀ፥ አንተገተገ (ውሃ፥ መስታወት፥..!)::

**በረቀሰ** ግ 1. ነደለ፥ በሳ፥ በረገደ፥ ከፈተ:: 2. አፈረሰ፥ ጣሰ፥ በጣጠሰ::

**ተበረቀሰ** ግ 1.ተነደለ፥ ተበሳ፥ ተበረገደ፥ ተከፈተ:: 2. ፈረሰ፥ ተበጣጠሰ::

**በረቅ** "በረቀ" ስር ተመ.

**በረቿ** ግ 1. ነጣ፥ ገረጣ:: 2. በሰለ፥ ደረሰ፥ ጎመራ(ሰብል)::

**በረበረ** ግ 1. ጎረጎረ፥ መረመረ፥ ፈተሸ፥ ፈለገ:: 2.በዘበዘ፥ ዘረፈ፥ ሰረቀ:: 3. በመወቃት ላይ ያለን ሰብል (ገብስ፥ ስንዴ፥...) የላዩን ወደታች፥ የታቹን ወደላይ አደረገ:: 4. ሆድ እቃን አተረማመሰ፥ አገለባበጠ፥ ጤና ነሳ::*በባዶ ሆዴ*

*ላረቁ ጠዋቹ ሆዴን በረበረኝ።*

**በርባሪ** ቅ 1.ዘራፊ፥ ቀማኛ፥ ከሰው ቤት ገብቶ የሰው ንብረት ዘርፎ የሚሄድ። 2. በመወቃት ላይ ያለን (እንደ ገብስ፥ ባቄላ፥...ያለን) ሰብል የላዩን ወደታች፥ የታቹን ወደላይ ለማድረግ በመንሽ የሚገለብጥ (ሰው)።

**ብርባሮ** ስ በመወቃት ላይ ያለን እህል ወይም ሰብል በመንሽ የመገልበጥ ስራ።

**እንቡርቧይ** ስ በመንሽ ተበርብሮ የወጣ ያልደቀቀ ገለባ፤ እንግውላይ።

**በረታ** ግ 1.ጠነከረ፥ ጎለበተ፥ ሃይል አገኘ። 2. አየለ፥ ተጋነነ፥ ጎላ (ነገር፥ጥል)። 3. አገገመ፥ ተሻለው።4.ተፍጨረጨረ፥ጎበዘ፥ታገለ። *በትምህርቱ በርትቷል*። 5.ተበረታታ፥ ተፅናና (ለሃዘን)።

**ብርቱ** ቅ ፅኑ፥ ጠንካራ፥ ጎበዝ።

**ብርቱ ነዎት?** ጤንነትን፥ ደህንነትን በተመለከተ የሚቀርብ የሰላምታ ቃል።

**ብርቱ ጉዳይ** ስ በጣም አስፈላጊና ጥብቅ የሆነ ነገር፥ ስራ።

**ብርታት** ስ ሃይል፥ ፅናት፥ ጥንካሬ፥ ጉልበት።

**ተበረታታ** ግ ተጠናከረ፥ ተፅናና፥ጎበዘ።

**ተበራታ** ግ ተበረታታ።

**አበረታታ** ግ 1.እንዲበረታ፥ እንዲጠነክር አገዘ፥ ገፋፋ፥ ደገፈ። 2.አፅናና።

**ማበረታቻ** ስ ማጠናከሪያ፥ ማፅናኛ (ስጦታ፥ ሽልማት፥...)።

**በረት** ስ እንደ ከብቶች፥ በጎች፥... ያሉ እንስሳት የሚያድሩበት ቤት።

**በረት ነው** በጣም ሰፊ ነው (ለቤት)።

**በረት አፍ**(ስድብ) 1. አፉ ሰፊ የሆነ (ሰው)። 2. እንደፈለገ የሚናገር፥ መጥፎ ተናግሮ ሰውን የሚያስቀይም (ሰው)።

**በረንዳ** ስ በቤት ዋና በር፥ በስተውጪ በኩል ከቤቱ ጣሪያ ጋር ተያይዞ የሚሰራ፥ ብዙውን ጊዜ በአንድ በኩል ብቻ ግድግዳ የሚኖረው የቤቱ የውጪ አካል(ስእሉን ቤት ስር ተመ.)።

**በረንዳ አዳሪ** ቅ 1.የሚያድርበት ወይም የሚጠለልበት ቤት የሌለው፥ ብዙውን ጊዜ በከተማ ውስጥ በየመንገዱ ዳር በሚገኙ ታላላቅ ህንፃዎች ታዛ ስር ወይም በየጥጋ ጥጉ ተኝቶ ሌሊቱን የሚያሳልፍ ሰው፤ ቦዘኔ። 2. (ዘይ.፥ስድብ) ወሮበላ፥ ዱር አዳሪ፥ ወስላታ፥ ሌባ፥ ቀማኛ። ቅ 3. ዘዋሪ፥ በቋምነገር ስራ ላይ በመዋል ፈንታ በስራ ፈትነት ሲያውደለድል የሚውል።

**በረኛ "በር"** ስር ተመ.

**በረከ** ግ ጉልበቱ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ፥ አቅም አጣ።

**ብርክ** ስ ከድንጋጤና ከፍርሃት የተነሳ በድንገት አቅመቢስ መሆን፥ መድከም፥ መዛል፥ መርበትበት፥ መልፈስፈስ።

**ብርክ ያዘው** በድንገተኛ ድንጋጤ ምክንያት ጉልበቱ ተልፈሰፈሰ፥ መንቀሳቀስ ተሳነው።

**ብርክርክ** ቅ ቀጥቃጣ፥ ድንጉጥ፥ ፈሪ።

**ብርክርክ አለ** ግ ተብረከረከ።

**ተብረከረከ** ግ 1.አቅም አጣ፥ ጉልበቱ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ። 2.ፈራ፥ ተርበደበደ፥ ተርበተበተ።

**አብረከረከ** ግ 1. አርገደገደ፥ አልፈሰፈሰ፥ አቅም አሳጣ። 2. አስፈራ፥ አርበደበደ፥ አራደ፥ አንቀጠቀጠ፥ አርበተበተ።

**በረከተ** ግ 1. በዛ፥ መጠኑ ጨመረ። 2. ተረፈ፥ ተትረፈረፈ። 3. ብዙ ቆየ፥ ሰነበተ(ለአላቂ ነገሮች)።

**በረከት** ስ 1. ረድኤት፥ መቅኖ። 2. ስጦታ። *እነሆ በረከት*። 3. ፀጋ፥ ምርቃት።

**በረከት የለውም** ረድኤት፥ መቅኖ የለውም።

**በረከት ያውርድ** ይብዛ፥ ይትረፍረፍ፥ ይባረክ፥ ረድኤት ያግኝ ለማለት የሚባል የበጎ ምኞት መግለጫ ወይም ምርቃት የማትረቢያ ቃል።

**በረከተ ስጋ** ስ ስጋዊ ፀጋ፥ ሃብት፥ ምድራዊ ብልፅግና።

**በረከተ ቢስ** ቅ ረድኤት የሌለው፤ አሲዳም።

**በርካታ** ቅ አያሌ፥ ብዙ።

**ብርካቴ** ስ 1.ብዛት። 2. ረድኤት፥ መቅኖ።

**ተበረከተ** ግ ተሰጠ (ስጦታ)።

**ተበራከተ** ግ እየበዛ ሄደ፥ ተትረፈረፈ።

**አበረከተ** ግ ሰጠ (ገፀበረከትን)።

***በረከከ**

**በርክክ አለ** ግ ተንበረከከ።

**ተንበረከከ** ግ 1. በጉልበቶቹ ቆመ፥ መሬት ነካ። 2.(ዘይ.) ተሸነፈ፥ ታዛዥ፥ ተገዢ ሆነ።

**አንበረከከ** ግ 1. በጉልበት አስቆመ። 2. አሸነፈ፥ የበታች አደረገ፥ ገዛ፥ አስገበረ።

**እንብርክክ (እንብርክ)** ስ በጉልበት መሬት የመንካት ወይም መሬት ላይ የመቆም ድርጊት።

**በእንብርክክ (በእንብርክ) ያስኬዳል** ሃይለኛ ነው፥ ያስድሃል። *ጠላው በእንብርክክ ያስኬዳል።*

**በረኪና** ስ ያደፈን ወይም የመነቸከን ነጭ ልብስ ለማፅዳት እንዲያግዝ ከውሃና ከሳሙና ጋር እየተደባለቀ ልብስ የሚታጠብበት ፈሳሽ የሆነ

ኬሚካል::

**በረካ** ስ በሃገር ባህል መሰረት ቡና በጀበና በሚፈላበት ጊዜ ከአቦሉና ከሁለተኛው ቀጥሎ የሚጠጣው ቡና ፤ ሶስተኛ ቡና::

**በረካ ሁን** (ምር.) የተባረክ፥ የተቀደስክ ሁን::

**በረኮተ** ግ ሊጥን በጋለ ድንጋይ ወይም በፍም ላይ አስቀምጦ ርሚጦ ወይም ቂጣ ጋገረ፥ አበሰለ::

**ብርኩታ** ስ ርሚጦ፤ በጋለ ድንጋይ ወይም በፍም ላይ ተደርጎ የበሰለ ቂጣ::

**በረዘ** ግ 1.ማርን በውሃ በጥብጦ ብርዝ አዘጋጀ:: 2. የጠላን ድፍድፍ በውሃ በጠበጠ፥ አቀጠነ፥ ሞላ:: 3. ሃይለኛውን መጠጥ ለስለስ ካለው ጋር ደባለቀ፥ ቀየጠ:: 4. ሙቅ ውሃን ከቀዝቃዛ ጋር ደባለቀ፤ ከለሰ::

**ብርዝ** ስ ጌሾ የማይገባበትና ማርን በውሃ በቀጭኑ በመበጥበጥ የሚዘጋጅ የመጠጥ አይነት::

**ተበረዘ** ግ ተመረዘ፥ ተበላሸ:: *ሓእምሮው በመጥፎ ኣስተሳሰብ ተበረዘ::*

**ተባረዘ** ግ አንዱ ከሌላው ጋር ተቀላቀለ፥ ተቀየጠ፥ ተደበላለቀ (ለፈሳሽ)::

**አበረዘ** ግ አበረደ፥ አበረሰ፥ አቀዘቀዘ::

**አባረዘ** ግ አቀላቀለ፥ አደባለቀ፥ ከለሰ::

**በረየ** ግ በረገገ፥ ደነበረ፥ ሸሸ:: *እባብ ያየ በልጥ በረየ::*

***በረየ**

**ተበራየ** ግ ከማሳ የተሰበሰበው ሰብል ውድማ ላይ ተደርጎ በከብት እግር እንዲረገጥ ሆነ (ፍሬውን ከገለባው ለመለየት)::

**አበራየ** ግ ከእርሻ ቦታ የተሰበሰበን ሰብል ውድማ ላይ አድርጎ በከብት እግር አስረገጠ፥ ወቃ፥ አሄደ::

**በረደ** ግ 1. ቀዘቀዘ፥ ሙቀት አልባ ሆነ:: 2-. ቆፈነነ፥ ብርድ ሆነ:: 3. ተረጋጋ፥ ሰላም ሆነ:: *ጠቡ በረደ::* 4. ከዝሙት ስራ ራቀ፥ ጨመተ::5.ደነዘ፥ አልቆርጥ፥ አልፈልጥ አለ:: *ስለቱ በረደ::*

**በረድ** የ"በረዶ"ን አንደኛ ፍቺ ተመ.

**በረዶ** ስ 1. እጅግ በጣም ከመቀዝቀዙ የተነሳ ወደ ጠጣርነት የተለወጠ ውሃ፤ በረድ:: 2. በጣም ቀዝቃዛ:: *እጁ በረዶ ነው::*

**በረዶ ቤት** ስ ምግብና መጠጥ ለማቀዝቀዝ ወይም ሳይበላሽ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲቆይ ለማድረግ የሚረዳ በረዶ ያለበት ቤት፥ ክፍል፥ እቃ::

**በረዷማ** ቅ በረዶ በብዛት ያለበት (ቦታ)::

**በራዳ (በራድ)** ቅ በጣም ቀዝቃዛ::

**ብርድ** ስ 1. ቁር፥ ቆፈን፥ ውርጭ፥ በጣም የሚቀዘቅዝ አየር:: 2. በቀዝቃዛ አየር ምክንያት የሚያጋጥም ህመም::

**ብርድ መታው** 1. የብርድ በሽታ ያዘው:: 2. በቀዝቃዛ አየር ምክንያት ብልሽት አገኘው (ሰብል)::

**ብርድ ብርድ አለው** ከብርድ ጋር የተያያዘ ወይም ከብርድ ጋር የተመሳሰለ የህመም ስሜት ተሰማው::

**ብርድ ፈደፈደው** ቀዝቃዛ አየር ሰውነቱን አሰቃየው::

**ብርድ ልብስ** ስ ከጥጥ ወይም ከሱፍ፥... የሚሰራና በመኝታ ጊዜ ሰዎች ለሙቀት የሚለብሱት እንደ ማቅ፥ ዝተት፥ ባና ያለ ወፍራም ልብስ::

**ብርዳም (ብርዳማ)** ቅ ሃይለኛ ቅዝቃዜ ያለበት(ቦታ፥ ወቅት)::

**ተባረደ** ግ 1. አየሩ ቀዘቀዘ፤ የቅዝቃዜ ስሜት አሰማ፥ ፈጠረ:: 2. ተባረዘ፥ ተካለሰ (ሙቅና ቀዝቃዛ ውሃ)::

**አበረደ** ግ 1. አቀዘቀዘ፥ ሙቀቱ እንዲቀንስ አደረገ:: 2. አስታገሰ፥ አስወገደ:: *በመካከላቸው ገብቶ ጥሉን አበረደ::*

**ማብረጃ** ስ የሹርቤ ብርሌ ቅርፅ ያለውና ከብርሌ ሳቅ ያለ የጠላና የጠጅ መያዣ ጠርሙስ::

**አብራጃ** ቅ ቀዝቃዛ፥ ነፋሻ (ቦታ)::

**በረደደ** ግ ጠና፥ በረታ፥ ጠነከረ::

**በረደድ(በርዳዳ)** ቅ ፅኑ፥ ብርቱ፥ ጠንካራ::

**በረድ "በረደ"** ስር ተመ.

**በረዶ** ዝ.ክ.

***በረጀረጀ**

**ተብረጀረጀ(ተብረዠረዠ)**ግ 1.በመጠጥ ወይም በሌላ ምክንያት ሰውነቱ ዛለ፥ ፈዘዘ፥ ተርገደገደ፥ ተንቦገቦገ:: 2. ተጥበረበረ (አይን በነፀብራቅ)::

**አብረጀረጀ(አብረዠረዠ)** ግ 1.ሰውነትን አዛለ፥ አደከመ፥ አርገ ደገደ፥ አንቦገቦገ:: 2. አይንን አጥበረበረ (ነፀብራቅ)::

**በረገደ** ግ 1. ሙሉ በሙሉ ከፈተ፥ ወለል አደረገ (ብዙውን ጊዜ ሃይልና ፍጥነት በተቀላቀለበት ሁኔታ):: 2. ከሁለት ከፈለ፥ ሰነጠቀ:: *ግንዱን በመጥረቢያ በረገደው::*

**በርጋዳ(ብርግድ)** ቅ 1.ያልተዘጋ፥ የማይዘጋ፥ ክፍት:: 2. (ስድብ) ስትቀመጥ፥ስትሄድ መሸፈን ያለበትን የሰውነቷን ክፍል የማትሸፍን፥ እርቃኗን

ስለ መጋለጡ የማትጨነቅ፥ የማትጠነቀቅ።

**ተበረገደ** ግ 1. ተከፈተ፥ ወለል አለ። 2.ተከፈተ፥ ተሰነጠቀ።

**ተበራገደ** ግ በአቋቋም፥ በአካሄድ፥ በአቀማመጥ እግሮቹን በጣም ከፈተ።

**በረገገ** ግ ደንግጦ ሸሸ፥ በረየ፥ደነበረ።

**በርጋጋ** ቅ ድንጉጥ፥ ፈሪ፥ ደንባሪ።

**ብርግግ ብርግግ አለ** ከፍርሃት፥ ከድንጋጤ የተነሳ ብትት ብትት አለ፥ ሰውነቱ የድንጋጤ እንቅስቃሴ አደረገ።

**ተበራገገ** ግ ተደናገጠ፥ ተደናበረ።

***በረጠጠ**

**በርጣጣ** ቅ ኩራተኛ፥ ጉረኛ፥ ትእቢተኛ፥ በጥራራ።

**ተንበራጠጠ** ግ ኮራ፥ ታበየ፥ ተንበጣረረ።

**አንበራጠጠ** ግ አኮራ፥ አንበጣረረ።

**በራ (ራሰ በራ)** ቅ ፀጉሩ ከወደ ግንባሩ የሸሸ፥ የተመለጠ (ሰው)።

**በራ**[1] ግ 1. ቦግ አለ፥ ብርሃን ሆነ። 2. ነጣ ፥ ፈካ፥ ብሩህ ሆኖ ታየ።

**መብራት** ስ ከችቦ ወይም ከሻማ ወይም ከጧፍ እሳት፥...የሚገኝ ወይም ከኤሌክትሪክ ሃይል የሚመነጭ ብርሃን።

**መብራት ሃይል** ስ 1. የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫውንና የአስተዳደሩን ጉዳይ አጠቃሎ የሚመራ መስሪያ ቤት። 2. የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ጣቢያ።

**ብሩህ (ብር)** ቅ የበራ፥ የፈካ፥ ንፁህ፥ የጠራ።

**ብሩህ አእምሮ** ስ ነገሮችን በፍጥነት መረዳት የሚችል አስተዋይ አእምሮ።

**ብርሃን** ስ 1. የመብራት፥ የፀሃይ፥...ውጋጋን፤ የጨለማ ተቃራኒ። 2. ፋና፥ መብራት። 3. ቀን፤ ፀሃይ ወጥታ እስከምትጠልቅ ያለው ጊዜ።4. የአይን የማየት ችሎታ። *ብርሃኑን ያጣው አንዷል ላይኑ ሰውር።*

**ብርሃነ ልደት** ስ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበት እለት፤ በአለ ልደት፤ ልደት።

**ብርሃነ ትንሳኤ** ስ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከመቃብር የተነሳበት እለት፤ በአለ ትንሳኤ፤ ትንሳኤ።

**ብርሃነ ጥምቀት** ስ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሃንስ እጅ የተጠመቀበት እለት፤ በአለ ጥምቀት፤ ጥምቀት።

**ተብራራ** ግ ተፍታታ፥ ግልፅ እንዲሆን ተደረገ (ሃሳብ)።

**አበራ** ግ 1. መብራት ለኮሰ፥ ብርሃን እንዲሆን አደረገ። 2. ቦግ አለ፥ አብለጨለጨ፥ አንፀባረቀ። 3. አዳነ፥ ፈወሰ (የታወረ አይንን)።

**ማብሪያ ማጥፊያ** ስ የኤሌክትሪክ አምፖል ወይም ሌላ በኤሌክትሪክ ሃይል የሚሰራ መሳሪያ እንዲበራ ወይም እንዲጠፋ ለማድረግ የሚያገለግል የኤሌክትሪክ እቃ።

**አብራራ** ግ ተነተነ፥ ግልፅ አደረገ፥ በሚገባ አስረዳ (ሃሳብን)።

**ማብራሪያ** ስ ግልፅነት የጎደለውን ሃሳብ ግልፅ ለማድረግ የሚረዳ መግለጫ።

**በራ**[2] ግ ዝናም መዝነሙን አቆመ፥ ብራ ሆነ።

**ብራ** ስ ዝናም የቆመበት ወይም የሌለበት ጊዜ።

**ብራ ሆነ** ዝናም ቆመ፥ ጠፋ።

**አበራ** ግ ዝናም መጣሉን ተወ፥ አቆመ።

**በረራ** "በረረ" ስር ተመ.

**በራድ**[1] ስ የሻይ ማፍሊያ ወይም ማቅረቢያ ማንቆርቆሪያ።

**በራድ**[2] "በረደ" ስር "በራዳ"ን ተመ.

**በራፍ** "በር" ስር ተመ.

**በሬ** ስ ከቀንድ ከብት ወገን የሆነ፥ ብዙውን ጊዜ ለእርሻ ስራ የሚያገለግል ተባእት የቤት እንስሳ(በእሉን የቤት እንሰሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ሞኝ፥ ቂል።

**በሬ ወለደ የሚል** ትንጣት ያህል እንኳ እውነትነት የሌለው ወሬ የሚያወራ።

**የበሬ ልብ** ስ መጠኑ ብርቱካን የሚያህል፥ ቅርፁ ልብ የሚመስል የፍራፍሬ አይነት።

**የበሬ ሸንት** ስ ቀጥታነት የሌለው፥ አንድ ጊዜ ወደቀኝ አንድ ጊዜ ወደግራ እየተጠማዘዘ የሚሄድ የመስመር ቅርፅ፥ መንገድ።



የበሬ ሸንት

**የበሬ ግንባር የምታህል** በጣም ትንሽ የሆነች (መሬት)።

**በር** ስ 1. ሰውም ሆነ ሌላ ነገር ሊተላለፍበት እንዲችል የተወሰነ ክፍተት እንዲኖረው ተደርጎ የተሰራ፥ ሲያስፈልግ ክፍተቱ በመዝጊያ ሊከለል የሚችል የቤት ወይም የግቢ መግቢያና መውጫ፤ መተላለፊያ (በእሉን ቤት ስር ተመ.)። 2.

መዝጊያ:: 3. ኪሳ፣ ከአንድ የተወሰነ የቦታ ክልል ወደሌላው ለመሄድ እንደ መተላለፊያ የሚያገለግል መንገድ::

**በር መታ** በር አንኳኳ፥ ደበደበ፥ ቆረቆረ::

**በር አወጣ** ለመተላለፊያ ወይም ለመግቢያና ለመውጫ እንዲያገለግል በር አበጀ፥ ሰራ::

**ከበር መልስ** ከቤት በር ጀምሮ ወደ ውስጥ ያለው ሁሉ በጠቅላላ::

**በራፍ(በር አፍ)** ስ ወደቤት ወይም ወደግቢ ለመግባትና ከቤት ወይም ከግቢ ለመውጣት እንደመተላለፊያ የሚያገለግል የቤት ወይም የአጥር በር፣ ደጃፍ::

**በር ጠባቂ** ስ ዘበኛ፥ ዋርዲያ፥ በረኛ::

**በረኛ** ስ 1. በር ጠባቂ፥ ዘበኛ:: 2. በእግር ወይም በእጅ ኳስ ጨዋታ ጊዜ ኳሷ ወደ ግብ እንዳትገባ የሚከላከል፥ የሚጠብቅ ተጫዋች፣ ግብ ጠባቂ::

**በርሜል(በርሚል)** ስ ከእንጨት ወይም ከቆርቆሮ ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራና ለጠጅ መጣያ ወይም ለጠላ መጥመቂያ ወይም ለሌላ ነገር መያዣ የሚያገለግል ትልቅ እቃ::

**በርሞሌ** ስ የሽቶ ስም::

**በርበሬ** ስ 1. የበሰለ፥ የጎመራ ወይም ከመብሰሉ የተነሳ ወደ ቀይነት የተለወጠ የቃሪያ ተክል ዛላ:: 2. ከበሰለ ወይም ከጎመራ የቃሪያ ዛላ በድልህ ወይም በአዋዜ ወይም በዱቄት መልክ የሚዘጋጅ ሲበሉት የሚፋጅ ወይም የሚያቃጥል የወጥ ቅመም:: 3. ከላይ የተገለፀውን ዛላ የሚያፈራ ተክል::

**በርባሪ** "በረበረ" ስር ተመ.

**በርባሮስ** ስ መቀመቅ፥ ሰፊና ጥልቅ የሆነ ጉድጓድ::

**በርኖሴ** ስ ፀረ እህል ተባይ፣ ተምች::

**በርኖስ** ስ ከጥቁር የበግ ፀጉር የሚሰራ፥ እንደ ካባ ከኩታ በላይ ተደርቦ የሚለበስ ወፍራም ልብስ(ስእሉን ልብስ ስር ተመ.)::

**በርካታ** "በረከተ" ስር ተመ.


**በርዳዳ** "በረደደ" ስር ተመ.

**በርጋዳ** "በረገደ" ስር ተመ.

**በርጋጋ** "በረገገ" ስር ተመ.

**በርጣጣ** "*በረጠጠ" ስር ተመ.

**በርጩማ** ስ 1. ቅርፁ ክብ ሆኖ መሃሉ ጎድጎድ ያለ፥ ከአንድ ግንድ ወጥ ሆኖ የተሰራ ባለ ሶስት እግር መቀመጫ፥ ወንበር:: 2. ሁለት አጫጭር እግሮች ያሉት የእንጨት መቀመጫ፥ አነስተኛ አግዳሚ ወንበር::



*በርጩማ 1ኛ ፍቺ*

**በሰለ** ግ 1. ለምግብነት ደረሰ፥ ጎመራ (ሰብል፥ ፍራፍሬ):: 2. አንድ የምግብ አይነት(ጥራጥሬ፥ ሊጥ፥...) በመቆላት ወይም በመጋገር፥... ለምግብነት ከሚያበቃው ደረጃ ላይ ደረሰ 3. ዳበረ፥ በለፀገ (አእምሮው በእውቀት):: 4. ቆሰለ፥ ተጎዳ፥ በጣም ተናደደ(አእምሮው በነገር):: 5. ለፍፃሜ ደረሰ፥ ተቃረበ(ጉዳይ):: 6.ህመሙ ለመዳን ተቃረበ፥ ስቃዩ ቀነሰ (ለምሳሌ ጉንፋን):: 7. መግል ያዘ፥ ሊፈነዳ ደረሰ (ያበጠ ቁስል):: 8.ብዙ ከመቆየቱ የተነሳ በካ፥ ከመጠጠ (ቅቤ):: 9.ሳይመስልበት ጠነከረ፥ ጠጠረ፥ ጉልበት አወጣ(ልጅ):: 10. ነፍስ አወቀ፥ ክፉና ደግ ለየ (ልጅ)::

**የበሰለ ቅቤ** ስ የቆየ፥ የበካ ቅቤ::

**በሰላ** ስ 1. ታርሶ ለዘሪት የተዘጋጀ፥ የለሰለሰ እርሻ ወይም ማሳ:: 2. ለባለእዳ መከፈል ያለበት ገንዘብ::

**የበሰላ ዋስ** ስ እዳን የመክፈል ሃላፊነት ያለበት ዋስ::

**በሰሎ** ስ ተዘጋጅቶ የተቀመጠ ምግብ፥ መጠጥ::

**በሳል** ቅ 1.ሲቀቅሉት ቶሎ የሚበስል (ጥራጥሬ ወይም ተክል):: 2. ብዙ የቆየ፥ የጠነከረ:: 3. በትምህርት፥ በእውቀት፥...የበለፀገ::

**ብሳይ** ቅ በጉድጓድ ተጠራቅሞና ተብላልቶ የቆየ (አዛባ፥ ፍግ)::

**ብስል** ቅ 1.የጎመራ፥ ለምግብነት የደረሰ (ፍራፈሬ):: 2. ተቀቅሎ ወይም ተቆልቶ፥... የሚገኝ (ምግብ):: 3. (ዘይ.)ሀ• አዋቂ፥ ማመዛዘን የሚችል (ሰው):: ለ• ብልህ፥ ብልጥ::

**ብስል ቀይ** በጣም ቀይ የሆነ::

**ብስል ተቀሊል** ከጥሩው ወይም ከመጥፎው ብቻ ያልሆነ፥ ሁለቱም ተቀላቅለው የሚገኙበት::

**ብስለት** ስ 1. የመጎምራት፥ ለምግብነት የመድረስ ሁኔታ (ለፍራፍሬ):: 2. (ዘይ.) ሀ• እውቀት፥ አዋቂነት:: ለ•ብልህነት፥ ብልጠት::

**ተባሰለ** ግ በነገር ተቋሰለ፥ ተበሻሸቀ፥ በጣም ተቃቃረ::

**አበሰለ** ግ 1. ምግብ አዘጋጀ (በመቀቀል፥ በመጋገር፥...) 2. በጣም አመመ፥ ጎዳ (በሽታ)::

3. በሃይል፥ በጣም አጥብቆ አደረገ፥ ከወነ። *ላብሰሉ ተማረ።*

**ማብሰያ** ስ 1. የምግብ ማዘጋጃ (መቀቀያ፥ መጋገሪያ፥...)እቃ። 2. ለምግብ ማዘጋጃ የሚያገለግል ማገዶ።

**አብሳይ** ስ ምግብ አዘጋጅ (በመቀቀል፥ በመጋገር፥...)።

**አብስል** ቅ አናዳጅ፥ አብሻቂ።

***በሰረ**

**ብስራት** ስ የምስራች፥ መልካም ዜና።

**ተበሰረ** ግ የምስራቹ ወይም ብስራቱ ተነገረ፥ ተወራ።

**አበሰረ** ግ የምስራች አለ፥ መልካም ወሬ ወይም ዜና ተናገረ።

**አብሳሪ** ቅ ብስራት ወይም የምስራች ነጋሪ።

**በሰቆለ** ግ ተንገላታ፥ ተጉላላ፥ ጎሰቆለ።

**በስቋላ(ብስቁል)** ቅ ችግር ያንገላታው፥ የተጉላላ፥ ጎስቋላ።

**ብስቁልና** ስ እንግልት፥ መጉላላት፥ ጉስቁልና።

**ተበሳቆለ** ግ ተንገላታ፥ ተጉላላ፥ ተጎሳቆለ።

**በሰበሰ** ግ 1. በውሃ ወይም ፈሳሽ በሆነ በሌላ ነገር ራሰ፥ ረሰረሰ፥ ረጠበ። 2. ንፅህናው ባለመጠበቁ ወይም አየር ሳያገኝ ታጅሎ በመቀመጡ ወይም በሌላ ምክንያት ተበላሸ፥ መጥፎ ጠረን ወይም ጣእም ፈጠረ። 3. በጣም አደፈ፥ ቆሸሸ (ለምሳሌ ልብስ)። 4. ክብካቤ ባለማግኘቱ ወይም እድሜውን በመጨረሱ ከጥቅም ውጪ ሆነ፣ ነገለ። *የግድግዳው እንጨት ስለ በሰበሰ ቤቱ ተገረሰሰ ።* 5. ፈረሰ፥ ፈራረሰ፥ ወደ አፈርነት ተለወጠ። 6. (የን.አነ.) በጣም አረጀ፥ ሸመገለ። 7. በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ በመሆን ብዙ ጊዜ አሳለፈ፥ እዚያው አረጀ፥ ተረሳ። *በወጣትነቱ እንደታሰረ ወህኒ ቤት በስብሶ ቀረ።*

**ብስባሽ** ቅ የበሰበሰ፥ ቆሻሻ፥ ውድቅዳቂ።

**ብስብስ(በሰበስ፥በስባሳ)** ቅ 1. የቆሸሸ፥ የተበላሸ፥ የበሸቀጠ። 2. (ስድብ) ሁ(ነውር) ግም፥ ክርፋታም። ለ• ያረጀ።

**ተበሰበሰ** ግ በመጠነኛ ውሃ እየታሸ እንዲርስ ተደረገ (ለበሶ ዱቄት)።

**ተበሳበሰ** ግ ተበሻቀጠ፥ ተግማማ፥ ተበላሸሸ።

**አበሰበሰ** ግ በሶን ወይም ለእንኩሮ የተዘጋጀን ዱቄት ከመጠነኛ ውሃ ጋር አደባልቆ አሸ፥ አዘጋጀ።

**አበሳበሰ** ግ አበሸቀጠ፥ አግማማ።

**በሰኘ** ግ የማይስማማ ምግብ በመመገቡ መጥፎ ጠረን ያለው ግሳት አገሳ።

**ብስና** ስ የማይስማማ ምግብ በመመገብ ወይም በሆድ መታወክ ምክንያት የሚፈጠር፥ መጥፎ ጠረን ያለው ከሆድ የሚወጣ ግሳት።

**ብስናታም** ቅ (ስድብ) ክርፋታም፥ ግማታም።

**በሰከ** ግ በትንሹ በጨቅ አደረገ፥ በጠቀ፥ በጨቀ፥ ቀደደ።

**ብስክ** ቅ ብጥቅ፥ ቡጭቅ።

**ብስክ ብስክ አለ** ግ ብጥስ ብጥስ አለ (ለምሳሌ ክር)።

**ብስክስክ** ቅ 1.ብጥስጥስ፥ ብትክትክ። 2. (ዘይ.) ነጭናጫ፥ ብስጩ።

**ተበሰከ** ግ ተበጠሰ።

**ተበሳሰከ** ግ ተበጣጠሰ።

**ተብሰከሰከ** ግ 1. አቅም አጣ፥ ተበጣጠሰ። 2. (ዘይ.) ተነጫነጨ፥ ተበሳጨ።

**አብሰከሰከ** ግ አቅበጠበጠ፥ ብስጭትጭት አደረገ፥ አነጫነጨ።

***በሰጨ**

**ብስጩ** ቅ ቁጡ፥ ተናዳጅ፥ ተነጫናጭ።

**ብስጭት** ስ ንዴት፥ መነጫነጭ፥ የሀሊና ሰላም ማጣት።

**ብስጭት አለ** ግ ተበሳጨ፥ ተናደደ፥ ተነጫነጨ።

**ተበሳጨ** ግ ተናደደ፥ ተነጫነጨ፥ ተቆጣ።

**አበሳጨ** ግ አናደደ።

**በሳ** ግ ሸነቆረ፥ ነደለ፥ ቀደደ።

**መብሻ** ስ መሸንቆሪያ፥ መንደያ (መሳሪያ)።

**ብስ** ቅ ሽንቁር፥ ቀዳዳ።

**ተበሳ** ግ ተሸነቆረ፥ ተቀደደ።

**በሳል "በሰለ"** ስር ተመ.

**በስቋላ "በሰቆለ"** ስር ተመ.

**በስባሳ "በሰበሰ"** ስር **"ብስብስ"**ን ተመ.

**በስተ** ___ አቅጣጫን ከሚያመለክቱ ቃላት በፊት እየገባ በ ___ በኩል የሚለውን ፍቺ የሚያመጣ ምእላድ። *በስተሰሜን/ በስተቀኝ/ በስተዚያ።*

**በስተሂላ** 1. ከሂላ፥ ከጀርባ። 2. ቆይቶ በመጨረሻ ጊዜ። 3. ከሂላ በኩል።

**በስተርጅና** በእርጅና ጊዜ___።

**በስቲያ** ወዲያ። *ከነገ በስቲያ እመለሳለሁ።*

**በሶ** ስ ዱቄቱ በውሃ እየተራሰ ከታሸ በሂላ እየተጨበጠ የሚበላ፥ ተቆልቶ ከተፈጨ ገብስ

የሚዘጋጅ የምግብ አይነት::

**በሶብላ** ስ ጥሩ ሽታና ጣእም ያለው የወጥ ቅመም አይነት፤ ዘቃቅቤ::

**በሸረከ** ግ ሸረከተ÷ ቀደደ÷ በሸከተ::

**በሸረክ(በሽራካ)** ቅ ሽርከት÷ ቀዳዳ::

**ተበሸረከ** ግ ተሸረከተ÷ ተቀደደ::

**በሸቀ**[1] ግ ተበሳጨ÷ ተናደደ::

**አብሽቅ(አብሻቂ)** ቅ አናዳጅ::

**በሸቀ**[2] ግ ረጠበ÷ ራሰ÷ በሰበሰ::

**ብሽቅ** ቅ የበሰበሰ÷ የገማ::

**በሸቀጠ** ግ 1. አደፈ÷ ቆሸሸ:: 2. ራሰ÷ በሰበሰ:: 3. ገማ÷ ሸተተ::

**በሸቀጥ(ብሽቅጥ÷ በሽቃጣ)** ቅ (ለድብ) ግም÷ በስባሳ::

**ተበሻቀጠ** ግ ተግማማ÷ ተበሳበሰ::

**አበሻቀጠ** ግ አኪያኪያሰ÷ አራከሰ÷ አጥላላ÷ አቃለለ÷ አዋረደ::

***በሸበሸ**

**በሽ(በሽ) ነው** ሞልቷል÷ ተርፏል÷ የተፈለገውን ያህል ይገኛል:: *ጠጁ በሽ በሽ ነው::*

**ተንበሸበሸ** ግ የፈለገውን ያህል አገኘ÷ ረካ::

**አንበሸበሸ** ግ የተፈለገውን ያህል በመስጠት ደስ አሰኘ÷ አረካ::

**በሸተ** ግ አመመ÷ አወከ (ሆድን)::

**በሽታ** ስ ህመም::

**በሽታ ላይ ወደቀ** ታመመ÷ በሽተኛ ሆነ::

**በሽታ ሸመተ/ገበየ/ገዛ/አተረፈ/ አፈራ** በሽታ ያዘው÷ አጋጠመው::

**በሽተኛ** ቅ በሽታ የያዘው÷ ያደረበት፤ ህመምተኛ::

**ተበሸተ** ግ ታመመ÷ ታወከ:: *ሆዱ ተበሽቷል::*

**በሽራካ** "**በሸረከ**" ስር "**በሸረክ**"ን ተመ.

**በሽቃጣ** "**በሸቀጠ**" ስር "**በሸቀጥ**" ን ተመ.

**በሽታ** "**በሸተ**" ስር ተመ.

**በሽ አለው** "**ብሽ**" ስር "**ብሽ አለው**"ን ተመ.

**በቀለ** ግ 1.አጎነቆለ÷ የብቅል ጭራ አወጣ (በውሃ ተርሶ የተቀመጠ እህል):: 2. ከማሳ ላይ የተዘራው ዘር (የእህል ወይም የሌላ እፅዋት ፍሬ) ተስማሚውን አፈር÷ አየርና ርጥበት ሲያገኝ እምቦቀቅላ ግንዱንና ቅጠሉን በትንሹ ከአፈር ውስጥ ብቅ አደረገ÷ ፀደቀ:: 3. ወጣ÷ አቀመቀመ (ፀጉር)::

**_በቀል** ቅ 1. ሆኖ የበቀለ÷ የወጣ÷ የተገኘ:: *አንድ በቀል ዛፍ:* 2. _ደራ÷ አደግ:: *አብሮ በቀል::* 3 . የ _ውስጥ:: *አገር በቀል::*

**በቆልት (በቀልት÷ በቆልቲ)** ስ በውሃ ርሶ የበቀለ ወይም የጎነቆለ ባቄላ ወይም ሌላ ጥሬ::

**ቡቃያ(ብቋያ)** ስ አዲስ የበቀለ ወይም ከበቀለ ብዙ ጊዜ ያልሆነው÷ በማደግ ላይ ያለ የእህል ሰብል::

**ብቅል** ስ ጠላ ለማዘጋጀት (ለመጥመቅ) ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ የሆነ÷ ለተወሰነ ጊዜ በውሃ ርሶ ከቆየ በሂላ በቅጠል ተሸፍኖ ጉድጓድ ውስጥ ወይም በተመሳሳይ ቦታ እንዲቀመጥ ተደርጎ የበቀለ ገብስ ÷ ስንዴ÷...::

**ብቅል ረገጠ** ገብስን ወይም ስንዴን ለተወሰነ ጊዜ በውሃ ውስጥ ነክሮ ካቆየ በሂላ ከውሃው ለይቶና ጉድጓድ ውስጥ በቅጠል ጀቡኖ በማስቀመጥ ብቅል እንዲሆን አደረገ::

**ብቅል አውራጅ** በጣም ረዥምም የሆነ (ሰው)::

**አበቀለ** ግ1. አጎነቆለ÷ አፈጠፈጠ:: 2. አቀነቀነ÷ አቀመቀመ(ፀጉር):: 3. አወጣ÷ አፈራ:: *አገር ሲያረጅ ጃርት ያበቅላል::*

**በቀል** ስ 1. ቂም:: 2. የክፉ ድርጊት ክፉ ምላሽ::

**በቀለኛ** ቅ ቂመኛ÷ ተበቃይ::

**ተበቀለ** ግ ቂሙን ተወጣ÷ ለተፈፀመ ክፉ ድርጊት ምላሹን በክፉ ሰጠ::

**_በቀል** "**በቀለ**" ስር ተመ.

**በቀልቲ** "**በቀለ**"ስር "**በቆልት**"ን ተመ.

**በቀልት** ዝ.ከ.

**በቀረ** "**ቀረ**" ስር ተመ.

**በቀር** ዝ.ከ.

***በቀቀ**

**ተንባቀቀ** ግ ተሰነጣጠቀ÷ ተላቀቀ÷ ተከፋፈተ (ኮትቻ መሬት በበጋ ወራት)::

**አንባቀቀ(አምባቀቀ)** ግ አዛጋ÷ አፋሸከ÷ አፉን አለልክ ከፈተ::

**በቀቀን** ስ መንቆሩ ወደታች ቆልመም ያለና ቀለሙ ደማቅ የሆነ የሰዎችን ንግግርም ሆነ ሌሎች ድምፆችን ማስመሰል የሚችል ወፍ(ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)::

**በቀበቀ** ግ ሰነጠቀ÷ ተረተረ÷ ማረሻውን አጥልቆ አረሰ::

**በቀበቅ** ስ የተገመሰ÷ የታረሰ መሬት::

**ተንበቀበቀ** ግ በቅ በቅ አለ÷ አፈ ጠባብ ከሆነ እቃ ውስጥ ውሃ ሲቀዳ (ሲንቆረቆር) የሚሰጠውን

አይነት ድምፅ ሰጠ፤ ተንደቀደቀ።

**አንበቀበቀ** ግ በቅ በቅ የሚል ድምፅ አሰማ (ለምሳሌ ከቅል ውስጥ ውሃ ሲቀዳ የሚሰማውን የድምፅ አይነት አሰማ)።

**በቀተ**[1] ግ ነዘነዘ፥ ነተረከ፥ ጨቀጨቀ።

**በቀታ(ብቀታ)** ስ ንዝነዛ፥ ጭቅጨቃ።

**በቀተ**[2] ግ ተሰደደ፥ አገር ጥሎ ሄደ።

**በቀት** ስ ስደት፥ አገር ጥሎ መሄድ።

**በቀደም "ቀደመ"** ስር ተመ.

**በቂ "በቃ"** ስር ተመ.

**በቃ** ግ 1. ልክ፥ በቂ ሆነ (ልብስ፥ ቦታ፥...)። 2.አለቀ፥ ተፈፀመ። *የእርሱ ነገር በቃ*: 3. ተሰለቸ፥ ተጠገበ፥ የማያስፈልግ ሆነ። *እስኪበቃው በላ*: 4. ደረሰ። *ለትዳር በቃ*: 5. ቻለ። *ጥሮ ግሮ አላማውን ለማሳካት በቃ*: 6. ከሃጢአት ነፃ፥ እግዚአብሄር ቀረበው፥ ፍፁም ፃድቅ ሆነ። *ሃጢአተኞች የነበሩም ከብዙ ተጋድሎ በሂላ ሊበቁ ችለዋል*። 7.ቀረ፥ ቆመ፥ ተተወ። *እንደልጅነት ጊዜ መሆን በቃ*: 8.የመጨረሻ ውሳኔ መሆኑን ለመግለፅ የሚነገር አባባል። *በቃ እሰጥሃለሁ / በቃ በዚህ እኔ አልስማማም።*

**በቃህ በለው** ማረው፥ ይቅር በለው፥ ተወው።

**በቃኝ** አልሻም፥ አልፈልግም።

**ለ __ በቃ** ለ __ ደረሰ። *ለትዳር በቃ።*

**የበቃ** ቅ ፍፁም ፃድቅ የሆነ።

**የበቃ የነቃ** ያወቀ፥ የተመራመረ።

**በቂ(የሚበቃ)** ቅ ልክ፥ አጥጋቢ። *ምክንያቱ በቂ ነው።*

**በቂ ቅፅል** ስ እንደ ስም ሆኖ ሊያገለግል የሚችል ቅፅል። (ለምሳሌ ሚች፥ ገዳይ፥...)።

**ብቁ** ቅ 1.ተገቢ፥ ተስማሚ ተፈላጊ ችሎታ፤ እውቀት፥...። *ብቁ ባለሙያ*: 2. በቂ።

**ብቃት** ስ 1. ሙሉነት፥ ተገቢነት፥ ተስማሚነት። 2.ፍፁምነት፥ ቅዱስነት።

**ብቅት አለ** ግ 1. ሰውነቱ ተጎዳ፥ ከሳ። 2. ተዳከመ ፥ ሊሞት ደረሰ።

**ተባቃ** ግ 1.ተዳረሰ። 2.ለጠብ፥ለኩርፊያ፥ ለመጋደል፥... ደረሰ። *ለዱላ የተባቃነው በርሷ ምክንያት ነው።*

**ተብቃቃ** ግ ተዳረሰ።

**አበቃ** ግ 1.ጨረሰ፥ ፈፀመ። 2. ከሳ፥ ደከመ፥ ወደደቀ። 3. አረጀ፥ አፈጀ። 4.አለቀ። *ስራው አበቃ።*

**አባቃ** ግ 1.አዳረሰ። 2.ለፀብ፥ ለኩርፊያ፥... አደረሰ።

**አብቃቃ** ግ እንዲበቃ፥ በቂ እንዲሆን አደረገ።

**በቅሎ** ስ 1.በአባቱ አህያ በእናቱ ፈረስ የሆነ፥ ለጭነት (ሰውን ወይም እቃን ለማጓጓዝ) የሚያገለግል የጋማ ከብት(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)። 2.(ዘይ.፥ ስድብ) ልትወልድ የማትችል፤ መሃን (ሴት)።

**በቅጡ(በቅጥ) "ቅጥ"** ስር ተመ.

**በቆልት "በቀለ"** ስር ተመ.

**በቆሎ (ቦቆሎ)** ስ በቆላና በወይና ደጋ ሊበቅል የሚችል፥ ቅጠሉ ሾጠጥ ብሎ ርዝመት ያለው፥ ድርብርብ በሆነ ሽፋን ተጠቅልለው የሚገኙ ብዙ ፍሬዎች ያሉት የአገዳ እህል አይነት፤ የባህር ማሽላ፤ ባርማሽላ። ተክሉም በቆሎ ይባላል።

**በቋል(በቋሊ)** ስ በእህል ሰብል ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ የወፍ አይነት፤ ጥሬ ፈጅ ወፍ፤ ጨረባ።

**በተሃ** ስ ጌሾ ያልበዛበት ለጋ ጠጅ።

**በተለይ "ለየ"** ስር ተመ.

**በተቀር "ቀረ"** ስር **"በስተቀር"** ን ተመ.

**በተበተ** ግ ቦጠቦጠ፥ ውስጥ ውስጡን በላ፤ በተቦተ።

**በተተ** ግ አረጀ፥ አለቀ፥ ተቀዳደደ (ልብስ)።

**ቡትቶ(ብቱቶ፥ብትቶ)** ስ እላቂ፥ ድሪቶ፥ የተቀዳደደ አሮጌ ልብስ።

**ቡትቷም** ቅ (ስድብ) 1. የተቀዳደደና የተጣጣፈ ልብስ የሚለብስ። 2. (ዘይ.) ዝባዝንኪያም።

**በተነ** ግ 1.ረጨ፥ ዘራ። 2. ለያየ፥ ለየብቻ አደረገ (በአንድነት የነበረን ነገር)። 3. አባከነ፥ ያለአግባብ አጠፋ (ገንዘብን) ። 4. (ስብሰባን ፥ አድማን፥...)እንዲቆም፥ እንዲቋረጥ፥ እንዲቀር፥... አደረገ።

**ብትን** ቅ በአንድነት ያይደለ፥ ተለያይቶና ለየብቻ ሆኖ የሚገኝ።

**ብትን ድልህ** ስ በውሃ ያልታሸ ወይም ያልተላቀጠ የበርበሬ ዱቄት።

**ብትን ጨርቅ** ስ ገና ያልተሰፋ በጣቃ ወይም በነዶ ደረጃ ያለ ጨርቅ።

**ብትንትኑ ወጣ** ተበታተነ።

**ተበተነ** ግ 1. ተረጨ፥ ተሰራጨ፥ ተዘራ። 2. ተለያየ፥ በየፊናው ሄደ።

**ተበታተነ** ግ ተበተነ።

**በተከ** ግ ቆረጠ፥ በጠሰ፥ በጠቀ፥ በሰከ።

**ብትክትክ** ቅ ቁርጥርጥ፥ብጥስጥስ፥ ብጥቅጥቅ፥ ብስክስክ።

**ተብተከተከ** ግ 1. ተበጣጠሰ፥ ተበጣጠቀ፥

**በዓል** (ብ.ቁ. **በዓላት**) ስ በሳምንት ወይም በወር ወይም በዓመት አንድ ቀን የሚከበር፥ ስራ የማይሰራበትና ታርፎ የሚዋልበት ቀን (ለምሳሌ ሰንበት፥ ጥምቀት፥...የሚውልበት ቀን)።

**በዓል አከበረ** በበዓል ምክንያት ስራ ሳይሰራ አርፎ ዋለ።

**በዓለ_** የ_በዓል። *በዓለ ልደት።*

**የበዓል ቀን** ስ በበዓል ምክንያት ስራ ሳይሰራበት ተከብሮ የሚውል ቀን።

**በእንተ(በንተ)** ስለ። *ምፅዋት ጠያቂው በእንተ ማርያም እያለ ይለምናል።*

**በከለ** ግ 1. አበላሸ፥ አቆሸሸ፥ አጠፋ (ስምን፥ ልብስን፥ አየርን፥...)። 2. አስተላለፈ፥ አጋባ (በሽታን፥ መጥፎ ባህርይን፥ አስተሳሰብን)።

**ብክላ** ስ የማበላሸት፥ የማቆሸሸ፥ የማጥፋት ድርጊት።

**ተበከለ** ግ ተበላሸ፥ ቆሸሸ፥ ጠፋ።

***በከረ**

**በኩረሎሚ(በህረ ሎሚ፥ በትረ ሎሚ)** ስ ጣእሙም ሆነ መልኩ ብርቱካን የሚመስል፥ መጠኑ ከሎሚ በለጥ ከብርቱካን አነስ ያለ የሎሚ አይነት(ስእሉን ፍራፍሬ ስር ተመ.)።

**በኩር(በክር፥በህር)** ቅ 1. አንጋፋ፥ የመጀመሪያ (ልጅ)። 2. አለቃ፥ ታላቅ፥ ግንባር ቀደም።

**በኩራት** ስ በኦሪት ህግ መሰረት ለቤተመቅደስ ይሰጥ የነበረ የሰውም ሆነ የእንስሳ የመጀመሪያ ልጅ፤ እንዲሁም መጀመሪያ የደረሰ የሰብል ፍሬ።

**ብኩርና** ስ 1. በኩር መሆን። 2. ልቅና (እልቅና)።

**በካር** ቅ ወልዳ የማታውቅና መውለድ የመጀመሪያ ጊዜዋ የሆነ (ሴት)።

**ተበከረች** ግ ለመጀመሪያ ጊዜ ወለደች።

**አበከሮ** ተው.ግ. 1. አስቀድሞ፥ ቀደም ብሎ። *ጉዳዩን አበከሮ ነው የነገረኝ።* 2. አጠንክሮ፥ አስተንክሮ።

**በክራ**[1] ስ ታላቅ የጋሻ አይነት።

**በክራ**[2] ስ 1.መካከሉ ቀጠን ያለ፥ ዳርዳሩ እንደ እንዝርት ራስ ክብ የሆነ፥ መሃሉ ላይ በክር ታስሮ ወደላይና ወደታች ሲወረውሩት የሚጠቀለልና የሚተረተር የልጆች መጫወቻ። 2. የስፌት መኪና ክር ማጠንጠኛ ወይም ክሩ የሚጠመጠምበት እንጨት።

***በከበከ**

**ተንበከበከ** ግ ተንደከደከ፥ ፈላ (ለምሳሌ የሽሮ ወጥ፥ የጠላ ድፍድፍ)።

**አንበከበከ** ግ አንደከደከ፥ አፈላ።

**በከተ** ግ 1. በሰበሰ፥ ገማ፥ ከረፋ:: 2. በጣም ራሰ፥ ረሰረሰ (በውሃ፥ በዝናብ):: 3. አደፈ:: 4. ተባርኮ ሳይታረድ ሞተ (ከብት)::

**በክት** ቅ 1. የጠነባ፥ የበሰበሰ:: 2. ሳይባረክ ወይም ሳይታረድ የሞተ (ከብት):: 3. (ስድብ) የማይረባ፥ ደደብ::

**በ__በኩል** 1. ከስም፥ ከተውላጠ ስም፥...ጋር እየተቀናጀ አቅጣጫን ለማመልከት የሚነገር ቃል:: *በታች በኩል/ በቀኝ በኩል*፥...:: 2. ከስም፥ ከተውላጠ ስም፥...ጋር እየተቀናጀ ድርሻን፥ ፈንታን፥ ሃላፊነትን ለመጠቆም የሚያገለግል ቃል:: *በእኔ በኩል ችግር የለም::*

**በኩረ ሎሚ** "***በከረ**" ስር ተመ.

**በኩራት** ዝ.ከ.

**በኩር** ዝ.ከ.

**በካር** ዝ.ከ.

**በከር** "***በከረ**" ስር "**በኩር**"ን ተመ.

**በክት** "**በከተ**" ስር ተመ.

**በወዘ** ግ ቀላቀለ፥ ደባለቀ::

**ብወዛ** ስ ማቀላቀል፥ ማደባለቅ::

**በዘበዘ** ግ 1. ዘረፈ፥ ገፈፈ፥ ቀማ፥ መዘበረ:: 2. አይንን እንፀባረቀ፥ አጥበረበረ፥ አፈዘዘ፥ ማየት ከለከለ::

**በዝባዥ** ቅ 1. ዘራፊ፥ ቀማኛ፥ ገፋፊ:: 2. ሰራተኛው ለሚያፈሰው ላብ ተገቢውን ክፍያ የማይሰጥ፥ በሰራተኛ ጉልበት አላግባብ የሚጠቀም::

**ብዝበዛ** ስ 1. ዘረፋ፥ ቅሚያ፥ ገፈፋ:: 2. የሰራተኛውን ጉልበት ያለ ተገቢው ክፍያ መጠቀም::

**ተበዘበዘ** ግ ንብረቱን፥ ጉልበቱን ያለአግባብ፥ ያለበቂ ክፍያ ተነጠቀ::

**ተበዝባዥ** ቅ እንደ ሶሻሊዝም ርእዮተ አለም አመለካከት፥ ለጉልበቱ ዋጋ ተገቢውን ክፍያ ሳያገኝ ለካፒታሊስቱ የሚሰራ፤ ምዝብር፤ ጭቁን::

**በዘፈቀደ** "**ፈቀደ**" ስር ተመ.

**በዚህ(በይህ)** "**እዚያ**" ስር ተመ.

**በዚህም በዚያም** ዝ.ከ.

**በዚያ** ዝ.ከ.

**በዛ** ግ 1. ከልክ፥ ከመጠን አለፈ፥ በረከተ:: 2. ወለደ፥ ረባ::

**ሲበዛ** 1. በሃይል፥ በጣም፥ ከመጠን በላይ:: *ሲበዛ ተናዳጅ ነው::* 2. ከመጠን ሲያልፍ:: *ሲበዛ ማርም ይመራል::*

**ቢበዛ** ቢጠና፥ ግፋ ቢል:: *ዋጋው ቢበዛ አስር ብር ቢሆን ነው::*

**ብዙ** ቅ አያሌ፥ በርካታ::

**ብዙሃኑ [ህዝብ]** ስ አብዛኛው፥ ሰፊው ህዝብ::

**ብዙ ቁጥር** ስ (ሰዋ.) ቁጥሩ ከአንድ በላይ ለሆነ ነገር (ስም፥ ቅፅል፥...) የተሰጠ መጠሪያ (ለምሳሌ የመምህር ብዙ ቁጥር መምህራን፥ የከቡር ደግሞ ከቡራን ነው)::

**ብዙ ጊዜ** ተው.ግ. በተደጋጋሚ::

**ብዛት** ስ 1.የአንድ ነገር ቁጥር፥ መጠን:: 2. አያሌ፥ በርካታ መሆን፥ በቁጥር፥ በመጠን ከፍ ማለት::

**ተባዛ** ግ 1. ተበራከተ:: 2. ተዋለደ፥ በዛ:: 3. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ያሉ ቁጥሮች እርስ በርሳቸው ተባዝተው ማስገኘት የሚችሉትን የቁጥር መጠን ያህል እንዲያስገኙ ሆነ:: (ለምሳሌ 2X4=8)::

**አበዛ** ግ 1. አበረከተ፥ ብዙ አደረገ:: 2. የማብዛት ስሌት ሰራ::

**አበዛው** ከመጠን በላይ አደረገ፥ ከገደብ አሳለፈ (ብዙውን ጊዜ መጥፎ ድርጊትን)::

**ማብዛት(ማባዛት)** ስ 1. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቁጥሮች እርስ በርሳቸው ተባዝተው የሚሰጡትን ትልቅ ቁጥር እንዲያስገኙ የሚያደርግ የስሌት መንገድ:: ለምሳሌ 3 X 2=6:: 2. ከአራቱ የሂሳብ መደቦች የአንዱ መጠሪያ::

**የማብዛት(የማባዛት) ምልክት** ስ ሁለት ወይም ከሁለት የሚበልጡ ቁጥሮች እርስ በርስ መባዛታቸውን ወይም የሚባዙ መሆናቸውን ለማሳየት በግራ በኩል ከቁጥሮቹ ጎን ወይም በቁጥሮቹ መሃል የሚቀመጥ ምልክት /X/::

**አብዛኛው** ብዙው፥ ይበልጡ::

**አባዛ** ግ 1. አንድን ፅሁፍ ወይም ስእል፥...ብዙ ቅጅ ወይም ኮፒ እንዲወጣው አደረገ:: 2. አበራከተ፥ ብዙ እንዲሆን አደረገ:: 3. አራባ፥ አዋለደ:: 4. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ቁጥሮች እርስ በርሳቸው ተባዝተው የሚፈለገውን ከፍተኛ ቁጥር እንዲያስገኙ አደረገ::

**የማባዣ መኪና** ስ አንድን ፅሁፍ፥ ስእል፥...እንዳለ ዋናውን አስመስሎ በተፈለገው ብዛት አትሞ የሚያወጣ ወይም የሚያራባ መኪና::

***በዛበዘ**

**በዝባዛ** ቅ አሰልቺ፥ ነገር ከጀመረ በቶሎ የማይተው (ሰው)::

**ተምበዛበዘ** ግ ተንዛዛ፥ አሰልቺ ሆነ::

**አምበዛበዘ** ግ አንዛዛ፥ አሰለቸ፥ አሰልቺ አደረገ::

**በዝባዥ** "በዘበዘ" ስር ተመ.

**በዣድ(በጀድ)** ስ ከእምብርት በታች ከብልት በላይ በግራና በቀኝ ያለ የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**በየ___** በማንኛውም፥ በሁሉም፥ በያንዳንዱ። *በየቦታው ይታያል።*

**በየነ** ግ 1. ደነገገ፥ ስርአት አበጀ። 2. ወሰነ።

**በያኝ** ቅ ፈራጅ፥ ወሳኝ፥ ዳኛ።

**ብያኔ** ስ 1. ውሳኔ። 2. ድንጋጌ፥ ደንብ፥ ስርአት።

**ብይን** ስ ውሳኔ።

**ብይን ሰጠ** የቀረበውን የክስ ጭብጥ መርምሮ ሊያስከስስ ወይም ላያስከስስ ይችል እንደሆነ በመለየት ውሳኔ ሰጠ።

**አስበየነ** ግ አስወሰነ።

**በየደ** ግ የተሰበረን ወይም የተሸነቆረን ብረት ወይም ብረት ነክ እቃን ቀላጭ ብረት እያፈሰሰ በከፍተኛ የሙቀት ሃይል እርስ በርሱ እንዲያያዝ አደረገ፤ ተከሰ፥ ደፈነ፥ ጠገነ።

**በያጅ** ስ ብረታ ብረት የሆኑ ነገሮችን እያቀለጠ በማያያዝ፥ በመድፈን፥...የሚሰራ ባለሙያ።

**ብይድ** ቅ በማቅለጥ የተደፈነ፥ የተበየደ (ብረት ነክ እቃ)።

**በያኝ** "በየነ" ስር ተመ.

**በይበልጥ** "በለጠ[1]" ስር "በበለጠ" ን ተመ.

**በደለ** ግ 1. በሌላው ላይ ክፉ ስራ ሰራ፥ ተገቢ ያልሆነ ነገር ፈፀመ። 2. ጎዳ። *አካባቢው ተፈጥሮ የበደለው ነው።*

**በደለኛ** ቅ 1. በሌላው ላይ በደል የፈፀመ፥ ጥፋተኛ፥ ስህተተኛ፥ ግፈኛ፥ በዳይ። *አምናለሁ በደለኛ ነኝና ይፈረድብኝ*። 2. ተበዳይ፥ በደል፥ ግፍ የተፈፀመበት፥ የተጠቃ፥ የተበደለ። *በደለኛው እኔ ነኝና ፍረዱልኝ።*

**በደል** ስ ተገቢ ያልሆነ ስራ፥ ግፍ፥ ጥፋት።

**በዳይ** ቅ በደል ፈፃሚ።

**ተበደለ** ግ 1.በደል ተዋለበት። 2. ተጎዳ።

**ተበዳይ** ቅ በደል የተፈፀመበት፥ ተጠቂ።

**ተባደለ** ግ ያንዱ ወገን በዛ የሌላው አነሰ፥ እኩል ለእኩል ሳይሆን ቀረ።

**ተባዳላ** ስ ያንዱ ወገን በዝቶ የሌላው አነስ ማለት፥ ያለ መመጣጠን። *ቀርቃባው ተባዳላ ሆኗል።*

***በደረ**

**ብድር** ስ 1. ለተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞ ለመመለስ ከሌላው ዘንድ የሚወስድ ወይም የተወሰደ ገንዘብ። 2. በተወሰደው መጠን፥ ተመሳሳዩን ከተወሰነ ጊዜ በሗላ ለመመለስ ቃል ተገብቶ የሚወሰድና ለራስ ግልጋሎት የሚውል የሌላ ሰው ንብረት (ለምሳሌ እህል)። 3. ውለታ፥ወሮታ፥ በጎ ምላሽ። 4. ክፉ ምላሽ፥ አፀፋ። *እንደተበደብኩ ላልቀርም ብድሬን እመልሳለሁ*። 5.እዳ።

**ብድሩን መለሰ** 1. ውለታውን ከፈለ። 2. እዳውን ከፈለ። 3. ቂሙን ተወጣ፥ ተበቀለ፥ ለተፈፀመው ክፉ ድርጊት አፀፋውን መለሰ።

**ብድር ይድረሰው** እንደ ስራው ያግኝ፤ ለሰራው ስራ አፀፋውን ወይም ተገቢውን ያግኝ።

**ብድራት** ስ ለተፈፀመ ጥሩ ወይም መጥፎ ድርጊት የሚመለስ ጥሩ ወይም መጥፎ አፀፋ።

**ተበደረ** ግ 1. ለተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞ ለመመለስ ከሌላ ሰው ወሰደ (ለምሳሌ ገንዘብን)። 2. በወሰደው መጠን ያንኑ የሚመስል ለመመለስ ቃል ገብቶ የሌላ ሰው እህል፥...ወሰደ።

**ተበዳሪ** 1. ለተወሰነ ጊዜ ተጠቅሞ በውለታው መሰረት ለመመለስ የሌላ ሰው ገንዘብ የወሰደ ወይም የሚወስድ። 2. በወሰደው መጠን ተመሳሳዩን ወይም አይነቱን ለመመለስ ቃል ገብቶ የሌላውን እህል፥...የወሰደ ወይም የሚወስድ። 3. መበደር የሚያዘወትር።

**አበደረ** ግ ብድር ወይም በብድር ሰጠ።

**አበዳሪ** ስ 1.ብድር ወይም በብድር የሚሰጥ (ሰው)። 2. ገንዘብ ያለውና ለሌላ እያበደረ የሚጠቀም።

***በደረገ**

**በድረግ(በርደግ) አለ** ግ ድንገት አፈፍ፥ ፈጠን ብሎ ተነሳ።

**ተበደረገ** ግ አፈፍ፥ ፈጠን ብሎ ተነሳ።

***በደበደ**

**በድባዳ(በደበድ)** ቅ 1. ቀጥቃጣ፥ እርብትብት። 2. ፈሪ፥ ቡከን።

**ተንበደበደ** ግ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ፥ ፈራ።

**አንበደበደ** ግ አራደ፥ አንቀጠቀጠ፥ አስጨነቀ።

**እንብድብድ** ቅ ቀጥቃጣ፥ ፈሪ፥ ቡከን።

**በደነ** ግ 1. ደነዘዘ፥ ፈዘዘ፥ እንደ በድን ሆነ። 2. የማይሰማ፥ የማይለማ ሬሳ ሆነ፤ ሞተ፥ በድን ሆነ።

**በድን** ስ 1. ሙት፥ ሬሳ፥ ነፍሱ ከስጋው የተለየች አካል። 2. (ዘይ.) የደነዘ፥ የፈዘዘ፥ ከሙት የማይሻል።

**በዳ** ግ (ነውር) ወንድ ሴትን በግብረ ስጋ ተገናኘ።

**በዴ** ቅ (ነውር) ከተለያዩ ሴቶች ጋር የግብረ

ስጋ ግንኙነት ማድረግ የሚያዘወትር።

**ብድ** ስ (ነውር) የግብረስጋ ግንኙነት ድርጊት።

**በዳይ "በደለ"** ስር ተመ.

**በድባዳ "*በደበደ"** ስር ተመ.

**በድን "በደነ"** ስር ተመ.

**በጀ**[1] ግ ረባ፥ ጠቀመ፥ ተሻለ። *የሚበጀውን ያውቃል።*

**በጀ**[2] ግ 1. ደግ፥ መልካም አደረገ። *በጅተሃል እንኳን መጣህ።* 2• ደግ፥ መልካም፥ ጥሩ ሆነ። *መምጣትህ በጀ እንጂ አትሰማም ነበር።*

**ተበጀ** ግ ተሰራ።

**ተበጃጀ** ግ 1. ተሰራ። 2. ተጊያጊያጠ፥ ተቆነጃጀ።

**አበጀ** ግ 1. ሰራ፥ አዘጋጀ። 2. መልካም፥ ጥሩ፥ ደግ አደረገ። 3. አፈራ፥ አገኘ። *ዘመድ ኣበጅቷል።*

**አበጃጀ** ግ 1. ሰራ፥ አዘጋጀ። 2. አሰማመረ፥ አቆነጃጀ።

**በጀት(ባጀት)** ስ ለስራ ማስኬጃ ወይም ለእቅድ ማስፈፀሚያ የሚመደብ ገንዘብ።

**የበጀት ኣመት** ስ ለስራ ማስኬጃ ወይም ለእቅድ ማስፈፀሚያ ተብሎ የሚመደብ ገንዘብ ስራ ላይ ሊውል የሚችልበት የተወሰነ ጊዜ (ኣንድ ኣመት)።

**በጀድ "በዠድ"** ን ተመ.

**በጄ** እሺ፥ ይሁን።

**በጅሮንድ** ስ ቀደም ባለው ጊዜ የነበረ የመንግስት ግምጃ ቤት ሃላፊ፤ የገንዘብ ሹም።

**በገረ**[1] ግ 1. ለካ፥ መጠነ፥ ምልክት አበጀ፥ ነደፈ። 2. ቀየሰ፥ መሰረት ጣለ፥ ቆረቆረ፥ ጀመረ።

**ቢጋር** ስ 1. ንድፍ፥ ምልክት። 2. ቅያስ፥ ጅምር።

**በገረ**[2] ግ ሞከረ፥ ደፈረ።

**ኣይበገርም** ኣይረታም፥ ኣይሸነፍም።

**በገበገ** ግ 1. ኣቃጠለ፥ በላ (እሳት፥ ቁስል)። 2. ገረፈ፥ ኣሳመመ፥ ኣቆሰለ።

**በገነ** ግ 1. ተቃጠለ፥ ኣረረ፥ ከሰለ። 2. በጣም ተናደደ፥ ጠፈ።

**ብገን** ስ ኣዘውትሮ እሳት ዳር በሚቀመጥ ሰው ቅልጥም ላይ የሚታይ የቆዳ መልክ መቀየርና ጉበት መምሰል፥ መደደር።

**ብገናም** ቅ (ስድብ) ብገን ያለበት።

**ኣበገነ** ግ 1. በጣም ኣሳመመ፥ ኣበሰለ። *ኣብግኖ መታው።* 2. ኣናደደ፥ ኣበሸቀ።

**ኣብግን** ቅ ኣናዳጅ፥ ኣብሻቂ።

**በገና** ስ ባለ ኣስር ኣውታር (ጅማት) የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**በገና መታ /ደረደረ** በገና ተጫወተ።

**በገና መች(ደርዳሪ)** ስ በገና ተጫዋች፤ በገነኛ።

**በገነኛ** ስ በገና መች።

**በገፊጅ "በግ"** ስር ተመ.

**በጋ** ስ 1. ከኣራቱ ኣመታዊ ወቅቶች ኣንዱ የሆነ፥ በመፀውና በፀደይ መካከል ያለ፥ ከታህሳስ 26 እስከ መጋቢት 25 ቀን ድረስ ያለው ፀሃይና ድርቅ የሚበዛበት ወቅት። 2. ከመስከረም እስከ ግንቦት ያሉትም ዘጠኙ ወራት በተለምዶ የበጋ ወራት እየተባሉ ይጠራሉ።

**በግ** ስ 1. ስጋው ለምግብ፥ ፀጉሩና ቆዳው ለልብስ የሚሆን፥ የላይ የፊት ጥርስ የሌለው ሳረበል የቤት እንስሳ(ስእሉን የቤት እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.፥ ስድብ) ሁ•ሞኝ፥ ቂል፥ የዋህ። ሉ• የፃድቅ ምሳሌ።

**በገፊጅ** ስ የኣንድ በግ ስጋ በኣንድ ጊዜ መቀቀል የሚችል ትልቅ ድስት።

**በጋማች (በግኣማች)** ስ በቀድሞ ጊዜ በግ እያረደ ይሸጥ የነበረ የስጋ ነጋዴ።

**በጎ** ቅ ደህና፥ ደግ፥ ማለፊያ፥ መልካም።

**በጎ ሆነ** 1.ተሻለው፥ ዳነ፥ ተፈወሰ። 2. ጥሩ፥ መልካም፥ ደግ ሆነ።

**በጎ ምግባር** ስ መልካም ስራ፥ ደገኛ ምግባር።

**በጎ ኣድራጊ** ቅ ለጋሽ፥ ችሮታ ኣድራጊ።

**በጎ ኣድራጎት** ስ ድሆችን፥ ኣቅመ ደካሞችን፥... ለመርዳት የሚደረግ መልካም ስራ።

***በጠለጠለ**

**ብጥልጣይ** ቅ የተበጫጨቀ፥ የተቀደደ።

**ብጥልጥል ኣለ** ግ ተብጠለጠለ።

**ተብጠለጠለ** ግ 1.ተቀዳደደ፥ ተበጫጨቀ። 2. ስሙ በሃሜት ክፉኛ ጠፋ ወይም ጎደፈ።

**ኣብጠለጠለ** ግ 1. ቀዳደደ፥ በጫጨቀ፥ ቆራረጠ። 2. ኣማ፥ በሃሜት የሌላውን ስም ኣጎደፈ።

***በጠረ**[1]

**ብጣሪ** ስ ከእህል ውስጥ በሰፌድ ወይም በማበጠሪያ ተለይቶ የወጣ ኣሰር፥ ንፋሽ፥...።

**ብጥር** ቅ ከቆሻሻው፥ ከንፋሹ ተለይቶ የወጣ፥ የጠራ፥ ጥሩ (እህል)።

**ብጥር ያለ** ጥሩ፥ ንፁህ፥ እንከን የሌለበት።

**ብጥርጥር አደረገ** ግ 1. አበጠረ። 2. (ዘይ.) አጣርቶ መረመረ፥ ፈተሸ። 3. ለያየ፥ ብትንትን፥ ግልፅልፅ አደረገ፥ ተነተነ።

**ተበጠረ** ግ ተነፈሰ፥ ተንጓለለ፥ ተፈላጊው ፍሬ ከአሰር ተለየ።

**አበጠረ** ግ 1. አነፈሰ፥ አንጓለለ፥ ጥሩውን ከመጥፎው ለየ። 2. (ዘይ.) አጣርቶ መረመረ፥ ፈተሸ።

**ማበጠሪያ** ስ ማንፈሻ፥ ማንጠርጠሪያ፥ ፍሬን ከገለባ መለያ ሰፌድ ወይም ሌላ ነገር።

***በጠረ**[2]

**ተበጠረ** ግ በሚዶ ተነቀሰ (ፀጉር)።

**አበጠረ** ግ ፀጉርን በሚዶ አፍታታ፥ ነቀሰ፥ አሳመረ።

**ማበጠሪያ** ስ ሚዶ፥ የፀጉር መንቀሻ።

***በጠረረ**

**በጥራራ(በጠረር)** ቅ ኩራተኛ፥ ትእቢተኛ።

**ተንበጣረረ(ተንበጠረረ)** ግ ተጓደደ፥ ተጀነነ፥ ተኩራራ።

**አንበጣረረ(አንበጠረረ)** ግ አኩራራ፥ ጀነነ።

**በጠሰ** ግ ቆረጠ፥ ጎመደ፥ በሰከ፥ በተከ።

**በጣሳ** ቅ 1. አቅመቢስ፥ በቀላሉ የሚበስክ፥ የሚቆረጥ። 2. (ዘይ.) ኩራተኛ፥ ትእቢተኛ።

**ብጣሽ** ቅ 1. ጉራጅ፥ ጉማጅ፥ ቁራጭ። 2. ትንሽ። *ብጣሽ ወረቀት ልኮልኝ አያውቅም።*

**ብጣሻም** ቅ (ስድብ) 1. ጎደሎ፥ ምናምንቴ፥ የማይረባ። 2.(ዘይ.) ያለአቅሙ የሚኮራ፥ ኩራተኛ።

**ብጥስ** ቅ የተቆረጠ፥ የተጎመደ።

**ብጥስጥስ** ቅ 1.ብስክስክ፥ ብትክትክ፥ ቁርጥርጥ። 2. የተቀዳደደ፥ የተበጫጨቀ፥ እላቂ (ጨርቅ)። 3. ምናምንቴ፥ ቆሻሻ። 4.(ዘይ.) ኩራተኛ፥ ያለአቅሙ የሚምበጣረር።

**ብጥስጣሽ** ቅ 1.ቁርጥራጭ። 2. ምናምንቴ፥ ቆሻሻ።

**ተበጠሰ** ግ ተቆረጠ፥ ተጎመደ፣ ተበሰከ፥ ተበተከ።

**ተበጣሽ** ቅ አቅመቢስ፥ በቀላሉ ሊጎመድ የሚችል።

**ተበጣጠሰ** ግ 1. ተበታተከ፥ ተበሳሰከ፥ ተጎማመደ። 2. ተበላሸ (ወተት)። 3. (ዘይ.) ተኩራራ፥ ተንቀባረረ።

**ተብጠሰጠሰ** ግ 1.ተበላሸ(ወተት)። 2. (ዘይ.)ተኩራራ፥ ተንቀባረረ።

**አብጠሰጠሰ** ግ 1.አኩራራ፥ አንቀባረረ፥ አሞላቀቀ። 2. አብሰከሰከ፥ የአእምሮ እረፍት አሳጣ፥ አቅበጠበጠ።

**በጠቀ** ግ በጨቀ፥ በጠሰ፥ ቆረጠ፥ በሰከ።

**በጣጠቀ** ግ በጫጨቀ፥ በጣጠሰ፥ ቆራረጠ፥ በሳሰከ።

**ብጥቅጥቅ(ብጥቅጣቂ)** ቅ ብጭቅጭቅ፥ ብጥስጥስ።

**ተበጣጠቀ** ግ ተበጫጨቀ፥ ተበጣጠሰ፥ ተቆራረጠ፥ ተበሳሰከ።

**በጠበጠ** ግ 1.ደበላለቀ፥ ቀላቀለ፥ አዋሃደ (ድፍድፍን ወይም ሽሮን፥... ከውሃ ጋር)። 2.አደፈረሰ፥ ጠርቶ ወይም ኮለል ብሎ የነበረውን የምንጭ ወይም የወንዝ ውሃ ከጭቃ ጋር አቀላቀለ። 3. ረበሸ፥ አወከ፥ ፀጥታ ነሳ።

**በጥባጭ** ቅ አዋኪ፥ አስቸጋሪ፥ ረባሽ።

**በጥብጥ** ዝ.ከ.

**ብጥብጥ** ቅ 1. ከውሃ ጋር የተቀላቀለ (ሽሮ ወይም ተልባ)። 2. አዲስ የተሞላና ገና ያልጠራ ወይም ከውሃ ጋር ከተቀላቀለ ብዙም ያልቆየ (የጠላ ድፍድፍ)። 3. ድፍርስ (ውሃ)። 4• ለዳቦ ማንሻነት እንዲሆን በወፍራሙ ተበጥብጦ የሚያድር የእርሾና የትንሽ ዱቄት ድብልቅ።

**ብጥብጥ** ስ ንዝንዝ፥ ጭቅጭቅ፥ ሁከት፥ ረብሻ ወይም ግርግር።

**ተበጠበጠ** ግ 1. ተጠመቀ(ጠላ፥ ጠጅ)። 2. ደፈረሰ፥ ጠሎ የነበረው ጎሽ (ፈሳሽ ነገር)። 3. ታወከ፥ ተረበሸ።

**ተበጣበጠ** ግ ተጣላ፥ ተራበሸ።

**አበጣበጠ** ግ አጣላ፥ አራበሸ።

**በጠጥ** ስ የፍየል ወይም የበግ አይነ ምድር።

**በጠጣም** ቅ (ነውር፥ስድብ) ፈሪ፥ ቦቅቧቃ።

**በጣ** ግ ቆራ፥ ሰነጠቀ፥ ሸነተፈ፥ ሰነጠቀ(አካልን)።

**ብጥ** ቅ የተቆራ፥ ሽንትፍ፥ ሽንትር።

**በጣም** ተው.ግ. ከቅፅሎችና ከግሶች በፊት እየገባ መልእክቱን የሚያጎላ ቃል። *በጣም ቀይ ነው በጣም ተደሰተ።*

**በጣሙን** እጅጉን፥ በብዙ፥ በአያሌው። *በጣሙን ደክሟል።*

**በጣሳ** **“በጠሰ”** ስር ተመ.

**በጥራራ** **“*በጠረረ”** ስር ተመ.

**በጥባጭ** **“በጠበጠ”** ስር ተመ.

**በጥብጥ** ዝ.ከ.

**በጨቀ** ግ በሰከ፥ በጠሰ፥ ቆረጠ(ጨርቅን፥ ቅጠልን)።

**ብጫቂ** ቅ ብጣሽ፥ ቅዳጅ።

**ብጭቅጫቂ(ብጭቅጭቅ)** ቅ ብጥስጣሽ ቁርጥራጭ፥ የተቀዳደደ።
**ተበጨቀ** ግ ተቆረጠ፥ ተበተከ።
**ተበጫጨቀ** ግ 1.ተበጣጠሰ፥ ተቀዳደደ። 2. ተቀራመተ፥ ተናጠቀ። *አህያይቱን ጅቦች ተበጫጨቋት።*
***በጨበጨ**
**በጭባጫ (በጨበጭ፥ብጭብጭ)** ቅ 1.የማይጣፍጥ፥ የማይረባ፥ መናኛ(ወጥ፥ ጠላ)። 2. (ስድብ) ፈሪ፥ ቡከን፥ በቅባቃ።
**ተንበጫበጨ(ተንበጨበጨ)** ግ 1.ጣእም የሌለው፥ የማይረባና መናኛ ነገር ሆነ (ወጥ፥ መጠጥ)። 2. (ነውር) ቀጭን አይነ ምድር አስቀመጠው። 3. (ዘይ.) ፈራ፥ ተርበደበደ፥ ከመጠን በላይ ተጨነቀ።
**አንበጨበጨ** ግ 1. ጣእመቢስ፥ መናኛ እንዲሆን አደረገ(ወጥን፥ መጠጥን)። 2. (ነውር) ቀጭን አይነምድር አስቀመጠው፥ ቀዘነ። 3. (ዘይ.) አስፈራ፥ አርበደበደ።
**አንበጫበጨ** ዝ.ከ.
**በፍታ** ስ ለስላሳና ስስ የሆነ የጨርቅ አይነት።
**ቡ** የ"በ" ፊደል ካእብ ዘር።
**ቡሃ (በሃ፥ቦሃ)** ስ 1. እንደቆረቆር፥ ደረመን ያለና ራስ ላይ የሚወጣ፥ ነጭነት ያለው ቁስል። ቅ 2. ራሰ መላጣ።
**ቡሃ ሃረግ** ስ ግንዱ ነጣ ያለ የሃረግ አይነት፣ ሃረግ እሬሳ።
**ቡሃ ራስ** ቅ 1. ራሰ መላጣ፥ በራ። 2. ነጣ ያለ ቆረቆር ወይም ቁስል ያለበት ራስ።
**ቡሃ ቀራ** ስ ራሱ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት፥ ሌላው አካሉ ግን ጥቁር የሆነ ቀራ፣ አሞራ።
**ቡሃ በግ** ስ ግንባሩ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት፥ ሌላው አካሉ ግን ጥቁር የሆነ በግ።
**ቡሃቃ** "ቦካ" ስር ተመ.
**ቡሄ** ስ ልጆች ጅራፍ አበጅተው የሚያጮሁበት፥ በዋዜማው ችቦ የሚበራበት፥ ሙልሙል ተዘጋጅቶ ለልጆች የሚታደልበት፥ በየአመቱ ነሃሴ አስራ ሶስት ቀን የሚከበር በአል፣ ደብረታቦር።
**ቡሆ** "ቦካ" ስር "ቡኮ" ን ተመ.
**ቡላ**[1] ቅ 1.ቀለሙ ወይም መልኩ አመድ የሚመስል። ስ 2. አመድማ መልክ ያለው (አህያ)።
**ቡልማ** ቅ አመድማ።
**ቡላ**[2] ስ ከእንሰት የሚዘጋጅ የምግብ አይነት።
**ቡላድ [ድንጋይ]** ስ ሲጋጭ እሳት ሊፈጥር የሚችል የድንጋይ አይነት።

**ቡልሃ** ቅ ሞኝ፥ የዋህ።
**ቡልቅ**
**ቡልቅ አለ** ግ 1.ፍልቅ፥ ቡጥልቅ ብሎ ወጣ፥ ፈሰሰ። 2. በሃይል ወጣ፥ ተፈተለከ፥ በነነ። *መድፉ ሲተኮስ ከአፈሙዙ ጪስ ቡልቅ ይል ነበር።*
**ቡልማ** "ቡላ[1]" ስር ተመ.
**ቡልኮ** ስ በውፍረትም ሆነ በርዝመት ከጋቢ የሚበልጥ፥ ከጥጥ የሚሰራ ትልቅ ሽማ።
**ቡልዶዘር** ስ መሬትን እየቆፈረ፥ ድንጋይን እየፈነቀለ ለመጥረግ ወይም ለመግፋት የሚያስችል ጠንካራ፥ ወፍራምና ሰፊ የብረት መጋፊያ (ምላጭ) በፊቱ በኩል የተገጠመለት ከባድ ተሽከርካሪ፣ የግንባታ መሳሪያ።
**ቡሎን (ቡሉን)** ስ ብረቶችን፥ እንጨቶችን፥...አንዱን ከሌላው ጋር ለማስተሳሰር የሚያገለግል፥ ከአንድ ጫፉ በኩል ዙሪያውን ክርክራት ያለው፥ እንደ ወፍራም ምስማር ያለ የብረት ችንካር።
**ቡርሽ** "ቦረሸ" ስር ተመ.
**ቡሩክ(ብሩክ)** "ባረከ" ስር ተመ.
**ቡራቡሬ** "ቡሬ" ስር ተመ.
**ቡራከረዩ አለ** ግ ደነፋ፥ ተቆጣ፥ ያዙኝ ልቀቁኝ አለ።
**ቡራኬ** "ባረከ" ስር ተመ.
**ቡሬ** ቅ 1.ዝንጉርጉር፥ የነጭና የጥቁር ቀለም አይነቶች የተፈነጣጠቁበት ወይም ቀለሞች እየተሰባጠሩ እዚህና እዚያ የሚታዩበት (የቀለም ቅይጥ መልክ)። 2. ቡራቡሬ።
**ቡራቡሬ** የተለያዩ ቀለማት ድብልቅ ወይም ቅይጥ የሆነ መልክ፣ ዝንጉርጉር።
**ቡርቅቅ** "ቦረቀቀ" ስር "ቦርቃቃ" ን ተመ.
**ቡርቡጭ አለ** ግ ሞላ አለ፥ በመጠኑ ጠገበ (ሆድ)።
**ቡርዲ**[1] ስ በላይኛው የሰው ከንፈር በሚገኘው ድድ ላይ ተለጥፎ የሚታይ ድርብና ወፍራም የድድ ስጋ።
**ቡርዲያም** ቅ ቡርዲ ያለበት።
**ቡርዲ**[2] ቅ ፈሪ፥ ቶስቷሳ።
**ቡሲ(ቡሴ)** ስ 1. ጥንካሬ የሌለው፥ ውስጠ ክፍት የሆነ የእፅዋት አይነት። 2. (ዘይ.) አቅመቢስ፥ ደካማ (ሰው)።
**ቡሽ** ስ ሳጋቱራ (የእንጨት ፍቅፋቂ) ከመሰለ ነገር የሚሰራ የጠርሙስ፥ የኮዳ፥...ክዳን።
**ቡቃ (ቡአ)** ስ በበገድ አካባቢ የሚሰማ የአንጀት ህመም አይነት።
**ቡቃ ወረደው** በበገድ አካባቢ የአንጀት

ሁመም ተሰማው።

**ቡቃያ** "በቀለ" ስር ተመ.

**ቡቅሬ (ቡቅሬ+ቡቅር)** ስ ጌሾ የሌለውና ያልፈላ ጠላ።

**ቡቡ** "ባባ" ስር ተመ.

**ቡትቷም** "በተተ" ስር ተመ.

**ቡታ** ስ እሪታ፥ ኡኡታ፥ ድረሱልኝ የሚል ጩሀት።

**ቡታ ፣ ሰደደ** እረ አለ፤ የደረሰበትን በደል በጩሀት፥ በእሪታ አሰማ፥ ኡኡ አለ።

**ቡታ ጋዝ** ስ 1. ከነዳጅ ድፍድፍ የሚመረትና መንደድ የሚችል፥ በሲሊንደር ተሞልቶ ለማብሰያ፥ ለመብራት፥...የሚያገለግል ፈሳሽ ጋዝ። 2. በሲሊንደር የተሞላ ቡታጋዝ በቀጭን ቱቦ ተላልፎለት ለማብሰያ የሚያገለግል ምድጃ።

**ቡትሌ** የ"ብጥሌ"ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**ቡትርፍ** "በተረፈ" ስር ተመ.

**ቡትቶ** "በተተ" ስር ተመ.

**ቡቺ** ውሻ የሚጠራበት ስም።

**ቡች ቡች አለ** ና ና ብሎ ጠራ(ውሻን)።

**ቡችላ** ስ የአንበሳ ወይም የውሻ፥...ግልገል።

**ቡና** ስ 1. ተቆልቶ፥ ተወቅጦና ከውሃ ጋር ተፈልቶ የሚጠጣውን ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ቡና ይባላል። 2. ከቡና ፍሬ (ተቆልቶ ተወቅጦና ከውሃ ጋር ተፈልቶ) የሚዘጋጅ መጠጥ።

**ቡና መፈልፈያ** ስ የቡናን ፍሬ ከገለፈቱ ለመለየት የሚያገለግል መሳሪያ።

**ቡና ቤት** ስ እንደ ቡና፥ ሻይ፥ ለስላሳ፥ የአልኮል መጠጦችና ምግብ የሚሸጥበት የንግድ ቤት።

**[የ] ቡና ቁርስ** ስ ቡና ሲጠጣ የሚበላ እንደ ቆሎ፥ ቂጣ ያለ ወይም መጠነኛ የሆነ ምግብ።

**[የ] ቡና ጀበና** ስ ለቡና ማፍያ የሚያገለግል ከሸክላ የተሰራ ጀበና (ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.)።

**ቡናማ(ቡኒ)** ቅ 1. የደረቀ የቡና ፍሬ ቅርፊት ወይም ጀንፈል ቡና የሚመስል መልክ ያለው። ስ 2. የደረቀ ጀንፈል ቡና የሚመስል የቀለም አይነት።

**ቡናኝ** "በነነ" ስር ተመ.

**ቡንኝ** ስ በሶስት ወር የሚደርስ የጥቁር ጤፍ አይነት።

**ቡአ** "ቡቃ" ን ተመ.

**ቡከን** ቅ ፈሪ፥ እርብትብት።

**ቡኬት** "ቦካ" ስር ተመ.

**ቡክቡካ** "ቦከቦከ" ስር ተመ.

**ቡኮ** "ቦካ" ስር ተመ.

**ቡይት** ስ ከገንቦ ከፍ ከእንስራ አነስ የሚል የሸክላ እቃ።

**ቡደን** ስ በአንድ እጅ ሊዘራ የሚችልና በግሬሻ የተሰነጠቀ ወይም የተከፈለ የእርሻ መሬት፤ እመም።

**ቡዳ** ስ 1. እንደ ህብረተሰቡ ልማዳዊ እምነት፥ የየውንና ቀልቡ ያረፈበትን ሰው ወይም እንስሳ ለህመም ወይም ለሞት የሚዳርግ መጥፎ አይን ያለው ሰው። ቅ 2. ክፉ። 3. እሱ የሚሰራው ነገር ሁሉ ድብቅ የሆነ፥ በሌላ በኩል ደግሞ በድብቅ ወይም በምስጢር የሚደረጉ ነገሮች የማያመልጡት (ሰው)።

**ቡዳ በላው** ቡዳ የሆነ ሰው ስለአየው ታመመ ወይም በጤናው ላይ ጉዳት ደረሰበት።

**ቡድስ** "ቦደሰ" ስር ተመ.

**ቡድን** "*ቦደነ[2]" ስር ተመ.

**ቡጉር** "ብጉር" ን ተመ.

**ቡግ**

**ቡግ አለ** ግ 1. ተስተካክሎ፥ አምሮና ደምቆ በብዛት በቀለ (ቡቃያ)። 2. ችፍ አለ፥ ግልብጥ ብሎ በብዛት ወጣ (የኩፍኝ፥ የፈንጣጣ፥...ሽፍታ፥ ቁስል)።

**ቡግሪት** ስ 1. ለጠላ መጥመቂያ የምትሆን እንደ እንስራ ያለች የሸክላ እቃ። 2. እንደ መንቀል ያለች ለመጠጫነት የምታገለግል የሸክላ ዕቃ።

**ቡጢ** ስ ጡጫ፥ በቅስ፥ የተጨበጠ እጅ።

**ቡጥ** "ቦጠቦጠ" ስር ተመ.

**ቡጥልቅ አለ** "*ቦጠለቀ" ስር ተመ.

**ቡጥጫ** "ቧጠጠ" ስር ተመ.

**ቡጫቂ** "ቦጨቀ" ስር ተመ.

**ቡጭር** "ቧጨረ" ስር ተመ.

**ቡጭርጭር** ዝ.ከ.

**ቡጭቅ** "ቦጨቀ" ስር ተመ.

**ቡጭቅጫቂ** ዝ.ከ.

**ቡፌ[1] (ቱፌ+ቱፍታ)** ስ ለማስተንፈሻነትና ቅቤ መውጣቱን ለማየት የምታገለግል፥ በሚያስፈልግበት ጊዜ ብቻ የምትከፈት፥ ለወተት መናጫ በሚያገለግል እቃ ጎን ላይ የምትገኝ ቀዳዳ፥ ሽንቁራት።

**ቡፌ[2]** ስ ብዙውን ጊዜ የምግብ እቃዎችን በውስጡ ለማስቀመጥ የሚያገለግል፥ በጠረጴዛ ወይም በቁምሳጥን ቅርፅ የሚዘጋጅ የቤት እቃ።

**ቡፍ**

**ቡፍ አለ** ግ 1. ድምፁ ዝቅ ያለ ጩሀት አሰማ

(ውኃ):: 2. ኩፍ አለ፥ ተነፋ፥ ወደላይ ከፍ፥ ብድግ አለ (ሊጥ):: 3. (ዘይ.) የኩርፊያ፥ የቁጣ ገፅታ አሳየ፥ ፊቱን አከበደ፥ አጠቆረ::

**ቡፍና** ስ 1. ጌሾ የሌለው ቀጭን ጠላ፤ ቡቅሬ:: 2. ያልፈላና ጉሽ የሆነ መናኛ ጠላ::

**ቢ** የ "በ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ቢ** "ብ-"ን ተመ.

**ቢላ**[1] **(ቢላዋ፥ ቢላዎ)** ስ በአንድ ጎኑ ስለት ያለው፥ ለስጋ፥ ለሽንኩርት፥...መቁረጫ፥ መክተፊያ የሚያገለግል የወጥ ቤት እቃ::

**ቢላ**[2] ስ በደረቁ ሳር ጫፍ ላይ የሚገኝ እንደ ምርቅ ያለ እሾህማ ጭጎጎት::

**ቢላቢሉ** "ቢል[2]" ስር ተመ.

**ቢል**[1]

**ቢል አለ** ግ 1. በቀላሉና በፍጥነት ነደደ፥ ተቀጣጠለ:: 2. (ዘይ.) በጣም ተናደደ::

**ቢል**[2]

**ቢላቢሉ (ቢሉ)** ቅ ስስ (ልብስ)

**ቢል አለ** ግ በጣም ስስ ሆነ::

**ቢል ያለ** በጣም ስስ የሆነ::

**ቢልቃጥ** "ብልቃጥ" ን ተመ.

**ቢራ** ስ በፋብሪካ ውስጥ ከገብስ ተዘጋጅቶ የሚቀርብ የአልኮል መጠጥ አይነት::

**ቢራቢሮ** ስ በተለያዩ ህብረቀለማት ያሸበረቁ ክንፎች ያሏት፥ በበጋ ወራት በብዛት የምትታይ የነፍሳት አይነት::



ቢራቢሮ

**ቢርካ** ስ ቦኖ ውሃ::

**ቢሮ** ስ የመንግስት ወይም የድርጅት ወይም የግል ጉዳይን ለማከናወን የሚያገለግል፥ የፅህፈት ስራ የሚካሄድበት ክፍል፥ ቤት::

**ቢስ**[1] ስ ቡዳ፥ ክፉ መንፈስ፥ ሰይጣን::

**ቢስ አይይህ** (ምር.) እክፉ ሰው አይን አትግባ፥ ክፉ፥ መጥፎ ነገር አይግጠምህ::

**ቢስ ገላ** ስ ደዋ፥ስጋ፤ ቁምጥና::

**ቢስ**[2] ቅ ንቁግ፥ ስስታም::

**ቢስ** የሌለው:: *እድለ ቢስ::*

**ቢስክሌት** "ብስክሌት" ን ተመ.

**ቢሻው** "ሻ" ስር ተመ.

**ቢሽቃጥ** ስ ጉጠት::

**ቢተዋ** ስ በጥንት ጊዜ አርበኛ ወይም ገዳይ ክንዱ ላይ የሚያጠልቀው እንደ አምባር ያለ ጌጥ::

**ቢትወደድ** ስ ቀደም ባለው ዘመን ለንጉሰነገስቱ እንደዋና አማካሪና ጉዳይ ፈፃሚ ሆኖ ለሚያገለግል ባለሟል ይሰጥ የነበረ የማእረግ ስም::

**ቢንጎ** ስ ፊደሎችና ቁጥሮች ያሉባቸውን የእጣ ካሶችና የመጫወቻ ካርዶችን በመጠቀምና በአጫዋቹ የሚሰጠውን ትእዛዝ ቀድሞ በመስራት ተእድለኞች ለወዋታው የተመደበውን ሽልማት የሚያገኙበትና በርካታ ሰዎች የሚሳተፉበት እንደ ሎተሪ ያለ ወዋታ(በወዋታው ቀድሞ ያሸነፈው ጮክ ብሎ "ቢንጎ " ማለትና የታዘዘውን መስራቱን ማስመርመር ይጠበቅበታል)::

**ቢኖ** "ቪኖ" ን ተመ.

**ቢያጆ** ስ አንድ ዙር ጉዞ:: *በትልቁ መኪና አስር ቢያጆ ድንጋይ ቢመጣልኝ ላሰብኩት የቤት ስራ ይበቃኛል::*

**ቢጃማ** "ፒጃማ" ን ተመ.

**ቢጋር** "በገረ[1]" ስር ተመ.

**ቢኅዲን** ስ የሴቶች ፀጉር መጠቅለያ::



ቢኅዲን

**ቢጤ(ብጤ)** ስ 1. በግብር፥ በጠባይ፥... ተመሳሳይ የሆነ ወይም የሚመሳሰል:: *ቢጤውን ፈልጎ ጓደኛ አበጀ::* 2. እንደ-ያለ:: *ዱላ ቢጤ አቀብለኝ::*

**ቢጫ** ቅ 1. የእንቁላል አስኳል ወይም አደይ አበባ የሚመስል:: ስ 2. አደይ አበባ የሚመስል የቀለም አይነት::

**ባ**[1] የ "በ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ባ**[2] በግ ሲጮህ የሚያሰማው የድምፅ አይነት::

**ባ አለ** ጮሀ (በግ)::

**ባ** - "ብ-" ን ተመ.

**ባህል** ስ የህብረተሰብ የአኗኗር ዘዴ፥ ወግ፥ ልማድ፥ እምነት፥...::

**የባህል ልውውጥ** ስ የየራስን ባህል አንዱ ለሌላው ለማስተዋወቅ በአገሮች መካከል የሚደረግ ግንኙነት::

**የባህል ስምምነት** ስ በተለያዩ አገሮች መካከል የሚደረግ ባህል ነክ ስምምነት፥ ውል::

**ባህላዊ** ቅ ባህልን የሚያንፀባርቅ፥ ባህል ነክ የሆነ።

**ባህረኛ** "ባህር[1]" ስር ተመ.

**ባህር[1]** ስ ሰፋትና ጥልቀት ያለውና በተወሰነ ቦታ የተከማቸ ውሃ።

**ባህሩን ቆርጦ ተሻገረ** ባህሩን በዋና አቋርጦ ተሻገረ።

**ባህር ነው** (ዘይ.) በጣም ሰፊ ነው።

**ባህረ ሰላጤ** ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ መሬት አካል የገባ የባህር ወሽመጥ፥ ምላስ።

**ባህረ ሸሽ(ባህር ሸሽ)** ስ የባህር ውሃ ተኝቶበት ከቆየ በኋላ ትቶት የሄደ መሬት።

**ባህረ አረብ (ባህር አረብ)** ስ የተለፋና የቀለመ ሌጦ።

**ባህረ ጥምቀት (ጥምቀተ ባህር)** ስ 1. የጥምቀት እለት ምእመናን ይጠመቁበት ወይም ይረጩት ዘንድ በየአመቱ በወንዝ ዳር ወይም አመቺ በሆነ ቦታ ላይ የሚከተር ውሃ፥ ባህር። 2. ከላይ የተጠቀሰው ስነ ስርአት የሚካሄድበትና ታቦት የሚያድርበት ቦታ።

**ባህረ ገብ** ስ ሾጠጥ ብሎ ወደ ባህር አካል መካከል የተዘረጋ መሬት፤ ልሳነ ምድር።

**ባህር መዝገብ** ስ ማንኛውም ጉዳይ ወይም ነገር (ንብረት ወይም ገቢና ወጪ፥...) በቋሚነት ተመዝግቦ የሚቀመጥበት ትልቅ መዝገብ።

**ባህር ማሽላ (ባር ማሽላ)** ስ በቆሎ።

**ባህር ማዶ** ስ ውጭ አገር።

**ባህር ቅል** ስ ዱባ።

**ባህር ወላድ** ስ የብዙ ልጆች እናት።

**[የ] ባህር ዛፍ** ስ በዳግማዊ ምኒልክ ጊዜ ፍሬው ከአውስትራሊያ እንዲመጣ ተደርጎ ኢትዮጵያ ውስጥ የለማ፥ የተለያዩ ዝርያዎች ያሉትና በጥቂት አመታት ውስጥ ለአገልግሎት የሚደርስ የትላልቅ ዛፎች አይነት።

**የባህር አሞራ** ስ ብዙውን ጊዜ በባህር ውስጥ የሚኖሩ ጥቃቅን ነፍሳትን (አሳዎችንና ሌሎችንም) ከባህር ውስጥ እያወጣ የሚመገብ የአሞራ አይነት፤፤

**የባህር እቃ** ስ እንደ ብርጭቆ፥ ብርሌ፥... የመሳሰሉና በቀላሉ ሊሰበሩ የሚችሉ እቃዎች አይነት።

**የባህር ወለል** ስ የመሬትን ከፍታ ወይም የውቅያኖስን ጥልቀት ለመለካት እንደ መነሻ ነጥብ ሆኖ ያገለግል ዘንድ በአማካይ የተወሰደ ከውቅያኖስ ውሃ ከላይኛው አካል ጋር ትይዩነት ያለው የመሬት ንጣፍ።

**የባህር ወሽመጥ** ስ ባህረሰላጤ።

**ባህረኛ** ስ መርከበኛ።

**ባህር[2]** ስ በደቡብና በምእራብ መካከል የሚገኝ የአለም ማእዘን። በተጨማሪ ማእዘንን ተመ.

**ባህርይ** ስ 1. የአንድ ነገር አፈጣጠር፥ ሁኔታ። 2. የአንድ ነገር ምንነት፥ ሁኔታ። 3. ጠባይ፥ አመል ወይም ግብር።

**ባህታዊ** ስ ከሰው ተለይቶ እየፆመ፥ እየፀለየና እየሰገደ በዱር በገደል የሚኖር መናኝ፤ ናዝራዊ፤ መነኩሴ።

**ብህትውና** ስ የባህታዊ ተግባር፥ የአኗኗር ስርአት።

**ባለ–**

**ባለሁለት** ስ ማህበረተኞቹን እቤቱ የማስተናገድ ተራ የደረሰው፥ ከባለ ሳምንት ቀጥሎ የሚደግስ የዕዋ ጠጪ ማህበረተኞች አባል።

**ባለህግ** ስ ጋብቻውን ከመሰረቱ ወይም ከጅምሩ በቁርባን ስርአት የፈፀመ ሰው።

**ባለመለዮ** ስ መደበኛ ወታደር።

**ባለመብት** ስ 1. የአንድ ነገር ባለቤት።2. ባለጊዜ፥ በጊዜው ስልጣን ወይም ተሰሚነት ያለው ሰው።

**ባለሙያ** "ሙያ" ስር ተመ.

**ባለማደሪያ** ስ የመንግስት መሬት ተሰጥቶት በእሱ እየተጠቀመ ለመንግስት ግልጋሎት ይሰጥ የነበረ ወታደር።

**ባለሟል** ስ 1. ከንጉስ ወይም ከታላቅ ባለስልጣን ጋር አብሮ የሚውል፥ አንድን ጉዳይ ለመፈፀምም ሆነ ለማስፈፀም ችሎታ ወይም ተሰሚነትና ተቀባይነት የነበረው ሰው። 2. ቤተኛ፥ የቅርብ ወዳጅና አገልጋይ።

**ባለርስት(ባለመሬት)** ስ 1. የራሱ የሆነ የተወሰነ የመሬት ይዞታ ያለው ሰው። 2. የብዙ ወይም የሰፊ መሬት ባለቤት የሆነ፤ የመሬት ከበርቴ።

**ባለሰሞን** ስ ተራ ሲደርሰው ለስምንት ቀን በቤተክርስቲያን አገልግሎት የመስጠት ሃላፊነት ያለበት ተረኛ ዲያቆን፥ ቄስ፤ ሰሞነኛ።

**ባለሳምንት** ስ 1. ድግስ ደግሶ የዕዋ ማህበረተኞቹን ለማስተናገድ ተራ ወይም እጣ የደረሰው የማህበሩ አባል። 2. የሚቀጥለው ተረኛ።

**ባለስልጣን** ስ ስልጣን ያለው ሰው።

**ባለስም** ስ ዝና፥ ታዋቂነት ያገኘ ሰው።

**ባለቀላድ** ስ በቀላድ እየተለካ የሚሰጥ መሬት ወይም ርስት የነበረው ሰው።

**ባለቅኔ** ስ ቅኔ የሚያውቅ፥ ቅኔ የተማረ ሰው።

**ባለቤት** ስ 1. የአንድ ነገር ባለይዞታ፥ ባለመብት። 2. ባል ወይም ሚስት። የእገሌ

*ባለቤት እገሊት ናት ወይም የእገሊት ባለቤት እገሌ ነው::* 2. በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኘው ግስ ደርጊት በማን ወይም በምን እን ደተፈፀመ የሚያመለክትና በአረፍተ ነገሩ መጀመሪያ እርከን ላይ የሚገኝ ቃል ወይም ቃላት::

**ባለቤት አከል** ስ እንደባለቤት የማዘዝና የመወሰን መብት ያለው ሰው::

**ባለተራ** "ተራ" ስር ተመ.

**ባለተስፋ** 1. አገኛለሁ ብሎ በተስፋ የሚጠብቅ:: 2. የሚጠብቀውን ነገር የማግኘት ተስፋ ያለው ሰው::

**ባለታሪክ** "ተረከ" ስር ተመ.

**ባለትዳር** ቅ ትዳር ያለው ወይም ያላት::

**ባለነገር** ቅ ክርክር ወይም ሙግት ያለበት (ሰው)::

**ባለነጋሪት** ስ ነጋሪት የማስጎሰም መብት የነበረው ራስ ወይም ደጃዝማች::

**ባለአልጋ** ስ የንጉስ ወገን፥ ባላባት፥ ንጉስ::

**ባለአጎዛ** ስ (ቤ.ክህ.) መምህር፥ አስተማሪ::

**ባለእኩል** ስ 1. ከተፋታች ንብረት ከባሏ ጋር እኩል የመካፈል መብት ያላት ሴት:: 2. ንብረትን ከሌላው ጋር በጋራ የያዘ ሰው::

**ባለእዳ** ቅ እዳ ያለበት (ሰው)::

**ባለእጅ (ባለጅ)** ስ (የን.አነ.) ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ የሸክላ እቃዎችን ወይም እንደ ማረሻ፥ ማጭድ ያሉ መሳሪያዎችን የሚሰራ ባለሙያ::

**ባለወልድ (በአለ ወልድ)** ስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደበትን ቀን ምክንያት በማድረግ በየወሩ በሃያ ዘጠኝ የሚከበር በአል::

**ባለወንበር** ስ (ቤ.ክህ.) ወንበር ዘርግተው የሚያስተምሩ መምህር::

**ባለወግ** ስ በቤተክህነት ወይም በቤተ መንግስት ድርጎ ወይም አበል የሚያሰጥ የተወሰነ ሹመት ወይም እልቅና የነበረው ሰው::

**ባለውለታ** "ዋለ²" ስር ተመ.

**ባለውቃቢ** "ውቃቢ" ስር ተመ.

**ባለዝና** ስ ስመጥር፥ የታወቀ ሰው::

**ባለደም** ስ በነፍስ ግድያ ምክንያት ጠላት የተሄሄነ ሰው::

**ባለጅ** "ባለእጅ"ን ተመ.

**ባለጊዜ** ስ 1. ጊዜ ያነሳው፥ ጊዜ የተስማማው፥ ጊዜ የሆነው ሰው::2. የጊዜው ሹም፥ የጊዜው ባለስልጣን::

**ባለ_** ተው.ግ. 1. በመሰለ:: *እከሌና እከሌ እንዲህ ባለ ነገር ተጣልተዋል / እንዲህ ባለ ወረቀት ላትምፍ::* 2. በኖረ፥ በነበረ፥በአለ::

**ባለቀ** ግ አደገ፥ ጎረመሰ፥ ለአቅመ አዳም ደረሰ::

**ያልባለቀ** ቅ ገና ለአቅመ አዳም ያልደረሰ (ልጅ)::


**ባለገ** ግ 1. ስርአት የለሸ፥ ህገወጥ፥ ስድ አደግ ሆነ:: 2. ከተቃራኒ ፆታ ጋር በስርቆሽ የግብረስጋ ግንኙነት ፈፀመ፤ አመነዘረ::

**ባለጌ** ቅ ስነስርአት የሌለው፥ ስድ አደግ፥ ያልታረመ::

**ብልግና** ስ አስነዋሪ ድርጊት::

**አባለገ** ግ 1. ስነስርአት በሌለው ሁኔታ አሳደገ፥ አስተዳደረ፥...:: 2. አማገጠ::

**ባለጠጋ(ባለፀጋ)** "በለፀገ" ስር ተመ.



**ባላ** ስ ከላዩ ላይ እቃ ለማንጠልጠል፥ ለመስቀል ወይም ለመውደቅ ያዘመመን አጥር፥ ቤት፥... ለመደገፍ የሚያገለግል ራሰ መንታ የሆነ እንጨት::

**ባላባልቻ** ስ የወስፈንጥር መስሪያ ባላ እንጨት::

**ባላና ደንቆሮ** ስ ድር ባላ በሚደራበት ጊዜ፥ ድሩን ለመዘርጋትና ወጥሮ ለመያዝ እንዲያገለግል፥ በድሩ በአንደኛው ጫፍ በኩል የሚተከለው መንትያ ጫፍ ያለው ባላ እንጨትና ሲባል፥ በሁለተኛው ጫፍ በኩል ያለውና ጫፉ መንታነት የሌለው እንጨት በአንድነት የሚጠሩበት ስም::

**ባላምባራስ** ስ ከግራዝማችነት ዝቅ የሚል የቀድሞ የማእረግ ስም::

**ባላባት** ስ 1. ጭሰኞች ይገብሩለት የነበረ የአንድ አካባቢ አለቃ፥ ሹም ወይም የመሬት ከበርቴ የነበረ ሰው:: 2. ከአያት ከቅድመ አያቱ ጀምሮ የአንድ የተወሰነ አካባቢ ተወላጅ የሆነ እውቅ ሰው::

**ባላና ደንቆሮ** "ባላ" ስር ተመ.

**ባላንጣ** ስ 1. ባላጋራ:: 2. ይህ የኔ ነው ወይም ለእኔ ነው የሚገባው ባይ፥ ተቀናቃኝ:: 3. ተፎካካሪ፥ ተወዳዳሪ (ለመብለጥ፥ የበላይ ለመሆን ለማሸነፍ)::

**ባላገር (ባለአገር)** ስ 1. ገጠር ወይም አገር ቤት:: 2. ገጠር ወይም አገር ቤት ውስጥ የሚኖር ሰው:: 3.(የን.አነ.) ያልሰለጠነ፥ ቅልጥፍና የሌለው::

**ባላጋራ** ስ ጠላት፥ ደመኛ::

**ባሌስትራ** ስ የመኪናውን ሻንሲ የመሸከም ሃይል ያለው ጠንካራና ጠፍጣፋ ደጋንማ ብረት::

**ባሌት** ስ በንግግር ወይም በዘፈን ሳይሆን በሙዚቃ እየታጀበ በተወዛዋዦች አካላዊ እንቅስቃሴ አማካይነት የሚከናወን ድራማ ወይም የሚተላለፍ የጥበብ ዘርፍ።

**ባል** ስ ባለ ሚስት፥ ሚስት ያለው ወንድ፥ የሚስት አጣማጅ፥ የትዳር ጓደኛ።

**ባልና ሚስት ቁልፍ** ስ እርስበርሱ የሚሰካካ፥ የሚገጣጠም የቁልፍ አይነት (ስእሉን ቁልፍ ስር ተመ.)።

**ባልቦላ** ስ የኤሌክትሪክ ሃይል በመስመር ላይ እንዲተላለፍ ወይም እንዳይተላለፍ ለማድረግ የሚያገለግል፥ ከቆጣሪ ጋር የሚያያዝ የኤሌክትሪክ እቃ።

**ባልቴት "በለተተ"** ስር ተመ.

**ባልትና** ስ የቤት አያያዝ፥ የምግብ አዘገጃጀት፥...እውቀት፥ ሙያ፥ ችሎታ።

**ባልትናቢስ** ቅ (ስድብ) ሙያ ቢስ፥ ሙያ የለሽ።

**ባልንጀራ** ስ 1.ጓደኛ፥ ምስጢረኛ። 2. አብሮ አደግ፤ እኩያ ወይም አቻ።

**ባልደረባ** ስ 1. ጓደኛ፥ ባልንጀራ። 2. አባል። *ሰውየው የመስሪያ ቤታችን ባልደረባ ነበሩ።* 3. አጋዥ፥ አገናኝ፥ አስታዋሽ። *ሃላፊው ጉዳዩን ከሰሙ በሂላ ባልደረባ ሰጡኝ።*

**ባልደራስ** ስ የመንግስት ፈረስና በቅሎ ቤት ሹም፥ አዛዥ።

**ባልዲ** ስ ለውሃ መቅጃና ማስቀመጫ፥... የሚያገለግል፥ ከብረት ወይም ከፕላስቲክ የተሰራ ባለማንጠልጠያ የቤት እቃ፤ ሸንኪሎ።

**ባልጩት** ስ እንደ ሻፎ ወይም እንደ ሱፋጭ ስለት የሚወጣው ድንጋይ።

**ባምባ(ባንባ)** ስ እንደ ሾላ የሚበላ ፍሬ ያለው የትልቅ ዛፍ አይነት።

**ባረቀ** ግ 1. በጥንቃቄ ማነስ ወይም በሌላ ምክንያት ሳይታሰብና ሳይፈለግ ድንገት ጥይቱ ተተኮሰ (ጠመንጃ፥ ሽጉጥ)። 2. ሰማይ ጮሀ፥ መብረቅ ተወረወረ። በተጨማሪ "በረቀ"ን ተመ.

**መብረቅ "በረቀ"** ስር ተመ.

**ብራቅ** ስ መብረቅ።

**አምባረቀ (አንባረቀ)** ግ 1. እንደ ብራቅ ጮሀ፥ ከፍተኛ ድምፅ አሰማ። 2. አብለጨለጨ፥ ተብለጨለጨ (ሰማይ፥ መብረቅ)።

**አባረቀ** ግ 1. ሳይታሰብና ሳይፈለግ መሳሪያው ራሱ በራሱ እንዲተኮስ የስህተቱ ምክንያት ሆነ። 2. አምባረቀ።

**ባረከ** ግ 1. መስቀል አሳለመ። 2. አማተበ። 3. ፀሎት አድርጎ ቀደሰ፥ አነፃ። 4. ጀመረ። 5. የሚበሉ እንስሳትን አንገት ቆረጠ፥ አረደ። 6. አመሰገነ(አምላክን)። 7. መረቀ። 8.ቆረሰ።

**ቡራኬ** ስ 1. ፀሎት፥ ምስጋና፥ ምርቃት። 2. ለባለ ወግ (ለቄስ፥ ላቃቢ፥...) የሚሰጥ ተባርኮ የተቆረሰ ትልቅ የዳቦ ቁራሽ።

**ቡራኬ ሰጠ** ፀሎት አድርጎ ባረከ፥ መስቀል አሳለመ።

**ቡሩክ** ቅ 1. ደግ፥ ምስጉን፥ ትሁት፥ የተመረቀ። 2. የተመሰገነ፥ የተቀደሰ፥ የተከበረ (አምላክ)።

**ቡሩክ ሁን** (ምር.) የተባረክ፥ የተቀደስክ ሁን።

**ተባረከ** ግ 1. ዘርማንዘሩ በዛ፥ በረከተ። 2. እድሜ አገኘ፥ ቆየ።

**ተባረክ**(ምር.) ቡሩክ ሁን።

**ባሩድ** ስ 1. የቀለህ ከምሱር፥ በመውጊያ ወይም በመወርወሪያ ሲመታ (ሲወጋ) ፍንዳታና ከፍተኛ ግፊት እንዲፈጠርና ከቀለሁ አፍ ላይ የተገጠመው የጥይት እርሳስ እንዲተኮስ ወይም ተስፈንጥሮ እንዲበር የሚያደርግ፥ በቀለህ ውስጥ የሚሞላ የማእድን ውሁድ። 2. የማእድን አይነት።

**ባሪያ(ባርያ)** ስ 1. በጦርነት ላይ እየተማረከ ወይም በገንዘብ እየተገዛና እየተሸጠ ወይም ካለበት አካባቢ በግድ ታፍኖ እየተወሰደ ለማራኪው ወይም ለገዛው ወይም አስገድዶ ለወሰደው ሰው በነፃ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ ሰው። 2. አገልጋይ፥ ታዛዥ፥ ሎሌ። 3. መብትና ነፃነት የሌለው፥ በተገዥነት የሚኖር ህዝብ። 4 (የን. አነ.) ጥቁር። 5. (ዘይ.) በጣም ጠንካራና ጥሩ አገልግሎት የሚሰጥ (ለእቃ)።

**ባርያ ድንጋይ** ስ በቀላሉ የማይሰበር፥ ጥቁርና ጠንካራ የሆነ የድንጋይ አይነት።

**[ ባሪያ] ፈንጋይ** ስ የባሪያ ነጋዴ፤ ሰዎችን አፍኖ እያስገደደ ለባርነት ይሸጥ የነበረ ሰው።

**የባርያ [አሳዳሪ] ስርአተ ማህበር** ስ በህብረተሰብ የእድገት ታሪክ ውስጥ ከጥንታዊው የጋርዮሽ ስርአተ ማህበር ቀጥሎ የመጣ ስርአተ ማህበር።

**ባራ** ግ አቆመ፥ አባራ (ዝናብ)።

**ብራ** ስ ዝናብ ያቆመበት ወይም የሌለበት ጊዜ፥ ቀን ወይም ወቅት።

**አባራ** ግ 1. ዝናብ መጣሉን አቆመ፥ ተወ። 2. (ዘይ.) (መናገሩን፥ መለፍለፉን፥ ማልቀሱን) ተወ፥ አቆመ።


**ባሬታ** ስ ሸንት መሽኛ፤ መከፈያ፤ ፖፖ።

**ባርማሽላ "ባህር ማሽላ"** ን ተመ።

**ባርባር**

**ባርባር አለው** ፍርሃት፥ ጭንቀት ተሰማው።

**ባርኔጣ** ስ ለዝናብና ለፀሃይ መከላከያ እንዲሁም ለጌጥ በራስ ላይ የሚደፋ፥ የሚደረግ፥ ከሱፍ ወይም ከጥጥ የሚሰራ ከፍያ::



ባርኔጣ

**ባርካ** ስ ለማጓጓዣነት የሚያገለግል የጀልባ አይነት::

**ባርያ**[1] ስ ራስ የሚያዞርና የሚጥል የበሽታ አይነት::

**ባርያ ጣለው** የሚጥል በሽታ አመመው::

**ባርያ**[2] - "ባሪያ" ን ተመ.

**ባሮ ሜትር** ስ የአየር ግፊት መለኪያ መሳሪያ::

**ባሰ** ግ 1.አንድ ነገር ከበፊቱ ይልቅ እየጠና፥ እየበረታ ሄደ፥ አየለ (በበጎ ወይም በክፉ መልኩ):: 2. የብስጭት፥ የሃዘን ስሜት ተሰማ:: *ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው::* 3.ችገረ፥ ገደደ:: *ምን ባሰሁ::* 4. ላቀ፥ በለጠ:: *አንተ ትብስ አንተ ትብስ ተባባሉ::*

**የባሰ** ከበፊቱ የበለጠ፥ የበረታ፥ የጠነከረ::

**የባሰ የባሰውን** ዋና ዋናውን::

**የባሰ ይባስ** የፈለገው ይሁን::

**ይባስ ብሎ** ጭራሹኑ::

**ብሶት** ስ በአእምሮ ውስጥ ታምቆ የተቀመጠ ችግር፥ በደል፥ ቅሬታ::

**ብሶተኛ** ቅ ብሶት ያለበት (ሰው)::

**ተባባሰ** ግ እያየለ፥ እየጨመረ፥ እየከፋ ሄደ::

**አባሰ** ግ ከበፊቱ ይበልጥ አጠነከረ፥ አበዛ::

**አብሶ** በተለይ፥ በይበልጥ:: *አብሶ አንተ::*

**አባባሰ** ግ ከበፊተኛው ይበልጥ የከረረ፥ የጠነከረ፥ የከፋ እንዲሆን አደረገ::

**ባሻገር** "ሻገረ" ስር ተመ.

**ባቄላ** ስ ከአበባ እህሎች ወገን የሆነ፥ ፍሬው ሞለል ብሎ ተለቅ ተለቅ ያለ፥ ብዙውን ጊዜ በሽሮ፥ በአሹቅ፥ በንፍሮ፥... መልክ ለምግብነት የሚውል የእህል አይነት::

***ባበለ**

**ተባበለ** ግ ተለመነ፥ ተቆላመጠ፥ ተሽበለበለ::

**አባበለ** ግ 1.ለመነ፥ አቆላመጠ፥ አሽበለበለ:: 2. ሸነገለ፥ ደለለ::

**ማባበያ** ስ መሸንገያ፥ መደለያ::

**ባቡር** ስ ከብረት በሚሰሩ በሁለት ሃዲዶች ላይ የሚጓዝ፥ በድንጋይ ከሰል ወይም በነዳጅ ወይም በሌላ ሃይል ግፊት የሚንቀሳቀስ የመጓጓዣ አይነት (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)::

**ባቡር መንገድ** ስ መኪና ወይም ባቡር የሚሄድበት መንገድ::

**ባቡር ጣቢያ** ስ የባቡር መነሻና መቆሚያ ቦታ::

**[የ]ባቡር ሃዲድ** ስ ለባቡር መጓጓዣ ተብሎ ጥርጊያ ይዞ የተዘረጋ የብረት መስመር::

**ባቡቲ** ስ ከስንዴ ዱቄት የሚዘጋጅ ጥቢኛ፥ ህብስት::

**ባባ** ግ 1. ራራ፥ አዘነ:: 2. ፈራ፥ ራደ፥ ተንቀጠቀጠ:: 3.ባነነ:: 4. የናፍቆት ስሜት አደረበት::

**ባባ**

**አንባባ** ግ ስሪያ የፈለገ ወጠጤ ፍየል እንስቷን በእግሩና በአፉ እየጓጎጠ በመጮህ ለስሪያ ጎተጎተ፥ አነሳሳ::

**ቡቡ(ብቡ)** ቅ 1. ስጉ፥ የሚፈራ:: 2. አዛኝ፥ ርህሩህ::

**አባባ** ግ 1. አሳዘነ፥ መንፈስን አሸበረ:: 2. አባነነ:: 3. አስፈራራ::

**ባተ** ግ አዲስ ወር ወይም አመት ገባ::

**መባቻ** ስ የወር መጀመሪያ ወይም መግቢያ (ቀን)::

**አባተ** ግ ጀመረ (አዲስ የገባ ወርን):: *መስከረምን የአባተው አገር ቤት ነው::*

**ባተለ** ግ 1. ብቻውን ለፋ፥ ደከመ:: 2. ሚስት አልባ ሆነ::

**ባተሌ** ቅ 1. አጋዥ፥ ረዳት የሌለው፥ ብቻውን የሚለፋ:: 2. ሚስት የሌለው (ወንድ) ወይም ባል የሌላት (ሴት)::

**ባተሎ(ዘባተሎ)** ስ ውዳቂ፥ ቡትቶ የሆነ ልብስ፥ ጨርቅ::

**ባት** ስ ከቅልጥም በስተሂላ፥ በቋንጃና በተረከዝ መካከል የሚገኝ፥ ፍርጥም ያለ የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::


**ባትህን አሳየኝ** ቶሎ ቶሎ ተራመድ፥ ሂድ::

**ባተ ሁለት** ከጉያና ከጭን አካባቢ ሰፊ ሆኖ ወደታች ጠበብ እያለ ይወርድና ባት ላይ የሚቆም የሱሪ አይነት ::

**-ባት** "-ቢት" ን ተመ.

**ባትሪ**[1] ስ በፈሳሽ ወይም በጠጣር መልክ ተዘጋጅቶ አስፈላጊውን ሃይል፥ ብርሃን፥ ሙቀት ለመስጠት የሚያገለግል የኤሌክትሪክ ጉልበት ክምችት::

**ባትሪ**$^{2}$ **(የእጅ ባትሪ)** ስ አነስተኛ በሆነ እሽግ ውስጥ በተሞላ የኤሌክትሪክ ሃይል (ባትሪ ድንጋይ) የሚሰራ፥ በጨለማ ጊዜ ብርሃን ለመስጠት የሚያገለግል፥ የተለያየ ቅርፅና መጠን ያለው እቃ፤ የባትሪ ቀፎ፥ ላምባዲና እየተባለም ይጠራል::



ባትሪ

**ባትሪ ድንጋይ** ስ ለባትሪ(ለእጅ ባትሪ)፥ ለሬዲዮ፥...ተግባር የሚያገለግል፥ በአነስተኛ እሽግ ውስጥ ተከማችቶ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ሃይል ወይም ጉልበት::

**-ባቸው "-በት"** ን ተመ.

**-ባችሁ** ዝ.ከ.

**ባነነ** ግ 1. እንቅልፍ ላይ እንዳለ ሰውነቱን በድንጋጤ አንቀሳቀሰ፥ ብትት አለ:: 2. ከእንቅልፍ ድንገት ነቃ፥ ተነሳ:: 3.(ዘይ.) ዘግይቶ ነቃ፥ አወቀ::

**ባና** ስ ከበግ ፀጉር የሚሰራ ነጭ ወይም ቀይ ወይም የተለያዩ ቀለማት ያሉት (ዝንጉርጉር የሆነ) እንደብርድ ልብስ የሚያገለግል ወፍራምና ሻካራ የሆነ የሱፍ ልብስ አይነት::

**ባንባ "ባምባ"** ን ተመ.

**ባንክ** ስ 1. ጥሬ ገንዘብና እንደ ወርቅ ያሉ ውድ ማእድናት በጥንቃቄ ተጠብቀው የሚቀመጡበት እንደሳጥን ያለ እቃ:: 2. ጥሬ ገንዘብን እንደውለታው ወለድ እየከፈለ ወይም ያለወለድ የሚያስቀምጥ ወይም ለደንበኞቹ በወለድ የሚያበድር፥ ልዩ ልዩ ሰነዶችንና ማእድናትን በአደራ የሚያስቀምጥ የአገልግሎት ሂሳብ እያስከፈለ የሃዋላና ሌሎች ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጥ ድርጅት::

**የባንክ ኖት** ስ በህግ የተፈቀደና ለመገበያያ አገልግሎት የሚውል የወረቀት ገንዘብ::

**ባንኮኒ** ስ በቡና ቤቶች ውስጥ የቡና ማፍሊያ መኪናና የአልኮል መጠጥ ጠርሙሶች በተደረደሩበት ቦታ አጠገብ የሚደረግ፥ በውስጡ ቀለል ያሉ እቃዎችን ለመደርደር ወይም ለማስቀመጥ የሚችል፥ በጠረጴዛ ቅርፅ የሚሰራ እቃ::

**ባንዲራ** ስ በአብዛኛው የተወሰኑና የተለያዩ ቀለማት ካሏቸው ጨርቆች የሚዘጋጅ፥ የአንድ አገር የነፃነት ምልክትና መለያ፤ ሰንደቅ አላማ::

**ባንድ** ስ በአንድ ቡድን ውስጥ ተደራጅተው የሚሰሩ የሙዚቃ ተጫዋቾች የሚገኙበት አካል::

**ባኞ** ስ የገላ መታጠቢያ ገንዳ::

**ባኞ ቤት** ስ የገላ መታጠቢያ ገንዳ የሚገኝበት ክፍል::

**ባእድ** (ብ.ቁ. **ባእዳን**) ቅ (ሰዋ.) 1. የስጋ ዘመድ ያልሆነ፤ ባዳ:: 2. ለአንድ ነገር የራሱ አካል ያልሆነ፥ ሌላ (አካል)::

**ባእድ መነሻ** ስ (ሰዋ.) መጀመሪያውኑ በስርወ ቃሉ ወይም በአንድ የቃል መነሻ ስር ላይ ያልነበረ፥ በእርባታ ጊዜ ከውልድ ቃል በስተመነሻ በኩል በተቀጣይነት ገብቶ የውልድ ቃሉ አካል ሆኖ የሚያገለግል እስር ምእላድ:: *መ-፥ቢ-፥አ-፥... (ለምሳሌ ሰራ ብሎ - መስሪያ፥ ቢሰራ፥ አሰራር፥...)*

**ባእድ መድረሻ** ስ (ሰዋ) በስርወ ቃሉ ላይ ያልነበረ፥ ከውልድ ቃል በስተመድረሻ በኩል በተቀጣይነት የሚገባ እስር ምእላድ:: *-ያ፥ -ሀ፥... (ለምሳሌ ሰራ ብሎ -መስሪያ፥ ሰራሀ፥...)::*

**ባእድ ቋንቋ** ስ አገርኛ ያልሆነ የውጪ አገር ቋንቋ::

**ባእድ አገር** ስ ውጪ አገር::

**[የ]ባእድ አገር ሰው** ስ የውጪ ዜጋ የሆነ ሰው::

**ባእድ ዘር** ስ (ሰዋ.) በስርወ ቃሉ ላይ ያልነበረ፥ በእርባታ መንገድ ተፈጥሮ በውልድ ቃል መነሻና መድረሻ ላይ በቅጥያነት ገብቶ፥ የውልድ ቃሉ አካል መስሎ ወይም ሆኖ የሚገኝ እስር ምእላድ:: *መ-፥-ያ፥...(ለምሳሌ ሰራ ብሎ መስሪያ)::*

**ባከነ** ግ 1. አለቀ፥ ጠፋ(ገንዘብ):: 2. ገንዘቡ ያለ አግባብና ያለ አላማ እንዲጠፋ፥ እንዲያልቅ ተደረገ:: 3. ለፋ፥ ዞረ፥ ደከመ::

**ባካና** ቅ 1. ገንዘብ የማይበረክትለት፥ የሚያጠፋ:: 2. እረፍት የለሽ፥ ባተሌ::

**ብኩን** ዝ.ከ.

**አባከነ** ግ 1. ገንዘብን ወይም ሌላ ነገርን ያለአግባብ አጠፋ፥ በተነ:: 2. አለፋ ፥ አደከመ፥ አዞረ::

**አባካኝ** ቅ ገንዘብ የማይበረክትለት፥ እጁ ላይ የማይቆይለት፥ ለሚረባውም ለማይረባውም ነገር ገንዘብ የሚያጠፋ::

**ተብከነከነ** ግ 1. በጣም ተናደደ፤ በቁጭት፥ በንዴት ተቃጠለ:: 2. ጠፋ፥ ተድፋፋ፥ አላግባብ አለቀ:: 3. ናወዘ፥ ተንከራተተ፥ ለፋ::

**አብከነከነ** ግ 1.በጣም አናደደ፤ የሀሊና እረፍት አሳጣ፥ ቆጨ፥ ከነከነ:: 2. አጠፋ፥ አጥፋፋ::

**ባክቴሪያ** ስ በአይን የማይታይና ረቂቅ የሆነ፥ በአየር፥ በውሃ፥ በአፈር፥ እንዲሁም ህይወት ባላቸው ወይም በሞቱ ነገሮችና በተክሎች ውስጥ የሚገኝ አንዳንዱ ጠቀሜታ ያለው አንዳንዱ ለበሽታ ምክንያት የሚሆን ህዋስ።

**ባውሌ** ስ ለድር ማድሪያና ለማዳወሪያ የሚያገለግል አንክርት፤ ዋግምበ።

**ባዘቀ** ግ ተነከረ፥ ተዘፈቀ (በእዳ ወይም በሌላ ነገር)።

**ባዘተ** ግ 1.በእጁ ፈለቀቀ፥ በጨቀ፥ አፍታታ፥ አለሰለሰ (ጥጥን)። 2.ተፍታታ፥ ተፈለቀቀ፥ ተበጨቀ፥ ለሰለሰ (ጥጥ)። 3. ላመ፥ ደቀቀ፥ ድርና ማጉ ቡን አለ፥ አለቀ (የተዘወተረ ልብስ)። 4. ዛለ፥ ደከመ፥ ጣመነ (ሰውነት)።

**ባዘቶ** ስ የተፈለቀቀ፥ የተበጨቀ፥ የለሰለሰ ጥጥ።

**ባዘቶ ገላ** ቅ ሰውነቱ ለስላሳ፥ ድንቡሽቡሽ የሆነ።

**ብዝት** ስ ባዘቶ።

**አባዘተ** ግ 1. የ"ባዘተ"ን አንደኛ ፍቺ ተመ. 2.(ዘይ.) አማ።

**ባዘነ** ግ 1. ወዲት እንደሚሄድ ትክክለኛውን መንገድ ስለሳተ ወደሌላ አቅጣጫ ሄደ። 2. ወዲያና ወዲህ ተንከራተተ።

**ባዙቃ** ስ በትከሻ ላይ የሚያደርጉት፥ ክብደት የሌለው አፈ ሰፊ የጦር መሳሪያ።

**ባዛር** ስ የተለያዩ ሸቀጣሸቀጦች የሚተዋወቁበትና ረከስ ባለ ዋጋ የሚሸጡበት፥ ብዙውን ጊዜ ለተወሰኑ ቀናት ብቻ የሚቆይ ወይም የሚካሄድ ገበያ።

**ባዜቃ** ስ ፈሳሽ ሆኖ ክብደት ያለው፥ በባሮ ሜትር፥ በቴርሞ ሜትር፥...ውስጥ የሚደረግ ንጥረ ነገር፤ ሜርኩሪ።

**ባዝራ** ስ ፈረስና በቅሎ የምትወልድ ፈረስ።

**ባዝራ ከድንጉል ወለደ** አስቀድሞ ሴት ቀጥሎ ወንድ ልጅ ወለደ።

**ባይተዋር** ቅ ለአካባቢው እንግዳ ወይም አዲስ የሆነ፤ መጤ።

**ባዳ** "ባእድ" ን ተመ.

**ባድማ** ስ ጠፍ፥ ወና፥ ባዶ ቦታ።

**ባድሚንተን** ስ ከመረብ ወዲያና ወዲህ በመሆን የላባ ኳስን በራኬት እየመቱ ነጥብ ለማስቆጠር ስልታዊ እንቅስቃሴ የሚታይበት የጨዋታ አይነት፥ የላባ ኳስ ጨዋታ።

**ባዶ** ቅ 1. ምንም ነገር በውስጡ የሌለበት ፥ ወና። ስ 2. ምንም ያለመኖር ሁኔታ።

**ባዶውን ቀረ** ምንም ሳይዝ፥ ምንም ሳይተርፈው ቀረ።

**በባዶ ሆዱ /አፉ** ሳይበላ፥ እህል ሳይቀምስ።

**ባዶ ለባዶ** ዜሮ ለዜሮ። *በሁለቱ ተፎካካሪ ቡድኖች መካከል ምንም አይነት ነጥብ ወይም ውጤት አልተገኘም፤ ባዶ ለባዶ ናቸው።*

**ባዶ ራስ** የማያስተውል፥ የማያመዛዝን፥ የማያገናዝብ፥ እውቀት የለሽ (ሰው)።

**ባዶ ቤት** ስ 1. ምንም ነገር (ምግብ፥ መጠጥ ወይም ገንዘብ፥...) የሌለበት ቤት። 2. ሰው የሌለበት ወና ቤት።

**ባዶ እጁን** ምንም ሳይዝ።

**ባዶ እጁን ቀረ** ያለ ወገን፥ ያለ ንብረት፥... ብቻውን ቀረ።

**ባዶ እግሩን** ጫማ ሳያደርግ፥ ያለጫማ።

**ባጀ** ግ ቆየ፥ ከረመ።

**ባጀት** "በጀት"ን ተመ.

**ባጎተ** "ቧገተ" ን ተመ.

**ባጎታ** "ቧገተ" ስር "ቧገታ"ን ተመ.

**ባጠጠ** ግ ተሞላቀቀ፥ ባለገ።

**ባጣጭ** ቅ ሞልቃቃ፥ ባለጌ።

**ባጥ** ስ የቤት ጣሪያ።

**ባጥ አለ** ወደላይ እመር፥ እንጣጥ አለ።

**ቤ** የ"በ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ቤርጎ** "አልቤርጎ" ን ተመ.

**ቤሳ** ስ እንደ ሳንቲም ያለ የድሮ ገንዘብ።


**ቤሳ ቤስቲን የለውም** ምንም ገንዘብ የለውም።

**ቤሳ ምላጭ** ስ ምላጭ።

**ቤት** ስ 1. ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከጡብ፥... የሚሰራና ለተለያየ አገልግሎት (ለሰው ወይም ለእንስሳት መኖሪያ፥ ለእቃ ማስቀመጫ፥...) የሚውል፥ ዙሪያው በግድግዳ፥ ላዩ በጣሪያ የተከለለ መጠለያ፤ ጎጆ፥ ሳር ቤት፤ ቆርቆሮ ቤት፥ ህንፃ፥...(ስእሉን በሚቀጥለው ገፅ ተመ.)። 2. የትውልድ ወይም የዝምድና ደረጃ፤ ሃረግ። *እኔና እንተ አራት ቤት ነን ወይም የአንድ ቅድመአያት ልጆች ነን ማለት ነው*። 3. የገበጣ መጫወቻ ጉድጓድ። 4. ትዳር። *ልጅህ ቤት ይዟል?* 5. የአሃዞች የአቀማመጥ ደረጃ። *የአንድ ቤት/የአስር ቤት*። 6. የአንድ ነገር ማስቀመጫ፥ መክተቻ፥ ሳጥን። *የክብሪት ቤት*። 7. የግጥም ስንኞች የመጨረሻ ሆሄ። 8. ንግድ ወይም ስራ የሚያካሄድበት ቦታ። *ንግድ ቤት/ፎቶ ቤት*።

**ቤቱ ሞቀ** ኑሮው ተሳካ፥ ተሟላ።

**ቤቱ ተዘጋ** የቤቱ ዋና የነበረው ሰው በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ስለተለየ በቤተሰቡ ላይ ችግር መጣ፥ ወደቀ።




ቤት

**ቤቱ ፈረሰ** 1. ንብረቱ፥ ሃብቱ ተበተነ፥ ባከነ ድህነት ላይ ወደቀ:: 2. ከትዳር ተፈናቀለ (በፍቺ ወይም በሌላ ምክንያት)::

**ቤቱን ሰው አያውቀውም** ከቤቱ ሰው ጋብዞ፥ አብልቶ፥ አጠጥቶ አያውቅም::

**ቤቱን አሸነፈ** ራሱን ችሎ ቤቱን አስተዳደረ፥ ሰርቶ በሚያገኘው የቤቱን ችግር አስወገደ::

**ቤቴ ቤቴ አለ** ለትዳሩ፥ ለንብረቱ ተጋ፥ አሰበ፥ ተትከረከረ፥ ጣረ::

**ቤት ለእንቦሳ** አዲስ ቤት ውስጥ የገቡ ሰዎችን ለመጠየቅ የሚሄድ ሰው መልካም ምኞቱን ለመግለፅ የሚያቀርበው የሰላምታ ቃል::

**ቤት ለእንግዳ** ከቤት ደጃፍ ላይ የቆመን እንግዳ ወደ ቤት ዝለቅ፥ ግባ ለማለት የሚነገር የመጋበዣ ቃል::

**ቤት ሙላ** (ቤ.ክህ.) ከጉባኤ ቃና ጀምሮ እየተማረ መወድስ ላይ ደረሰ፤ የቅኔ ትምህርቱን አዳረሰ::

**ቤት አሳየ** መልስ ጠርቶ ጋበዘ (ሙሽሮችን)::


**ቤት ከቤቱ ገባ** በሃብት፥ በደረጃ ÷ ... ተመሳሳይነት ያላቸው ሰዎች በጋብቻ ተሳሰሩ ወይም ተጋቡ::

**ቤት ያፈራው** ከቤት ውስጥ ሊገኝ የቻለ ማንኛውም ምግብና መጠጥ::

**ቤት ይቁጠረው** የችግሩ፥ የመከራው፥ የሚቼ ሰው ብዛት ልክ በትክክል ሊታወቅ አይችልም፤ ስፋት አለው::

**[ከ]ቤት (እቤት) ዋለ** በህመም ወይም በሽምግልና ምክንያት ከቤት ተቀመጠ፥ ከቤት ለመውጣትና ወዲያ ወዲህ ብሎ ለመስራት አቅም አጣ::

**ቤቶች(እዚህ ቤት)** ከውጪ የቆመ እንግዳ በቤት ውስጥ ሰው እንዳለና እንደሌለ ለማወቅ




ወይም ሰዎቹ ከቤት ውስጥ ብቅ ብለው እንዲያነጋግሩት ሲፈልግ ሰዎቹን የሚጠራበት ቃል::

**ቤተልሔም** ስ 1. በኢየሩሳሌም የምትገኝ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ የተወለደባት ቦታ:: 2. በቤተክርስቲያን ቅፅረ ግቢ ውስጥ ከቤተክርስቲያኑ በስተምስራቅ በኩል የምትገኝና መስዋእት የሚዘጋጅባት አነስተኛ ቤት::

**ቤተመቅደስ** ስ 1. የእሪት እምነት ተከታዮች ፀሎትና አምልኮ የሚያደርጉበት ቤት:: 2. በቤተክርስቲያን ውስጥ የቅዳሴ ፀሎት የሚደርስበት፥ መስዋእት የሚፈተትበት ክፍል፤ መቅደስ::

**ቤተመንግስት** ስ የአንድ ሃገር መሪ ወይም ርእሰ ብሄር የሚኖርበት የመንግስት ቤት::

**ቤተመዘክር** ስ ጥንታዊና ታሪካዊ የሆኑ ቅርሶች ተጠብቀው የሚቀመጡበትና በህዝብ የሚጎበኙበት ቤት::

**ቤተመዛግብት** ስ ልዩ ልዩ ሰነዶችና ፅሁፎች የሚከማቹበትና ተጠብቀው የሚቀመጡበት ቤት::

**ቤተመፃህፍት** ስ የተለያዩ መፃህፍት የሚገኙበትና አንባቢያን በትውስት ወይም ከውስጡ ገብተው በማንበብ የሚገለገሉበት ቤት::

**ቤተምርፋቅ "ረፈቀ"** ስር **"ምርፋቅ"** ን ተመ.

**ቤተሞገስ** ስ የቤተክርስቲያን ወይም የትልቅ ቤት ጉልላት::

**ቤተሰብ** ስ 1. የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች:: 2. በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች:: 3. የሚቀራረቡ፥ የሚተሳሰቡ፥ የሚዋደዱና እንደ ዘመድ የሚተያዩ ጓደኞሞች፥ አብሮ አደጎች::

**ቤተሰብ አፈራ** ትዳር መሰረተ፥ ልጅ ወለደ::

**ቤተሳልገኝ** ስ ከጎድን ጋር የተያያዘ የከብት ስጋ ብልት::

**ቤተንጉስ** ስ ሰቀላ ወይም ሞላላ ያልሆነ ክብ ቤት።

**ቤተአምልኮ** ስ 1. ሃይማኖታዊ ስነ ስርአት የሚፈፀምበት ቤት። 2. ባእድ አምልኮ የሚፈፀምበት ቦታ፥ ቤት።

**ቤተእግዚአብሄር** ስ እግዚአብሄር የሚወደስበት፥ የሚመለከበት፣ ሃይማኖታዊ ስነ ስርአት የሚካሄድበት ቤት፣ ቤተ መቅደስ፥ ቤተክርስቲያን፥...።

**ቤተክህነት** ስ የሃይማኖትና የካህናት አስተዳደር ነክ ስራ የሚካሄድበት ድርጅት፥ መስሪያ ቤት ወይም ቢሮ።

**ቤተክርስቲያን** ስ የክርስትና እምነት ተከታዮች ለፀሎት፣ ለስግደት፣ ስብከተ ወንጌልን ለመከታተል፥... የሚሰበሰቡበት፥ ለዚሁ አላማ ተብሎ የተሰራ ቤት፤ ቤተእግዚአብሄር።

**ቤተክርስቲያን ሳመ** ወደቤተክርስቲያን ሄዶ እጅ ነሳ፥ ሰገደ፥ ተሳለመ፥ ፀሎት አደረገ፥...።

**ቤተክርስቲያን ሳሚ** ቅ አዘውትሮ ወደቤተክርስቲያን እየሄደ እጅ የሚነሳ፥ የሚሰግድ፥ የሚሳለም፥ የሚፀልይ (ምእመን)።

**ቤተክርስቲያን ዘጋ** 1. የቤተክርስቲያን አገልግሎት እንዲቋረጥ ወይም እንዳይካሄድ አደረገ። 2. የቤተክርስቲያንን በር በመዝጋት መሃላ ፈፀመ(አላደረግሁም፥ አልፈፀምኩም በማለት)።

**ቤተዘመድ** ስ ዘመዳሞች፤ የስጋ ዝምድና ያላቸው ሰዎች።

**የቤተዘመድ ዳኛ/ጉባኤ** ስ የተጣሉ ባልና ሚስትን ወይም ዘመዳሞችን ለማስታረቅ ወይም ለማስማማት የተመረጡ፤ የፍርድ ቤት ድጋፍ ያላቸው የሽምጋይ ዳኞች አካል።

**ቤተፀሎት** ስ ሃይማኖታዊ ትምህርት የሚሰጥበት፥ ፀሎት የሚደረግበት፥... ቤት።

**ቤተፈት** ቅ 1. አግኝቶ ያጣ፥ የደሀየ። 2. ትዳሩ የፈረሰ።

**ቤት ማያ** ስ አዲስ ለተጋቡ ሰዎች የሚደረግ ግብዣ፤ መልስ።

**ቤት ሰርሳሪ** ስ ዘራፊ፥ ሌባ።

**የቤት ልጅ** ስ 1. (የን.አነ.) ከቤት አገልጋይ የተወለደ ልጅ። 2. ዘዋሪ ያልሆነ፥ ጨዋና ጭምት የሆነ ልጅ። 3. በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ያደገ የሌላ ሰው ልጅ።

**የቤት መኪና** ስ ሰዎች በየግላቸው ለመጓጓዣነት የሚጠቀሙበት አነስተኛ መኪና (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።

**የቤት ሰራተኛ** ስ በግለሰቦች መኖሪያ ቤት ተቀጥሮ የሚያገለግል ሰው።

**የቤት ስራ** ስ 1. በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚከናወን እንደ ምግብ ማብሰል፥ ልብስ ማጠብ፥... ያለ ስራ። 2. ተማሪዎች ከትምህርት ሰአት ውጪ ከመኖሪያ ቤታቸው ወስደው እንዲሰሩት የሚሰጣቸው የትምህርት ስራ።

**የቤት ስር(ስራ)** ስ ከቤት ውስጥ ተፈትሎ የተዘጋጀ ሸማ።

**የቤት እመቤት** ስ በቢሮ ስራ ወይም በሌላ ከቤት ውጭ በሆነ መተዳደሪያ ላይ ያልተሰማራች ባለትዳር ሴት።

**ቤተኛ** ቅ እንደቤተሰብ የሚታይ፣የሚታሰብ ወዳጅ።

**ቤንዚን** ስ ፔትሮሊየም ከሚባል ድፍድፍ የሚገኝ፥ በፍጥነት የመቀጣጠል ባህርይ ያለውና የተለያዩ ሞተሮችን ለማንቀሳቀስ የሚችል እንዲሁም እንደ ሱፍ ያሉ ልብሶችን በደረቁ ለመጥረግና ለማፅዳት የሚረዳ በፈሳሽ መልክ የሚገኝ ነዳጅ።

**ቤዛ** ስ 1. አዳኝ፥ መድሃኒት። *ክርስቶስ ቤዛችን ነው።* 2. ዋቢ፥ ሃላፊ፥ መድን። *የገዛሁት ፈረስ ቤዛ አለው።* 3. መከላከያ። *ባርኔጣ የፀሃይና የብርድ ቤዛ ነው።* 4. በካሳ መልክ ወይም እንደምትክ፥ እንደ መለወጫ፥ እንደ መያዣ ሆኖ የሚቀርብ ነገር። *ጠላፊዎቹ ተጠላፊውን የለቀቁት ቤዛ ተቀብለው ነው።*

**ቤዠ**

**ተቤዠ** ግ አዳነ፥ ታደገ፥ ቤዛ ሆነ።

**ብ** የ"በ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ብ __** (ከ "ይ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ቢ-" ፥ ከ "አ" ድምፅ በፊት ሲገባ "ባ-" ይሆናል። በሃላፊ ጊዜ በሚነገር ግስ ላይ "በ-" ይሆናል)። በግስ መነሻ ላይ እየተቀጠለ ምክንያትን፥ ምኞትን፥ ፀፀትን፥... የሚገልፅና ግስን ከማሰር የሚያስቀር ምእላድ። *ብፈልግ እሄዳለሁ/ ቢመጣም ባይመጣም ቦታው ይዘጋጅ/ በአገለገልሁ እመሰገናለሁ እንጂ አልወቀስም /ሽልማቱን በተቀበለ ኖሮ ጥሩ ነበር።*

**ብሃ "በሃ"** ን ተመ.

**ብሄር** ስ 1. ሃገር። 2. አንድ አይነት ቋንቋ፥ ባህልና ስነልቡናዊ አመለካከት ያለው፥ በታሪክ፥ በኢኮኖሚ፥...የተሳሰረና በተወሰነ ክልል ውስጥ የሚኖር ህዝብ።

**ብሄረሰብ** ስ ከደም አንድነት ይልቅ በክልል፥ በቋንቋና በባህል አንድነት ላይ የተመሰረተ፥ የተለያዩ ነገዶች የተዋሃዱበት ማህበረሰብ።

**ብሄር አቀፍ** ቅ አገር አቀፍ።

**ብሄራዊ** ቅ የሃገር።

**ብሄራዊ ወታደር** ስ በብሄራዊ ውትድርና አገልግሎት ላይ ያለ ዜጋ።

**ብሄራዊ ውትድርና** ስ በተወሰነ የእድሜ ክልል ውስጥ ለተወሰነ ጊዜ በውትድርና ተግባር ተሰልፎ አገርን የማገልገል የዜግነት ግዴታ::

**ብሄራዊ ጦር** ስ በአንድ አገር ውስጥ ከሚገኙ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጣ ሰራዊት::

**-ብህ** "-ብት"ን ተመ.

**ብህትውና** "ባህታዊ" ስር ተመ.

**ብሆር** ስ መልኩ በአብዛኛው ድፍርስ ያለ ቢጫ ሆኖ በአይኖቹ ዙሪያ ነጫጭ ፀጉሮች ያሉበት፥ ቀጫጭን ሁነው ወደፊት ቀልበስ ያሉ ቀንዶች ያሉት፥ በብዛት አለትና ቁጥቋጦ በሚገኝበት ተራራማ ስፍራ የሚኖር፥ ሳርና ቅጠላ ቅጠል የሚመገብ የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)::

**-ብሽ** "-ብት"ን ተመ..

**-ብን** ዝ.ከ.

**-ብኝ** ዝ.ከ.

**ብሉል** "በለለ" ስር ተመ.

**ብሉይ[ኪዳን]** ስ ከአሪት ዘፍጥረት እስከ ትንቢተ ሚልክያስ ያለው የመፅሃፍ ቅዱስ ክፍል::

**ብላሽ** "*በለሸ" ስር ተመ.

**ብላታ** ቅ በቤተመንግስት ውስጥ ለሚያገለግልና ለንጉሱ ዋና ጉዳይ ፈፃሚ ለሆነ ሲቢል ሰው ይሰጥ የነበረ ከበላቴን ጌታ ዝቅ የሚል የማእረግ ስም::

**ብላቴና** ስ ወጣት ወይም ሴታ የሆነ ወይም የሆነች ልጅ::

**ብላቴን ጌታ** ስ በሚኒስተርነት ደረጃ ላለ ወይም በሌላ ከፍተኛ የስልጣን እርከን ላይ ለደረሰና ዝንባሌው ወደ ስነፅሁፍና ጥናት ለሆነ ሲቢል ሰው ይሰጥ የነበረ ማእረግ::

**ብላጊ** "በለገ" ስር "ብልግ"ን ተመ.

**ብሌን (የአይን ብሌን)** ስ የአይን ጥቁሩ ክፍል፥ የአይን ማማሚቶ ያለችበት ጥቁር አካል (ስእሉን አይን ስር ተመ.)::

**ብል** ስ ልብስን፥ ቆዳን፥...የሚበላ፥ የሚበሳሳ የተባይ አይነት፥ ነቀዝ::

**ብልህ** ቅ አዋቂ፥ አስተዋይ፥ ዘዴኛ::

**ብልሃት** ስ 1.እውቀት፥ ጥበብ፥ ዘዴ:: 2. ምክንያት፥ ሰበብ:: *ያለብልሃት ሊቀር ላይችልም::*

**ብልሃተኛ** ቅ ጥበበኛ፥ ዘዴኛ::

**ብልሹ** "*በለሸ" ስር ተመ.

**ብልሽት** ዝ.ከ.

**ብልቃጥ(ቢልቃጥ)** ስ ለሽቶ ወይም ለቀለም፥...መያዣ የሚሆን አነስተኛ ጠርሙስ::

**ብልት** "በለተ" ስር ተመ.

**ብልዝ** "በለዘ" ስር ተመ.

**ብልግና** "ባለገ" ስር ተመ.

**ብልጠት** "በለጠ[2]" ስር ተመ.

**ብልጣ ብልጥ** ዝ.ከ.

**ብልጥ** ዝ.ከ.

**ብልጫ** "በለጠ[1]" ስር ተመ.

**ብልጭልጭ** "*በለጨ" ስር ተመ.

**ብልጭልጭታ** ዝ.ከ.

**ብልጭታ** ዝ.ከ.

**ብልፅግና** "በለፀገ" ስር ተመ.

**ብሎት** "በላ" ስር ተመ.

**ብረት** ስ 1. የህንፃ መሳሪያዎችን፥ እንደ መጥረቢያ፥ ዶማ፥ ቢላዋ፥... ያሉ ቁሳቁሶችን ለመስራት በጥሬ እቃነት የሚያገለግል ጠንካራ የማእድን አይነት:: 2. ጠመንጃ:: 3. (ዘይ.) ብረቱ፥ ጠንካራ::

**ብረት አውርድ** ጠመንጃህን ከትከሻህ ላይ አውርድ የሚል የወታደራዊ ሰልፍ ስነስርአት ትእዛዝ::

**ብረት አውጣ** ጠመንጃህን ከትከሻህ ላይ አድርግ የሚል የወታደራዊ ሰልፍ ስነስርአት ትእዛዝ::

**በብረት ሰላም በል(በብረት ሰላምታ ስጥ)** በወታደራዊ የጠመንጃ ሰላምታ አሰጣጥ ደንብ መሰረት ሰላምታ አቅርብ ወይም የሰላምታ ምልክት አሳይ የሚል ትእዛዝ::

**ብረት ለበስ ተሽከርካሪ** ስ አካሉ በብረት የተሸፈነ ተሽከርካሪ፥ መኪና::

**ብረት ማእዘን** ስ አናጢዎች፥ ግንበኞች፥... የማእዘን ቅርፅ ለማውጣት ወይም የቅርፁን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የሚለኩበት የማእዘን ቅርፅ ያለው መሳሪያ፤ እስኳድራ እየተባለም ይጠራል::

**ብረት ምጣድ** ስ ለቡና፥ ለጥራጥሬ መቁያና ለቂጣ መጋገሪያ፥... የሚያገለግል ከብረት የተሰራ ምጣድ::

**ብረትቀለም** ስ ብረትና ብረት ነክ የሆኑ ነገሮችን ለመቀባት (ለማስጌጥ) የሚያገለግል፥ በቀላሉ የማይለቅ የቀለም አይነት::

**ብረት ቀጥቃጭ** ስ (የን. አነ.) በገጠር አካባቢ እንደ ማረሻ፥ ቢላዋ፥ ማጭድ ያሉ መሳሪያዎችን ከቤቱ ውስጥ እያዘጋጀ ለተጠቃሚው የሚሸጥ የእጅ ባለሙያ:: 2. (ስድብ) ቡዳ፥ ጠይብ::

**ብረት ቆብ** ስ ከብረት የተሰራ ቆብ፤ የራስ ቁር::

**ብረት አቅላጭ** ስ ብረት የሚገኝበትን አፈር ወይም ማእድን እያነጠረ የተጣራውን ብረት በማውጣት እንደ ማረሻ፥ ዶማ፥...ያሉ ልዩ ልዩ መሳሪያዎችን የሚሰራ ጥበበኛ።

**ብረት ድስት** ስ ከብረትና ብረት ነክ ከሆኑ ነገሮች የተሰራ ድስት።

**የብረት ቆሎ /አለሎ** (ዘይ.) ጠንካራ፥ የማይበገር፥ ጀግና።

**የብረት አር** ስ የብረት ማእድን ወይም ብረት የሚወጣው አፈር በእሳት እንዲቀልጥ ከተደረገና ብረቱ ተለይቶ ከወጣ በሂላ የሚቀረው ዝቃጭ፥ ጠጣር ጓል።

**ብሩህ** "በራ" ስር ተመ.

**ብሩሽ** "ቦረሸ" ስር ተመ.

**ብራ** "በራ" ስር ተመ.

**ብራሪ** "በረረ" ስር ተመ.

**ብራሮ** ዝ.ከ.

**ብራቅ** "በረቀ" ስር "መብረቅ" ን ተመ.

**ብራና** ስ እንደ ወረቀት ለመፃፊያነት የሚያገለግል የተፋቀና የለሰለሰ የበግ ወይም የፍየል፥... ቆዳ።

**ብራና ራስ** ስ (ስድብ) መላጣ።

**ብራኳ** ስ ከወገብ በላይ ከማጅራት በታች የሚገኝ የትከሻ አጥንት፤ መጋፊያ።

**ብር** ስ ውስጠ ክፍት የሆነ የገብስ ወይም የስንዴ፥...አገዳ።

**የብር እህል** ስ እንደ ገብስ፥ ስንዴ፥ አጃ፥... ያለ የእህል አይነት።

**ብረሽሽ** ጎላ ብሎ የማይታይ፥ ኮሳሳ ሰው።

**ብረሽሽ እህል** አገዳው ወይም ብሩ አጠር አጠር ብሎ ፍሬው ጥሩ የሆነ የገብስ ወይም የስንዴ ሰብል።

**ብር** ስ 1. ገንዘብ። 2. መቶ ሳንቲም ወይም የመቶ ሳንቲም ዋጋ ያለው የወረቀት ገንዘብ። 3. ከአፈር ተነጥሮ የሚወጣ፥ደረጃው ከወርቅ ቀጥሎ ዝቅ ብሎ የሚገኝ የማእድን አይነት።

**ብርአለንጋ** ስ 1. እጀታው ከብር የተሰራ አለንጋ። 2. የዛር ስም።

**ብርአምባር** ስ 1. ከብር የተሰራ አምባር። 2. ክብረንፅህና፥ ድንግልና።

**ብርአፍሳሽ** ስ ብር እያቀለጠ የተለያዩ ጌጣጌጦችን የሚሰራ የእጅ ባለሙያ።

**ብር ጉብጉባት** ስ በለምድ፥ በካባ፥ በቀሚስ፥... ጥልፍ ላይ የሚደረግ፥ ልዩ ልዩ ቅርፅ ያለው የብር ጌጥ።

**ብርጣፋ ጋሻ** ስ በብር የተጌጠ ጋሻ።

**የብር ኢዮቤልዩ** ስ የአንድ ድርጊት 25ኛ አመት በአል።

**ብርሃን** "በራ" ስር ተመ.

**ብርሌ** ስ ከአንገቱ ቀጠን ብሎ ከሆዱ ሰፋ የሚል፥ ከብርጭቆ መስሪያ ቁሳቁስ የሚሰራ፥ ለጠላና ለጠጅ መጠጫ የሚያገለግል እቃ።



አፈ ድስት ብርሌ



ሹርቤ ብርሌ

**ብርቅ** ቅ 1. አዘውትሮ የማይታይ፥ የማይገኝ፥ የማይደረግ ነገር ግን ሲያጋጥም ተወዳጅነት፥ ማራኪነት፥ ተፈላጊነት የሚኖረው። 2. ገና ያልተጠገበ፥ ያልተሰለቸ፥ አዲስ ወይም እንግዳ የሆነ።

**ብርቅዬ** ቅ 1. ደስ የሚል፥ የሚያምር። 2. ድንቅ።

**ብርቅርቅ** "በረቀ" ስር ተመ.

**ብርባሮ** "በረበረ" ስር ተመ.

**ብርብራ** ስ ፍሬው ወይም ቅጠሉ አሳን አስክሮ ለመያዝ የሚያገለግል የዛፍ አይነት።

**ብርቱ** "በረታ" ስር ተመ.

**ብርታት** ዝ.ከ.


**ብርቱካን** ስ ከሎሚ ከፍ የሚልና ጣእሙ ጣፋጭ የሆነ ውሃ ያለው የፍራፍሬ አይነት። ፍሬውን የሚያፈራው ተክልም ብርቱካን ይባላል።

**ብርት** ስ ከመዳብ ወይም ከነሃስ የተሰራ የእጅ መታጠቢያ ሳህን።

**ብርንዶ[ስጋ]** ስ ያልተቀቀለ ወይም ያልተጠበሰ ቀይ ሙዳ ፥ ጥሬ ስጋ።

**ብርእ** "ብእር" ን ተመ.

**ብርኩማ[1]** ስ 1. ከእንጨት የሚሰራ ትራስ። 2. በእጆቻቸው እየተመረኮዙ በእንፉቅቅ የሚሄዱ የአካል ጉዳተኞች እጆቻቸው እንዳይጎዱ እንደ እጅ መጫሚያ የሚገለገሉበት ከእንጨት የሚሰራ አጭር የእጅ መርገጫ። 3. የበገና ወይም የክራር፥... አውታር መደገፊያ፥ መወጠሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።



ብርኩማ 1ኛፍቺ

**ብርኩማ**[2] ስ የበርበሬ ዛላ ቂጥ እንጨት::
**ብርኩታ** "በረኮተ" ስር ተመ.
**ብርካቴ** "በረከተ" ስር ተመ.
**ብርክ** "በረከ" ስር ተመ.
**ብርክርክ** ዝ.ከ.
**ብርኮት(ብርኳኔ)** ስ ቆዳ የለበሰ የእንጨት ትራስ፤ ብርኩማ::
**ብርዝ** "በረዘ" ስር ተመ.
**ብርድ** "በረደ" ስር ተመ.
**ብርጉድ** ስ ጣፋጭ መአዛ ወይም ሽታ ያለው፥ ሴቶች ገላቸውን በጭሱ የሚታጠኑበት የእንጨት አይነት፤ ቡክቡካ::
**ብርጌድ** ስ 1. በውስጡ የተወሰነ ቁጥር ወይም ብዛት ያላቸውን የጦር አባላት የሚይዝ የአንድ ክፌለ ጦር እግረኛ ክፍል:: 2. ለተወሰነ አላማ የተደራጁ ሰዎች የሚገኙበት ቡድን::
**ብርግድ** "በረገደ" ስር "በርጋዳ" ን ተመ.
**ብርጭቆ** ስ መስታወት ከሚሰራበት ንጥረ ነገር የሚሰራ ለውሃ፥ ለጠላ፥... መጠጫ የሚያገለግል እቃ::
**ብርጭቆ ወረቀት** ስ እንደብረትና እንጨት ያሉ ነገሮችን ለመፈግፈግና ለማለስለስ የሚያገለግል፥ አንደኛው ገፁ ለስላሳ ሁለተኛው ደግሞ እንደ አሸዋ የደቀቀ የጠርሙስ ስብርባሪ የተጣበቀበት ሻካራ ወረቀት::
**ብሳና (ምሳና)** ስ ቅጠሉ ሰፋ ያለና ለስላሳ የሆነ፥ በአብዛኛው ወይናደጋ ላይ የሚበቅል የዛፍ አይነት::
**ብሳይ** "በሰለ" ስር ተመ.
**ብስ** "በሳ" ስር ተመ
**ብስለት** "በሰለ" ስር ተመ.
**ብስል** ዝ.ከ.
**ብስራት** "*በሰረ" ስር ተመ.
**ብስቁል** "በሰቆለ" ስር ተመ.
**ብስቁልና** ዝ.ከ.
**ብስባሽ** "በሰበሰ" ስር ተመ.
**ብስብስ** ዝ.ከ.
**ብስና** "በሰና" ስር ተመ.
**ብስናታም** ዝ.ከ.
**ብስናት** ዝ.ከ.
**ብስኩት** ስ ዱቄት፥ ውሃ፥ ቅባት፥ ጨው ወይም ስኳር (እንደየአስፈላጊነቱ እንቁላል፥ ወተት ወይም የተለያዩ ቅመማት ሊጨመሩበት ይችላል) ተደባልቆ ከተቦካ በሂላ በስሱ በተለያየ ቅርፅ የሚጋገር የደረቅ ምግብ አይነት::
**ብስክ** "በሰከ" ስር ተመ.
**ብስክሌት** ስ በእግር በሚንቀሳቀሱ መዘወሪያዎች አማካይነት ሊሽከረከር የሚችልና ብዙውን ጊዜ ባለ ሁለት ጎማ የሆነ መጓጓዣ (ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)::
**ብስክስክ** "በሰከ" ስር ተመ.
**ብስጩ** "*በሰጨ" ስር ተመ.
**ብስጭት** ዝ.ከ.
**ብሶተኛ** "ባሰ" ስር ተመ.
**ብሶት** ዝ.ከ.
**ብሽ አለ(በሽ አለ)** ግ 1. አቅለሸለሸ፥ ቅልብሽ አለ:: 2. ድንገት ግልፍ አለ፤ የንዴት፥ የቁጣ ስሜት ተሰማ::
**ብሽሽት** ስ በጭንና በሆድ መጋጠሚያ ላይ በፍርንትት አካባቢ የሚገኝ ገላ (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::
**ብሽቅ** "በሸቀ[2]" ስር ተመ.
**ብሽቅጥ** "በሸቀጠ" ስር ተመ.
**ብቀታ** "በቀት" ስር "በቀታ" ን ተመ.
**ብቁ** "በቃ" ስር ተመ.
**ብቃት** ዝ.ከ.
**ብቅ**
**ብቅ አለ** ግ 1. ወጣ፥ ተገለጠ፥ ታየ:: 2. መጣ:: *ዛሬ ከየት ብቅ አላችሁ::* 3. ሄደ፥ ደረሰ:: *ወደገጠር ብቅ ብዬ እመጣለሁ::*
**ብቅ አደረገ** ግ አወጣ፥ ገለጠ፥ አሳየ::
**ብቅ ጥልቅ አለ** ወጣ ገባ አለ::
**ብቅ ጥልቅ አደረገ** ወጣ ገባ አደረገ::
**ብቅል** "በቀለ" ስር ተመ.
**ብቋያ** "በቀለ" ስር "ቡቃያ" ን ተመ.
**ብቡ** "ባባ" ስር "ቡቡ" ን ተመ.
**ብብት(ብብቻ)** ስ እጅና ትከሻ ከሚጋጠሙበት ላይ በስተውስጥ በኩል የሚገኝ፥ ከተወሰነ እድሜ በሂላ ለስላሳ ፀጉር የሚበቅልበት የሰውነት ክፍል (ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)::
**ብቱቶ** "በተተ" ስር "ቡትቶ" ን ተመ.
**ብትር** "በትር" ን ተመ.
**ብትቶ** "በተተ"ስር "ቡትቶ"ን ተመ.
**ብትን** "በተነ" ስር ተመ.
**ብትክትክ** "በተከ" ስር ተመ.
**ብቻ** 1. በተናጠል፥ ሌላ ሳይጨምር:: *እሱ ብቻ ይምጣ::* 2.ይሁን እንጂ:: *የበፊቱን ሂሳብ አልከፈልከኝም፤ ብቻ ለዛሬው አልጠይቅህም::* 3.ቅሬታን፥አለመርካትን፥...ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል:: *የተሰጠኝ ርስት የእርሻ አይደለም፤ ብቻ ለሌላ ተግባር ይጠቅም ይሆናል::*

4\. ግን:: *ወደማታ እንድትመጣ ብቻ እንዳታመሽ::*

**ለየብቻ** በተናጠል፥ ለየራስ:: *ለየብቻ መብላት ባገራችን እምብዛም ያልተለመደ ባህል ነው::*

**ብቻ ለብቻ** 1. አንድ ለአንድ:: *ዳዊትና ጎልያድ ብቻ ለብቻ ተፋለሙ::* 2. በተናጠል፥ ለየራስ:: *ብቻ ለብቻ እየመጣችሁ አነጋግሩኝ/ብርጭቆዎቹ እንዳይሰበሩ ብቻ ለብቻ አስቀምጣቸው::*

**የብቻ** 1. የግል፥ የራስ:: 2. ልዩ፥ ድንቅ:: *የሱ ቅጥልፍና የብቻ ነው::*

**ብቸኛ** ቅ 1. ከሌላ ሰው ጋር የማይገጥም፥ ጓደኛ የሌለው:: 2. አንድ በቀል፥ አንድያ:: *ብቸኛ ልጁን ለሞት አሳልፎ ሰጠው::*

**ብናኝ "በነነ"** ስር ተመ.

**ብንታ** ዝ.ከ.

**ብእር(ብርእ)** ስ ጫፉን ቀለም እያስነኩ ወረቀት ወይም ብራና ላይ ለመፃፍ የሚያገለግል ከመቃ ወይም ከሌላ ነገር የሚሰራ ወይም የተወሰነ የቀለም መጠን በውስጡ የሚይዝና እስካለቀ ድረስ ሳያቋርጥ ሊያስፅፍ የሚችል ጫፉ ብረት የሆነ የፅህፈት መሳሪያ::

**የብእር ስም** ስ ማንነቱ እንዲታወቅበት የማይፈልግ ፀሃፊ ለህዝብ በሚያቀርባቸው ፅሁፎች ላይ የሚጠቀምበት የምስጢር ስም::

**ብከላ "በከለ"** ስር ተመ.

**ብኩርና "*በከረ"**ስር ተመ.

**ብኩን "ባከነ"** ስር ተመ.

**ብክካ "በሃ ድንጋይ"** ን ተመ.

**ብወዛ "በወዘ"** ስር ተመ.

**ብው**

**ብው አለ** 1. በሃይል ተቀጣጠለ፥ ነደደ (እሳት):: 2. (ዘይ.) በሃይል ተቆጣ፥ ተናደደ:: 3. ፈነዳ፥ የፍንዳታ ድምፅ አሰማ::

**ብው ብሎ ሰከረ** በጣም ሰከረ፥ ጥንብዝ አለ::

**ብዙ "በዛ"** ስር ተመ.

**ብዙሃን** ዝ.ከ.

**ብዙውን** ዝ.ከ.

**ብዛት** ዝ.ከ.

**ብዝበዛ "በዘበዘ"** ስር ተመ.

**ብዝት "ባዘተ"**ስር ተመ.

**ብዥ**

**ብዥ አለ** ግ ግልፅ ሆኖ በትክክል አልታይ አለ::

**ብዥታ** ስ በግልፅ ወይም በትክክል ያለመታየት ሁኔታ::

**ብያኔ "በየነ"** ስር ተመ.

**ብይ** ስ ብርጭቆ ከሚሰራበት ንጥረ ነገር የተሰራ የተለያየ መልክ (ቀለም) ያለው ድቡልቡል የልጆች መጫወቻ::

**ብይን "በየነ"** ስር ተመ.

**ብይድ "በየደ"** ስር ተመ.

**ብድ "በዳ"** ስር ተመ.

**ብድራት "*በደረ"** ስር ተመ.

**ብድር** ዝ.ከ.

**ብድግ**

**ብድግ አለ** ግ ከተቀመጠበት ወይም ከተኛበት ተነሳ፥ ቆመ::

**ብድግ አደረገ** ስ አነሳ::

**ብገናም "በገነ"** ስር ተመ.

**ብገን** ዝ.ከ.

**ብጉር(ቡጉር)** ስ ብዙውን ጊዜ በጉርምስና እድሜ አካባቢ ባሉ ሰዎች ፊት ላይ የሚወጣ፥ ጥቃቅን እትራት ወይም እበጥ መሰል የቆዳ ህመም አይነት::

**ብጉንጅ** ስ ብዙውን ጊዜ ለስለስ ባለ የሰውነት ክፍል ላይ የሚወጣ እበጥ፥ መግልና ቁስል የሚያስከትል የህመም አይነት::

**ብጣሪ "*በጠረ"** ስር ተመ.

**ብጣሻም "በጠሰ"** ስር ተመ.

**ብጣሽ** ዝ.ከ.

**ብጤ "ቢጤ"** ን ተመ.

**ብጥ "በጣ"** ስር ተመ.

**ብጥሌ** ስ 1. እንጎቻ:: 2. መጠኑ አነስተኛ የሆነ እቃ (ለምሳሌ የቢራ ጠርሙስ)፤ ቡትሌም ይባላል::

**ብጥልጣይ "*በጠለጠለ"** ስር ተመ.

**ብጥር "በጠረ"** ስር ተመ.

**ብጥስ "በጠሰ"** ስር ተመ.

**ብጥስጣሽ** ዝ.ከ.

**ብጥስጥስ** ዝ.ከ.

**ብጥቅጣቂ "በጠቀ"**ስር **"ብጥቅጥቅ"**ን ተመ.

**ብጥቅጥቅ "በጠቀ"**ስር ተመ.

**ብጥብጥ "በጠበጠ"** ስር ተመ.

**ብጥብጥ** ዝ.ከ.

**ብጫቂ "በጨቀ"** ስር **"ቡጫቂ"** ን ተመ.

**ብጭቅጫቂ "በጨቀ"** ስር ተመ.

**ብጭቅጭቅ "በጨቀ"** ስር **"ብጭቅጫቂ"**ን

ተመ.

**ብጭብጭ** "*በጨበጨ" ስር "በጭባጫ" ን ተመ.

**ብፁእ** ቅ ክቡር፥ ምስጉን፥ ብሩክ፥ ፃድቅ።

**ብፅኣት** ስ ስለት፥ የስለት ስጦታ።

**ብፅእና** ስ መንፈሳዊ ክብር፥ ብፁእነት፥ ቅድስና።

**ብፌ** ስ ተጋባዥ የፈለገውን እያነሳ እንዲመገብ የተለያዩ የምግብ ኣይነቶች በተለያዩ እቃዎች ላይ እየተደረጉ ጠረጴዛ ላይ ተደርድረው የሚቀርቡበት የግብዣ ኣይነት።

**ቦ** የ "በ" ፊደል ሳብእ ዘር።

**ቦሃ** "ቡሃ" ን ተመ.

**ቦሃቃ** "ቡሃቃ"ን ተመ.

**ቦለለ**[1] ግ ቦነነ፥ ጨሰ (ኣቧራ፥ ጪስ፥...)።

**ቡል ኣለ(ቡልል ኣለ)** ግ በሃይል ቦነነ፥ ጨሰ።

**ቡል ቡል ኣለ (ቡልል ቡልል ኣለ)** ግ ቡን ቡን ኣለ፥ ተትጎለጎለ፥ ጨሰ።

**ተንቧለለ** ግ በሃይል ጨሰ፥ ጪሱ ወደላይ ተነሳ፥ ተትጎለጎለ።

**ቦለለ**[2] ግ ቦላሌ፥ ሰፊ ሆነ።

**ቦላሌ[ሱሪ]** ስ ከወገብ በታች እስከ *መጫሚያ* ኣካባቢ የሚደርስና ሰፊ የሆነ ሱሪ፤ የቁምጣ ሱሪ ተቃራኒ።

**ተንቧለለ** ግ 1. ሰፋ፥ ቦላሌ ሆነ። 2. ሰፊ ልብስ (ቀሚስ) ለብሶ በዙር ተሽከረከረ።

***ቦለቦለ**

**ቦለቦል(ቦልቧላ)** ቅ ተግባቢ፥ ተጫዋች፥ ቦረቦር።

**ተንቦለቦለ** ግ 1. በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ፈሳሽ)። 2. በብዛት ወጣ፥ ተትጎለጎለ (ጪስ)።

**ኣንቦለቦለ** ግ 1. ኣንዶለዶለ፥ በብዛት ኣፈሰሰ። 2. በሰፊው ኣወራ።

**ቦለደ** ግ 1. እንጨትና እንጨትን በማፋጨት፥ ድንጋይና ድንጋይን በማጋጨት እሳት እንዲፈጠር ኣደረገ፤ ኣስቴ ኣወጣ። 2. (ዘይ.) ፋኖ፥ በረሀኛ ሆነ፥ ሸፈተ።

**ቦለድ(ቦለዴ)** ቅ 1. ከጅሪው (ከወገኖቹ) ተለይቶና ለብቻው ተሰማርቶ የሚታይ (ዝንጀሮ)። 2. (ዘይ.) ቤቱን ለቆ፥ ከህዝብ ለየት ብሎ ጫካ ለጫካ የሚዞር (ኣጋሚዶ፤ ሽፍታ)።

**ቦሊንግ** ስ ትልቅነትና ክብደት ያለውን ኳስ ከጣውላ በተሰራ ወለል ላይ በማሽከርከር፥ በጠርሙስ ቅርፅ የተሰሩና በወለሉ ጫፍ የተደረደሩ ኣስር እንጨቶችን በመጣል የሚደረግ ጨዋታ።

**ቦላሌ** "ቦለለ[2]" ስር ተመ.

**ቦልቧላ** "*ቦለቦለ" ስር "ቦለቦል"ን ተመ.

**ቦምብ** ስ የተለያየ መጠንና ቅርፅ ያለው፥ ሲፈነዳ በሰውም ሆነ በንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ኣደገኛ የጦር መሳሪያ ኣይነት።

**በቦምብ ደበደበ** በተወሰነ ነገር ወይም ቦታ ላይ ቦምብ በተደጋጋሚ በመወርወር ወይም ከኣየር በመጣልና በማፈንዳት ኣደጋ ኣደረሰ።

**ቦምብ ጣለ** በቦምብ መታ፤ ቦምብ ወረወረ።

**ቦምብ ጣይ ኣይሮፕላን** ስ በተወሰነ ኢላማ ላይ ቦምብ ከኣየር ለመወርወር የሚያገለግል የጦር ኣይሮፕላን።

**ቦረሸ** ግ በቡርሽ ጠረገ፥ ኣፀዳ።

**ቡርሽ(ብሩሽ)** ስ ከፀጉር ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ ቀለም ለመቀቢያ፥ ልብስ ለመጥረጊያ፥ ጠርሙስ ለማጠቢያ፥...የሚያገለግል እቃ።

**ተቦረሸ** ግ በቡርሽ ፀዳ፥ ተጠረገ።

**ቦረቀ** ግ ፈነጨ፥ ፈነጠዘ፥ ዘለለ።

**ቡረቃ** ስ ፍንጠዛ፥ የደስታ ዝላይ።

***ቦረቀቀ**

**ቦርቃቃ(ቡርቅቅ)** ቅ በጣም የሰፋ፥ የተንቧለለ። *ቦርቃቃ ሱሪ።*

**ተንቦረቀቀ** ግ ኣለቅጥ ሰፋ፥ ተንቧለለ።

**ኣንቦረቀቀ** ግ ኣለቅጥ ሰፊ ኣደረገ፥ ኣንቧለለ።

**ቦረቦረ** ግ 1. በመሮ ወይም በመቆፈሪያ፥... በመፈልፈል ኣጎደጎደ( እንደ ግንድ፥ ኣለት፥ መሬት፥...ድፍን የነበረን ነገር)። 2. ሸረሸረ (ጎርፍ መሬትን)። 3. ሞረሞረ (የረሃብ ስሜት)። 4. ቀስ በቀስ ውስጥ ውስጡን እየጎዳ ኣደከመ።

**ቦረቦር** ቅ 1. ቀይነት ያለውና ፍርክስ፥ ፍርክስ የሚል (የኣፈር ኣይነት)። 2. (ዘይ.) ገራም፥ የዋህ የሆነ (ሰው)።

**ቦርቧራ** ቅ (ዘይ.) ገራም፥ የዋሀ፥ ተንኮል የሌለው (ሰው)።

**ተቦረቦረ** ግ 1. ጎደጎደ፥ ተሸረሸረ፥ ተበላ። 2. ሃይሉ ቀስ በቀስ፥ ውስጥ ውስጡን እየተቀነሰ ሄደ።

**ቦረቦጭ** ስ የተለያየ ቀለም ያለውና ብርጭቆ የሚመስል የድንጋይ ኣይነት።

**ቦረንትቻ** ስ ለኣድባር፥ ለቆሌ ተብሎ የሚታረድ ከብት፥ የሚጋገር ቂጣ፥...።

**ቦራ** ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ ፀጉር ያለው (ፈረስ፥ በሬ ወይም ላም)።

**ቦርማ(ቦሩማ)** ዝ.ከ.

**ቦርሳ** ስ ከቆዳ ወይም ከፕላስቲክ የሚሰራ፥ የተለያየ መጠን ያለው ለገንዘብ ወይም ለአንዳንድ እቃዎች መያዣ የሚያገለግል እቃ።

**ቦርቦርቲ** ስ የብረት ቆብ፥ የራስ ቁር።

**ቦርቧራ** "ቦረቦረ" ስር ተመ.

**ቦርዴ** ስ በጠላ መልክ በወፍራሙ የሚዘጋጅ፥ ጌሾ የማይገባበት የመጠጥ አይነት።

**ቦርጭ** ስ ወደውጪ ዘርጠጥ ብሎ የሚታይ የሆድ ውፍረት፤ ቀፈት።

**ቦርጭ አወጣ** ሆዱ ተንዘረጠጠ፥ ቀፈታም ሆነ።

**ቦርጫም** ቅ ሆደ ዘርጣጣ።

**ቦቀልት** "በቀለ" ስር "በቆልት"ን ተመ.

**ቦቀረ** ግ 1. መሃሉን ቀንብቦ የራስ ፀጉርን በመላጨት ሳዱላ ወይም ጋሜ አወጣ። 2. ማሳን አለፍ አለፍ እያለ በማረሻ ተለመ። 3. በአንድ ማሳ ላይ ከተዘራው እህል ውስጥ የደረሰ የደረሰውን ብቻ አለፍ አለፍ እያለ አጨደ።

**ቡቅራት** ስ 1. መሃል ራስን መላጨት። 2. መሃሉ ላይ የተላጨ የራስ ፀጉር።

**ቦቀሰ** ግ በቦቅስ መታ።

**ቦክስ(ቦቅስ)** ስ 1. ቡጢ፥ የተጨበጠ እጅ። 2. (ስፖ.) የራሱ የሆነ የአጨዋወት ህግና ስርአት ያለው፥ በተወሰነ የቦታ ክልል ወይም መድረክ ላይ ጓንት ባጠለቁ ሁለት ተጋጣሚዎች መካከል የሚካሄድ በቡጢ የመደባደብ ውድድር።

**ቦክሰኛ(ቦቅሰኛ)** ቅ 1. በቦቅስ የሚማታ፥ የሚደባደብ። 2. በቦቅስ ስፖርት ትምህርት የሰለጠነና በዚሁ ሙያ የሚተዳደር ስፖርተኛ።

***ቦቀቦቀ**

**ቦቅ** ስ ሳያቋርጥ ለረዥም ጊዜ የሚጥል ዝናም የሚያስከትለው ፍሳሽ።

**ቦቅቧቃ(ቦቀቦቅ)** ቅ ፈሪ፥ ቡከን።

**ተንቦቀቦቀ** ግ 1. በብዛት ወረደ፥ ፈሰሰ (ውሃ፥ ጎርፍ)። 2. በጣም ፈራ።

**አንቦቀቦቀ** ግ 1. በሃይል ዘነመ፥ ረዘም ላለ ሰአት ሃይለኛ ዝናም ጣለ። 2 አስፈራራ።

**እምቡቅቡቅ** ቅ ፈሪ፥ ቡከን።

**ቦቃ** ቅ ግንባሩ ላይ ነጭ ፀጉር ያለው (ከብት)።

**ቦቅማ** ዝ.ከ.

**ቦቅ** "*ቦቀቦቀ" ስር ተመ.

**ቦቅስ** "ቦቀሰ" ስር ተመ.

**ቦቅቧቃ** "ቦቀቦቀ" ስር ተመ.

**ቦቆሎ** "በቆሎ"ን ተመ.

**ቦተረፈ** ግ በሃይል ቦጨቀ፥ ዘነጠለ።

**ቡትርፍ** ቅ ቡጭቅ።

**ተቦተረፈ** ግ ተቦጨቀ፥ ተዘነጠለ።

**ቦታ** ስ 1. ስፍራ፤ የተወሰነ አካባቢ፥ ክልል። 2. ይዞታ (የመሬት)። 3. መገኛ፥ መኖሪያ፥ መቀመጫ። 4. መስማሪያ (የስራ)። 5. ደረጃ፥ ማእረግ(የስልጣን)።

**ቦታ ለቀቀ** 1. የነበረበትን ስፍራ ተወ። 2. ከነበረበት ስፍራ ተነሳ፥ ተወገደ።

**ቦታ ሰጠ** 1. አስቀመጠ። *ለእንግዶቹ ቦታ ሰጣቸው።* 2. ከቁም ነገር ቦታ አገባ። *ላንተ ልፍለፋ ማን ቦታ ይሰጠዋል።*

**ቦታ ያዘ** ተቀመጠ፥ ተደላደለ።

**ቦታ ቦታ አለው** ለሁሉም ነገር ጊዜ፥ ሁኔታ፥ ዘዴ፥ አጠቃቀም፥ አፈፃፀም አለው።

**ቦታ ቦታውን ያዘ** እንደየአግባቡ ተቀመጠ፥ ተደላደለ።

**ቦት** ስ ከቆዳ ወይም ከፕላስቲክ፥... የሚዘጋጅ እስከ ባት ድረስ የሚሸፍን ረዥም ጫማ።

**ቦነነ** ግ 1. ጨሰ፥ በነነ። *አቧራው ቦነነ።* 2. ላመ፥ ደቀቀ፥ አለቀ፥ በነነ። *ተዘውትሮ ከመለበሱ የተነሳ ሱሪው ከጉልበቱ ላይ ቦነነ።*

**ቡናኝ** "በነነ" ስር "ብናኝ"ን ተመ.

**አቦነነ** ግ 1. አጨሰ፥ አበነነ (ጪስን፥ አቧራን፥...)። 2. ጨረሰ፥ አበነነ(ልብስን)። 3. ጨረሰ፥ ፈፀመ(ስራን)። 4. በሃይል መታ፥ አዘረጠ። *በሽመል አቦነነው።*

**ቦና** ስ ዝናም፥ ልምላሜ የሌለበት ወቅት፤ ድርቅ።

**የቦና ጥጃ** ስ በድርቅ ምክንያት የተጎዳ ወይም የከሳ ጥጃ።

**ቦኖ** ስ በሆቴል ቤቶች፥ በሻይ ቤቶች፥... የሽያጭንና የግገርን ሁኔታ ለመከታተያ እንዲያገለግል ከፕላስቲክ፥ ከቆርቆሮ፥... የሚዘጋጅ የገንዘብ ምትክ።

**[የ]ቦኖ ውሃ** ስ በነፃም ሆነ በግገር የቧንቧ ውሃ የሚታደልበት ስፍራ፤ ቢርካም ይባላል።

**ቦከቦከ** ግ በሰበሰ። *ከእድሜው ብዛት የተነሳ የዛፉ ስር ቦከቦከ።*

**ቡክቡካ** ስ ጪሱ ጥሩ መአዛ ወይም ሽታ ያለው እንጨት፥ ስራስር።

**ቦካ** "ቦኬ"ን ተመ.

**ቦኻ** ግ 1. ኩፍ፥ ብድግ አለ፤ ለመጋገር ደረሰ (ሊጥ)። 2. ጨቀየ፥ ጭቃ ሆነ (መሬት)። 3. ለቤት ምርግ እንዲሆን ከጭድና ከውሃ ጋር የተረገጠ ወይም የታሸ ጭቃ ተብላላ፥ ሸተተ፤ ለምርግ ደረሰ። 4. በጣም ወፈረ፥ ሰባ። 5. ራደ፥ ፈራ። 6. ኮመጠጠ፥ ሆመጠጠ።

**ቡሃቃ(የቡሆ እቃ፥ ቦሃቃ)** ስ 1. ሊጥ ወይም ቡኮ የሚዘጋጅበትና የሚቀመጥበት እቃ። 2. (ስድብ) የፊቱን ላይ ንፅህና የማይጠብቅ፤

ትርክርክ::

**ቡሃቃ ለዩ** አንድነት እየኖሩ በጋራ እያዘጋጁ ይመገቡ የነበሩ፥ ለየብቻ እያዘጋጁ ለየብቻ መመገቢ ያዙ፥ ተለያዩ::

**ቡኮ(ቡሆ፥ቡኪ፥ቡኬት)** ስ ከእርሾ ጋር በውሃ የተለወሰ ዱቄት፤ ሊጥ::

**ማቡኪያ** ስ 1. ሊጥ የሚቦካበት እቃ (ዋዲያት፥ ገበቴ፥ ትልቅ ሳህን):: 2. ቡሃቃ::

**ቦኬ(ቦካ)** ስ ከከብት ሃሞት ውስጥ የሚገኝ እንደጠጠር ያለ ቢጫ እንክብል፤ ሳዙና::

**ቦክሰኛ** "ቦቀሰ" ስር ተመ.

**ቦክስ** ዝ.ከ.

**ቦዘ** ግ1. ፈዘዘ፥ ነሆለለ፥ ዘነጋ:: 2. መልኩ ተቀየረ፥ ገረጣ፥ ነበዘ::

**ቦዝ** ቅ ልበ ቢስ፥ ዝንጉ::

**ቦዝ አንቀፅ** ስ (ሰዋ.) እንደ "በልቼ"፥ "በልተን"፥ "በልተህ"፥ "በልቶ"፥.....ያለ፥ ብዙውን ጊዜ በማሰሪያ አንቀፅነት የማይገኝ አንቀፅ ወይም የግስ እርባታ ክፍል::

**ቦዘነ** ግ 1. ስራ ፈቶ ዋለ:: 2. ስራ ተወ፥ ቸል አለ:: 2. ስራ ፈተ፥ ቦዜ ሆነ::

**ቦዘና ሽሮ** ስ ስጋ ጣል ጣል የተደረገበት ወይም ስጋ በመጠኑ ያለበት የሽሮ ወጥ፤ ቦዘና ወጥ እየተባለም ይጠራል::

**ቦዜ** ስ ስራ የሌለው፤ ስራ ፈት፥ አውደልዳይ::

**ቦዘን** ስ ስራ መፍታት::

**ቦዘንተኛ** ቅ 1. ስራ ፈት:: 2. ቸልተኛ፥ ዝንጉ::

**አቦዘነ** ግ አሰነፈ፥ ስራ አስፈታ::

***ቦዠቦዠ**

**ተንቦዠቦዠ** ግ 1. በመጠጥ ሞቅታ ሁለንተናው ተደሰተ፥ ተፍነከነከ:: 2. ተንቀዠቀዠ፥ ግራ ተጋባ:: 3.ፈራ፥ ተርበደበደ::

**አንቦዠቦዠ** ግ 1. በመጠጥ ሞቅታ ሰውነቱን አስደሰተ፥ አፍነከነከ:: 2. አንቀዠቀዠ፥ ግራ አጋባ:: 3. አስፈራራ፥ አርበደበደ::

**ቦዬ**[1] ስ ተቀቅሉ የሚበላ እንደ ስኳር ድንች ያለ ስር ያለው ሃረግማ የሆነ የተክል አይነት::

**ቦዬ**[2] ስ አሳማ::

**ቦይ**[1] ስ ለውሃ ወይም ለፍሳሽ መሄጃ እንዲያገለግል ጎድጎድ እንዲል ተደርጎ የተቆፈረ የፍሳሽ መስመር::

**ቦይ**[2] ስ የሻይ ወይም የሆቴል ቤት ወንድ አስተናጋጅ::

**ቦይና** ስ ስኳር ድንች የሚመስል፥ ሻካራ የሆነ ስር ያለው፥ ቅጠሉ ረዘም ብሎ ሰፋ ሰፋ የሚል፥ ስሩ ተቀቅሉ የሚበላ የተክል አይነት::

**ቦደሰ** ግ በሰፊው ገመሰ፥ ጎመደ፥ በጨቀ (የአንድን ነገር አካል)::

**ቡድስ** ቅ በሰፊው የተገመሰ፥ የተቦጨቀ::

**ተቦደሰ** ግ በሰፊው ተገመሰ፥ ተጎመደ፥ ተቦጨቀ::

**ቦደነ**[1] ግ 1. ቀኝ እጁን ወደውጪ አድርጎ፥ ጋቢውን ወይም ኩታውን በቀኝ ብብቱ ስር በማሳለፍ በግራ ትከሻው ላይ አጣፋ፥ አደገደገ:: 2. ከሚሰነዘርበት የዱላ ወይም የድንጋይ ጥቃት ለመከላከል ወይም ለምክቶሽ ይረዳው ዘንድ ልብሱን እግራ እጁ ላይ ጠመጠመ፥ ደገለለ:: 3.ጋረደ፥ መከተ::

***ቦደነ**[2] ወገነ፥ ቡድን አበጀ፥ ያዘ::

**ቡድን** ስ 1.አንድን የተወሰነ ተግባር በቅንጅት የሚያከናውኑ ሰዎች የሚገኙበት አካል:: 2. የተወሰነ ወገን፥ ክፍል፥ ምድብ::

**የቡድን መሪ** ስ የቡድን አለቃ፥ ሃላፊ፥ አስተባባሪ::

**የቡድን አባት** ስ በተለይ እንደገና ባሉ የባህል ጨዋታዎች ላይ እንደ አለቃ ሆኖ በመሰየም ለራሱ ቡድን የሚሆኑትን ተጫዋቾች የሚመርጥና አብሮ የሚጫወት ሰው::

**ተቧደነ** ግ 1.ከቡድን አባቶች ፊት ቀርቦ ለመመረጥ አንዱ ከሌላው ጋር ተጣመረ፥ ተጓደነ፥ ተቀናጀ::2. ቦደነ::

**አቧደነ** ግ አንዱን ከሌላው ጋር አጣመረ፥ አጓደነ፥ አቀናጀ::

**ቦዳ መሬት** ስ የሰባ መሬት::

***ቦገቦገ**

**ቦግታ** ስ ብልጭታ፥ ተግታ (የመብረቅ፥ የብርሃን)::

**ቦግ አለ** ግ 1. ብልጭ፥ ተግ አለ፤ በራ:: 2. ድንገት በሃይል ነደደ፥ ተቀጣጠለ (እሳት):: 3. ፏ ብሎ፥ ደምቆ ወይም ጎልቶ ታየ::

**ቦግ ቦግ አለ** ግ ብልጭ ብልጭ፥ ተግ ተግ አለ::

**ተንቦገቦገ** ግ 1. ተብለጨለጨ:: 2. በሃይል ነደደ፥ ተንበለበለ::

**አንቦገቦገ** ግ 1. አብለጨለጨ፥ አንተገተገ:: 2. አንቀለቀለ፥ አንበለበለ::

***ቦጠለቀ**

**ቡጥልቅ አለ** ግ ተቦጠለቀ::

**ተቦጠለቀ** ግ ድንገት በሃይል ተስፈንጥሮ ወጣ (ትውከት፥ አክታ፥...)::

**ቦጠቦጠ** ግ 1. ቦረቦረ፥ የውስጥ የውስጡን ወይም ልብ ልቡን በላ (ለምሳሌ የዳቦን):: 2. በጥርሱ እየፈለቀቀ በላ (የባቄላ፥ የአተር

እሸትን)::3. ጎጠጎጠ፥ ኮረኮረ (ብብትን):: 4. በቡጢ ውስጥ ውስጡን መታ፥ ደበደበ:: 5. (ዘይ.) ውስጥ ውስጡን በላ፥ በዘበዘ፥ አራቆተ (ገንዘብን)::

**ቡጢ** ስ የተጨበጠ እጅ፥ ጡጫ::

**ቡጥ** ስ 1. የዳቦ ውስጠኛ ክፍል፥ ልብ:: 2. የእንጨት መሃለኛውና ለስላሳው ክፍል፥ ልቡ:: 3. ጉጥ:: 4. የባቄላና የአተር እሸት ፍሬ ልባስ::

***ቦጨረቀ**

**ቦጭራቃ** ቅ 1.ቦጭቧጫ፥ ውሃ የበዛበት (ወጥ፥ ጠላ፥...):: 2. (ዘይ.) ቁምነገር የሌለው፥ ፍሬቢስ::

**ተንቦጫረቀ (ተምቦጫረቀ)** ግ 1. እጁን ወይም እግሩን ውሃ ውስጥ ከቶ ተንቧቸ፥ ተፈራገጠ ወይም በሙሉ አካሉ ውሃ ውስጥ ገብቶ ተወራጨ፥ ተንደፋደፈ:: 2. ውል፥ መልክ ሳይዝ ቀረ፥ ተበላሸ::

**አንቦጫረቀ(አምቦጫረቀ)** ግ1. አንቧቸ፥ በጠበጠ (ውሃን):: 2 መልክ፥ ቅጥ አሳጣ፥ አበላሸ::

**ቦጨቀ** ግ 1. ቦተረፈ፥ በደሰ፥ ቀደደ፥ ነጨ፥ ዘነጠለ:: 2. ጥጥን አፍታታ፥ አባዘተ::3. (ዘይ.) አማ፥ በሃሜት የሰው ስም አነሳ::

**ቡጫቂ** ቅ ከዋናው አካሉ ላይ በመቦትረፍ ወይም በመቀደድ ተለይቶ የወጣ (ቁራጭ፥ ዝንጣይ፥ ቅዳጅ፥...)::

**ቡጭቅ** ቅ 1.ቡጫቂ:: ስ 2. የተባዘተ ጥጥ፥ ባዘቶ::

**ቡጭቅጫቂ** ቅ የተበጣጠሰ፥ የተቀዳደደ::

**ተቦጨቀ** ግ ተቦተረፈ፥ ተቀደደ::

**ተቦጫጨቀ** ግ ተበጣጠሰ፥ ተቀዳደደ::

**ተቧጨቀ** ግ 1. እርስ በርስ ተናከሰ፥ ተባላ:: 2. ተቀራመተ፥ ተሻማ፥ ተናጠቀ::

***ቦጨቦጨ**

**ቦጭቧጫ** ቅ 1. ውሃ የበዛበት፥ ጣእም የሌለው፥ መናኛ የሆነ (ጠላ፥ ወዘተ ...):: 2. በቅቧቃ፥ ቡከን፥ ፈሪ:: 3. (ዘይ.) ቁምነገር የሌለው፥ ፍሬቢስ የሆነ ነገር::

**ቡጭ ቡጭ አለ** ግ 1.ጎደል ያለ ፈሳሽ ነገር (ለምሳሌ ውሃ) የያዘ እቃ ሲነቀነቅ በውስጡ ያለው ፈሳሽ የሚያሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ:: 2. (ዘይ.) ከሃዘን፥ ከርሀራሄ የተነሳ ተንሰፈሰፈ (ሆድ)::

**ተንቦጫቦጨ(ተምቦጫቦጨ)** ግ 1. ቦጭ ቦጭ የሚል ድምፅ አሰማ::2. ፍርሃት ፍርሃት አለው:: *ከዘመድ ሲለይ ሆዱ ተንቦጫቦጨ::*

**አንቦጫቦጨ(አምቦጫቦጨ)** ግ 1.ወዘወዘ፥ ናጠ፥ ቦጭ ቦጭ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ (ጎደሎ ፈሳሽ የያዘን እቃ):: 2. (ዘይ.) አበለሻሸ፥ ጣእም አሳጣ::

**እንቡጭቡጭ** ቅ 1. ጣእመቢስ፥ መናኛ፥ የማይረባ:: 2. ቡከን፥ ፈሪ::

**ቦጭራቃ** "*ቦጨረቀ" ስር ተመ.

**ቦጭቧጫ** "*ቦጨቦጨ" ስር ተመ.

**ቦፍ**

**ቦፌ** ቅ ውፍረት እንጂ ጥንካሬ የሌለው፥ ውስጠ ልል::

**ቦፍ አለ** ግ ዘጭ አለ፥ በአወዳደቁ ቦፍ የሚል አይነት ድምፅ አሰማ፥ ወደቀ::

**እምቦፍ(እንቦፍ) አለ** ዝ.ከ.

**ቧ** የ "በ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::

**ቧሄ ሃረግ** ስ ግንዱ ነጭ የሆነ ሃረግ፣ ሃረግሬሳ፥ እፀሳቢቅ እየተባለም ይጠራል::

**ቧሄ ቁራ** ስ ራሱ ላይ ነጭ ምልክት ያለበት ቁራ::

***ቧለተ**

**ቧልት(ቧልታ)** ስ 1. ፌዝ፥ ቀልድ፥ ዋዛ ፈዛዛ:: 2. ተረብ::

**ቧልተኛ** ቅ 1.ፌዘኛ፥ ቀልደኛ:: 2. ተረበኛ::

**አቧለተ** ግ 1. አፌዘ፥ ቀለደ:: 2. ተረበ::

**ቧምቧ** "ቧንቧ" ን ተመ.

***ቧቧ**

**ተንቧቧ(ተምቧቧ)** ግ በብዛት ፈሰሰ፥ ተንዶለዶለ(ፈሳሽ)::

**አንቧቧ (አምቧቧ)** ግ በብዛት አፈሰሰ፥ አንዶለዶለ(ፈሳሽን)::

***ቧተረ**

**አንቧተረ(አምቧተረ)** ግ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት ተጋበዘ፥ የተነሳሁበትን አደርጋለሁ፥ አትገላግሉኝ ብሎ ወዲያ ወዲህ ዘለለ፤ ተቁነጠነጠ፥ ጉራ ነዛ፥ ሳያደርገው ተግደረደረ::

**አንቧታሪ (አምቧታሪ)** ቅ ጉረኛ፥ የማያደርገውን እንደሚያደርግ አስመሳይ የሚታይ፥ ለመደባደብ የሚቃጣ፥ ለማስፈራራት የሚሞክር::

***ቧቸ**

**ተንቧቸ(ተምቧቸ)** ግ 1. በውሃ ተንቦጫረቀ:: 2. ተጫወተ፥ ተንጫጫ፥ ተንቻቻ:: 3. እንደልቡ፥ እንደፈለገው ሆነ:: *ያባትህን ቤት ማን ይከለክልሃል ግባና ተንቧቸበት::*

**አንቧቸ(አምቧቸ)** ግ 1. ውሃ አንቦጫረቀ:: 2. አጫወተ፥ አንጫጫ፥ አንቻቻ::

**ቧንቧ(ቧምቧ)** ስ ውሃ ወይም ፈሳሽ ነገር በውስጡ ሊሄድበት የሚችል፥ ክብነት ያለው

ውስጠ ክፍት ብረት ወይም ፕላስቲክ ወይም ሌላ ነገር።

**ቧገተ(ባጎተ)** ግ 1. በየውድማው እየዞረ እህል ተመፀወተ። 2. ለመነ፥ ቀፈፈ።

**ቧገታ(ባጎታ)** ስ 1. በየውድማው እየሄዱ እህል የመመፅወት፥ የመቀበል ድርጊት። 2. ልመና፥ ቀፈፋ።

**ቧጋች** ስ 1. የውድማ ላይ ተመፅዋች። 2. ለማኝ።

**አቧገተ** ግ 1.ውድማ ላይ ለተገኙት ተመፅዋቾች ከምርቱ እያፈሰ ሰጠ፥ መፀወተ። 2. አለመነ፥ ቸረ፥ ሰጠ።

**አቧጋች** ቅ 1.ውድማው ላይ ከተንጣለለው ምርት ወይም ከተቆለለው እህል ለተመፅዋቾች እያፈሰ የሚሰጥ። 2. አለማኝ፥ የሚቸር።

**ቧጠጠ** ግ 1. በጥፍር ሟጨረ፥ ቧጨረ፥ ጫረ። 2. ፍግፍግ አድርጎ ጠረገ፥ ፈቅፍቆ አነሳ(እንደ ጭቃ፥ አዛባ፥ ቅቤ፥...ያለን ነገር ከሚገኝበት ቦታ ላይ)። 3. ጠረገ(ጉረሮን)። 4. በእጁ ጣቶች ወግቶ ያዘ፥ አጥብቆ ጨመደደ። *ዳገቱን የወጣው በእጁ እየቧጠጠ ነው።*

**ቡጥጫ** ስ ሙጭሪያ፥ በጥፍር መቧጠጥ።

**ቧጨረ** ግ ሟጨረ፥ ጫረ።

**ቡጭር** ቅ የተሟጨረ፥ የተጫረ።

**ቡጭርጭር** ቅ 1. አካሉ በጥፍር ወይም በሌላ ነገር የተሞጫጨረ፥ የተቧጠጠ። 2. ትክክለኛውን ቅርፅ ያልያዘ፥ የተወላገደ (ፅሁፍ)።

**ተቧጨረ** ግ ተሟጨረ፥ ተጫረ።

# ቨ

**ቨ** በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ"በ" ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ቩ** የ"ቨ" ፊደል ካእብ ዘር::

**ቪ** የ"ቨ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ቪላ [ቤት]** ስ ፎቅ ያልሆነና የተለያዩ ክፍሎች ያሉት፥ ለብቻው ራሱን ችሎ በዘመናዊ መልክ የተሰራ መኖሪያ ቤት::

**ቪታሚን(ቫይታሚን)** ስ ለሰውም ሆነ ለእንስሳት ጤንነት አስፈላጊ የሆነ፥ ከተለያዩ ምግቦች ሊገኝ የሚችል ንጥረ ነገር::

**ቪኖ(ቢኖ)** ስ ከወይን የሚዘጋጅ የአልኮል መጠጥ፤ ወይን ጠጅ::

**ቪዛ** ስ አንድ ሰው ወደ አንድ ሌላ አገር እንዲገባ፥ እንዲተላለፍ ወይም ከአገር ውስጥ እንዲወጣ መፈቀዱን ለመግለፅ በሚመለከተው አገር ባለስልጣን በተጓዡ ፓስፖርት ላይ የሚደረግ ማህተም::

**ቪዛ ተሰጠው/አገኘ/ተመታለት** ወደ አንድ አገር እንዲገባ ወይም ከአገር እንዲወጣ ፈቃድ አገኘ::

**ቪዛ ታደሰለት** በአንድ ሌላ አገር ውስጥ እንዲቆይ የተፈቀደለት ጊዜ ወይም ከአገር ውስጥ እንዲወጣ የተሰጠው የጊዜ ገደብ ተራዘመለት::

**ቪዮላ** ስ ከቫዮሊን ከፍ የሚል የክር ሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)::

**ቪዲዮ** ስ በቪዲዮ ክር (ጥብጣብ) ላይ የተቀረፀን ምስልና ድምፅ በቴሌቪዥን አማካይነት ለማሳየትና ለማሰማት የሚያስችል መሳሪያ::

**የቪዲዮ መቅረጫ** ስ በቪዲዮ ክር ላይ ምስልና ድምፅን ለመቅረፅ የሚያስችል መሳሪያ::

**የቪዲዮ ክር** ስ በቴሌቪዥን ሊተላለፍ የሚችል ምስልና ድምፅ የሚቀረፅበት ማግኔታዊ ጥበጣብ::

**ቫ** የ"ቨ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ቫርኒሽ** ስ በአብዛኛው እንደ ጠረጴዛ፥ ሳጥን፥ መደርደሪያ በመሳሰሉ ወይም ሌሎች የእንጨት ስራዎች ላይ ከላይ በስሱ እንዲያለብስ ተደርጎ የሚቀባና መልክ የሚሰጥ፥ እንደ ቀለም ያለ ፈሳሽ ነገር::

**ቫክዩም** ስ ከማንኛውም አይነት ነገር ወይም ጋዝ ነፃ የሆነ ባዶ ቦታ ወይም በአንድ ሳጥን ወይም በሌላ መያዣ ነገር ውስጥ የሚገኝ አየር በሙሉ ወይም በከፊል ከውስጡ የወጣለት ባዶ ቦታ::

**ቫውቸር** ስ ለአንድ ነገር ክፍያ መፈፀሙን የሚያሳይ ሰነድ፥ ደረሰኝ::

**ቫዝሊን** ስ ለሰውነት ቆዳ ማለስለሻና ማውዣ የሚያገለግል የቅባት አይነት::

**ቫይረስ** ስ ከባክቴሪያ የሚያንስ፥ ተላላፊ በሽታን የሚያስከትል ህዋስ::

**ቫይታሚን** "ቪታሚን"ን ተመ.

**ቫዮሊን** ስ አገጭ ስርና ትከሻ ላይ አድርገው ደጋን በመሰለ ማንዘሪያ እንደመሰንቆ እየገዘገዙ የሚጫወቱበት የክር ሙዚቃ መሳሪያ (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ)::

**ቬ** የ"ቨ" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ቬሎ** ስ ሴት ሙሽራ የጋብቻ ስነስርአቷን በምትፈፅምበት እለት የምትለብሰው በገበር ተደርጎ በልዩ ሁኔታ የሚሰፋ ስስ የሆነ የሰርግ ልብስ::



ቬሎ

**ቬቶ** ስ ድምፅን በድምፅ ወይም ውሳኔን በውሳኔ የመሻር ስልጣን::

**ቬነስ(ቬኑስ)** ስ በሜርኩሪና በመሬት መካከል የምትገኝ ከፀሀይ ሁለተኛ ተራ ላይ ያለች ፕላኔት:: በተጨማሪ "ፕላኔት"ን ተመ.

**ቭ** የ"ቨ" ፊደል ሳድስ ዘር::

**ቮ** የ"ቨ" ፊደል ሳብእ ዘር::

**ቮልት** ስ የኤሌክትሪክ ሃይል መጠን መለኪያ አሃድ::

**ቯ** የ"ቨ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::

**ቯልስ** ስ በለስላሳ ሙዚቃ እየታጀቡ ጥንድ በመሆን በዝግታ የሚደንሱት ዳንስ::

# ተ

**ተ** በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ "ሸ" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ተ** (ሰዋ.) 1. በአድራጊ አምድ ግስ መነሻ ላይ እየተቀጠለ ተደራጊ አምድን የሚመሰርት ምእላድ:: *ገደለ→ተገደለ*: 2.ድርጊት ተቀባይነትን የሚያሳይ ምእላድ:: *ተሾመ*: 3. በአደራራጊ አምድ ግሶች መነሻ ላይ እየተቀጠለ ሁለት ነገሮች እርስ በርስ አንድ ነገር መደራረጋቸውን ለመግለፅ የሚያገለግል፥ ተደራራጊ አምድን ለመመስረት የሚያስችል ምእላድ:: *ፈላለገ→ተፈላለገ*: 4. በእስር አምድ ላይ እየተቀጠለ ተዳራጊ አምድን የሚመሰርት ምእላድ:: *ጋደለ→ተጋደለ*: 5. በአንድ አይነት ሁኔታ ውስጥ መገኘትን ለማመልከት የሚያገለግል ምእላድ:: *ተቸገረ / ተደሰተ::*

**ተሃዋስያን** (ነ.ቁ.**ተሃዋሲ**) ስ ጥቃቅን የሆኑ ተንቀሳቃሽ ነፍሳት በሙሉ::

**ተለለ**[1] ግ ፈሰሰ፥ ኮለል ብሎ ወረደ::

**ተለል አለ** ግ ኮለል ብሎ ወረደ:: *እንባው በጉንጮቹ ላይ ተለል ብሎ ወረደ::*

**ተለለ**[2] ግ ጠራ፥ ጠለለ፥ ጥሩ ሆነ (ፈሳሽ)::

**አተለለ** ግ አጠለለ፥ አጠራ::

**ተለሳ** ስ መስመር፥ መደዳ፥ ረድፍ::

**ተለመ** ግ 1. አንድ ፈር አወጣ፥ ቀደደ፥ ሰነጠቀ፥ ገመሰ (በማረሻ):: 2. አቀደ፥ ወጠነ፥ ጀመረ:: 3. ሰንበር እስኪያወጣ በጅራፍ፥ በአርጩሜ ገረፈ::

**ትልም** ስ 1. አንድ ጊዜ የተሄደበት የእርሻ ፈር፥ ጅምር:: 2. እቅድ፥ ጅምር፥ ውጥን:: 3. በግርፊያ ምክንያት ሰውነት ላይ የወጣ ሰንበር፥ ምልክት::

**ተተለመ** ግ 1. ትልም ወጣ:: 2. ተጀመረ፥ ተወጠነ::

**ተለምዶ "ለመደ"**ስር ተመ.

**ተለቀ** ግ 1. አደገ፥ ትልቅ ሆነ:: 2. ከሚፈለገው መጠን በላይ ሆነ::

**ታላቅ** ቅ 1. (ብ.ቁ.**ታላላቅ**) ከፍ ያለ (በእድሜ፥ በማእረግ):: 2. የስጋ ብልት ስም::

**ትልቅ**(ብ.ቁ. **ትልልቅ፥ትላልቅ**) ቅ 1. ታላቅ፤ በቁመት፥ በርዝመት፥ በመጠን፥በእድሜ፥ በማእረግ ከፍ ያለ:: 2. ጥሩ፥ ከፍተኛ የሆነ:: *ትልቅ ስራ ሰርቷል::*

**አተለቀ** ግ ትልቅ አደረገ ፥ አገዘፈ::

**ተለተለ** ግ 1. ተረተረ፥ ፈታ፥ መዘዘ፥ ለየ (ማግን ከድር):: 2. ቀደደ፥ ሰነጠቀ:: 3. በጣ፥ሸነተፈ (ሰውነትን በስለት):: 4. ገረፈ፥ አሰነበረ፥ አደማ (ሰውነትን በጅራፍ፥ በአለንጋ፥...)::

**ትልታይ** ስ 1. ከድር የወጣ ማግ ወይም ከማግ የተለየ ድር:: 2. ቀጠን ረዘም ያለ የጨርቅ ቅዳጅ::

**ትልትል** ቅ 1. ትርትር(ጨርቅ):: 2. ስንጥቅ፥ ብጥ፥ ስንትር (ሰውነት)::

**ትልትላት** ስ ከሰውነት ላይ በስለት የተደረገ ትፍትፋት፥ ስንጥቃት፥ ስንትራት::

**ተለዘ** ግ ደከመ፥ አቅም አጣ::

**ትልዝ ትልዝ አለ** ግ ደከመ፥ ጭልጭል አለ::

**ተላ** ግ በመበስበስ ወይም በመበላሸት ትል አወጣ፥ ፈጠረ::

**ትል** ስ አካሉ በለስላሳ ቆዳ የተሸፈነና በበሰበሱ ነገሮች ላይ፥ በውሃና በአፈር ውስጥ የሚገኝ፥ በደረት እየተሳበ የሚሄድ፥ መተጣጠፍና መጠቅለል የሚችል አነስተኛ ነፍሳት::

**ትላበራ(ትልአበራ)** ስ በጨለማ ውስጥ ስትሄድ ብልጭ ድርግም የሚል ብርሃን የምታሳይ ትል::

**ትላም** ቅ 1. ትል ያለበት ወይም የበዛበት:: 2. (ነውር፥ ስድብ) የበሰበሰ፥ ቆሻሻ::

**አተላ** ግ 1. ትል አወጣ:: 2. እንዲተላ አደረገ::

**ተላላ "*ታለለ"** ስር ተመ.

**ተልባ** ስ 1. ፍሬው ቅባትነት ያለው የሰብል አይነት:: 2. ከተልባ ፍሬ በዱቄት መልክ ተዘጋጅቶ በዘይት ፈንታ ወጥ ውስጥ የሚገባ ማጣፈጫ:: 3. (ዘይ.) በቃሉ የማይረጋ፥ የማይታመን፥ ሸርታታ፤ የ"ተልባ ስፍር"ም ይባላል::

**ተልባ ማሻ** ስ ተልባ የሚታሸበት ገበቴ::

**[የ] ተልባ ድርጥ** ስ በውሃ የታሸ የተልባ ልጥልጥ::

**ተልብማ** ቅ መልኩ ተልባ የሚመስል::

**ተልእኮ** ስ አንድን ነገር ለማከናወንና ከግብ ለማድረስ የያዙት አላማ፤ የሚቀበሉት ሃላፊነት ወይም ግዳጅ:: *ለአገርንና ወገንን ማገልገል የዜጎች ሁሉ ተልእኮ ሊሆን ይገባል::*

**የተልእኮ ትምህርት** ስ በተወሰነ የትምህርት ዘርፍ ላይ የተዘጋጁ ፅሁፎችን ከትምህርት ሰጭው ክፍል ጋር በመላላክ የሚካሄድ ትምህርት፤ የመላላክ ትምህርት::

**ተልካሻ(ተልካሳ)** ቅ 1.ደካማ፥ አቅመቢስ:: 2. ኀታታ፥ ሰነፍ፥ ስራ ጠብ የማይልለት:: 3.

መናኛ፥ ተራ፥ የማይረባ።

**ተመመ** ግ 1. እም... የሚል ድምፅ አሰማ (የውሃ አወራረድ፥ የብዙ ሰው ንግግር፥ የንብ ጉዞ፥...)። 2. ብዙ ሆኖ ተጓዘ። 3. ድምፅ አሰማ፥ ጮሀ (ከበሮ፥ አታሞ)።

**ተመሰጠ** "**መሰጠ**"ስር ተመ.

**ተመተመ** ግ 1. መታ፥ ለተመ፥ ገጨ። 2. አስተካከለ፥ ደመደመ። 3. እንጀራ ወይም ዳቦን በማባያው ጠቀሰ፥ አረመደ። 4. በማባበል በእጁ ቸብ ቸብ፥ ነካ ነካ አደረገ (ህፃንን፥ ፈረስን፡...)።

**ትምትም** ስ በልጥፍና በልስን መካከል ያለ የቤት ምርግ ስራ አይነት።

**ተመነ** ግ ገመተ፥ ወሰነ(ዋጋን)።

**ተመን** ስ ዋጋ የዋጋ ግምት።

**ተመን አወጣ** የዋጋ ዝርዝር፥ ግምት አወጣ፤ ዋጋ መደበ።

**ተማኝ** ስ ዋጋ መዳቢ።

**ተመከሮ** "**መከረ**" ስር ተመ.

**ተሙን(ትሙን)** ስ የብር አንድ ስምንተኛ የነበረ የጥንት ዘመን ገንዘብ።

**ተማሪ** "***መሃረ**" ስር ተመ.

**ተማኝ** "**ተመነ**" ስር ተመ.

**ተምር(ቴምር)** ስ በጣም ሞቃት የሆነ የአየር ጠባይ ባለው አካባቢ የሚበቅል፥ ዘንባባ የሚመስል ረዣዥም ቅጠሎች ያሉትና ሲበስል ቡና አይነት መልክ የሚኖረው፥ ውስጡ ቀጭንና ሞላላ የሆነ ጠንካራ የዘር ፍሬ ያለው ጣፋጭ ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ተምር ይባላል።

**ተምሳሌት** "**መሰለ**" ስር ተመ.

**ተምች** ስ የእህል ቡቃያን ወይም ሳርን በልቶ የሚያጠፋ የትል አይነት።

**ተሞከሮ** "**ሞከረ**" ስር ተመ.

**ተረር**[1] ስ ፍሬው የሚበላ አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

**ተረር**[2]

**ተረር አለ** ግ ስንጥቅ አለ፥ ተቀደደ፥ ተተረተረ።

**ተረር ብሎ ሄደ** በአንድ መስመር ተከታትሎ ሄደ።

**ተረር አደረገ** ግ ስንጥቅ፥ ክፍል አደረገ።

**ተረበ** ግ 1. ቀለደ፥ አፌዘ፥ አላገጠ፥ አሾፈ። 2. ነደፈ፥ ጠቅ አደረገ፥ ወጋ(በነገር)።

**ተረብ** ስ ቀልድ፥ ፌዝ፥ ሽሙጥ።

**ተረበኛ** ቅ ቀልደኛ፥ ፌዘኛ፥ ጨዋታ አዋቂ።

**ተራቢ** ቅ አሽሟጣጭ፥ ፎታች።

**ትረባ** ስ ማሽሟጠጥ፥ ፉተታ።

**ተረተ** ግ 1. በእውነት ያልተፈፀመን ነገር ወይም የፈጠራ ታሪክን፥ በእውን እንደተደረገ አድርጎ ተናገረ፥ አወራ፥ ተረከ። 2. ምሳሌያዊ ንግግርን በንግግሩ ውስጥ ተጠቀመ።

**መተረቻ** ስ መዘባበቻ፥ መቀለጃ ወይም ለመቀለጃ በምሳሌነት የሚጠቀስ፥ የሚቀርብ ድርጊት።

**ተረት** ስ 1. እውነት ለመሆኑ ማስረጃ የሌለው ወይም እንደተደረገ ሆኖ የሚነገር በፈጠራ የተቀነባበረ ታሪክ። 2. ምሳሌያዊ አነጋገር፤ አባባል።

**ተረት ተረት** በተለይ ረዥም ተረት የሚያወራ ሰው ለተረቱ እንደ መግቢያ ወይም እንደመነሻ አድርጎ የአድማጮቹን ትኩረት የሚጠይቅበት ቃል (አድማጩ "የላምበረት" ወይም "የመሰረት" በማለት ተረቱን ለማዳመጥ መዘጋጀቱን ይገልፃል)።

**ተረትና ምሳሌ** ምሳሌያዊ አነጋገር።

**የተረት አባት** ስ ልጆችን ሰብስቦ ተረት የሚያወራ ተረት አዋቂ ሽማግሌ።

**ተረተኛ** ቅ 1. ተረት አዋቂ፥ ባለተረት። 2. በሆነ ባልሆነው ተረት ማቅረብ የሚወድ።

**ተራች** ስ ተረት ተናጋሪ።

**ተተረተ** ግ በተረት መልክ ተነገረ።

**ተረተረ** ግ 1.ፈታ፥ ለያየ፥ አላቀቀ (የተሰፋን፥ የተገመደን፥ የተቋጠረን ነገር)። 2. ቀደደ፥ ሰነጠቀ። 3. ፈነከተ፥ ከፈለ፥ ገመሰ። *ሳናቱን በዱላ ተረተረው*። 4. አረሰ፥ ገመሰ። 5. ውሸት ተናገረ፥ አወራ።

**ትርትር** ቅ ስንጥቅ።

**ትርታሮ** ስ ገመሰ፥ ገመስ የሚያደርጉት የአስተራረስ አይነት፤ ጭፍለቃ፤ ገመሳ።

**ተተረተረ** ግ 1. እንደገና ተፈታ፥ ተለያየ፥ ተላቀቀ (የተገመደ፥ የተሰፋ ነገር)። 2. ተቀደደ፥ ተሰነጠቀ። 3. ተፈነከተ፥ ተከፈለ፥ ተገመሰ። 4.ታረሰ፥ ተገመሰ። 5.(ዘይ.) ዋሸ።

***ተረተረ**

**ተረተር** ስ የተራራ፥ የኮረብታ፥ የጉብታ ተዳፋት።

**አተረተረ** ግ በረድፍ፥ በተራ ተሰለፈ፥ ተሰደረ።

**ተረተኛ** "**ተረተ**" ስር ተመ.

**ተረት** ዝ.ከ.

**ተረኛ** "**ተራ**" ስር ተመ.

**ተረከ** ግ ስላለፈ ነገር ዘርዝሮ ተናገረ፥ አወራ፥ አወጋ፥ አተተ።

**ተራኪ** ስ ታሪክ ተናጋሪ፤ ፀሃፊ፤ አንባቢ።

**ታሪክ** ስ 1. በጊዜ ቅደም ተከተል የሚሄድ፥ ስላለፈ የህዝብ፥ የመንግስታት፥ የመሪዎች ድርጊትና ሁኔታ የሚዘረዝር፥ የሚያጠናና አጠቃላይ መግለጫ የሚሰጥ የህብረተሰብ ሳይንስ። 2. የአንድን ነገር ሁኔታና የእድገት ሂደት የሚያሳይ ዝርዝር መግለጫ። *የአማርኛ ስነፅሁፍ ታሪክ።* 3. በልቦለድ ፈጠራ ላይ የተመሰረተ የአንድ ወይም የብዙ ሰዎች የተያያዘና የተጠላለፈ ክንዋኔን፥ የኑሮ ገጠመኝ ሂደትን የሚገልፅ ፅሁፍ።

**ታሪክ ነው** ግሩም፥ አስደናቂ ነው።

**ባለታሪክ** ስ 1. የአንድ አኩሪ ስራ ክንዋኔ ባለቤት የሆነ፥ ጥሩ ወይም ትልቅ ስራ የሰራ። 2.ገፀ ባህርይ።

**ታሪክ ፀሃፊ** የህዝብን፥ የመንግስታትን፥ የመሪዎችን ክንዋኔ እያጠና መዝግቦ አጠቃላይ ገፅታውን የሚያሳይ ባለሙያ፤ ፀሃፊ ታሪክ።

**ታሪከኛ** ቅ 1. ተደናቂ፥ አስገራሚ። 2. ዝነኛ፥ ስመጥር።

**ታሪካዊ** ቅ 1. በታሪክ የተመዘገበ ክንዋኔ የተካሄደበት፥ በታሪክ የሚታወቅ። *ታሪካዊ ስፍራዎች /ታሪካዊ ቅርሶች*። 2. የተለየ ወይም ድንቅ የሆነ ነገር ወይም ድርጊት የተፈፀመበት። *በዚህ ታሪካዊ ቀን...።*

**ትረካ** ስ ታሪክ መተረክ።

**ተረከከ** ግ ሰነጠቀ፥ ፈነከተ።

**ተንተረከከ** ግ 1. በሰለ፥ ጎመራ (ፍራፍሬ)። 2. ፍም ወረደ፥ መረተ (የእሳት)። 3. ወፈረ ደለበ።

**አንተረከከ** ግ 1. አበሰለ(ፍራፍሬን)። 2. ፍም እንዲወርደው አደረገ (እሳትን)። 3. አወፈረ፥ አደለበ፥ አሰባ።

**ተረከዝ** ስ ከሂላ በኩል የሚታየውና መሬት የሚረግጠው የውስጥ እግር ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**ባለተረከዝ ጫማ** በተረከዙ በኩል መርገጫው ረዥምም የሆነ ጫማ፤ ታኮ ጫማ።

**ተረከዘ ሎሚ** ስንጥቅ ወይም ምልክት የሌለበት እንደሎሚ የሚያምር ተረከዝ ያላት።

**ተረከዘ ክት** ቅርፀ መልካም የሆነ አጭር ተረከዝ ያላት።

**ተረኮሰ** ግበሚነድ ወይም በሚቃጠል የእንጨት፥ የቧፍ፥... ጫፍ ላይ የሚገኘውን ክሳይ ወይም አመድ አስወገደ።

**መተርኮሻ** ስ ከእንጨት ወይም ከሸክላ... የሚሰራ የሲጋራ አመድና ቁራጭ ማጠራቀሚያ።

**ትርኳሽ** ስ እሳቱ፥ ፍሙ እንዲጠፋ የተደረገ (እንጨት፥ ሲጋራ፥...)።

**ተረገረገ**[1] ግ ተጠቀጠቀ፥ ታጨቀ፥ ሞላ።

**ተረጎመ** ግ 1. በአንድ ቋንቋ የተነገረን ሃሳብ ወደ ሌላ ቋንቋ መለሰ፥ ለወጠ። 2. አንድን አባባል ወይም የተነገረ ነገር ፈታ፥ አብራራ። 3. አንድም እንደዚህ እንደዚህ ማለት ነው፥... እያለ በቅዱሳት መፃህፍት ውስጥ የሚገኝን አንድ ሃሳብ ወይም አባባል በተለያየ መልክ እያገናዘበ ዘርዝሮ፥ አፍታትቶ፥ ተንትኖ አስረዳ። 4. አንድን ሃሳብ በአንድ በሌላ አይነት መልክ ተረዳ።

**ተርጓሚ** ስ 1. በአንድ ቋንቋ የተነገረን ሃሳብ በሌላ ቋንቋ ለውጦ የሚናገር፥ የሚያሰማ፤ "አስተርጓሚ"፥ "ትርጁማን"ም ይባላል። 2. በአንድ ቋንቋ የተፃፈን ነገር ወደሌላ ቋንቋ እየመለሰ የሚፅፍ። 3. ቅዱሳት መፃህፍትን በአንድምታ ትርጓሜ መንገድ የሚተነትን።

**ተርጓሚ ደርጋሚ** በፅሁፍ ተፅፎ እንዲተላለፍ የሚፈለገውን መልእክት ሌላ ፍቺ በመስጠት አዛብቶ ወይም አጣሞ የሚያቀርብ።

**ትርጉም** ስ 1. ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላ ቋንቋ የተመለሰ፥ የተለወጠ፥ የተተረጎመ ሃሳብ፥ ፅሁፍ፥...። 2. የአንድ ቃል ፍቺ። 3. አንድ የተባለን፥ የተነገረን፥ የተፃፈን፥... ሃሳብ ለማብራራት ወይም ግልፅ ለማድረግ የተነገረ ወይም የተሰጠ ተጨማሪ መግለጫ።

**ትርጉም ሰጠው** በሌላ ሃሳብ (መልክ) ተረጎመው፥ በመጥፎ ተረዳው።

**ትርጉም አይሰጠኝም** ስሜት አይሰጠኝም፥ አያረካኝም አያስደስተኝም።

**ትርጉም የለውም** ምንም የሚያመጣው ለውጥ የለም፥ ጥቅም የለውም። *ባለፈ ነገር ፀፀት ማብዛት ትርጉም የለውም።*

**ትርጓሜ** ስ 1.ፍቺ፥ ማብራሪያ። 2. አንድ ሃሳብ ተሰፋፍቶ፥ ተዘርዝሮና ተመስጥሮ በአንድምታ የአተረጓጎም ወይም የአፈታት ስልት የሚቀርብበት የትረካ፥ የገለፃ፥ የትንተና መንገድ።

**ተተረጎመ** ግ 1. ተፈታ፥ ተብራራ፥ ተገለፀ። 2. በአንድ ቋንቋ የተነገረ ቃል፥ አረፍተነገር፥...ወደሌላ ቋንቋ ተመልሶ፥ ተለወጠ። 3. አንድ አባባል ወይም አገላለፅ ተናጋሪው ያላሰበውን ትርጉም ወይም መልእክት አስተላለፈ።

**አስተረጎመ** ግ በአንድ ቋንቋ የተነገረውን ወደ ሌላ ቋንቋ በቃል እየተረጎመ ተናገረ።

**አስተርጓሚ** የ "ተርጓሚ" ን 1ኛ ፍቺ ተመ.

**ተረፈ** ግ 1. ከሚፈለገው መጠን በላይ ሆነ፥ ከተወሰነው መጠን አለፈ፥ በዛ (በቁጥር፥ በስፍር፥...)። 2. ቀረ (ሳያልቅ፥ ሳይጠፋ፥...)። *አንድ ብር ተረፈኝ*። 3. ለሌላ ሆነ፥ ወደ ሌላ

ተሻገረ:: *ለሃጥአን የወረደ ለፃድቃን ይተርፋል::* 4. ሞላ:: *ሃብት ተረፈው::* 5. አገኘ:: *በጠጪነቱ የተነሳ በሽታ ተረፈው::* 6. ዳነ፥ አመለጠ (ከበሽታ፥ ከሞት፥...)::

**አልተረፈም** በጣም ተጎድቷል::

**በተረፈ** ከዚህ ሌላ ወይም በተጨማሪ ለማለት የሚያገለግል:: *በተረፈ በሰላም እንገናኝ / በተረፈ ደብዳቤ እፅፍልሃለሁ::*

**ተረፍ** ስ የተረፈ ወይም የቀረ::

**ተረፈ መስዋእት** ስ ለመስዋእት ከቀረበ ነገር ላይ የተረፈ፥ የቀረ (ህብስት ወይም ሌላ ነገር)::

**ተረፈ ምርት** ስ ትርፍ ምርት::

**ትሩፋት** ስ ለፅድቅ ተብሎ የሚሰራ መልካም ስራ፤ በጎ አድራጎት::

**ትራፊ** ቅ 1. ቀሪ፥ የተረፈ:: ስ 2.ፍርፋሪ፥ ቁርስራሽ፥ ከመብል የተረፈ (እንጀራ፥ ዳቦ፥...)::

**ትርፍ** ቅ 1.አብላጫ፥ ከሚፈለገው በላይ ሆኖ የሚገኝ:: 2. ቀሪ:: ስ 3. ከአንድ ነገር የሚገኝ ውጤት:: 4. በሽያጭ ወይም በንግድ ከሚገኘው ገቢ ዋናውን ወይም ወጪውን ከቀነሱ ወይም ከመለሱ በሗላ የሚቀረው ገንዘብ:: 5. ጥቅም::

**ትርፍ ንግግር** የማያስፈልግ፥ የሚያጣላ መጥፎ ንግግር::

**ትርፍ ሰአት** ስ 1. ከተመደበው የስራ ሰአት በላይ የሆነ የስራ ጊዜ:: 2. ለማንኛውም የስራ አይነት ከተመደበው ሰአት ውጪ ያለ ጊዜ::

**ትርፍ አንጀት** ስ 1. በትልቁ አንጀት መዳረሻ ላይ ተቀጥሎ የሚገኝ አጭርና ቀጭን የሆነ የአንጀት ቅጥያ:: 2. ትርፍ አንጀት የተባለው የሰውነት ክፍል በሽታ ወይም ህመም::

**ትርፍ የኩል/የጋራ** ስ ከንግድ ስራ ወይም ሽያጭ የሚገኘውን ትርፍ በጋራ እኩል ለመከፋፈል የሚደረግ ስምምነት፥ ውለታ::

**የትርፍ ትርፍ** ስ 1. አንድ ትርፍ እንደዋና (ካፒታል) ሆኖ ስራ ላይ ውሎ የሚያስገኘው ሌላ ትርፍ:: 2. ከመጠን ያለፈ ብዙ ትርፍ::

**ትርፍራፊ** ቅ የተራረፈ፤ ፍርፋሪ፥ ቁርስራሽ::

**ትርፍርፍ አለ** ግ ሞላ፥ ተንቻረፈፈ፥ በጣም ብዙ ሆነ::

**ተራረፈ** ግ በብዛት ተረፈ፥ ቀረ::

**የተራረፈ** ቀሪ የሆነ፥ የተመለሰ (ምግብ ወይም ሌላ ነገር)::

**ተትረፈረፈ** ግ ከልክ አለፈ፥ በጣም በዛ፥ ከበቂ በላይ ሆነ::

**አተረፈ** ግ 1. ከንግድ፥ ከሽያጭ ትርፍ አገኘ:: 2. ትርፍ አስገኘ:: 3. አጋጠመ፥ አመጣ፥ አገኘ፥ ውጤት አስከተለ:: *ባንድ ባለመርጋቱ በሽታ አተረፈ / በመልካም ስራው መልካም ስም አተረፈ::* 4. አዳነ (ከአደጋ፥ ከመጥፎ አጋጣሚ)::

**አትራፊ** ስ 1. የችርቻሮ ነጋዴ:: ቅ 2. ትርፍ የሚያስገኝ::

**አታረፈ** ግ አባለጠ፥ አዛነፈ (ልብስን)::

**አትረፈረፈ** ግ በጣም አበዛ፥ በብዛት አቀረበ፥ ከልክ አሳለፈ::

**ተረፈሰ** ግ 1. አፈሰ፥ አብዘቶ ዘገነ:: 2. ቃመ:: 3. በስፋትና በፍጥነት ተራመደ::

***ተረፈፈ**

**ተንተረፈፈ** ግ ተንደረበበ፥ ሞላ::

**አንተረፈፈ** ግ አንደረበበ፥ ሞላ::

**ተረፍ** "**ተረፈ**" ስር ተመ.

**ተራ** ስ 1.ረድፍ፥ ሰልፍ፥ ተርታ፥ መደዳ፥ መስመር:: 2. ወረፋ፥ ቅደም ተከተል:: 3. ተመሳሳይ ሸቀጦችን የሚያቀርቡ ወይም ተመሳሳይ የንግድ ሥራ የሚሰሩ ነጋዴዎች በመደዳ ተሰባስበው የሚገኙበት አካባቢ፥ ሰፍራ:: *ሸንኩርት ተራ::* ቅ 4. ሹመት፥ ማእረግ የሌለው:: 5. ደረጃው ዝቅ ያለ፥ መናኛ::

**በተራ** 1. በመደዳ፥ በሰልፍ:: 2. በወረፋ፥ አንድ ባንድ::

**ባለተራ** አንድ ነገር ለማድረግ ወረፋ የደረሰው::

**ተራ መታ** በቅደም ተከተል፥ በረድፍ በረድፍ ሆነ፥ ተሰለፈ::

**ተራ ሰጠ** 1. አንድ ነገር ለማድረግ ለሌላው ሰው እድል፥ ወረፋ ሰጠ:: 2. በቅደም ተከተል አስቀመጠ፥ ወረፋ አስያዘ::

**ተራ ያዘ** በቅደም ተከተል ወይም እንዳመጣጡ ከተሰለፈው ወይም ከተደረደረው በመቀጠል ቦታ ያዘ::

**ተራ ደረሰው** ለመስራት፥ ለመውሰድ ወይም አንድ ነገር ለማድረግ ወረፋው ወይም ተራው ሆነ::

**ተራ ገባ** በወረፋ ለመስራት፥ ለማድረግ ተሰለፈ፥ ተዘጋጀ::

**ተራ ጠበቀ** ወረፋ እስኪደርሰው ቆየ::

**ተራ ቁጥር** ስ 1. ቅደም ተከተልን የሚያሳይ ወይም በቅደም ተከተል ያለ ቁጥር:: 2. አንድ ሰው ወይም ነገር የያዘውን ተራ የሚያመለክት ቁጥር::

**ተራ ንግግር** 1. ፍሬ ነገር ወይም ቁም ነገር የሌለው አነጋገር:: 2. መደበኛ ወይም ያደባባይ ያልሆነ አነጋገር፥ ወሬ::

**ተራ ወታደር** ስ ወታደራዊ ሹመትና ማእረግ ያልተሰጠው የፖሊስ ወይም የመከላከያ

ሰራዊት አባል።

**ተረኛ** ቅ ባለወረፋ፥ ባለተራ፥ ባለፋንታ።

**ተራራ** ስ ከአካባቢው መሬት በጣም ከፍ ብሎ የሚገኝ የመሬት አካል፥ ትልቅ ጉብታ።

**ተራራ ያህላል** 1. ትልቅ ወይም ግዙፍ ነው። 2. ብዙ ነው (እዳ፥ ችግር፥...)።

***ተራመሰ**

**ትርምስ** ስ 1. ግርግር፥ ሽብር፥ ሁከት፥ ብጥብጥ። 2. ምስቅልቅል ያለ ሁኔታ።

**ትርምስምስ** ስ 1. ብዙ ግርግር፥ ሽብር፥ ብጥብጥ። 2. ምስቅልቅል።

**ትርምስምሱ ወጣ** ተደበላለቀ።

**ትርምስ አለ** ግ ተመሳቀለ፥ ድብልቅልቅ አለ።

**ትርምስምስ አለ** ግ ተመሰቃቀለ፥ ተደበላለቀ፥ ስርአት አጣ።

**ተተራመሰ** ግ 1. ተሸበረ፥ ተበጠበጠ። 2. ተመሰቃቀለ።

**ተተረማመሰ** ግ 1.ተሸበረ፥ ታወከ፥ ተበጠበጠ። 2. ተበጣበጠ። 3. ተመሰቃቀለ።

**አተራመሰ** ግ 1. በጠበጠ፥ አሸበረ። 2. አመሳቀለ፥ አደበላለቀ።

**አተረማመሰ** ግ 1. በጠበጠ፥ አሸበረ። 2. አመሰቃቀለ፥ አደበላለቀ።

***ተራሰ**

**ትራስ** ስ በመኝታ ላይ ራስን ለማሳረፍ የሚያገለግል እንደ መከዳ፥ ብርኩማ ያለ ወይም ሞላላ ቅርፅ እንዲኖረው ተደርጎ በተዘጋጀ ከረጢት ውስጥ ጥጥ ወይም ስፖንጅ ወይም ሌላ ለስላሳ ነገር ተሞልቶበትና ተሰፍቶ የሚዘጋጅ ድጋፍ።

**ትራስጌ** ስ በመኝታ ጊዜ ራስ ወይም ጭንቅላት የሚውልበት ወይም የሚያርፍበት የትራስ ቦታ፥ አቅጣጫ፤ "ራስጌ"ም ይባላል።

**ተንተራሰ** ግ 1.ራስን በትራስ ወይም በሌላ ድጋፍ ላይ አድርጎ ተኛ። 2.መሰረት አደረገ፥ ተደገፈ። *የተፈጠረውን ሳለመግባባት ተንተርሶ የተላለፈው ውሳኔ ትክክል አይደለም።*

**አንተራሰ** ግ 1.የሌላን ሰው ራስ በትራስ ወይም በሌላ ድጋፍ ላይ አሳረፈ። 2. መሰረት አደረገ፥ አስደገፈ። *የደረሰውን ኪሳራ አንተርሶ ድርጅቱን ዘጋ።*

**ተራቢ** "ተረበ" ስር ተመ.

**ተራች** "ተረተ" ስር ተመ.

**ተራኪ** "ተረከ" ስር ተመ.

**ተራክቦ** "*ረከበ[1]" ስር ተመ.

**ተራዳ** ስ የድንኳን ምሰሶ።

**ተራድኦ** "ረዳ" ስር ተመ.

**ተሬ** ስ 1. ከአካባቢው መሬት ከፍ ብሎና ተያይዞ አግድም የሚሄድ የመሬት አካል፥ ተረተር። 2. በተራራ፥ በተረተር ላይ አግድም ተያይዞ በመደዳ የሚገኝ ዛፍ፥ ደን። 3. የቀረው ወገን ተላጭቶ ከግንባር እስከ መሃል ራስ ድረስ በቀጭኑ የሚቀር የወንድ ልጅ ፀጉር(ስእሉን ፀጉር አሰራር ስር ተመ.)።

**ተርብ** ስ 1.ተናዳፊና መርዘኛ የሆነ በራሪ ነፍሳት፤ የውሻ ንብም ይባላል። 2. (ዘይ.) ነገረኛ፥ ተንኳሽ።

**ተርቡት** ቅ ነገረኛ፥ ጠቅሚቃ (ሴት)።

**የተርብ እንጀራ** ስ ተርብ የሚሰራው የማር እንጀራ የሚመስል ከዳ።

**ተርታ** ስ 1.ረድፍ፥ መደዳ። 2. ወረፋ። ቅ 3. ሹመት፥ ማእረግ የሌለው። 4.መናኛ።

**በተርታ** በመደዳ፥ በሰልፍ።

**ተርጓሚ** "ተረጎመ"ስር ተመ.

**ተርፏ**

**ተርፏ ተርፏ አለ** በድንጋጤ ተሸበረ (ስሜት)። *ሆዴ ተርፏ ተርፏ አለ! ምን እንደሚያስጨንቀኝ እንጃ።*

**ተሰባ** ግ መረዳት፥ ማወቅ ተቻለ። *ነገሩ አሁን ተሰብቶኛል።*

**ተሰባኝ** ነገሩ ገባኝ፥ ተረዳሁት።

***ተሰተሰ**

**ተስታሳ (ተሰተስ)** ቅ ቶስቷሳ፥ ፈሪ።

**ተንተሰተሰ** ግ ፈራ።

**አንተሰተሰ** ግ አስፈራራ።

**ተሰጥኦ** "ሰጠ" ስር ተመ.

**ተሲያት** "ሰአት" ስር ተመ.

**ተሳልቆ** "*ሰለቀ" ስር ተመ.

**ተሳቢ** "ሳበ" ስር ተመ.

**ተሳቦ** ስ ቀንድአውጣ ወይም ትል።

**ተሳትፎ** "ሰተፈ"ስር ተመ.

**ተሳነ** ግ አቃተ፥ አቅም የሌለው ሆነ (አንድ ነገር ለማድረግ)። *ከሀመሙ የተነሳ መናገር ተሳነው።*

**ተስቦ** ስ ተላላፊ በሽታ፤ ወረርሽኝ።

**ተስፋ** ስ 1. ይገኛል፥ ይፈፀማል፥ ይሆናል፥ ይደረጋል ተብሎ የሚጠበቅ ፥ ምኞት። 2. አለኝታ። 3. አነስተኛ ሙልሙል፤ ጢቢኛ (በቤተክርስቲያን ለነዳያን የሚሰጥ)።

**ተስፋ ሰጠ** 1. ለመፈፀም ቃል ገባ። 2. አፅናና፥ አበረታታ።

**ተስፋ ቆረጠ** የተሻለ ነገር እንደማይገኝ

ወይም እንደማይመጣ አመነ፤ ምኞቱን፥ አለኝታውን ከሃሳቡ ሰረዘ፥ ተወ።

**ተስፋ አደረገ** 1. አንድ ነገር እንደሚገኝ፥ እንደሚሆን፥ እንደሚፈፀም አሰበ፥ ገመተ፥ ጠበቀ፥ ተማመነ። 2. አለኝታ አደረገ።

**ተስፋ አገኘ** (አንድ ነገር) ይሆንልሃል፥ ይፈፀምልሃል ተባለ ወይም እንደሚሆንለት ከሁኔታዎች ገመተ፥ ተማመነ።

**ተስፋ የለውም** 1. ፍላጎቱን፥ ምኞቱን፥ እቀዱን ለመፈፀም ወይም ለማግኘት አይችልም። 2. አይድንም፥ አይተርፍም (ከሞት፥ ከበሽታ፥ ከአደጋ፥...)።

**ተስፋ ጣለበት** በአንድ ነገር ላይ እምነት አሳደረ፥ ተማመነ።

**ተስፋ ቢስ** ከንቱ፥ ወደፊት ደህና ነገር የማይጠብቀው ወይም የማይጠበቅ።

**ተስፈኛ** ስ በአዳሪ ትምህርት ቤት አካባቢ ከተማሪዎች የሚተርፈውን ምግብ እየተመገበ የሚኖር ጥገኛ ተማሪ።

**ተሽ**

**ተሽ አለ** ግ የመቃጠል፥ የመጠበስ፥ የመፍላት፥...ድምፅ ሰጠ።

**ተሽሞረሞረ** ግ በልዩ ልዩ ጌጥ ተዋበ፥ ተሸቀረቀረ።

**ተቀምጪ** ስ ፍሬው ብዙ የሆነ ቁመተ አጭር የማሽላ አይነት።

**ተቀብኦ** ስ የተፈጥሮ ስጦታ (እንደ ግርማ ሞገስ፥ በሰው የመወደድ፥ የመከበር፥ የመሳሰለው)።

**የተቀብኦ ስም** ስ የሹመት ወይም የማእረግ ስም (የንግስና፥ የጵጵስና፥...)።

**ተቀናቀነ** ግ ተፎካከረ፥ ተሻኮተ፥ ተጋፋ (የሌላውን ይዞታ ለመንጠቅ)።

**ተቀናቃኝ** ቅ ባላንጣ፤ ተፎካካሪ።

**ተቃውሞ** "*ቀወመ" ስር ተመ.

**ተቅማጣም** "*ቀመጠ" ስር ተመ.

**ተቅማጥ** ዝ.ከ.

**ተቋም** "ቆመ" ስር ተመ.

**ተበተ(ተቤተ፥ታበየ)** ግ ኮራ፥ ተጀነነ፥ ሰው ናቀ፥ በትእቢት ተሞላ።

**ትእቢት** ስ ኩራት፥ ንቀት፥ ማንአለብኝነት።

**ትእቢተኛ** ቅ ኩራተኛ፥ ሰውን የሚንቅ።

**አተበተ** ግ አኮራ፥ ትእቢተኛ አደረገ።

**ተበተበ** ግ 1. ብዙ ቦታ ላይ አሰረ፥ ጠመጠመ፥ ጠላለፈ። 2. ከበበ፥ ያዘ። 3. በአስማት፥ አዚም በማድረግ፥ በድግምት አሰረ፥ አፈዘዘ፥...። 4.ነገር ቋጠረ፥ ዶለተ፥ አሴረ።

**ተብታቢ** ቅ 1. መተተኛ፥ ጠንቋይ፥ አስማተኛ። 2. መሰሪ፥ ሴረኛ፥ ነገረ ሰሪ።

**ትብትብ** ቅ የታሰረ፥ የተተበተበ፥ የተጠላለፈ፥ የተቆላለፈ (ነገር)።

**ትብትብ** ስ ዝብዝብ፥ አተካራ።

**ተተባተበ** ግ ተሳሰረ፥ ተጠላለፈ፥ ተቆላለፈ፥ ተወሳሰበ።

***ተበተበ[1]**

**ተብታባ** ቅ አፉ የሚተሳሰር፥ በትክክል የማይናገር፤ ኮልታፋ።

**ተንተባተበ** ግ ሲናገር አንደበቱ ተሳሰረ፤ ተኮላተፈ።

**አንተባተበ** ግ አፍን ያዘ፥ አሰረ፤ አኮላተፈ።

***ተበተበ[2]**

**ተንተበተበ** ግ እሳት በደንብ ሳይገባው እስኪንጣጣ ድረስ ብቻ ተቆላ፤ በዝቅተኛ የመብሰል ደረጃ ታመሰ (ገብስ፥ ስንዴ፥...)።

**አንተበተበ** ግ እሳት በደንብ ሳይገባውና እስኪንጣጣ ድረስ ብቻ ቆላ፤ በደንብ ሳያበስል አመሰ።

**እንትብትብ** ቅ በዝቅተኛ የመብሰል ደረጃ የታመሰ፥ የተቆላ (ገብስ፥ ስንዴ፥...)።

**ተባ** ግ 1. ሰላ፥ ተሞረደ። 2. ቀለጠፈ (በንግግር)።

**ትብ** ቅ ስል፥ ስለት ያለው።

**አተባ** ግ ሳለ፥ ሞረደ።

**ተባለ** "አለ" ስር ተመ.

**ተባእት** ስ ወንዴ ፆታ።

**ተባእታይ** ቅ ወንዴ።

**ተባይ** ስ 1.እንደ ቅማልና ቁንጫ ያለ ደም መጣጭ ወይም ሰብል የሚያጠፋ ነፍሳት። 2. (ዘይ.) በጥባጭ።

**ተቤተ** "ተበተ" ን ተመ.

**ተብታቢ** "ተበተበ" ስር ተመ.

**ተብታባ** "*ተበተበ[1]" ስር ተመ.

**ተተገ** "ተገተገ[1]" ን ተመ.

**ተትጎለጎለ** ግ ቡልቅ እያለ በብዛት ወጣ (ጪስ)።

**ተቸ** ግ 1. አተተ፥ አስተያየት ሰጠ፥ ማስረጃ እየጠቀሰ ተናገረ። 2. ነቀፈ፥ አንቋሸሸ።

**ተቺ** ስ 1.አታች፥ አስተያየት ወይም ትችት የሚሰጥ ሰው። ቅ 2. ነቃፊ።

**ትችት** ስ 1.አተታ፥ በማስረጃ የተደገፈ አስተያየት። 2. ነቀፋ።

**ተተቸ** ግ 1. በማስረጃ የተደገፈ አስተያየት ተሰጠበት። 2. የነቀፋ አስተያየት ተሰጠበት።

**አስተቸ** ግ ነቀፋ አስከተለ፥ አስነቀፈ።

**ተነበየ** ግ አንድ ነገር ከመደረጉ ወይም ከመድረሱ አስቀድሞ ነገሩ ወደፊት እንደሚደረግ ወይም እንደሚደርስ በቅድሚያ ተናገረ።

**ትንቢት** ስ ወደፊት ይደረጋል፥ ይደርሳል፥ ይፈፀማል ተብሎ በቅድሚያ የተነገረ ቃል፣ ንግርት።

**ትንቢት ተናገረ** ተነበየ።

**[የ]ትንቢት አንቀፅ** ስ (ሰዋ.) ያልተፈፀመ ድርጊት ወይም ወደፊት የሚፈፀም ድርጊት የሚገለፅበት የግስ ቅርፅ (ለምሳሌ እንደ ይበላል፥ ይጠጣል፥... ያሉ)።

**ትንቢተኛ** ስ ትንቢት ተናጋሪ።

**ተተነበየ** ግ እንዲህ ይሆናል ተብሎ አስቀድሞ ተነገረ።

**ተነተነ** ግ 1. ከፋፈለ፥ መደበ፥ ደለደለ፥ ሸነሸነ። 2. ዘረዘረ፥ እየነጣጠለ አብራራ፥ አስረዳ።

**ተንታኝ** ቅ በዝርዝር አብራርቶ የሚያስረዳ፥ የሚያቀርብ።

**ትንተና** ስ 1. የማብራራት ወይም የመዘርዘር ተግባር። 2. ማብራሪያ፥ ዝርዝር ሃሳብ።

**ትንታኔ** ስ 1. የመከፋፈል፥ የመዘርዘር፥ የማብራራት ተግባር። 2. በዝርዝር ተከፋፍሎና ተብራርቶ የቀረበ ሃሳብ።

**አስተነተነ** ግ በአእምሮው አወጣ፥ አወረደ፥ አሰበ፥ አሰላሰለ።

**አስተንታኝ** ስ 1. ስራ ደልዳይ፥ አከፋፋይ፥ መሪ። 2. አመዛዛኝ፥ አስተዋይ።

**ተነነ** ግ 1. ወደ እንፋሎትነት ተለወጠ። 2. ጨሰ፥ በነነ፥ ቦነነ። 3. ከነፈ፥ በረረ።

**ተን** ስ 1. እንደጤዛ በአንዳንድ ነገሮች ላይ ተንቆርቁሮ የሚገኝ ውሃ፥ እንፋሎት። 2. በሙቀት ምክንያት የሚፈጠር እንደ ጭስ ያለ የፈሳሽ ነገር ብናኝ።

**አተነነ** ግ 1.ወደ እንፋሎትነት እንዲለወጥ አደረገ። 2. አጨሰ፥ አበነነ።

**ተነከለ** ግ ሸር፥ ተንኮል ሰራ።

**ተንኮል** ስ ሌላውን ለመጉዳት ወይም ለማታለል፥ ለማስደንገጥ፥... በዘዴ የሚከናወን ድርጊት ወይም ክፉ ስራ፣ ሸር።

**ተንኮለኛ** ቅ በሌላው ላይ መጥፎ ስራ የሚሰራ፥ ክፉ፣ ሸረኛ።

**ተተናኮለ** ግ ጠብ ለመፍጠር፥ ለመጣላት ፈለገ፥ ነገር ቆሰቆሰ።

**ተነኮሰ** ግ ነገር ፈለገ፥ ጠብ አጫረ።

**ተንኳሽ** ቅ ጠብ አጫሪ፥ ነገር ፈላጊ።

**ትንኩሽት** ስ 1. ጠብ አጫሪ፥ ነገረኛ፥ ቁጡ። 2. ተናካሽ የሆነ በቆላ የሚገኝ የቁጫጭ አይነት።

**ትንኮሳ** ስ ጠብ መጫር፥ ነገር መፈለግ።

**ተተናኮሰ** ግ ነገር ፈለገ፥ ተነኮሰ።

**ተነፈሰ** ግ 1. አየር ወደ ሳንባው እያስገባ አስወጣ። 2. እውስጥ ታምቆ የነበረው አየር ወጣ። *ጎማው ተነፈሱ*። 3. አወራ፥ ተናገረ። *እስከመቼ ዝም ትላለህ፣ ተንፍስ እንጂ*። 4. እረፍት፥ ፋታ አገኘ፣ ችግሩ፥ ስቃዩ ተቃለለለት።

**ትንፍሽ እንዳትል** ምንም ቃል እንዳትናገር፣ ዝም በል።

**መተንፈሻ ከለከለ** እረፍት ነሳ፥ ፋታ ከለከለ፣ አስጨነቀ።

**ትንፋሽ** ስ ከሳንባ የሚወጣ አየር።

**ትንፋሹን ዋጠ** 1. ሳይናገር ወይም ሳይተነፍስ ፀጥ ብሎ ቆየ። 2. ከድካሙ ጥቂት አረፈ።

**ትንፋሼ እስካለ** በህይወት እስካለሁ።

**አስተነፈሰ** ግ 1. በአንድ ነገር ውስጥ የተሞላን፥ የታመቀን አየር አስወጣ። 2 ገላገለ አሳረፈ፥ እፎይ አሰኘ። 3. አበረደ (ጥጋብን፥ ትእቢትን)።

**አላስተነፍስ አለ** 1. እረፍት ነሳ፥ ፋታ ከለከለ፥ ጨነቀ። 2. አላናግር አለ፥ መናገር ከለከለ።

**ማስተንፈሻ** ስ በአንድ ነገር ውስጥ የተሞላን አየር፥... ማስወጫ፥ መልቀቂያ ቀዳዳ ወይም መቆጣጠሪያ።

**ተነፈገ** ግ ገማ፥ ሸተተ፥ ከረፋ (ከመታፈን የተነሳ)።

**ትንፋግ (ትንፋገን)** ስ 1. ርጥበት ካለው ቆሻሻ ነገር ላይ እንደጢስ እየሆነ የሚነሳ መጥፎ ሽታ። 2. አየር እንደልብ በማይገኝበትና በማይዘዋወርበት ቦታ የሚፈጠር የታፈነ ጠረን፥ ትንፋሽ።

**ተነፋነፍ[ሱሪ]** ስ ከሰውነት ጋር ልክክ የማይል በጣም ሰፊ የሆነ የረዥም ሱሪ አይነት።

**ተን "ተነነ"** ስር ተመ.

**ተንበረክ** ስ ለፀሎት በርከክ በሚባልበት ጊዜ ለጉልበት ማሳረፊያ ያገለግል ዘንድ በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የሚገኝ እንደ መከዳ ያለ ነገር።

**ተንታኝ "ተነተነ"** ስር ተመ.

**ተንኮለኛ "ተነከለ"** ስር ተመ.

**ተንኮል** ዝ.ከ.

**ተንኳሽ "ተነኮሰ"** ስር ተመ.

**ተኛ** ግ 1. ጎኑ ምድር ነካ ወይም ተጋደመ፥ ተዘረረ፥ ወደቀ። 2. እንቅልፍ ላይ ሆነ፥ እንቅልፍ ወሰደው። 3. ተለሸለሸ፥ ለጥ አለ

(ፀጉር፣ ጤፍ፣...)። 4. በግብረ ስጋ ተገናኘ። 5. ረጋ፣ አንድ ቦታ ተቀመጠ። *ሜዳው ላይ ውሃ ተኝቶበታል።* 6. መስራት አቆመ። *ሰዓቱ ተኝታለች*፡ 7. መንቀሳቀስ ወይም አንድን ስራ ማንቀሳቀስ ተወ። 8. አዘነበለ፣ አጎነበሰ፣ ተንጋደደ።

**መኝታ** ስ 1. በእንቅልፍ፣ በድካም፣ በህመም፣... ጊዜ ሰውነት የሚያርፍበት፣ የሚጋደምበት ቦታ፣ አልጋ፣ መደብ፣...። 2. አልጋ ላይ መጋደም፣ መተኛት። *ሰነፍ ሰው መኝታ ያበዛል።*

**መኝታ ቤት** ስ ለመኝታ ወይም ለመተኛ እንዲሆን የተዘጋጀ ክፍል።

**አስተኛ** ግ 1. አጋደመ፣ ዘንበል አደረገ። 2. መተኛት አስቻለ። *አልጋው ሰስት ሰው ያስተኛል።* 3. እንቅልፍ አስወሰደ። 4. ወዘፈ (ስራን)። 5. ጠብን ወይም ነገርን አበረደ፣ አረገበ።

**ተኛ** ግስ ወይም ስም በሆኑ በአንዳንድ ቃላት ላይ በስተመድረሻ በኩል እየታከለ ሌሎች ስሞችን ወይም ቅፅሎችን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ። *በላተኛ/ ቀለብተኛ/ዝምተኛ።*

**ተአማኒ "አመነ"** ስር **"ታማኝ"**ን ተመ.

**ተአምር(ታምር)** ስ አስደናቂ ፣ አስገራሚ፣ ልዩ የሆነ ነገር። "ታምራት"ም ይባላል።

**ተአምረኛ** ቅ ተአምር የሚሰራ፣ ልዩ ችሎታ ያለው።

**ተአቅቦ "*አቀበ"** ስር ተመ.

**ተከለ** ግ 1. የተክልን ፍሬ፣ ዘር ወይም የችግኝን ስር ከአፈር ውስጥ አስገባ፣ ሻጠ፣ ሸጎጠ፣ ቀበረ (እንዲለማ፣ እንዲፀድቅ፣ እንዲበቅል)። 2. ቸከለ። 3. ሰራ፣ መሰረተ፣ አቆመ (ቤተክርስቲያንን ወይም ሌላ ድርጅትን)። 4. ጣለ፣ ፈጠፈጠ። *መሬት ላይ በራሱ ተከለው።* 5. ሰጠ፣ አፀና፣ አስያዘ (መሬትን፣ ስራን፣...)። 6.መደበ፣ ደነባ (ግብርን፣ ስርአትን፣...)።

**ተክል ነቀል** ተዘዋዋሪ፣ በተወሰነ ቦታ ፀንቶ የማይቀመጥ።

**ተካይ ነቃይ** ስ ሺሚ ሻሪ፣ ርስት ለመስጠትና የተሰጠውንም ለመንጠቅ የሚችል የቀድሞ ጊዜ ባለስልጣን።

**ተክል** ስ 1. ልምላሜ ያላቸው የእፅዋት ዝርያዎች በጠቅላላ የሚጠሩበት ስም። 2. ሰው ይሆነኝ ብሎ ተክሎ የሚንከባከበው እንደ ጌሾ፣ ጎመን፣ አበባ ያሉ የሚበሉ ወይም የማይበሉ እፅዋት አጠቃላይ ስም። "አትክልት"ም ይባላል።

**አትክልት(አታክልት)** ስ 1. ለመብልነት የሚያገለግሉ እንደጎመን፣ ድንች፣ ቀይ ስር የመሳሰሉ የእፅዋት ዝርያዎች። 2. የ "ተክል" ን 2ኛ ፍቺ ተመ.

**አትክልት ሻጭ** ስ በፍራፍሬ፣ በአትክልት ንግድ ስራ ላይ የተሰማራ ነጋዴ።

**አትክልተኛ** ስ አትክልትን በመትከልና በመንከባከብ ሙያ ላይ የተሰማራ ሰራተኛ።

**ትክል** ቅ የተተከለ፣ የቆመ።

**ትክለ መልካም** አቋመ መልካም፣ ያማረ (ብዙውን ጊዜ ለሴት)።

**ትክለ ሰውነት** ስ 1. አቋም፣ የሰውነት ቅርፅ። 2. የአንድ ሰው አጠቃላይ የማንነቱና የባህርዩ ሁኔታ።

**ትክል ድንጋይ** ስ በመቃብር ላይ ወይም በሌላ ቦታ ሆን ተብሎ ለምልክት የተተከለና ቅርፅ ያለው ድንጋይ።

**ትክለኛ** ስ በቀድሞ ዘመን ከመንግስት በቋሚ ባለቤትነት ርስት ወይም መሬት የተሰጠው፣ ባለቀላድ፤ "ተተካይ" ም ይባላል።

**ተተከለ** ግ 1. እፅዋት፣ ተክል፣ ፍራፍሬ፣...እንዲበቅል፣ እንዲፀድቅ በመሬት ወይም በአፈር ውስጥ ተሸጎጠ። 2. ወደቀ፣ ተፈጠፈጠ። *ባፍጢሙ ተተከለ።* 3. ተመሰረተ፣ ተቋቋመ። 4. ተመደበ(ግብር፣ በጀት፣...)።

**ተከተከ** ግ 1. ጠቀጠቀ፣ ጨቀጨቀ፣ መላልሶ ወጋ። 2. ጥሬን እየለቀመ በላ (ዶሮ፣ ወፍ፣...)።

**ትክትክ** ቅ የተወጋጋ፣ የተበሳሳ፣ የተጠቀጠቀ።

***ተከተከ**

**ትክትክ አለ** ግ በጣም ፈልቶ በሰለ፣ ተንተከተከ (ወጥ፣ አጥሚት፣...)።

**ትክትክ አደረገ** ግ በጣም አፍልቶ አበሰለ፣ አንተከተከ (ወጥን፣ አጥሚትን፣...)።

**ተንተከተከ** ግ በጣም ፈላ፣ በሰለ።

**አንተከተከ** ግ በጣም አፈላ፣ አበሰለ።

**እንትክትክ** ስ አጥሚት፣ ሙቅ።

**ተከነ** ግ 1.በጣም ተንተከተከ፣ በሰለ (ውሃ ብዙ የሌለበት ወጥ)። 2. ተናደደ፣ በገነ።

**ትክን አለ** ግ 1. በጣም በሰለ (ውሃ ብዙ የሌለበት ወጥ)። 2. በጣም ተናደደ።

**ትክን ያለ ወጥ** (ውሃ ሳይበዛበት) በደንብ የበሰለና የጣፈጠ ወጥ።

**ተትከነከነ** ግ በሃዘን፣ በብስጭት፣ በንዴት ተብሰለሰለ።

**አትክን(አትካኝ)** ቅ አብሻቂ፣ አናዳጅ።

**አትከነከነ** ግ በሃዘን፣ በብስጭት፣ በንዴት አብሰለሰለ።

**ተከዘ** ግ 1. በሃሳብ ተዋጠ፣ አዘነ፣ ቆዘመ። 2. ዋናው እስኪመጣ ድረስ ለጊዜው ሌላ ነገር ይዞ አዘገመ፣ ጠበቀ። *ምግብ እስኪቀርብ በዚች ቆሎ*

*ተከዝ።*

**መተከዣ** ስ መቆያ።

**ትካዜ** ስ ሃዘን፥ ቁዘማ፥ በሃሳብ መዋጥ።

**ትካዜ ገባው** በጭንቀት፥ በሃሳብ ተዋጠ።

**ተኩላ** ስ ክብና ሰፋፊ ጆሮዎች ያሉት፥ ትልቅ ውሻ የሚያክል፥ በዋሻ፥ ጥቅጥቅ ባለ ሳር ወይም በጉራንጉር ውስጥ የሚኖር ስጋ በል የሆነ የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ተኩስ "ተኮሰ"** ስር ተመ.

**ተካ** ግ 1.በጠፋ፥ በተወሰደ፥ በሄደ ነገር ፋንታ ሌላ ሰጠ፥ አመጣ፥ መለሰ፥ ከፈለ። 2.ወከለ። 3. በሌላ ሰው ወይም እቃ ፋንታ ገባ፥ አገለገለ።

**መተኪያ** ስ በአንድ ነገር ፋንታ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚያገለግል፥ መለወጫ።

**መተኪያ የሌለው** በእሱ ፋንታ ሊሆን፥ ሊገባ፥ ሊያገለግል የሚችል ምትክ፥ ለዋጭ የማይገኝለት፤ ብቸኛ የሆነ።

**ምትክ** ስ 1. ተተኪ። 2. ለዋጭ።

**በምትኩ** 1. በፋንታው። *ተፈላጊው እቃ ስለጠፋ በምትኩ ሌላ ገዛሁ*። 2. በለውጡ። *እሱን ስጠኝና በምትኩ ይሄን እሰጥሃለሁ።*

**ትክ** ስ ምትክ።

**ተተካ** ግ 1. በጠፋ፥ በተወሰደ፥ በሄደ ነገር ፋንታ ሌላ ተሰጠ፥ ተመለሰ፥ ተከፈለ። 2. በሌላ ነገር ፋንታ መጣ፥ ገባ፥ አገለገለ። 3. ተወከለ።

**ተተኪ** ቅ በአንድ ሰው ወይም ነገር ፋንታ ተተክቶ የሚገባ ወይም የሚመጣ ቀጣይ፥ ተከታይ።

**ተተኪ ትውልድ** ካለው ትውልድ ቀጥሎ የሚመጣ አዲስ ትውልድ።

**ተካሬፅ(አተካሪስ)** ስ በቀሚስ ላይ የሚሰፋ ወፈር ያለ መታጠቂያ ወይም መቀነት።

**ተካነ "ካነ"** ስር ተመ.

**ተክሊል** ስ 1. የቤተክህነት ሰዎች፥ የነገስታት ቤተሰቦች በበአል ቀን ወይም ሙሽሮች በቤተክርስቲያን ጋብቻቸውን ሲፈፅሙ ራሳቸው ላይ እንደቆብ የሚደፉት ከብር፥ ከወርቅ፥... የሚሰራ የክብር ወይም የማእረግ ምልክት (የ"**አክሊል**" ን ስእል ተመ.)። 2. በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን አማካኝነት የሚፈፀም ስርአተ ጋብቻ።

**ተክሊል አደረገ** በስርአተ ተክሊል አገባ።

**ተክል "ተከለ"** ስር ተመ.

**ተኮረ** ግ ትክ ብሎ አየ፥ ተመለከተ፥ አስተዋለ።

**ተኳር** ቅ አተኩሮ የሚመለከት፥የሚያስተውል።

**ትኩረት** ስ አፅንኦት፥ ሃሳብን በይበልጥ አንድ ነገር ላይ ማሳረፍ።

**ትኩረት ሰጠ** (ለጉዳዩ) ከፍ ያለ ግምት ሰጠ፤ ይበልጥ አሰበበት።

**ትኩረት ሳበ** የሰው ሃሳብ ወደእሱ እንዲሆን አደረገ።

**ትኩረት አገኘ** ይበልጥ ታሰበበት።

**ትኩር ብሎ አየ** አተኩሮ ተመለከተ።

**ተተኮረ** ግ ትኩረት ተደረገበት፥ በደንብ ታየ። *በዚህ ጉዳይ ላይ ለምን እንደተተኮረ አልገባንም።*

**አተኮረ** ግ 1. አይኑን በአንድ ነገር ላይ ተክሎ፥ አስተውሎ ተመለከተ። 2. ሃሳቡን በሙሉ ወደ አንድ ነገር ላይ አደረገ።

**አትኩሮት** ስ አፅንኦት፥ ትኩረት።

**ተኮሰ** ግ 1. አቃጠለ፥ ለበለበ፥ ፈጀ። 2. በጣም ተፋጀ፥ ከመጠን በላይ ሞቀ። 3. በጣም ሞቀ(ሰውነት)። 4. በጋለ ብረት ጠበሰ(ገላን)። 5. በካውያ ዳመጠ፥ ለመጠጠ፥ አስተካከለ (የተጨማደደ ልብስን)። 6. በሙቀት ሃይል በሚሰራ መሳሪያ እየጠቀለለ፥ እያስተካከለ አስዋበ (ፀጉርን)። 7. በግንብ ድንጋዮች መጋጠሚያ ላይ የሚገኘውን ቦታ በሲሚንቶ እየመረገ ዳመጠ፥ ለመጠጠ። 8. መሳሪያን ወይም እንደሮኬት፥ ሚሳይል የመሳሰሉ ሩቅ የሚሄዱ ተወርዋሪ ነገሮችን አስፈነጠረ፥ ሰደደ። 9. በመሳሪያ (በጠመንጃ፥በሽጉጥ፥...)ጥይትን ወደፊት አስፈነጠረ፥አበረረ። 10.(ዘይ.) ፈፀመ፥ አከናወነ (ጉዳይን)።

**መተኮሻ** ስ 1. በእሳት ወይም በኤሌክትሪክ ሃይል አግሎ አንድን ነገር ለመተኮስ የሚያገለግል እንደ ብረት ዘንግ፥ ሽቦ ያለ ነገር ወይም መሳሪያ። 2. ካውያ። 3. ኢላማ።

**ተኩስ** ስ 1.የእሳት ጠባሳ ምልክት። 2. በጦር መሳሪያ የመተኮስ ወይም የመታኮስ ሁኔታ። 3. ከጦር መሳሪያ የሚወጣ የጥይት ድምፅ። 4. በካውያ የተተኮሰ ልብስ እጥፋት፤ የአተኳኮስ ሁኔታ።

**ተኩስ ከፈተ** በሌላ ወገን ላይ የጦር መሳሪያ መተኮስ ጀመረ።

**የተኩስ ልውውጥ** በተለያዩ ወገኖች መካከል በመሳሪያ የሚደረግ የተኩስ ምልልስ፤ ውጊያ።

**የተኩስ አቁም ስምምነት** በተኩስ ወይም በውጊያ ላይ ያሉ ወገኖች፥ ባሉበት ሁኔታ ላይ እንዳሉ ውጊያውን ለማቆም የሚያደርጉት ጊዜያዊ ስምምነት።

**ተኳሽ** ቅ 1. አንድን መሳሪያ ለመተኮስ የተመደበ ሰው። 2. ተኩሶ ኢላማውን ሳይስት የመምታት ችሎታ ያለው ሰው፤ አነጣጣሪ።

**ትኩስ** ቅ 1.ሙቀት ያለው፤ ገና ከእሳት ላይ የወረደ። 2. አዲስ፥ ለጋ።

**በትኩሱ** 1.ሳይቆይ፥ ሳይዘገይ 2. ሳይበርድ፥

ሳይቀዘቅዝ።

**ትኩስ ስጋ** ያልዋለ ያላደረ ስጋ።

**ትኩስ ዜና** አዲስ ዜና፥ ከዚህ በፊት ያልተሰማ ወይም ያልተነገረ።

**ትኩሳት** ስ 1 ብዙ ጊዜ የህመም ምልክት የሆነና ከተለመደው መጠን በላይ የሚወጣ የሰውነት ሙቀት። 2. ወበቅ፥ ሃሩር። 3. ንዳድ፥ የወባ በሽታ። 4. ጠባሳ (የእሳት)።

**ተተኮሰ** ግ 1. ተዳመጠ ወይም ተስተካከለ (ልብስ በካውያ)። 2. በሙቀት ሃይል በሚሰራ መሳሪያ እንዲስተካከል፥ እንዲዋብ ተደረገ። *ልጅቷ ፀጉሯን ተተኩሳለች*። 3. ወደ ላይ ወጣ፥ ናረ (ዋጋ)። 4. መልክና ቅርፅ ተበጀለት (የግንብ መጋጠሚያ በሲሚንቶ)። 5. የጦር መሳሪያ (ጥይት፥ ሮኬት፥ ሚሳይል፥...) ተስፈነጠረ፥ ተወረወረ፥ ፈነዳ። 6. ተበየደ።

**አተኮሰ** ግ ሰውነት በጣም ሞቀ (ከበሽታ የተነሳ)።

**አስተኮሰ** ግ 1. ተኩስ እንዲከፈት አዘዘ፥ የውጊያ ወይም የተኩስ መመሪያ ሰጠ። 2. በእሳት አስጠበሰ፥ አስበየደ።

**አስተኳሽ** ስ ኩሩቅ ቦታ ሆኖ ከከባድ መሳሪያ ተኳሾች ጋር በሬዲዮ መገናኛ እየተነጋገሬ ተፈላጊውን ኢላማ፥ ቦታ የሚያስደበድብ፤ አዋጊ።

**ተኳር** "ተኮረ"ስር ተመ.

**ተኳሽ** "ተኮሰ" ስር ተመ.

**ተወ** ግ 1. አንድን ስራ፥ ድርጊት፥ ግንኙነት፥ ልማድ መፈፀም ወይም ማካሄድ፥...አቆመ፥ አቋረጠ፥ ከማድረግ ተቆጠበ። 2. ይዞት፥ ወብጦት የነበረውን ነገር ለቀቀ። 3. አንድን ነገር ችላ አለ፥ ትኩረት የማይሰጠው ሆነ። 4. ገደፈ፥ አስቀረ፥ ጣለ። 5.ይቅር አለ፥ ማረ። 6. ለቀቀ(ህመም)። *7.በአካባቢው መታየቱ፥ መገኘቱ ቀረ። ሰፈሩን ትቶታል።*

**ተወኝ እባክህ** አታስቸግረኝ፥ አትጨቅጭቀኝ፥ ... ለማለት የሚነገር።

**ተተወ** ግ 1. ተገደፈ፤ ቀረ፥ ተጣለ፥ ታለፈ። 2. ተማረ፥ ይቅር ተባለ።

**ተወነ** ግ በተውኔት መልክ ስራ ወይም አሳየ።

**ተዋናይ** ስ በትያትር ውስጥ አንድን ገፀባህርይ ወክሎ የሚጫወት፥ ትያትር የሚሰራ የጥበብ ሰው።

**ተውኔት** ስ በስነፅሁፍ መልክ ተዘጋጅቶና በመድረክ ላይ ለተመልካች ቀርቦ የሚታይ የስነጥበብ ውጤት፤ ትያትር።

**ተዋህዶ** "*ዋሃደ" ስር ተመ.

**ተዋናይ** "ተወነ" ስር ተመ.

**ተዋፅኦ** ስ ከአንድ ነገር የተገኘ ውጤት (ለምሳሌ ቅቤ ፥አይብ፥...ከወተት የሚገኝ ተዋፅኦ ነው)።

**ተውላጠ ስም** ስ ሰዋ. በስም ፋንታ ተተክቶ የሚገባና እንደ ስም ሆኖ የሚያገለግል የንግግር ክፍል (ለምሳሌ እኔ፥ አንተ፥ እሱ፥...)።

**ተውሳከ ግስ** ስ ሰዋ. "እንዴት"፥ "መቼ"፥ "የት" የሚለውን ጥያቄ የሚመልስና የግስን፥ የቅፅልን ወይም የሌላ ተውሳከ ግስን ሁኔታ የሚገልፅ የንግግር ክፍል (ለምሳሌ:- ቶሎ፥ እዚህ፥ በፍጥነት፥...)።

**ተውሳክ** ስ በሽታ።

**ተውኔት** "ተወነ" ስር ተመ.

**ተዛምዶ(ተዘምዶ)** "*ዘመደ" ስር ተመ.

**ተዛንብ** ስ ከግድግዳ ውጭ ዙሪያውን የሚገኝ፥ ዝናብ ግድግዳን እንዳይጎዳ ለማድረግ የሚያገለግል የጣራ ክፍል፤ ታዛ፤ ሰበሰብ።

**ተየበ** ግ በታይፕ ፃፈ።

**ታይፕ** ስ በወረቀት፥ በስቴንስል ላይ ለመፃፍ የሚያገለግል የፅህፈት መኪና።

**ታይፕ መታ** በታይፕ ፃፈ።

**ተደለቀ** ግ ተቆነነ፥ በዝግታ ሄደ፥ ተጀነነ።

**ተዳፋት** "ደፋ" ስር ተመ.

**ተድላ** "ደላ" ስር ተመ.

**ተገበ** ግ 1. በነፋስ ሃይል የሚወነጨፍ ዝናብ ጣለ፥ ውሽንፍር ሆነ። 2. ያለማቋረጥ አካፋ፥ ችፍ ችፍ አለ።

**ተግብ** ስ ውሽንፍር ያለው የክረምት ዝናብ፤ ወሊስ።

**ተገብሮ ግስ** "ገበረ[1]" ስር ተመ.

**ተገተገ[1](ተተገ)** ግ 1. ገረፈ። 2. ተኮሰ፥ አያያዘ (በእሳት)።

**ትንታግ** ቅ 1. የእሳት ክፋይ። 2.(ዘይ.) ሃይለኛ፥ ቀጡ፥ ተናጋሪ፥ ምላሰኛ።

**ተንተገተገ** ግ በራ፥ አበራ፥ ተብለጨለጨ፥ ተብረቀረቀ።

**አንተገተገ** ግ አበራ፥ አብለጨለጨ፥ አብረቀረቀ።

**ተገተገ[2]** ግ አጠጋግቶ በብዛት ተከለ (ችግኝን)።

**ተገነ** ግ ከለለ፥ ጋረደ።

**ተገን** ስ 1. ከነፋስ፥ ከብርድ፥...የሚከላከል የእንጨት፥ የድንጋይ፥ የዛፍ ከለላ፤ መከታ። 2. ረዳት፥ ወገን፤ መመኪያ።

**ተገን አደረገ** ግ 1. መከታ፥ ከለላ አደረገ። 2. አንድን ሰው መመኪያ አደረገ።

**ተገድራ** ስ እንደ ዋርካ፥ ወይራ፥...ባሉ ዛፎች ግንድ ላይ በጥገኝነት እጅብ ብሎ የሚበቅል የእፅዋት አይነት።

**ተጉመጠመጠ** ግ አፉን (ውስጡን) በውሃ

አጠበ፥ አፀዳ።

**ተጋ** ግ 1. በረታ፥ ጠነከረ፥ ከስንፍና ራቀ። 2. አሰበ፥ ስለ አንድ ጉዳይ ተጨነቀ።

**ትጉህ(ትጉ)** ቅ 1. ብርቱ፥ ታታሪ። 2. ንቁ፥ አሳቢ።

**ትጋት** ስ 1. ብርታት፥ ታታሪነት፥ ጥረት። 2. ንቁነት።

**አተጋ** ግ አነቃ፥ አበረታ፥ ጎተጎተ።

**ተጋባ** "ገባ" ስር ተመ.

**ተጋድሎ** "ገደለ" ስር ተመ.

**ተግ**

**ተግታ** ስ የዝናብ መቆም ወይም ብራ መሆን።

**ተግ አለ** ግ 1. በግ፥ ብልጭ አለ፥ በራ። 2. ቆመ፥ አባራ(ዝናብ)።

**ተግ አደረገ** ግ አበራ።

**ተግሳፅ** "ገሰፀ" ስር ተመ.

**ተግባር** "*ገበረ[1]" ስር ተመ.

**ተግባ** "ተገበ" ስር ተመ.

**ተግታ** "ተግ" ስር ተመ.

**ተግዳሮት** "*ገደረ" ስር ተመ.

**ተጠናወተ** ግ 1. ጥል ፈለገ፥ ባላጋራ ሆነ፥ ተተናከለ፤ ተጣላ። 2. አዘውትሮ በተደጋጋሚ አመመ።

**ተጠናወታት** አስወረዳት፣ ጨነገፈች።

**ተጣባ** ግ (የኮሶ ትል በሰውነት ውስጥ) መኖሩ ታወቀ፥ ታየ።

**ተፈሪ ሱሪ** ስ ከላይ ሰፊ ሆኖ ከጉልበቱ በታች እስከ ቁርጭምጭሚት በጠባቡ የሚወርድ ሱሪ።

**ተፈተፈ** ግ ላይ ላዩን በስለት ከብዙ ቦታ ላይ በጣ፥ ሰነተረ፥ ሰነጠቀ።

**ትፍትፍ** ቅ 1. ከብዙ ቦታ ላይ በስለት የተወጋጋ፥ የተሸነታተረ። 2. በኩታ ወይም በነጠላ ዳር ዳር ላይ ተሰባጥሮ የተጣለና የተለያዩ ቀለማት ያሉት ጥለት።

**ትፍትፋት** ስ የተሰነጠቀ፥ የተሰነተረ፥ የተበጣ የአካል ላይ ሽንትፋት።

**ተተፈተፈ** ግ ከብዙ ቦታ ላይ በስለት ተቆረጠ፥ ተበጣ።

***ተፈተፈ**

**ተፎ** ቅ ፈጣን፥ ከተፍ።

**ተፍተፍ አለ** ግ ስራን ለማከናወን በፍጥነት ወዲያ ወዲህ አለ።

**አተፈተፈ** ግ ፈጠነ፥ ቸኮለ፥ ወዲያ ወዲህ አለ (ለስራ፥ ለወሬ፥…)።

**አተፍታፊ** ቅ ወሬን ወዲያ ወዲህ የሚያመላልስ።

**ተፈጥሮ** "ፈጠረ[1]" ስር ተመ.

**ተፋ** ግ 1. ከፉ አስወጣ፥ አስወገደ፥ እንትፍ አለ (ምራቅን፥ ምግብን ወይም ሌላን ነገር)። 2. አስመለሰ፥ አስታወከ። 3. ወደ ዳር አወጣ፥ ጣለ (ውሃ የወሰደውን ሰው ወይም እንስሳ)። 4. አዳነ፥ አተረፈ፥ አወጣ (ከችግር፥ ከአደጋ፥ ከመጥፎ አጋጣሚ…)። 5. ወደ ውጭ መለሰ፥ አልወሰድ፥ አልቀበል አለ። 6. የያዘውን (ኳስ) ለቀቀ። 7. (እስክሪብቶ ወይም ብእር) ቀለሙ ገነፈለ፥ አፈሰሰ። 8. (ዘይ.) ጠላ፥ አገለለ። *ህዝብ የተፋቸው ባለስልጣናት።*

**ትፋት** ስ 1. ከአፍ የወጣ ምራቅ፥ አክታ። 2.ትውከት።

**ትፋታም** ቅ 1. (ስድብ) ትውከታም (ለሰካራም)። 2. አነጋገሩ ያልታረመ፥ ባለጌ።

**ተተፋ** ግ (ዘይ.) በጣም ተጠላ፥ ተገለለ፥ እንዲወገድ ተደረገ።

**አስተፋ** ግ (ዘይ.) አስጨንቆ አስከፈለ (ገንዘብን፥ እቃን፥…)።

**ተፌ** "*ተፈተፈ" ስር ተመ.

**ቱ** የ"ተ" ፊደል ካእብ ዘር።

**ቱሃን** "ትሂን" ን ተመ.

**ቱሊ** ስ 1. (ነውር) የቂጥ ቀዳዳ፥ ቱኒ። 2. ተረፈ ኩስ።

**ቱሊያም** ቅ (ነውር ፥ ስድብ) ቱሊውን በሚገባ የማያፀዳ።

**ቱልቱላ** ስ 1. ከቀንድ ወይም ከነሃስ፥… የሚሰራ እንደጥሩንባ ድምፅ የሚሰጥ ባህላዊ የትንፋሽ ሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) የውሸት፥ የጉራ ወሬ ማውራት የሚወድ።

**ቱልት** ስ ሲቀጠቀጥ ማላጋ የሆነ ጭማቂ የሚወጣው፥ ስሩ ረዥም የሆነ የእፅዋት አይነት።

**ቱማታ** ስ ጫጫታ፥ ውካታ፥ ጩሀት፥ ረብሻ፥ ትርምስ።

**ቱምቢ** ስ ግንብን በትክክል ቀጥ አድርጎ ለመገንባት ወይም ወደ አንድ ወገን አለማዘንበሉን ለማረጋገጥ ግንበኞች የሚገለገሉበት በሲባጎ የሚንጠለጠል የቆራጭ ብረት መሳሪያ።



ቱምቢ

**ቱሪስት** ስ ብዙውን ጊዜ ለደስታና ለመዝናናት ሲል ልዩ ልዩ ድንቅና ታሪካዊ

ቦታዎችን በየአገሩ እየዞረ የሚያይ ጎብኚ::

**ቱሪናፋ** ቅ ወሬኛ፥ ጉራ የሚያበዛ::

**ቱር**[1]

**ቱር አለ** ግ 1. ነጣ፥ ንፁህ ሆነ:: 2.ነጭ ልብስ ለበሰ::

**ቱር አለ** ግ በረረ (ወፍ)::

**ቱርኪ** ቅ ፈሪ፥ ቡከን::

**ቱስ**

**ቱስ አለ** ግ 1. ተነፈሰ፥ የታመቀው አየር ወጣ (ከጎማ ወይም ከሌላ ነገር):: 2. ቀስ ብሎ በጆሮ ነገረ::

**ቱስ አደረገ** ግ ድምፅ ሳያሰማ ፈሱን ለቀቀ::

**ቱስክ**

**ቱስኪያም** ቅ ፈሳም::

**ቱስክ አለ** ግ በነነ፥ ጨሰ(ፈሰ)::

**ቱስክ አደረገ** ግ ፈሳ::

**ቱሽ**

**ቱሽ አለ** ግ ቱሽ የሚል ድምፅ ሰጠ፤ በተቆላ ትኩስ ባቄላ ወይም አተር ላይ ውሃ ሲጨመርበት የሚሰማውን አይነት ድምፅ አሰማ::

**ቱቢት** ስ 1. ለሃዘን የሚለበስ፥ ዳርና ዳሩ ጥቁር ናይለን ጨርቅ የተመታበት ነጠላ:: 2. የሃዘን ምልክት ጥቁር ጨርቅ::

**ቱባ** ስ 1. በጥንተ መሰረቱ ላይ ሌላ ያልታከለበት፥ ያልተቀየጠ፥ ያልተከለሰ ንፁህ ነገር:: *ቱባ ጥይት*: 2. ያልተቀነሰ ሙሉ የድር ወይም የሹራብ ክር ጥቅል::

**ቱቦ** ስ ውስጠ ክፍት ሆኖ በተለያየ መጠን ከሲሚንቶ ወይም ከብረት ወይም ከፕላስቲክ፥... የሚሰራ በውስጡ እንደ ፈሳሽ ነገር፥ የኤሌክትሪክ ሽቦ ያሉትን ነገሮች ለማስተላለፍ የሚያገለግል እቃ::

**ቱታ** ስ በስራ ልብስነት የሚያገለግል፥ ሸሚዝና ሱሪው ከአንድ አይነት ወፈር ያለጨርቅ ወጥ ሆኖ ወይም ተያይዞ የተሰፋ ወይም ባለማንገቻ ሆኖ ደረት የሚሸፍን ቅጥያ ያለው ሰፊ የሆነ ሱሪ::

**ቱቻ(ቱሻ)** ስ ገመድ ለመስራት የሚያገለግል፥ ሳር፥ ከዚህ ሳር የሚዘጋጀው ገመድም ቱሻ ገመድ ይባላል::

**ቱኒ** ስ 1. (ነውር) የቂጥ ቀዳዳ:: 2. ቡከን፥ ፈሪ::

**ቱኒያም** ቅ (ነውር፥ ስድብ) ፈሳም::

**ቱኪ** ስ 1. ዋና ሹም ያልሆነ እንደ ምትክ ወይም የዋናው ሹም ረዳት ሆኖ የሚያገለግል (ሰው):: 2. (ዘይ.) ወሬ አቀባይ፥ አሳባቂ::

**ቱክ**

**ቱክ ቱክ አለ** ግ ፈላ፥ ተንደከደከ::

**ቱጃር** ስ ሃብታም ነጋዴ::

**ቱግ**

**ቱግታ** ስ የቁጣ፥ የንዴት ንግግር፥ ሁኔታ::

**ቱግ አለ** ግ 1. በፍጥነት ነደደ:: 2. በሃይል ተቆጣ፥ ተናደደ:: 3. አንድ ላይ ብዙ ሆኖ በቀለ::

**ቱፋህ** ስ ፖም

**ቱፌ** "ቡፌ[1]" ን ተመ.

**ቱፍ**

**ቱፍ አለ** ግ ተፋ፥ እንትፍ አለ::

**ቱፍታ** "ቡፌ[1]" ን ተመ.

**ቲ** - የ"ተ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ቲማቲም** ስ ውስጡ በጥቃቅን ፍሬዎችና ፈሳሽ አዘል በሆነ አካል የተሞላ፥ ድቡልቡል ወይም ሞላላ ቅርፅ ያለው፥ ሲበስል የሚቀላ፥ ቆዳው ለሰላሳ የሆነ የሚበላ አትክልት፤ ተክሉም ቲማቲም ይባላል::

**ቲም**

**ቲም አለ** ግ ከአፍ እስከ ገደፉ ሞላ፤ ጢም፥ ቲፍ አለ::

**ቲኬት** ስ ሲኒማ ቤት ወይም ቲያትር ቤት ለመግባት፥ በአውቶቡስ፥ በባቡር፥...ለመጓዝ ወይም እቃ ለመግዛትም ሆነ ሌላ አገልግሎት ለማግኘት የሚያስችልና በላዩ ላይ አስፈላጊው መረጃ (ዋጋ፥ ተራ ቁጥር፥ ማህተም፥...) የተፃፈበት ቁራጭ ወረቀት ወይም ካርድ::

**ቲኬት ቆረጠ** ቲኬት ገዛ ወይም ሸጠ::

**ቲኬት ቆራጭ** ስ ቲኬትን የሚሸጥ ሰራተኛ::

**ቲዎሪ** ስ ንድፈ ሃሳብ::

**ቲፍ**

**ቲፍ አለ** ግ በጣም ሞላ::

**ታ** የ"ተ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ታህሳስ** ስ ከህዳር ወር ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አራተኛ ወር ስም::

***ታለለ**

**ተላላ** ቅ ሞኝ፥ በቀላሉ የሚታለል::

**ተታለለ** ግ 1. ተሞኘ፥ ተጭበረበረ:: 2. ተሸነገለ::

**አታለለ** ግ 1. አሞኘ፥ አጭበረበረ፥ አቄለ:: 2. ሸነገለ::

**ማታለያ** ስ ማባበያ፥ መሸንገያ፥ መደለያ፤ ትንሽ ስጦታ::

**አታላይ** ቅ 1. ውሸታም:: 2. እያባበለ ወይም እየሸነገለ ጉዳዩን የሚፈፅም ወይም የሚያስፈፅም፤ ሸንጋይ:: ስ 3. ሌባ::

**ታለ አይሰጥ** ስ የከብት ሰረሰር፥ አጥንት።
**ታላላቅ "ተለቀ"** ስር ተመ.
**ታላቅ** ዝ.ከ.
**ታልማ** ስ 1. የወተት አንጀትና የጨጓራ መገናኛ የትንሹ አንጀት ጥቅል። 2. (ዘይ.) አቅመቢስ፥ ለንቋሳ።
**ታምር "ተአምር"** ን ተመ.
**ታምቡር** ስ ጠቅላላ ቅርፁ ክብ ሆኖ ሁለት አፎቹ በቆዳ የተለበጹ፥ አብዛኛውን ጊዜ ስልፈኞች የሚታጀቡበት፥ በአንድ ወይም በሁለት አጫጭር በትሮች እየተመታ የከበሮ ድምፅ የሚሰጥ የሙዚቃ መሳሪያ።
**ታሪክ "ተረከ"** ስር ተመ.
**ታሪፍ** ስ 1. በገቢ ወይም በወጪ ሸቀጦች ላይ መንግስት የሚጥለው ቀረጥ። 2. ሆቴሎችና ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ለምግብ ወይም ለሚሰጡት አገልግሎት የሚያስከፍሉት የተወሰነ የዋጋ ዝርዝር።
**ታርጋ** ስ በተሽከርካሪዎች የፊትና የሂላ አካል ላይ ተዐፎ በግልፅ የሚታይ የመለያ ቁጥር።
**ታበየ "ተበተ"**ን ተመ.
**ታቦት** ስ 1. ፅላት። 2. ፅላት የሚቀመጥበት ሳጥን፤ የፅላት ማህደር።
**ታቦት ነገሰ** ታቦት ከቤተክርስቲያን ወጥቶ በመንፈሳዊ ስነስርአት ተከበረ።
**የታቦት ራት** ስ የከተራ እለት ታቦት በሚያድርበት ቦታ ከምእመናን ለካህናቱ የሚሰጥ ምግብና መጠጥ።
**ታተረ** ግ ተፍጨረጨረ፥ ጣረ፥ ተጋ። *መሻሻል እንዲኖር በስራ መታተር ያስፈልጋል።*
**ታታሪ** ቅ ትጉህ፥ ተፍጨርጫሪ።
**ታታ[1]** ግ ጠላለፈ፥ አሰባጠረ፥ አወሳሰበ ወይም እንደወንፊት፥ አቴና፥ መረብ ያለ ነገር ሰራ።
**ትት** ቅ 1. እንደወንፊት፥ መረብ፥...ጥልፍልፍ የሆነ። ስ 2. ቱባ (የድር ወይም የጥለት ክር)።
**ታታ[2]**
**ታታ አለ** ግ ተንታታ፥ ተከታታይ የእሩምታ ተኩስ ድምፅ ሰጠ ወይም ተሰማ።
**ተንታታ** ግ የተከታተለ የተኩስ ድምፅ ሰጠ፥ ተሰማ፥ ተንጣጣ።
**አንታታ** ግ የተከታተለ የተኩስ ድምፅ አሰማ።
**ታታሪ "ታተረ"** ስር ተመ.
**ታች** መዋ. 1. ከአንድ ነገር ስር ወይም በስተግርጌ ያለ። 2. ቀልቀል፥ ዝቅተኛ የሆነ (ስፍራ፥ መንገድ፥...)።
**በታች** መዋ. 1. በግርጌ፥ በስር [በኩል]። 2. በቀልቀለት [በኩል]።
**የበታች** ቅ 1. ዝቅተኛ። 2. ከታች ያለ። 3. ታናሽ።
**የበታች መኮንን** ስ ከምክትል መቶ አለቃ በታች ከተራ ወታደር በላይ ሹመት ያለው ወታደር።
**ከ __በታች** 1. ከ___ግርጌ ወይም ስር። 2. ከ __ቀጥሎ። *ከዚህ በታች የተዘረዘሩት፥...።* 3. ከ __ ዝቅ የሚል ወይም የሚያንስ። *ከዚህ በታች በሆነ ዋጋ አይገኝም።*
**ወደታች አለው** አስቀመጠው(ተቅማጥ)።
**ታችኛ** ቅ 1. በስተስር፥ በስተግርጌ ያለ። 2. ዝቅ ብሎ የሚገኝ።
**ታች አምና "ሣች አምና"** ን ተመ.
**ታኒካ** ስ ገረወይና። በአንዳንድ አካባቢ እንደ ጣሳ፥ ኩባያ፥... ያሉ እቃዎችም ታኒካ እየተባሉ ይጠራሉ።
**ታናሽ "አነሰ"** ስር ተመ.
**ታንክ** ስ መላ አካሉ ብረት ለበስ የሆነ፥ የሚሽከረከርበት የብረት ሰንሰለት ወይም ጎማ ያለው፥ አስፈላጊውን ትጥቅና ስንቅ ከነወታደሮቹ በውስጡ ሸፍኖ ሊይዝ የሚችል ከባድ የጦር ተሽከርካሪ ወይም መኪና።
**ታንከኛ** ስ በታንክ ምድብ የጦር ክፍል ውስጥ የሚያገለግል ወታደር።
**ታንኳ** ስ ከቀርከሃ ወይም ከሸንበቆ ወይም ከደንገል፥... የሚሰራ የውሃ ላይ መጓጓዣ(ስእሉን መጓጓዣ ስር ተመ.)።
**ታከተ** ግ ሰለቸ፥ ደከመ።
**አታከተ** ግ አሰለቸ፥ አደከመ።
**አታካች** ቅ 1. አድካሚ፥ አሰልቺ የሆነ (ስራ)። 2. በጠባዩ አሰልቺ የሆነ (ሰው)።
**ታኬታ** ስ ለእግር ኳስ ጨዋታ የሚያገለግል፥ ስሩ(ሶሉ) መሬት ለመቆንጠጥ የሚያስችሉ የላስቲክ ወይም የብረት ጡቶች ያሉት የቆዳ ጫማ።
**ታክሲ** ስ በከተማ ውስጥ መንገደኞች ገንዘብ እየከፈሉ ከቦታ ወደ ቦታ የሚጓጓዙበት አነስተኛ አውቶሞቢል።
**ታክሲ ያዘ/ወሰደ** በታክሲ ተሳፈረ፥ ሄደ።
**ታክቲክ** ስ ዘዴ፤ አንድን አላማ ለመፈፀም፥ ተግባራዊ ለማድረግ የሚገለገሉበት ስልት።
**ታክቲከኛ** ቅ ዘዴኛ።
**ታከ[1]** ስ 1. ታኮ ጫማ፤ ባለተረከዝ ጫማ። 2. ከመሬት ከፍታ ያለው የጫማ ተረከዝ።
**ታከ[2]** ስ የቆመ መኪና እንዳይንሸራተት ጎማዎቹ ስር የሚደረግ የብረት፥ የእንጨት ወይም የድንጋይ፥... ድጋፍ።

**ታወሰ** ግ ትዝ አለ፥ ታሰበ (የተረሳ ነገር)።
**ትውስታ** ስ ትዝታ።
**ትውስ አለ** ግ ትዝ አለ፥ ታሰበ።
**አስታወሰ** ግ 1. የቆየን፥ ያለፈን፥ የተረሳን ነገር ትዝ አሰኘ፥ ትዝ እንዲል አደረገ። 2. የተረሳን ሰው ወይም ነገር ማን ወይም ምን እንደሆነ ሊያውቅ ቻለ፥ ትዝ አለው። 3. የቆየን ወይም ያለፈን ነገር እንደገና አሰበ። 4. አሳሰበ፥ እንዳይረሳ አደረገ(ሌላን ሰው)።
**ማስታወሻ** ስ 1. እንዳይረሳ፥ እንዳይዘነጋ፥ ትዝ እንዲል በመታሰቢያነት የሚቀመጥ ሃውልት ወይም ሌላ ነገር። 2. አንድ ነገር እንዲሰራ ወይም እንዲፈፀም የሚያሳስብ ፅሁፍ። 3. እንዳይረሳሱ፥ እንዲተሳሰቡ ወይም ፍቅርና አክብሮትን ለመግለፅ ለዘመድ፥ ለወዳጅ የሚደረግ ስጦታ። 4. ማስታወሻ [ደብተር] ፣ የተለያዩ የግል ጉዳዮች፥ ነጥቦች አድራሻዎች፥... የሚፃፉበት ትንሽ ደብተር።
**አስታዋሽ** ቅ 1. የማይረሳ፥ ዝንጉ ያልሆነ። 2. አሳሳቢ፥ አስገንዛቢ። 3 ጠያቂ ፥ ረዳት።
**ታዋቂ** "**አወቀ**" ስር ተመ.
**ታዘበ** ግ 1. ሌላው የሰራውን መጥፎ ተግባር በማየት ቅር ተሰኘ። 2. ሁኔታዎችን በመገምገም ተመለከተ ፥ አስተዋለ።
**ታዛቢ** ስ 1. ተመልካች። 2. ተቆርቋሪ። 3. ምስክር፥ እማኝ።
**ትዝብት** ስ አንድ ሰው የሚያደርገውን መጥፎ ተግባር የመገምገም አመለካከት።
**ተዛዘበ** ግ አንዱ ሌላውን በመታዘብ ሁኔታ ገመገመ።
**አስተዛዘበ** ግ አንዱ ሌላውን (እርስ በርስ) እንዲታዘብ፥ እንዲተዛዘብ፥ እንዲገማገም፥ እንዲገማመት አደረገ።
**ታዛ** ስ በስተውጭ ያለ የቤት ዙሪያ ጣሪያ።
**ታዛቢ** "**ታዘበ**" ስር ተመ.
**ታይፐ** "**ተየበ**" ስር ተመ.
**ታደገ** ግ አዳነ፥ ቤዛ ሆነ።
**ትድግና** ስ መታደግ፥ ማዳን።
**ታዳጊ** ቅ አዳኝ፥ ቤዛ።
**ታዲያ** አንድን ሃሳብ ቀደም ብሎት ከተነገረው ጋር ለማያያዝ የሚያገለግል ቃል፥ የንግግር፥ የአረፍተ ነገር ማያያዣ።
**ታዲያስ** 1. ከዚያስ፥ እናስ እያሉ አንድ ሰው በጀመረው ነገር ወይም ገለፃ እንዲቀጥልበት፥ እንዲገፋበት ለማድረግ ከአድማጭ የሚሰነዘር ቃል። 2. "አዎን" ለማለት በቃል ንግግር ላይ የሚያገለግል ቃል። ጠያቂ: *ስራውን ጨረስክ ማለት ነው?* መላሽ: *ታዲያስ።* 3. በጣም በሚቀራረቡ ሰዎች መካከል ለሰላምታ የሚባል ቃል።
**ታዳጊ**[1] "**ታደገ**" ስር ተመ.
**ታዳጊ**[2] "**አደገ**" ስር ተመ.
**ታጀረ** ግ ኩራ፥ ተጀነነ።
**ታገለ** ግ 1. አንዱ ሌላውን ለመጣል፥ ለማጥቃት፥...ተያያዘ፥ ተናነቀ፤ ግብግብ ወይም ትግል ገጠመ። 2. አንድን ነገር ለማከናወን፥ ለማግኘት፥... ተጣጣረ፥ ለፋ፥ መስዋእትነት ከፈለ። 3. አስቸገረ፥ በቀላሉ የሚከናወን አልሆን አለ።
**ታጋይ** ቅ 1.ትግል፥ ግብግብ የመግጠም ችሎታ ያለው። ስ 2. ለአላማው፥ ለእምነቱ መከበር ወይም እውን መሆን የሚታገል፥ መስዋእትነትን የሚከፍል (ብዙውን ጊዜ ለፖለቲካ አላማ)።
**ትግል** ስ 1.አንዱ ሌላውን ለመጣል ወይም ለማጥቃት፥... የሚያደርገው ትንቅንቅ፥ ፍትጊያ፥ ግብግብ። 2. ተግባርን፥ ስራን ለማከናወን የሚደረግ ጥረት፥ መፍጨርጨር። 3. (ብዙውን ጊዜ የፖለቲካ) አላማን ለማሳካት የሚደረግ ጥረት፥ መፍጨርጨር።
**አታገለ** ግ 1.አለፋ፥ አደከመ፥ በቀላሉ የማይከናወን ሆነ። 2.ትግልን መራ።
**ታገሰ** ግ ረጋ አለ፥፥ ሳይቸኩል በእርጋታ ጠበቀ። 2. ትንኮሳን ቻለ።
**ታጋሽ** ቅ ረጋ ያለ፥ ቻይ፥ የማይቸኩል፥ ቶሎ የማይናደድ።
**ትእግስት** ስ እርጋታ፥ መቻል፥ አለመቸኮል።
**ትእግስተኛ** ቅ ረጋ ያለ፥ ቻይ፥ ችኩል ያልሆነ።
**አስታገሰ** ግ 1. ዝም አሰኘ፥ አቀዘቀዘ፥ ረጋ እንዲል አደረገ። 2. ቀነሰ፥ አበረደ፥ ለጊዜው አቆመ (ህመምን፥ ረሃብን፥...)።
**ማስታገሻ [መድሃኒት]** ስ ለጊዜው ህመምን፥ ስቃይን የሚቀንስ መድሃኒት።
**ታጠቀ** ግ 1. በወገቡ ላይ ሸብ አደረገ፥ አሰረ (ቀበቶን፥ ዝናርን፥...)። 2. ለበሰ (ሱሪን፥ ቁምጣን)። 3. አሸረጠ፥ አደገደገ። 4. እንደ ሽጉጥ ወይም ጠመንጃ ያለ መሳሪያ ያዘ፥ በቀላልም ሆነ በከባድ የጦር መሳሪያ ተደራጀ፥ ተዘጋጀ። 5. ተዘጋጀ፥ ተጠንቀቀ፥ ቆርጦ ተነሳ። *መሃይምነትን ለማጥፋት ታጥቀን ተነስተናል።*
**መታጠቂያ** ስ መቀነት፥ ቀበቶ።
**ታጣቂ** ስ የጦር መሳሪያ የያዘ ሰው።
**ትጥቅ** ስ 1. ሸርጥ፥ ድግድግ። 2. የጦር መሳሪያ። 3. አንድ ነገር ለማካሄድ (ጦርነት፥ ስራ፥ ጉዞ፥...) የሚያስፈልግ ነገር፥ ዝግጅት።
**ትጥቅ ፈታ** የያዘውን የጦር መሳሪያ

አስረከበ፥ ተቀማ።

**ትጥቀ መልካም** በአለባበሷ ጥሩ የሆነች ሴት።

**ትጥቅና ስንቅ** ስ ጦርነትን ለማካሄድ የሚያስፈልገው የጦር መሳሪያ፥ ቀለብና ሌላም ቁሳቁስ፤ ስንቅና ትጥቅም ይባላል።

**የትጥቅ ትግል** ስ በጦር መሳሪያ አማካኝነት የሚካሄድ ትግል።

**አስታጠቀ** ግ 1. አለበሰ (ሱሪን፥ ቱታን)። 2. የጦር መሳሪያ ሰጠ፥ አደለ፥ በጦር መሳሪያ አደራጀ። 3. (ዘይ.) ሰደበ፥ አዋረደ። *በስድብ አስታጠቀው።*

**ታፋ** ስ ከጭን በላይ ከወገብ በታች ከመቀመጫ በስተጎን በኩል ያለ አካል፥ ስርጎድ ያለው የሰውነት ክፍል(ስእሉን ሰውነት ስር ተመ.)።

**ቴ** የ "ተ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ቴሌስኮፕ** ስ የቱበ ቅርፅ ያለውና ሩቅ ያሉ ነገሮችን አቅርቦና አጉልቶ የሚያሳይ መሳሪያ።

**ቴሌቪዥን** ስ ከቴሌቪዥን ጣቢያ የሚሰራጨውን ስእል፥ እንቅስቃሴና ድምፅ ከአየር እየጠለፈ የሚያሳይና የሚያሰማ መሳሪያ።

**ቴሌቪዥን ጣቢያ** ስ በኤሌክትሪክና በልዩ ልዩ ዘመናዊ መሳሪያ፥ ድምፅ፥ ስእልና ማንኛውም አይነት እንቅስቃሴ በአየር ውስጥ ወደተፈለገው ቦታ እንዲሰራጭ የሚያደርግ ጣቢያ።

**ቴሌክስ** ስ መልእክትን በተየበ መልክ በሚፅፍና በኤሌክትሪክ ሞገድ አማካኝነት ወደተፈለገው ቦታ በሚያስተላልፍ ወይም በዚሁ መልክ የተሰራጨን መልእክት ተቀብሎ ወዲያውኑ በሚፅፍ መሳሪያ አማካኝነት የሚካሄድ ግንኙነት፤ መሳሪያውም "ቴሌክስ" ይባላል።

**ቴሌግራም** ስ በኤሌክትሪክ ሞገድ አማካኝነት የሚተላለፍ የፅሁፍ መልእክት።

**ቴሌፎን** "ስልክ"ን ተመ.

**ቴምር** "ተምር"ን ተመ.

**ቴምብር** ስ ተፈላጊው ቀረጥ ለመንግስት መከፈሉን እንዲያረጋግጥ በፖስታዎች፥ በደብዳቤዎች፥ በሸቀጦች፥...ላይ የሚለጠፍ፥ በላዩ ላይ የቀረጡ ዋጋና ልዩ ምልክት (አርማ) የታተመበት፥ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በመንግስት የሚዘጋጅ ስስ ወረቀት።

**ቴርሞ ሜትር** ስ የሙቀት መጠን መለኪያ መሳሪያ፤ የሙቀት መጠን መለኪያ።

**ቴስተር** ስ በኤሌክትሪክ ሽቦ ውስጥ ወይም የኤሌክትሪክ ሃይል በሚያልፍበት እቃ ውስጥ የኤሌክትሪክ ሃይል መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያገለግል መሳሪያ።

**ቴክኒክ** ስ 1. ከሞተር፥ ከሜካኒክ፥ ከእንጨት ስራ ጋር የተያያዘ የእጅ ሙያ ጥበብ። 2. ዘዴ፥ ብልሃት።

**የቴክኒክ ትምህርት** ስ የእደጥበብ፥ የሜካኒክ፥ የኤሌክትሪክ፥... ዘርፍን የሚመለከት የሙያ ትምህርት።

**ቴክኒሽያን** ስ የቴክኒክ ስራዎችን የሚያከናውን ባለሙያ።

**ቴክኖሎጂ** ስ የሳይንሳዊ ግኝቶች በተለይ ለኢንዱስትሪያዊ ጠቀሜታ ተግባራዊ የመሆን ስልት ጥናትና እውቀት፤ ተግባራዊ ሳይንስ።

**ቴፕ (ቴፕሪኮርደር)** ስ በቴፕ ክር ላይ ድምፅን ለመቅረፅና የተቀረፀውንም ድምፅ መልሶ ለመስማት የሚያገለግል መሳሪያ።

**የቴፕ ክር** ስ ማግኔትነት ያለው፥ በቴፕ አማካኝነት ድምፅን እየቀረፀ የሚያስቀር፥ ስስ የሆነ የፕላስቲክ ጥብጣብ።

**ት** የ"ተ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**ትሁት** ቅ ቅን፥ ታዛዥ፥ ሰው አክባሪ።

**ትህትና** ስ ቅንነት፥ ታዛዥነት፥ ሰው አክባሪነት፤ ራስንና የራስን ዝቅ አድራጊነት።

**ትህርምት** ስ መጥፎ የተባሉ ድርጊቶችን ከመፈፀም ራስን የመቆጣጠር ሃይማኖታዊ ተግባር።

**ትህትና** "ትሁት" ስር ተመ.

**ትኋን(ቱኻን)** ስ እንደቁንጫና ቅማል የሰውን ደም በመምጠጥ የሚኖር የቤት ውስጥ ተባይ።

**ትኋናም** ቅ (ስድብ) ትኋን ያለበት ወይም የበዛበት።

**ትላም** "ተላ" ስር ተመ.

**ትላበራ** ዝ.ከ.

**ትላንት** "ትናንት"ን ተመ.

**ትል** "ተላ" ስር ተመ.

**ትልልቅ** "ተለቀ" ስር ተመ.

**ትልም** "ተለመ" ስር ተመ.

**ትልቅ** "ተለቀ" ስር ተመ.

**ትልታይ** "ተለተለ" ስር ተመ.

**ትልትላት** ዝ.ከ.

**ትልትል** ዝ.ከ.

**ትልአበራ** "ተላ" ስር "ትላበራ" ን ተመ.

**ትሙን** "ተሙን" ን ተመ.

**ትምህርት** "*መሃረ" ስር ተመ.

**ትምቡሽ**

**ትምቡሼ(ትንቡሼ)** ቅ ድንቡሼ፥ ወፍራም።

**ትምቡሽ አለ** ግ ድቡልቡል አለ፥ ወፈረ።

**ትምባሆ (ትንባሆ)** ስ ርጥቡን ቅጠል ለጥልጠው በአፍ የሚይዙት ወይም አድርቀውና አሽተው በሲጋራ መልክ ጢሱን የሚምጉት ሱስ የሚያሲዝ እፅ::
**ትምባሂም** ቅ (ስድብ) ትምባሆ የሚያጤስ፥ የትምባሆ ሱስ ያለበት::
**ትምትም "ተመተመ"** ስር ተመ.
**ትምክ**
**ትምክ አለ** ግ ስርጉድ፥ ስምጥ አለ፥ ላላ::
**ትምክ ትምክ አለ** ግ ሲነኩት ስምጥ ስምጥ፥ ስርጉድ ስርጉድ አለ::
**ትምክህተኛ "*መካ"** ስር ተመ.
**ትምክህት** ዝ.ከ.
**ትረባ "ተረበ"** ስር ተመ.
**ትሩፋት "ተረፈ"** ስር ተመ.
**ትራምፔት** ስ ጥሩምባ የሚመስል በትንፋሽ የሚሰራ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ(ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)::
**ትራስ "*ተራሰ"** ስር ተመ.
**ትራስጌ** ዝ.ከ.
**ትራንስፎርመር** ስ 1. በኤሌክትሪክ ሃይል በሚሰሩ በሬዲዮ፥ በቴፕሪኮርደር፥ በቴሌቪዥን፥... ውስጥ የሚገኝ የኤሌክትሪክ ሃይልን እየመጠነ የሚያሰራጭ መሳሪያ:: 2. የኤሌክትሪክ ኃን::
**ትራንስፖርት** ስ መጓጓዣ መንገድ ወይም መኪና፥ አውሮፕላን፥... የመሳሰለው መገልገያ::
**ትራክተር** ስ የእርሻ መኪና::
**ትራኮማ** ስ የሚያቃጥልና የሚያሳክክ ተላላፊ የአይን በሽታ፤ አይነ ማዝ::
**ትራጀዲ** ስ መድረኩ በሃዘን ድባብ የተሞላ ሆኖ በዋና ገፀባህርዩ ውድቀት ወይም ሞት የሚያበቃ የትያትር አይነት::
**ትራፊ "ተረፈ"** ስር ተመ.
**ትራፊክ** ስ 1. በመንገድ ላይ የሚታየው የሰዎች፥ የተሽከርካሪዎች፥... እንቅስቃሴ ወይም በመንገድ ላይ የሚንቀሳቀሱ ሰዎች፥ ተሽከርካሪዎች፥... በአንድነት የሚጠሩበት ስም:: 2. አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብ የሚጠይቀውን ስነስርአት ማሟላታቸውን የሚከታተል ፖሊስ፤ ትራፊክ ፖሊስ ::
**የትራፊክ ህግ/ደንብ** ስ ስለተሽከርካሪዎች ደህንነት፥ ስለአሽከርካሪዎችና የመንገድ ስነስርአትን የሚመለከት በትራፊክ ፅ/ቤት የወጣ ወይም የተዘጋጀ መመሪያ፥ ደንብ፥ ህግ::
**የትራፊክ መብራት** ስ መስቀለኛ መንገድ ባለበት አካባቢ ተሽከርካሪዎች ተራቸውን ጠብቀው እንዲቆሙ ወይም እንዲሄዱ ምልክት የሚያሳይ ባለቀለም (አረንጓዴ፥ ቢጫ፥ ቀይ) መብራት::
**ትር**
**ትርታ** ስ ምት ንዝረት (ብዙውን ጊዜ የልብ)::
**ትር ትር አለ** ግ ድው ድው አለ፥ መታ ነዘረ (ብዙውን ጊዜ ልብ)::
**ትርምስ "*ተራመሰ"** ስር ተመ.
**ትርሽም**
**ትርሽም አለ** ግ ተሰበረ::
**ትርሽም አደረገ** ግ ሰበረ::
**ትርታ "ትር"** ስር ተመ.
**ትርታሮ "ተረተረ"** ስር ተመ.
**ትርትር** ዝ.ከ.
**ትርንጎ** ስ መጠኑ ከፓፓዬ አነስ የሚል፥ ሽፋኑ ሳሳ፥ አካሉ ጠንከር ያለ፥ ጥሩ መአዛ ያለውና የሚበላ ፍሬ የሚያፈራ ተክል፤ ፍሬውም ትርንጎ ይባላል::
**ትርኢት** ስ እንደ ሙዚቃ፥ ትያትር፥ አክሮባት፥... ያለ ለህዝብ ቀርቦ የሚታይ ዝግጅት::
**ትርኪምርኪ** ስ 1. ቅራቅንቦ፥ ኮተት:: 2. (ዘይ.) የማይረባ ነገር::
**ትርክም**
**ትርክምክም** ቅ የማይረቡ እቃዎች ስብስብ::
**ትርኳሽ "ተረኮሰ"** ስር ተመ.
**ትርጁማን** ስ በአንድ ቋንቋ የተነገረን ነገር በሌላ ቋንቋ ለውጦ የሚናገር፤ አስተርጓሚ::
**ትርጉም "ተረጎመ"** ስር ተመ.
**ትርግ**
**ትርግታ** ስ ምት፥ ንዝረት (የልብ፥ የእርግብግቢት፥ የደምስር፥...)::
**ትርግ ትርግ አለ** ግ መታ፥ ተርገበገበ (ልብ፥ እርግብግቢት፥...)::
**ትርጓሜ "ተረጎመ"** ስር ተመ.
**ትርፍ "ተረፈ"** ስር ተመ.
**ትስብእት** ስ (ክር.) ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ የለበሰበት ቀን (መጋቢት 29)::
**ትቢት "ተበተ"** ስር ተመ.
**ትቢያ** ስ ደቃቅ አፈር፥ አቧራ::
**ትብ "ተባ"** ስር ተመ.
**ትብትብ "ተበተበ"** ስር ተመ.
**ትብትብ** ዝ.ከ.
**ትት "ታታ[1]"** ስር ተመ.

**ትቸት** **"ተቸ"** ስር ተመ.
**ትናንሽ** **"አነሰ"** ስር ተመ.
**ትናንት(ትላንት÷ትናንትና)** ስ. 1. ከዛሬው ቀን በፊት የነበረው÷ ያለፈው ቀን:: *ትናንትናን የማስታውስበት ብዙ የሚገርም ነገር አጋጥሞኛል::* 2. (ዘይ.) ከዚህ በፊት÷ ባለፈው ዘመን ወይም ያለፈው ዘመን:: *ትናንት ህዝብን ሲበድሉ የነበሩ ባለስልጣናት...*
**ከትናንት ወዲያ(በስቲያ)**ከትናንት በፊት የነበረው ቀን::
**ትናጋ(ትናግ)** ስ ከአፍ ወደ ጉሮሮ በሚወስደው መስመር ላይ ከላንቃ መዳረሻ አካባቢ የሚገኝ የአፍ ውስጥ የላይኛው ክፍል(ስእሉን አፍ ስር ተመ.)::
**የትናጋ ድምፅ** ስ (ስነል.) እንደ ቀ÷ ገ÷ ከ ያለ የምላስን የሗለኛ ክፍል ከትናጋ ጋር በማገናኘት የሚፈጠር የንግግር ድምፅ::
**ትን**
**ትንታ** ስ የሚያፍን÷ የሚያስነጥስ÷... ወደ ሰርን ወይም ወደ አየር ቧንቧ የገባ የምግብ እኛኪ ወይም የመጠጥ ፍንጣቂ የሚያስከትለው የማፈን÷የማስነጠስ÷...ሁኔታ ::
**ትን አለ** ግ የምግብ እኛኪ ወይም የመጠጥ ፍንጣቂ ወደአየር ቧንቧ ወይም ወደ ሰርን በመሄድ አፍንጫን÷ ጉሮሮን ዘጋ ወይም አስነጠሰ÷ አሳለ::
**ትንሳኤ** ስ 1.(ክር.) ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከመቃብር የተነሳበት እለት፣ ፋሲካ:: 2. ከሞት ወይም ከውድቀት በሗላ መነሳት::
**ትንሳኤ ሙታን** ስ (ክር.) በአጠቃላይ ሙታን ሁሉ የሚነሱበት ቀን፣ ዳግም ምፅአት::
**ትንሽ** **"አነሰ"** ስር ተመ.
**ትንቡሼ** **"ትምቡሽ"** ስር **"ትምቡሼ"** ን ተመ.
**ትንቢተኛ** **"ተነበየ"** ስር ተመ.
**ትንቢት** ዝ.ክ.
**ትንባሆ** **"ትምባሆ"** ን ተመ.
**ትንተና** **"ተነተነ"** ስር ተመ.
**ትንታ** **"ትን"** ስር ተመ.
**ትንታኔ** **"ተነተነ"** ስር ተመ.
**ትንታግ** **"ተገተገ[1]"** ስር ተመ.
**ትንኝ** ስ ብዙውን ጊዜ እርጥበት ወይም ፈሳሽ ነገር ባለበት አካባቢ የምትገኝ አነስተኛ የሆነች በራሪ ነፍሳት::
**ትንኩሽት** **"ተነከሰ"** ስር ተመ.
**ትንኮሳ** ዝ.ክ.
**ትንግርተኛ** **"ነገረ"** ስር ተመ.
**ትንግርት** ዝ.ክ.
**ትንፋሽ** **"ተነፈሰ"** ስር ተመ.
**ትንፋገን** **"ተነፈገ[1]"** ስር **"ትንፋግ"** ን ተመ.
**ትንፋግ** **"ተነፈገ[1]"** ስር ተመ.
**ትእምርት** ስ ምልክት (አንድን ሰው÷ ሃሳብ÷ አላማ÷... የሚጠቁም)::
**ትእምርተ መስቀል** ስ የመስቀል ምልክት::
**ትእምርተ ስላቅ** ስ የተባሊው ነገር ስላቅ መሆኑን ለማሳየት የሚደረግ ምልክት:: ምልክቱም / ነው::
**ትእምርተ ጥቅስ** ስ ሌላ ሰው የተናገረው÷የፃፈው÷... መሆኑን ለማመልከት ከሚጠቀሰው ነገር መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በስተ አናት በኩል የሚደረግ ምልክት:: ምልክቱም " " ነው::
**ትእቢተኛ** **"ተበተ"** ስር ተመ.
**ትእቢት** ዝ.ክ.
**ትእዛዝ** **"አዘዘ"** ስር ተመ.
**ትእግስተኛ** **"ታገሰ"** ስር ተመ.
**ትእግስት** ዝ.ክ.
**ትከሻ** ስ 1. ከአንገት መቆሚያ እስከ ክንድ መብቀያ (መጋጠሚያ) ድረስ ያለው የሰውነት ክፍል (ስእሉን "ሰውነት" ስር ተመ.):: 2. (ዘይ.) እድል::
**በ ___ ትከሻ** ቡእርዳታ:: በሰው ትከሻ ነው እዚህ የደረሰው::
**ትከሻ ሰጠ/አሳየ** ታበየ÷ ንቀት አሳየ÷ አልታዘዝ አለ::
**ትከሻ ወረደ** እስክስታ ወረደ÷ እስክስታ መታ÷ እስክስ አለ::
**ትከሻ የለውም** እድል የለውም ወይም እድሉ ጥሩ አይደለም::
**ትኩረት** **"ተኮረ"** ስር ተመ.
**ትኩሳት** **"ተኮሰ"** ስር ተመ.
**ትኩስ** ዝ.ክ.
**ትካዜ** **"ተከዘ"** ስር ተመ.
**ትክ** **"ተካ"** ስር ተመ.
**ትክ**
**ትክ አለ** ግ ትኩር አለ÷ አይኑን አንድ ቦታ ተከለ::
**ትክ ብሎ ተመለከተ** ትኩር ብሎ ተመለከተ÷ አስተዋለ::
**ትክል** **"ተከለ"** ስር ተመ.
**ትክትክ** **"ተከተከ"** ስር ተመ.

**ትኽትኽ** ስ ብዙውን ጊዜ ህፃናትን የሚያጠቃ ቶሎ ቶሎ የሚያስል በሽታ::
**ትክክለኛ** **"አከለ"** ስር ተመ.
**ትክክል** ዝ.ከ.
**ትውልድ** **"ወለደ"** ስር ተመ.
**ትውር**
**ትውር እንዳትል** ድርሽ፥ ዝር እንዳትል:: *ምንም ቢቸግርህ እነዚያ ከፉዎች ወዳሉበት አካባቢ ትውር እንዳትል::*
**ትውስታ** **"ታወሰ"** ስር ተመ.
**ትውከት** **"*አወከ"** ስር ተመ.
**ትውውቅ** **"አወቀ"** ስር ተመ.
**ትዛዝ** **"አዘዘ"** ስር ተመ.
**ትዝ**
**ትዝታ** ስ 1.ትውስታ(የናፍቆት፥ የፍቅር፥...):: 2. የሙዚቃ ዜማ ቅኝት አይነት::
**ትዝ አለ** ግ ታወሰ፥ ታሰበ::
**ትዝብት** **"ታዘበ"** ስር ተመ.
**ትያትር** ስ በልብወለድ የድርሰት ዘዴ ተዘጋጅቶና ተቀናብሮ በመድረክ ላይ ለህዝብ የሚታይ የስነፅሁፍ ዘርፍ፤ ተውኔት::
**ትያትር ቤት** ስ ትያትር የሚታይበት አዳራሽ::
**ትይዩ** **"አየ"** ስር ተመ.
**ትዳር** ስ 1. ወንድና ሴት ባልና ሚስት ሆነው እንዲኖሩ የሚያስችላቸው፥ በቃልኪዳን የታሰረና ህጋዊ የሆነ ጥምረት፥ አንድነት:: 2. የባልና የሚስት የአንድነት ኑሮ፤ ጋብቻ:: 3. ቤት፥ ንብረት:: 4. ባል ወይም ሚስት::
**ባለትዳር** ያገባ፥ ትዳር ያለው::
**ትዳሩ ሞቀ** ትዳሩ ተመቻቸ፥ ኑሮው ተሟላለት::
**ትዳሩ ፈረሰ** ከትዳር ጓደኛው ተለያየ::
**ትዳር ያዘ/ያዘች** ሚስት አገባ/ባል አገባች::
**የትዳር ጓደኛ** ስ ሚስት ወይም ባል::
**ትጉህ** **"ተጋ"** ስር ተመ.
**ትጋት** ዝ.ከ.
**ትግ**[1]
**ትግ አለ** ግ አባራ፥ ቆመ (ዝናብ)::
**ትግ**[2]
**ትግ ትግ አለ** ግ በቁጣ ወይም በንዴት ቶሎ ቶሎ ተናገረ፤ ግንፍል ግንፍል አለ::
**ትግል** **"ታገለ"** ስር ተመ.
**ትጥቅ** **"ታጠቀ"**ስር ተመ.
**ትፋታም** **"ተፋ"**ስር ተመ.
**ትፋት** ዝ.ከ.
**ትፍ** **"እንትፍ"** ን ተመ.
**ትፍትፋት** **"ተፈተፈ"** ስር ተመ.
**ትፍትፍ** ዝ.ከ.
**ቶ** የ"ተ" ፊደል ሳብእ ዘር::
**ቶሎ** ተው.ግ ወዲያው፥ በፍጥነት፥ በአስቸኳይ::
**ቶሎ በል** ፍጠን፥ ቀልጠፍ በል::
**ቶሎ ቶሎ** ተው.ግ. 1. ወዲያው ወዲያው፥ እያከታተለ:: *ቶሎ ቶሎ ያመዋል::* 2 .በፍጥነት:: *ቶሎ ቶሎ ይራመዳል::*
**ቶሎ ቶሎ አለ** ግ ፈጠነ፥ ቸኮለ::
**ቶረበ** ግ አራርቆ በመውጋት በክር አያያዘ፥ ተራ ስፌት ሰፋ፥ ወሰወሰ፥ ሸደሸደ::
**ቶራ ፈረስ** ስ ጋማና ጭራ ያለው ባለሁለት ቀንድ የዱር እንስሳ(ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)::
***ቶሰቶሰ**
**ቶስቷሳ** ቅ 1. አርፎ የማይቀመጥ ሰክሏካ:: 2. ወሬኛ:: 3. ፈሪ::
**ተንቶሰቶሰ** ግ 1. ወዲያ ወዲህ አለ፥ አውደለደለ:: 2. በጣም ፈራ::
**አቶሰቶሰ** ግ ከስር ከስር ተከተለ፥ ወዲያ ወዲህ አለ (ለወሬ፥ ለሰብቅ፥...)::
**አቶስቷሽ** ቅ ሰብቀኛ፥ አቶክቷኪ::
**ቶታን** ስ በመፃህፍት ጥራዝ ራስጌና ግርጌ ላይ እንደ ክፈፍ ወይም እንደጌጥ ተደርጎ የሚሰፋ ከብራና ወይም ከባህር አረብ ትልታይ የሚሰራ ጉንጉን::
**ቶኒክ** ስ ከጥራጥሬና ከፍራፍሬ የሚሰራ ውሃ የሚመስል የመጠጥ አይነት::
**ቶንሲል** **"ቅምሆ"** ን ተመ.
**ቶፋ**[1] ስ 1.እንደማሰሮ የሚያገለግልና ማሰሮ የሚመስል የሸክላ እቃ(ስእሉን የሸክላ እቃ ስር ተመ.):: 2. (ዘይ.) መልከ ጥፉ::
**ቶፍቷፋ** ቅ ወፍራምና ውስጠ ልል፤ ዶፈዶፍ::
**ቶፋ**[2] ስ የሌላን ሰው ስራ ወክሎ የሚሰራ (ለምሳሌ ቄስን ወክሎ የሚቀድስ ወይም ባለርስትን ወክሎ የሚገብር)::
**ቷ**[1] የ"ተ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::
**ቷ**[2]
**ቷ አለ** ግ 1. ጧ አለ፥ ፈነዳ፥ ተበጠሰ:: 2. ፈጥኖ ወጣ፥ ፈሰሰ (ደም):: 3. ቦግ አለ፥ በራ::
**ተንቷቷ** ግ ተንጧጧ፥ ተከታታይ የፍንዳታ ድምፅ ሰጠ::
**አንቷቷ** ግ አንጧጧ፥ አከታትሎ ተኮሰ፥ አፈነዳ::

# ቸ

**ቸ** ከ"ተ" ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)::

**ቸለሰ** ግ 1. አብዝቶ ጨመረ:: 2. ከነበለ፥ አፈለሰ፥ ደፋ (ፈሳሽን)::

**ቸል**

**ቸልታ** ስ 1. ምንቸገረኝነት፥ ለምንም ነገር ያለመጨነቅ:: 2. ተገቢ ምላሽ ለመስጠት ያለመፍጠን፥ ያለመፈለግ ስሜት:: 3. ልግመት::

**በቸልታ** ተው.ግ. በመናቅና በመተው፥ በምንቸገረኝነት፥ ምንም አይነት እርምጃ ባለመውሰድ:: *የተቃጣብንን ጥቃት በቸልታ ላናልፈውም::*

**ቸልተኛ** ቅ 1. አንድን ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ የማይፈፅም፥ ግደየለሽ፥ ዳተኛ:: 2. ልግመኛ::

**ቸልተኝነት** ስ የምንቸገረኝነት፥ የግዴለሽነት ስሜት::

**ቸል አለ (ችላ አለ)** ግ ተወት አደረገ፥ ንቆ ተወ፥ ትኩረት ሳይሰጥ ቀረ፥ ለመፈፀም ወይም ለማከናወን ዳተኛ ሆነ::

**ችላ ባይ** ቅ ቸልተኛ፥ ግዴለሽነት የሚያበዛ::

**ቸመቸመ** ግ 1. አደለደመ፥ አደነዘ፥ ቸረቸመ:: 2. ደመደመ፥ አስተካከለ (አባጣ ጎባጣ የሆነውን):: 3. በመደዳ አሰለፈ፥ ገጠገጠ::

**ቸምቻማ** ቅ ዶልዷማ፥ ስለቱ የደነዘ::

**ችምችም**1. የተቸመቸመ፥ የተጠጋጋ:: *ችምችም ያለ መንደር::* 2. ተጠግግቶና በቁመት ተስተካክሉ የበቀለ::

**ተቸመቸመ** ግ 1. በብዛት እጅብ ብሎ፥ ተጠጋግቶ በቀለ፥ ተቀመጠ፥... ተገጠገጠ:: 2. ዶለዶመ::

**ቸረ** ግ ለገሰ፥ ሰጠ::

**ቸር** ቅ 1. ለጋስ፥ ደግ:: 2. በጎ፥ ደህና፥ መልካም:: *ቸር ያውልህ/ ቸር ያሰማህ::*

**ቸር ወሬ** የሚያሳዝን ነገር የሌለበት፥ ጥሩ የሆነ፥ የሚያስደስት ወሬ::

**ቸርነት** ስ ርህሩህነት፥ ለጋስነት፥ ደግነት::

**ችሮታ** ስ ስጦታ፥ ልገሳ::

***ቸረረ**

**ቸረር አለ (ቸር አለ)** ግ እመር አለ፥ ተወርውሮ አለፈ፥ ዘለለ፥ ተስፈነጠረ::

**ተንቻረረ** ግ ተወረወረ፥ ተስፈነጠረ::

**አንቻረረ** ግ ወረወረ፥ አስፈነጠረ::

**ቸረቸመ**[1] ግ አደለደመ፥ አደነዘ፥ ቸመቸመ::

**ችርችም** ቅ ስለቱ የደነዘ፥ ዱልዱም::

**ቸረቸመ**[2] ግ በአፉ ሙሉ ቃመ (ጥሬን፥ ቆሎ፥...)::

**ቸረቸረ** ግ 1. እቃን ወይም ሸቀጥን በጅምላ ሳይሆን እየከፋፈለ በትንሽ በትንሹ ሸጠ፥ ሸቀጠ፥ ነገደ:: 2. ነዛ፥ አወራ:: *ጉራውን ይቸረችራል::*

**ችርቻሪ** ስ እቃን ወይም ሸቀጥን በጅምላ ሳይሆን፥ በክፍልፋይ መልክ በትንሽ በትንሹ ለተጠቃሚ የሚሸጥ ነጋዴ::

**ችርቻሪ** ቅ ጅምላ ያልሆነ፥ በነጠላ ወይም በአነስተኛ መጠን የተገዛ(ሸቀጥ)::

**ችርቻሮ** ስ የሸቀጥ እቃ በጅምላ ሳይሆን በነጠላ ወይም በአነስተኛ መጠን ለተጠቃሚ የሚቀርብበት የንግድ አይነት::

**ችርቻሮ ነጋዴ** ስ ሸቀጥን በችርቻሮ የሚሸጥ ነጋዴ::

***ቸረቸፈ** ግ አደለደመ፥ ቸረቸመ::

**ችርችፍ** ቅ ዱልዱም፥ ችርችም::

**ተቸረቸፈ** ግ ስለቱን አጣ፥ ዶለዶመ::

**ቸረፈፈ**

**ችርፍፍ አለ** ግ ሞላ፥ ተንቸረፈፈ::

**ተንቸረፈፈ** ግ ሞላ አለ፥ ተንደረበበ፥ ስፍር ሊሆን ትንሽ ቀረው::

**አንቸረፈፈ** ግ ሞላ አደረገ፥ አንደረበበ::

**ቸር** "ቸረ" ስር ተመ.

**ችርቻሪ** "ቸረቸረ" ስር ተመ.

**ቸርነት** "ቸረ"ስር ተመ.

***ቸሰሰ**

**ቸሰስ(ቸስ)አለ** ግ 1. ውሃ በእሳት ወይም በጋለ ብረት ላይ ሲፈስ የሚሰጠውን አይነት ድምፅ ሰጠ:: 2. በረደ፥ ቀዘቀዘ (የጋለ ነገር በውሃ)::

**ቸሰስ(ቸስ) አደረገ** ግ 1. ቸስ የሚል ድምፅ እንዲሰጥ አደረገ:: 2. አበረደ፥ አቀዘቀዘ:: 3. አረካ (ውሃ ጥምን)::

**ቸበቸበ** ግ 1. በዱላ፥ በዘንግ ወቃ (እህልን በአውድማ ላይ):: 2. ሳይጎዳ በትንሹ መታ መታ አደረገ፥ ገረፈ:: 3. በብዛት ሸጠ፥ ሸቀጠ::

**ቸብቸቦ** ስ 1. ከአንገት በላይ ያለ አካል ከነቁንዳላው ወይም ከነፀጉሩ:: 2. ፍጥነት ያለው የቤተክርስቲያን ወረብ ወይም የከበሮ ምት አይነት::

**ቸብ አደረገ** ግ1. በማይጎዳ ሁኔታ በቀስታ መታ አደረገ:: 2. ሸጠ::

**ቸብ ቸብ አደረገ** ግ 1.መታ መታ

አደረገ:: 2. አጨበጨበ::

**ተቸበቸበ** ግ 1. ተወቃ:: 2. ተገረፈ:: 3. በብዛት ተሸጠ::

**ችነከረ** ግ 1. በችንካር ወይም በምስማር መታ፣ ጠረቀ፣ አጣበቀ፣ ሰፋ፣ እያያዘ:: 2. ቀረቀረ::

**ችንካር** ስ 1. ለመዝጊያነት እንዲያገለግሉ በተፈለፈሉ የሳንቃ ቀዳዳዎች ውስጥ የሚሰካ የእንጨት ቅርቃር:: 2.ብረት ነክ የሆኑ ነገሮችን ለማያያዝ የሚረዳ እንደ ሙጫ ያለ መጣበቅ:: 3. ከብረታ ብረት የሚሰራ የድሮ የምስማር አይነት::

**ተቸነከረ** ግ 1. ተጣበቀ፣ ተሰፋ፣ተያያዘ፣ ተወጋ (በምስማር ወይም በችንካር):: 2. ተቀረቀረ::

**ችነፈር** ስ የተላላፊ በሽታ አይነት፤ ወረርሽኝ፤ ተስቦ ፣ እልቂት፣ መቅሰፍት::

**ችንቧ**

**ችንቧ አለ** ግ (ግዙፍ አካል) ከውሃ፣ ከባህር ውስጥ ተወርውሮ ሲገባ ቦጭ የሚል ድምፅ ተሰማ::

**ችንቧ ችንቧ አለ** ግ ውሃ ውስጥ ገብቶ ተንቦጫረቀ::

**ችንች** ስ ድድ:: *በቡጢ ችንቹን ብሎት ሄደ::*

**ችከ** ግ 1. አደፈ፣ ቆሸሸ:: 2. ሙዝዝ አለ፣ መነቸከ፣ አልለቅ፣ አልተው አለ::

**ችክ** ስ ጥርስ ላይ የሚጋገር እድፍ፣ ቆሻሻ፣ ልማም::

**ችኮ** ቅ ከያዘ የማይለቅ፣ መንቻካ፣ ሞዛዛ::

**ችክ አለ** ግ 1. በጣም ከመቆሸሹ የተነሳ ቢያጥቡት የማይለቅ ሆነ:: 2. አልለቅ አለ፣ ቸከ:: 3. አልተው አለ፣ ተሟዘዘ፣ ድርቅ አለ::

**አቸከ** ግ በጣም አሳደፈ፣ አቆሸሸ::

**ቸከለ** ግ ተከለ(ችካልን እመሬት ላይ)::

**ችካል** ስ መሬት ላይ የሚተከል ብረት፣ እንጨት፣ ካስማ::

**ተቸከለ** ግ መሬት ላይ ተተከለ::

**ቸከቸከ** ግ 1. መላልሶ ወጋ፣ ጨቀጨቀ:: 2.ነቀሰ፣ ጠቀጠቀ:: 3. አጠጋግቶ፣ አቀራርቦ ተከለ (አትክልትን):: 4. ነዘነዘ፣ ነተረከ፣ ዘበዘበ:: 5. ጥቅጥቅ አድርጎ አብዝቶ ፃፈ::

**ቸክቻካ** ቅ ነዝናዛ::

**ተቸከቸከ** ግ ጥቅጥቅ ያለ ሆነ (የአተካከል፣ የአፃፃፍ)::

***ቸከቸከ**

**ተንቸከቸከ** ግ ተንፈቀፈቀ፣ ተንተከተከ፣ በሰለ (ለምሳሌ ወጥ)::

**አንቸከቸከ** ግ አንፈቀፈቀ፣ አንተከተከ፣ አበሰለ (ለምሳሌ ወጥን)::

**ቸክቻካ** "ቸከቸከ"ስር ተመ.

**ቸኮለ** ግ 1.ተጣደፈ:: 2. ፈጠነ::

**ችኩል** ቅ ርጋታ የሌለው፣ የሚጣደፍ፣ ረጋ ብሎ አስቦ የማይሰራ::

**ችኮላ** ስ ጥድፊያ::

**ተቻኮለ** ግ 1.ተጣደፈ:: 2. ፈጠነ::

**አቻኮለ** ግ አጣደፈ::

**አስቸኮለ** ዝ.ከ.

**አስቸኳይ** ቅ አጣዳፊ፣ ጊዜ ወይም ፋታ የማይሰጥ::

**የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ** ስ በጦርነት ወይም ከባድ አደጋ ምክንያት በመላ ሃገሪቱ ወይም በተወሰነ አካባቢ ጊዜያዊ ህግን ለመደንገግ የሚያስገድድ ሁኔታ::

**ቸገረ** ግ 1. ታጣ፣ ጠፋ:: *መቼ ገንዘብ ቸገረ:* 2. ጨነቀ፣ ጠበበ:: 3. ተሳነ፣ አቃተ::

**ችጋር** ስ እጦት፣ ረሃብ::

**ችጋራም** ቅ 1.(የን.አነ.) ያጣ የነጣ፣ ምንም የሌለው ደሃ:: 2. (ስድብ) ገብጋባ፣ ስስታም፤ በልቶ የማይጠግብ::

**ችግር** ስ 1. እክል፣ እንቅፋት፣ ሳንካ:: 2. መከራ፣ ጭንቅ፣ ፈተና:: 3. አዳጋች ነገር:: 4. ድህነት:: 5. እጦት:: *በመለዋወጫ እቃ ችግር ስራው አልተሰራም::*

**ችግሩን ተወጣ** ችግሩን ተቋቋሞ አሳለፈ::

**ከችግር ወጣ** ከችግር፣ ከጭንቅ ተላቀቀ፣ ተገላገለ::

**ችግረኛ** ቅ1. ያጣ፣ ርዳታ ፈላጊ:: ስ 2. ደሃ::

**ተቸገረ** ግ 1. አጣ (የሚፈልገውን ነገር):: 2. ደሀየ:: 3. መከራ፣ ጭንቅ ደረሰበት:: 4. ተጨነቀ፣ ተጠበበ:: 5 አቃተው፣ ተሳነው::

**አስቸገረ** ግ 1. አቃተ፣ አሸነፈ፣ አዳገተ:: 2. አወከ:: 3. አንድ ነገር እንዲደረግለት፣ እንዲሰራለት፣ እንዲፈፀምለት ጠየቀ፣ ወተወተ::

**አስቸጋሪ** ቅ 1. ለመስራት፣ ለመፈፀም፣ ወይም ለመገልገል የሚያዳግት፣ የሚያቅት:: 2. አዋኪ፣ ጠባየ መጥፎ::

**ቸገነ** ግ የእፅዋትን ፍሬ ተቆፍሮ በተሰናዳ መሬት ላይ በመዝራት እንዲበቅል፣ እንዲፈላ አደረገ፤ ችግኝ አዘጋጀ::

**ችግኝ** ስ አዲስ የበቀለ የእፅዋት ፍል::

***ቸፈረረ**

**ቸፍራራ** ቅ ጨፍራራ::

**ተንቸፈረረ** ግ ደረቀ፣ ከችች አለ፣ ተንጨፈረረ::

**አንቸፈረረ** ግ አደረቀ፣ ከችች አደረገ፣

እንጨፈረረ::

**ቾፈቾፈ** ግ 1.ተፈተፈ፥ ብዙ ቦታ ላይ መላልሶ ወጋ፥ ጨቀጨቀ:: 2. አካፋ::

**ቾፈቾፍ** ስ የማያቋርጥ ካፊያ::

**ቾፍቻፋ** ቅ ጨቅጫቃ::

**ችፍቻፊ** ስ ቁርጥራጭ፥ ፍቅፋቂ (የእንጨት)::

**ችፍ ችፍ አለ** ግ ያለማቋረጥ የካፊያ ዝናብ ዘነበ::

**ቾፈገ** ግ ጠቀጠቀ፥ እጅብ አደረገ፥ ጨፈቀ::

**ችፍግ** ቅ እጅብ ያለ፥ ጭፍቅ::

**ችፍግ አለ** ግ አንድ ላይ እጅብ ብሎ በቀለ::

**ቾፍራራ** "*ቾፈረረ" ስር ተመ.

**ቾፍቻፋ** "ቾፈቾፈ" ስር ተመ.

**ቹ** የ"ቾ" ፊደል ካእብ ዘር::

**ቺ** የ"ቾ" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ቺንጊያ** ስ ለሞተር ማዞሪያ የሚያገለግልና ከላስቲክ፥ ከሸራ፥... የተሰራ ክብ ጥብጣብ::

**ቻ** የ "ቾ" ፊደል ራብእ ዘር::

**ቻለ** ግ 1. አንድ ነገር ለማድረግ፥ ለማከናወን፥... አቅም አገኘ ወይም ብቁ ሆነ:: *ሃምሳ ኪሎ ጆኆ ለማንሳት ቻለ ለቤቱ አስር ሰው መያዝ ቻለ::* 2. እውቀት፥ ችሎታ አገኘ፤ አወቀ:: *ቋንቋውን መናገር ቻለ / አማርኛ ይችላል / መኪና መንዳት ቻለ::* 3. መብት አገኘ፥ ኖረው:: *መስፈርቱን የሚያሟሉት በሙሉ መምረጥና መመረጥ ይችላሉ::* 4. በቂ ሆነ:: *ገንዘቡ ሙሉ ልብስ መግዛት ቻለ::* 5. ከፈለ፥ ሸፈነ(ወጪን):: *ዩኒቨርሲቲው መኝታና ምግብህን ይችላል::* 6. ታገሰ:: 7. ተቋቋመ:: *ብርዱን አልቻልኩትም /ጫማው አደጋ ይችላል::*

**ቻይ** ቅ 1. ታጋሽ:: 2.አደጋ ወይም አስቸጋሪ ሁኔታን የሚቋቋም::

**ችሎት** ስ የዳኝነት ስራ የሚካሄድበት ቦታ፥ ሸንጎ::

**ችሎት አስቻለ** ዳኝነት ለማየት ተሰየመ::

**ችሎታ** ስ 1.አቅም:: 2. አንድን ነገር የማካሄድ፥ የመስራት እውቀት:: 3. ስልጣን::

**ተቻለ** ግ አንድን ነገር ለማድረግ፥ ለማከናወን፥...አቅም፥ መብት፥ ፈቃድ፥...ተገኘ::

**በተቻለ መጠን** የአቅምን ያህል በመሞከር ወይም እንደምንም:: *በተቻለ መጠን ነገ ለመመለስ ሞክር::*

**አልተቻለም** 1. አዳጋች ሆነ፥ አቃተ:: 2. አልተሳካም::

**የተቻለው ነው** ሃብታም ነው::

**የተቻለውን ያህል** አቅም የፈቀደውን ያህል::

**ይቻላል** 1. (ማድረግ፥ ማካሄድ፥ መሆን፥...) የተፈቀደ ነው፥ ክልክል የለውም:: 2. (ለማድረግ፥ ለማካሄድ፥ ለመሆን፥...) እድሉ፥ አቅሙ አለ:: *ከዚያ በሂላ መሃንዲስ ለመሆን ይቻላል::*


**አይቻልም** 1. በጣም ሃይለኛ፥ አስቸጋሪ ነው፤ ሊቋቋሙት ያዳግታል:: 2. አይሆንም፥ አይደረግም፥ አይፈቀድም::

**ተቻቻለ** ግ 1. (ክፍያ፥ ወጪ፥ ኪሳራ፥ እዳ፥...) ተጣጣ፥ ተብቃቃ፥ ተካካሰ:: 2. አንዱ ሌላውን ታግሶ፥ እርስ በርስ ተከባብሮ፥ ተፈቃቅዶ አብሮ ኖረ::

**አቻቻለ** ግ አጣጣ፥ አብቃቃ (እዳን፥ ክፍያን)::

**አስቻለ** ግ 1. አበቃ፥ ብቁ አደረገ፥ ረዳ:: 2. ትእግስት ሰጠ:: 3. ችሎት ላይ ተቀመጠ፥ ተሰየመ (ለመዳኘት ወይም በዳኝነት ለመመልከት)::

**ቻርኔላ** ስ ተካፋች በሆነ ኮት፥ ቦርሳ፥ ሻንጣ፥...ላይ የሚሰፋና እርስ በርሱ ሊቆላለፍ የሚችል መዝጊያና መክፈቻ፤ ዚፕ እየተባለም ይጠራል::



ቻርኔላ

**ቻቻ**

**ቻቻታ** ስ ጫጫታ፥ ውካታ::

**ተንቻቻ** ግ ተንጫጫ::

**አንቻቻ** ግ አንጫጫ::

**ቻይ** "ቻለ" ስር ተመ.

**ቼ**[1] የ"ቾ" ፊደል ሃምስ ዘር::

**ቼ**[2] ፈረስ እንዲሄድ፥ እንዲሮጥ፥ እንዲጋልብ ለማድረግ የሚባል::

**ቼቼ** ስ ልዘልህ ወይም ና ታዘል (ፈረስ ልሁንልህ እንደ ማለት) ለማለት ለህፃን የሚነገር ቃል::

**ቼቼ አለ** ግ በጀርባ ተሸከመ፥ አዘለ (ልጅን)::

**ቼዝ** ስ ሰንጠረዥ ጨዋታ::

**ች** የ"ቾ" ፊደል ሳድስ ዘር::

**-ች** በግስ ላይ በስተመድረሻ እየተቀጠለ ሶስተኛ መደብ አንስታይ ፆታን የሚያመለክት ምእላድ:: (ለምሳሌ ወሰደች፥ ትማራለች...)::

**ችላ ባይ** "ቾል"ስር ተመ.

**ችሎታ** "ቻለ"ስር ተመ.

**ችሎት** ዝ.ክ.

**ችምችም** "ቾመቾመ" ስር ተመ.

**ችርቻሪ** "ቾረቾረ" ስር ተመ.

**ችርቻሮ** ዝ.ክ.

**ችርችም** "ቾረቾመ[1]"ስር ተመ.

**ችርችፍ** "ቾረቾፈ" ስር ተመ.

**ችሮታ "ቸረ"** ስር ተመ.

**ችብሃ** ስ ውኃት የሚወጣውና ለምለምነት የማይለየው እንደሾላ ያለ ዛፍ።

**ችቦ** ስ 1. በመብራትነት የሚያገለግል ባንድነት የታሰረ ጭራሮ፣ ሽማ ወይም ጳቦት። 2. ለቡሄ ወይም ለእንቁጣጣሽ ዋዜማ እንዲሁም የደመራ እለት (ለመስቀል ዋዜማ) የሚበራ ባንድነት ከታሰረ ጭራሮ የሚዘጋጅ የበአል መቀበያ መብራት (ችቦ የሚበራበት እለት እንደየአካባቢው ሊለያይም ይችላል) ።

**ችንካር "ቸነከረ"** ስር ተመ.

**ችኩል "ቸኮለ"** ስር ተመ.

**ችካል "ቸከለ"** ስር ተመ.

**ችክ**[1]

**ችክ ችክ አለ** ግ ያለማቋረጥ የካፊያ ዝናብ ዘነበ።

**ችክ**[2] ግ **"ቸከ"** ስር ተመ.

**ችኮ** ዝ.ክ.

**ችኮላ "ቸኮለ"** ስር ተመ.

**ችጋራም "ቸገረ"** ስር ተመ.

**ችጋር** ዝ.ክ.

**ችግ**[1] በግን ለማባረር፥ ሂድ ለማለት የሚባል።

**ችግ አለ** ግ ሂድ አለ (በግን)።

**ችግ**[2]

**ችግ አለ** ግ ተንገረገበ (ጥሬ)።

**ችግ አደረገ** ግ አንገረገበ (ጥሬን)።

**ችግ**[3]

**ችግ አለ** ግ እጅብ ብሎ ወጣ፥ በቀለ (እፅዋት)።

**ችግረኛ "ቸገረ"** ስር ተመ.

**ችግር** ዝ.ክ.

**ችግኝ "ቸገነ"** ስር ተመ.

**ችፌ** ስ አብዛኛውን ጊዜ በእጅና በእግር ላይ ሽፍ ብሎ የሚወጣ፣ የሚያሳክክና እኽር የሚይዝ የቁስል አይነት።

**ችፍ**

**ችፍታ** ስ ሽፍ ብሎ በሰውነት ላይ የሚወጣ እንደ እከክ ያለ ነገር።

**ችፍ አለ** ግ በሰውነት ላይ ሽፍ ብሎ ወጣ (እከክ፣ ሽፍታ)።

**ችፍርግ** ስ ቁመቱ በጣም አጭር ከመሆኑ የተነሳ ብዛት ያላቸው ቅርንጫፎቹ መሬት ላይ ተኝተው የሚታዩ፣ ጠንካራ ሆኖ ውልግድግድ ያለ ግንድ ያለው አነስተኛ የእፅዋት አይነት።

**ችፍታ "ችፍ"** ስር ተመ.

**ችፍቻፌ "ቸፈቸፌ"** ስር ተመ.

**ችፍግ "ቸፈገ"** ስር ተመ.

**ቾ** የ"ቸ" ፊደል ሳብእ ዘር።

**ቾክ** ስ ለስላሳና ነጭ ከሆነ ድንጋይ የሚሰራ፥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ ለመፃፍ የሚያገለግል ብዙ ጊዜ ቀለሙ ነጭ የሆነ የፅህፈት መሳሪያ፣ "ጠመኔ" እየተባለም ይጠራል።

**ቿ** የ"ቸ" ፊደል ፍንፅቅ ዘር።

# ነ

**ነ** በዚህ መዝገበ ቃላት ፊደል ተራ መሰረት ከ"**ቸ**" ፊደል ዘር ቀጥሎ የሚመጣ የአማርኛ ፊደል (ግእዙ ሆሄ)።

**ነሃሴ (ናሴ)** ስ ከሃምሌ ቀጥሎ የሚመጣ የአመቱ አስራ ሁለተኛ ወር ስም።

**ነሃስ(ንሃስ፥ናስ)** ስ ቀለሙ ወደ ቢጫ የሚጠጋ፥ ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚውል፥ የቆርቆሮና የመዳብ ቅይጥ የሆነ የማእድን አይነት።

**ነሁላላ "ነሆለለ"** ስር ተመ.

**ነህ** (አፍ. "**አይደለህም**") "**ነው**"ን ተመ.

**ነሆለለ** ግ ሞኘ፥ ቂል፥ ፈዘዘ ሆነ፤ ጀለ።

**ነሁላላ (ነሆለል)** ቅ ሞኝ፥ ቂል፥ ፈዛዛ፥ጅል።

**ተነሃለለ** ግ ነሆለለ፥ ቄለ፥ ተጃጀለ።

**ነረተ**[1] ግ ከፋኛ መታ፥ ጠለዘ፥ ደበደበ።

**ነረተ**[2] ግ 1. ነፋ፥ ቀበተተ(ሆድን) 2. አወፈረ፥ አደነደነ።

**ናረት** ስ ዳውላ፥ ትልቅ አቁማዳ፥ ጭልጊ።

**ናረት ሆድ** ቅ (ዘይ.)ሆዱ ትልቅ የሆነ፤ በርጫም።

***ነረነረ**

**ነርነርቱ** ቅ አነጥናጭ፥ አደዝዳዥ፥ ወደላ።

**አነረነረ** ግ አደዘደዘ፤ አነጠነጠ፥ ወደለ።

**ነርስ** ስ በሆስፒታል ውስጥ ሃኪሙን በስራ ለመርዳትና የህመምተኞችን ጤና ለመከታተል የሰለጠነ ወይም የሰለጠነች የህክምና ባለሙያ።

**ነሰረ** ግ ከአፍንጫ ውስጥ ደም ወጣ፥ ፈሰሰ (በህመም)።

**ነስሮታል** 1. ነስር አሞታል። 2. በዝቶበታል። *ወጡ ቅቤ ነስሮታል።*

**እስኪነስረው** እስኪበቃው፥ እስኪያቅለሸል ሸው። *እስኪነስረው ልክ ልኩን ነገረው።*

**ነስር** ስ ከአፍንጫ ውስጥ ደም እንዲፈስ የሚያደርግ ህመም፤ የሚፈሰው ደምም ነስር ይባላል።

**አነሰረ** ግ ከአፍንጫ ውስጥ ደም ወጣ፤ ፈሰሰ (በህመም ምክንያት)።

**አይነስረውም** ምንም ገንዘብ አይሰጥም፣ ስስታም ነው።

**አስነሰረ** ግ አደማ (አፍንጫን)።

**ነሰነሰ** ግ 1. ጎዘጎዘ፤ በተነ (ሳርን)። 2.አንቀሳቀሰ፣ ወዘወዘ (ጭራን)። 3. በቁጣ ፀጉሩን አቆመ (ለምሳሌ ድመት)። 4. በተነ። ቁስሉ ላይ መድሃኒት ነሰነሰበት። 5. (ዘይ.) ሀ. ነዛ። *ጉራውን ነሰነሰ*፤ ለ. ያላግባብ አባከነ፥ በተነ፥ አጠፋ (ገንዘብን)።

**መነሳንስ** ስ በጭራ መልክ የሚሰራና እንደጭራ ያለ የሃር ጎፍላ ወይም የሃር ፈትል።

**ተነሰነሰ** ግ ተሰራጨ፥ ተዘራ። *በሽታ በአገሩ ላይ ተነሰነሰ።*

**ነሲብ** ስ ያልተለካ፥ ያልተመዘነ የግምት አስተያየት።

**በነሲብ** በግምት፥ ሳይለካ፥ ሳይመዘን። *እህሉን የገዛሁት በሚዛን ሳይሆን በነሲብ ነው።*



መነሳንስ

**ነሳ**[1] ከለከለ፥ ሳይሰጥ ቀረ። *ስጋ ሰጥተው ቢላዋ ነሱ።*

**ተነሳ(ተነሳው)** ግ አጣ፥ ራቀው፥ ተከለከለ። ረድኤት ነሳው።

**ነሳ**[2] ግ ወሰደ። *ከስጋዎ ስጋ ከነፍስ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆነ።*

**ነሳ**[3] ግ "**እጅ**" ስር "**እጅ ነሳ**" ን ተመ.

**መንስኤ** ስ ሰበብ፥ ምክንያት መነሻ።

**ተነሳ** ግ 1. ብድግ አለ፥ ቆመ። 2. ተላወሰ፥ ተንቀሳቀሰ፥ ነቃ (ለምሳሌ ከእንቅልፍ)። 3. ተንቀሳቀሰ፥ ጉዞ ጀመረ። *ባቡሩ ከጧቱ በሁለት ሰአት ተነሳ።* 4. ተጀመረ፥ መጣ። *ጦርነት ተነሳ/ጠቡ በምን ተነሳ ።* 5. መጣ ፥ ገባ። *በሽታ ተነሳ*፡ 6. ተሻለው፥ ዳነ። *ታሞ የነበረው ተነሳ*፡ 7. ነፍስ ዘራ፥ ከሞት ወደ ህይወት ተመለሰ። *አልአዛር ከሞተ ከአራት ቀን በሂላ ከመቃብር ተነሳ*፡ 8. በካ፥ ኩፍ አለ። *ሊጡ ተነሳ*፡ 9. ተሸጠ፥ ገበር አገኘ። *ሸቀጡ ተነሳ*፡ 10. ሃብት አገኘ፥ ከበረ፥ ገነነ። *የተነሳው በቆዳ ንግድ ነው*። 11. ተወሳ፥ ተጠራ፥ ተነገረ። *በዚህ ጉዳይ ስሙ ተነስቶም አያውቅ*፡ 12. ተቀነሰ፥ ተከፈለ፥ ተወሰደ። *ከሰባቱ ላይ አራቱ ስለተነሳለት ቀሪው ሶስት ብቻ ነው*። 13. ተሻረ፥ ተሰረዘ፥ ተለቀቀ። *ሰአት እላፊው ተነሳ*፡ 14. በልቡ አሰበ፥ ወሰነ፥ ቆረጠ። *ልቡ ተነስቷልና ከመሄድ አይቀርም*፡ 15. ተቀሰቀሰ፥ አበረ፥ በአንድ አላማ ተሰለፈ። *ህዝቡ ተነሳ*፡ 16. ተወገደ። *መሰናክሉ ወይም እንቅፋቱ ተነሳ።*

**መነሻ** ስ የአንድ ነገር ወይም ድርጊት መጀመሪያ (በታ፥ ጊዜ፥ ምክንያት)።

**መነሾ** ስ 1. መንስኤ፥ ሰበብ፥ ምክንያት። 2. ለጠበቃ ወይም ለስራ ተዋዋይ መጀመሪያ ላይ የሚከፈል የገንዘብ መጠን። 3. በሙታን ስም ተዘጋጅቶ ለካህናት ከሚቀርብ ፀበል ፀዲቅ ላይ ተቀንሶ ለካህናቱ አለቆች የሚሰጥ መጠነኛ ምግብና መጠጥ።

**ተነሳሳ** ግ ተነቃቃ፥ ተደፋፈረ፥ ተገፋፋ (አንድ ነገር ለማድረግ)።

**አነሳ** ግ 1. ከፍ፥ ብድግ አደረገ። 2. ጀመረ፥ አጫረ። *ጦርነት አነሱ*፡ 3. አከበረ፥ አበለፀገ፥ አላቀ። እሱን ያነሳው የጨው ንግድ ነው። 4. አወሳ፥ አስታወሰ። *ያለፈውን እያነሳ ተጫወተ*። 5. ወሰደ። *እዚህ የነበረውን እቃ ማን አነሳው?* 6. ተወ፥ ሰረዘ። *አቅርቦት የነበረውን የተቃውሞ ሃሳብ አንስቷል*። 7. በብዛት ወሰደ፥ ፈጀ። *ዱቄቱ ውሃ ያነሳል*። 8. አጠቃሎ ያዘ፥ ቻለ። *በሶስት ማድጋዎች የነበረውን ድፍድፍ አንድ በርሜል አነሳው*። 9. አምኖ ተቀበለ። *ያባቱን እዳ አነሳ*። 10. ተከተለ፥ አጠና፥ ያዘ፥ ተማረ። *ልጅየው ያባቱን ሙያ አንስቷል*። 11.(ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የሚቀጥለው ጊዜ ተረኛ በመሆኑ የእለቱ ተረኛ መሪ የሚያዜመውን እየተቀበለ አዜመ።

**ንሳ** በል፥ እባክህ። *ንሳ ያንን እቃ አቀብለኝ / ንሳ ተቀበል*።

**አንሺ** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ከእለቱ ተረኛ የዜማ መሪ ቀጥሎ ተረኛነቱን የሚረከብ (መዘምር፥ ደብተራ)።

**አነሳሳ** ግ 1. አበረታታ፥ አደፋፈረ፥ ገፋፋ። 2. ቀሰቀሰ፥ አሳደመ።

**አነሳሽ** ቅ ቀስቃሽ፥ አሳዳሚ።

**አስነሳ** ግ እንዲነሳ አደረገ።

**ነስር** "**ነሰረ**" ስር ተመ.

**ነሸጠ** ግ በል በል፥ አድርግ አድርግ የሚል ስሜት ተሰማ፥ ገፋፋ፥ አነሳሳ።

**ነሸጥ አደረገ** ግ ነሸጠ።

**ንሽጥ አደረገ** ዝ.ከ.

**ነሽ** (አፍ. **አይደለሽም**) "**ነው**" ን ተመ.

**ነቀለ** ግ 1. መዘዘ፥ መነገለ። 2. አወለቀ፥ ለያየ። 3. አባረረ፥ አስወገደ(ከርስት)። 4. ሰረዘ፥ ፋቀ (ከመዝገብ)። 5. አጠፋ (በሽታን)። 6. ጥርግ ብሎ ሄደ። *ሰራዊቱ ካደረበት ቦታ በጧት ነቅሎ ሄደ*። 7. (ዘይ.) አራቆተ፥ አደሀየ። *ብድር ወጪው / ነቀለኝ*።

**ነቀላ** ስ እንግጫ የሚነቀልበት የእንቁጣጣሽ ዋዜማ።

**ነቀል ተከል** ቅ በአንድ በተወሰነ ቦታ ፀንቶ የማይኖር፥ እንደዘላን ጎጆ ወይም ቋሚ ቦታ የሌለው።

**ነቃሳ** ቅ 1. ሲራመድ ድፍት ድፍት ያለ የሚመስልና ፈጠን ያለ አረማመድ ያለው፥ ቀትረ ቀላል (ሰው)። 2. (ስድብ) ጥላቢስ።

**ነቃይ ተካይ** ስ የመሻር፥ የመሾም፥ ከርስት ላይ የማባረር፥... ስልጣን ያለው ሹም።

**ንቃይ(ንቅል)** ስ አገልግሎት ላይ እንዲውል ተደርጎ ከቆየ በሗላ ፈርሶ ወይም ከነበረበት ተነስቶ ለሌላ ተግባር ሊውል የሚችል (የአጥር እንጨት፥ የቤት ክዳን ቆርቆሮ፥...)።

**ነቀልቃል** "***ቀለቀለ**" ስር ተመ.

***ነቀረ**

**ንቃሪ (እንቃሪ)** ስ ጭላጭ፥ ሙጣጭ (ፈሳሽ ለሆነ ነገር)።

**አነቀረ** ግ ሙጥጥ አድርጎ ወሰደ፥ ጨለጠ (ፈሳሽን ከመያገኘው ውስጥ)።

**አንቅሮ ተፋ** ፈፅሞ ጠላ፥ ተወ፥ የነበረውን ግንኙነት አቋረጠ።

**ነቀርሳ** ስ ብዙውን ጊዜ በአንገት፥ በጡት፥ በደረት፥...አካባቢ የሚፈጠርና በቀላሉ የማይሽር ወይም ጭራሹኑ ሊሽር የማይችል ጠንቀኛ የቁስል በሽታ አይነት።

**ነቀርሳ ሆነበት** 1. ሲጀምር ቀላል የነበረው የቁስል ህመም ውሎ አድሮ ወደ ነቀርሳ ተለወጠበት። 2. (ዘይ.) የማይገላገለውና የማይላቀቀው ችግር ሆነበት (ለነገር)።

**ነቀሰ**[1] ግ 1. የጥላሸት ቀለም በተቀባ የመርፌ ወይም የሾህ ሜፍ ገላን(ድድን፥ አንገትን፥...) ደጋግሞ በመውጋት ወይም በመጨቅጨቅ የተወጋው ገላ ጌጠኛ እንዲሆን አደረገ፥ በንቅሳት አስጌጠ፥ ወቀረ። 2. ከወርቅ፥ ከብር፥... በሚሰራ ጌጥ ላይ የተለያየ ቅርፅ በመንደፍ ጌጡን አስዋበ።3. የተፍተለተለውን፥ የተቆጣጠረውን የራስ ፀጉር በሚዶ አበጠረ ወይም ከፈከፈ። 4. ቆሻሻን ወይም ጉድፍን ከልብስ ወይም ከጥጥ ላይ አነሳ። 5. ነቀለ፥ መነገለ (እሾህን ከእግር፥ ፀጉርን ከአይን ቆብ ዳር ላይ)።

**መንቀሻ** ስ 1. ለንቅሳት ስራ የሚያገለግል መርፌ ወይም እሾህ። 2. ማበጠሪያ፥ ሚዶ።

**በነቂስ** አንድም ሳይቀር፥ በሙሉ። *ህዝቡ በነቂስ ወጣ*።

**ንቃሽ** ስ ከልብስ፥ ከጥጥ፥... ላይ የተለቀመ ጉድፍ ወይም ቆሻሻ የበዛበት ጥጥ ወይም በርበሬ።

**ንቅሳት** ስ ጥላሸትን በውሃ በጥብጦ በመርፌ ወይም በእሾህ ሜፍ እያጠቀሱ ገላን (ድድን፥ አንገትን፥...) ደጋግሞ በመጠቅጠቅ የሚሰራ የሰውነት ላይ ጌጥ፥ ውቅራት።

**ንቅስ** ስ 1. ንቅሳት። 2. ለጌጥ፥ ለውበት ተብሎ እንደ ሽክና፥ መስቀል፥ ዝናር፥... ባሉ ቁሳቁሶች አካል ላይ የሚሰራ ቅርፅ፥ ሽልማት።

**ነቀሰ$^{2}$** ግ መስከረ፥ እውነትን ከውሸት ለይቶ ተናገረ።

**ነቃሽ** ስ ምስክር፥ እማኝ።

**ነቀሰ$^{3}$** ግ ቀነሰ፥ ወረደ (ዋጋ)።

**ንቃሽ** ቅ የዋጋ ቅናሽ።

**በንቃሽ** በቅናሽ።

***ነቀሸ**

**አነቀሸ** ግ ሰበረ፥ አነከተ።

**እንቅሽ አለ** ግ ተሰበረ፥ ነከተ።

**እንቅሽ አደረገ** ግ ሰበረ፥ አነከተ።

**ነቀነቀ** ግ 1. ወዘወዘ፥ ናጠ፣ ጎነተለ፥ ጎሸመ። 2. ቀሰቀሰ፥ አነሳሳ። *ፕሮፓጋንዳው ህዝቡን ነቀነቀው።*

**ንቅናቄ** ስ 1. ቅስቃሴ፥ ውዝዋዜ። 2. እንቅስቃሴ (የአመፅ፥ የተቃውሞ)።

**ንቅንቅ ብሎ ወጣ** ግልብጥ ብሎ በብዛት ወጣ። *ህዝቡ ንቅንቅ ብሎ ወጣ።*

**ንቅንቅ አይልም** አይበገርም፥ አይሞከርም፥ ፍንክች አይልም።

**ተነቀነቀብኝ** - ተገቢ ካልሆነ አነጋገር ጋር የትእቢት፥ የንቀትና የቁጣ አካላዊ እንቅስቃሴ አሳየኝ፣ ተረገረገብኝ።

**ተነቃነቀ** ግ 1. ተወዛወዘ። 2. ተንቀሳቀሰ። 3. ተነሳሳ፥ ተቀሰቀሰ።

**ተነቃናቂ** ቅ ተዘዋዋሪ፥ ተንቀሳቃሽ።

**አነቃነቀ** ግ 1. አወዛወዘ፥ አንቀሳቀሰ። 2. አነሳሳ።

**ነቀዘ** ግ 1. በነቀዝ ተበላ፥ ተበላሸ። 2. ነቀዝ አፈራ፥ ፈጠረ።

**ነቀዝ** ስ 1. ሙቀት ባለበት አካባቢ የሚፈጠርና አንዳንድ የእህልና የእንጨት አይነቶችን ውስጣዊ አካል በመቦርቦርና በመብላት ለብልሽት የሚዳርግ አነስተኛ የተባይ አይነት። 2. (ስድብ፥ ዘይ.) ብዙ የሚበላና በልቶም የማይጠረቃ (ሰው)።

**ነቀፈ** ግ 1. ተቸ፥ ተቃወመ። 2. አንኳሰሰ፥ አጥላላ፥ እንከን አወጣ።

**ነቀፋ** ስ1. ትችት፥ ቅዋሜ። 2. እንከን፥ ነውር ማውጣት።

**ነቀፌታ** ዝ.ክ.

**ነቃፊ** ቅ 1. ተቺ፥ ተቃዋሚ። 2. አቃቂር፥ እንከን አውጪ።

***ነቀፈ**

**አነቀፈ** ግ 1. አደናቀፈ፥ አሰናከለ፥ መታ (እንቅፋት እግርን)። 2. ጣልቃ በመግባት ችግር ፈጠረ፥ መሰናከል ሆነ።

**እንቅፋት** ስ 1. ሲራመዱ እግርን የሚያደናቅፍ፥ የሚያሰናክል እንደ ድንጋይ፥ ጉቶ፥... ያለ ነገር። 2. ሳይታሰብ የሚያጋጥምና አንድን ጤናማ ሂደት የሚያውክ ችግር፥ መሰናከል።

**እንቅፋት አነደደው** እንቅፋት እግሩን መታው።

**ነቀፋ** "**ነቀፈ**" ስር ተመ.

**ነቀፌታ** ዝ.ክ.

**ነቁጥ** "***ነቆጠ**" ስር ተመ.

**ነቃ$^{1}$** ግ 1. እንቅልፋን ጨረሰ፥ ከእንቅልፉ ተነሳ። 2. ባነነ፥ ከእንቅልፉ ተቀሰቀሰ። 3. ንቁ፥ ትጉህ፥ ቀልጣፋ ሆነ። 4. ጠረጠረ። 5. አወቀ፥ ተረዳ፥ ፈጥኖ ተገነዘበ።

**ንቁ** ቅ 1. እንቅልፍ የማያሸንፈው፥ ባስፈላጊው ጊዜ መነሳት የሚችል። 2. ትጉህ፥ ቀልጣፋ፥ ጮሌ።

**ንቃት** ስ 1. ትጋት፥ ቅልጥፍና። 2. አርቆ የማስተዋል፥ ሁኔታዎችን ፈጥኖ የመረዳት ችሎታ። 3. ከፖለቲካዊ ትምህርት የሚገኝ እውቀት፥ ግንዛቤ።

**ንቃተህሊና** ስ የተግባራዊና የነባራዊ ሁኔታ ነፀብራቅ ውጤት የሆነ የሰው ልጅ የአእምሮ ግንዛቤ፥ አስተሳሰብ፥ እውቀት።

**አነቃ** ግ የፖለቲካ ትምህርት አስተማረ፣ ቀሰቀሰ።

**አንቂ** ስ የፖለቲካ ትምህርት ለህዝብ የሚሰጥ፣ ቀስቃሽ።

**አነቃቃ** ግ አበረታታ፥ ገፋፋ፥ ጎተጎተ፥ ቀሰቀሰ።

**ማነቃቂያ** ስ ማበረታቻ።

**ነቃ$^{2}$** ግ ተሰነጠቀ፥ ተተረተረ።

**ንቃቃት** ስ ስንጥቃት፥ ትርትራት (የመሬት፥ የእግር፥...)።

**ንቃቃታም** ቅ (ስድብ) እግሩ ላይ ንቃቃት ያለበት፥ በንቃቃት የተጎዳ (ሰው)።

**ነቃላ** "**ነቀለ**$_{2}$" ስር ተመ.

**ነቃሽ** "**ነቀሰ$^{2}$**" ስር ተመ.

**ነቃፊ** "**ነቀፈ**" ስር ተመ.

***ነቆረ**

**መንቆር** ስ 1. የወፍ፥ የአሞራ፥ የዶሮ አፍ። 2. ባላ ያለው ረዘም ያለ እንጨት። 3. እንደ እግር ብረት ሆኖ ለማሰሪያነት የሚያገለግል ቀዳዳ ወይም ብስ ያለው ግንድ።

**ነቋራ** ቅ አንድ አይኑ የጠፋ።

**ተናቆረ** ግ 1. አንዱ ከሌላው ጋር ተነካከሰ (ዶሮ)። 2. አንዱ ከሌላው ጋር ተጣላ፥ ተጣመደ፥ ተያያዘ።

**አነቆረ** ግ1. ወጋ፥ ደነቆለ፥ ጠነቆለ (አይንን)፡፡ 2. ጫረ፥ ቆሰቆሰ (ነገርን)፡፡

**አናቆረ** ግ አጣላ፥ አናከሰ፡፡

***ነቆጠ**

**ነቁጥ** ስ በቃል፥ በሃረግና በአረፍተ ነገር መጨረሻ ላይ የሚደረግ ነጥብ፡፡

**አነቆጠ** ግ ነጥብ አደረገ፥ አስቀመጠ፡፡

**ነቋራ** "*ነቆረ" ስር ተመ.

**ነበልባል** "*በለበለ" ስር ተመ.

**ነበረ(ነበር)** ግ የ "ነው" እና የ "አለ" ሃላፊ ጊዜ ግስ፡፡ *ዛሬ ፀሃይ ነው ትናንት ግን ዝናም ነበረ /አለች እንጂ ነበረች አይጠቀምም፡፡*

**ለነበር** ለወግ፥ ለዝና፥ ለማስታወሻ፥ ለታሪክ፡፡ *ለነበር ይጠቅማልና ታሪካችን በወጉ ተፅፎ ቢቀመጥ አይከፋም፡፡*

**ነበርኩ ባይ** እንዲህ ነበርኩ እያለ በማውራት የሚኩራራ፤ ጉረኛ፡፡

**ነባሪ** ስ ምስክር፥ እማኝ፡፡

**ነባራዊ** ቅ ተጨባጭ የሆነ (ነገር)፡፡

**ነባር** ቅ የኖረ፥ የቆየ፡፡ *ሰውየው በዚህ ቦታ ነባር ናቸው፡፡*

**ነበረረ** ግ 1. ቄለ፥ ነሆለለ፡፡ 2. ተንዠባረረ፡፡

**ነበረር(ነብራራ)** ቅ 1 ነሁላላ፡፡ 2. ዠብራራ፡፡

**ተነባረረ** ግ ነበረረ፡፡

**አነባረረ** ግ 1. አቄለ፥ አነሆለለ፡፡ 2. አንዠባረረ፡፡

***ነበረበረ**

**ንብርብር (ንብብር)** ቅ ድርብርብ (አንዱ በሌላው ላይ ተደርቦ መገኘት)፡፡

**ንብርብር አለ** ግ ተነባበረ፡፡

**ተነባበረ** ግ 1. ተደራረበ፥ አንዱ በሌላው ላይ ሆነ፡፡ 2. ተጋዘ፥ ተረዳዳ፡፡

**አነባበረ** ግ አንዱን በሌላው ላይ አደረገ፤ አደራረበ፡፡

**አነባበሮ** ስ በሰሉ የወጣን እንጀራ ምጣድ ላይ ከተሰፋና ገና ካልበሰለ ሊጥ (እንጀራ) ላይ በመደረብና አብሮ በማብሰል የሚዘጋጅ ወፍራምና ድርብርብ እንጀራ፡፡

**ነበር** "ነበረ" ን ተመ.

**ነበበ** ግ 1. ታወቀ፥ ከበረ፥ ገነነ፡፡ 2. በሃይል ጮሀ፥ ጩሁቱ አስተጋባ፥ ከሩቅ ተሰማ (የከበሮ፥ የመረዋ)፡፡

***ነበበ**

**ምንባብ** ስ 1. አጠር ያለና ለንባብ ማስተማሪያ የተዘጋጀ ፅሁፍ፡፡ 2. መፅሃፍ፥ መጣጥፍ፥ ፅሁፍ፡፡

**ንባብ** ስ 1. በፅሁፍ ላይ የሰፈረን ነገር በአንደበት ወይም በድምፅ አማካይነት ጮክ አድርጎ የማነብነብ፥ የመናገር፥ የማሰማት ድርጊት፡፡ 2. በቤተክህነት ትምህርት ቤት ከውርድ ንባብ ቀጥሎ የሚሰጥ የአነባበብን ጥራትና ፍጥነት የሚመለከት ትምህርት፡፡

**ንባብ ቤት** ስ (ቤ.ክህ.) ከፊደል እስከ ዳዊት ያለውን ትምህርት የሚማሩበት ትምህርት ቤት፡፡

**ተነበበ** ግ 1. በንባብ ተባለ፥ ተነገረ (ፅሁፍ ላይ የሰፈረው ነገር)፡፡ 2. የሚታይና የሚነበብ ወይም ሊነበብ የሚችል ሆነ፡፡ *ፅሁፉ አይነበብም፡፡*

**ተነባቢ** ቅ 1. አጣጣሉ ግልፅና ጥሩ ሆኖ የተፃፈና ለአንባቢ የማያስቸግር (ፅሁፍ)፡፡ 2. ተወዳጅ ፅሁፍ በመሆኑ ብዙዎች የሚያነቡት፡፡

**ተናበበ** ግ1. ተመሳከረ፥ ተያየ (ዋናው ፅሁፍ ከቅጂው ጋር አንድ አይነት ስለመሆኑ)፡፡ 2. አንዱ የሌላውን ሃሳብ ተረዳ፥ በዚህም መንገድ ተግባባ፥ ተዋወቀ፡፡

**ተናባቢ** ስ 1. ለየብቻቸው ሳይሆን እንደ አንድ ቃል ተደርገውና በአንድነት ተጠቅለው የሚነገሩ ጥምር ቃላት (ለምሳሌ ቤተመንግስት፥ ርእሰብሄር፥...)፡፡ 2.(ስነል.) ከአፍ ውስጥ የሚወጣው አየር ሲቆም ወይም ሲታገድና ሲጋጭ የሚፈጠር እንደ በ፥ረ፥ከ፥... ያለና አናባቢ ያልሆነ ድምፅ፡፡

**አነበበ** ግ በፅሁፍ ላይ የሰፈረን ነገር ድምፅ እያሰማ በአንደበቱ አለ፥ ተናገረው ወይም ድምፅ ሳያሰማ በአእምሮው ዘለቀው፡፡

**አንባቢ** ቅ 1. የማንበብ ችሎታ ያለው፡፡ 2. አዘውትሮ መፃህፍትን ማንበብ የሚወድ፡፡3.ስራው ጮክ ብሎ ማንበብ የሆነ፡፡*ዜና አንባቢ፡፡*

**አናበበ** ግ 1. ዋናውን ፅሁፍ ከቅጂው ጋር አስተያየ፤ አመሳከረ፡፡ 2. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ የተለያዩ ቃላትን በመገጣጠም እንደ አንድ ቃል አድርጎ በድምፅ ጠራ (ለምሳሌ ቤት፣ መንግስት ቤተመንግስት)፡፡

**አናባቢ** ስ ከአፍ ውስጥ የሚወጣው አየር ሳይቆም ወይም ሳይታገድና ሳይጋጭ በሚወጣበት ጊዜ የሚፈጠር እንደ አ፥ኡ፥... ያለና ተናባቢ ያልሆነ ድምፅ፡፡

**አስነበበ** ግ 1. (አንድን ፅሁፍ) ሌሎች እንዲያነቡት አደረገ፡፡ 2. ንባብ ወይም አነባበብ አስተማረ፡፡

**አስነባቢ** ስ በመፃህፍት ማንበቢያ ክፍል ለአንባቢዎች አስፈላጊውን እገዛ የሚያደርግ የቤተ መፃህፍት ሰራተኛ፡፡

***ነበነበ**

**መነባንብ** ስ በአእምሮ የሚመላለስን ሃሳብ ለአድማጭ ሳይሆን ለገዛ ራስ ብቻ ጮክ ተብሎ የሚደረግ ንግግር(ትያትር)፡፡

**አነበነበ** ግ 1. ባለማቋረጥ ተናገረ፥ ቀባጠረ። 2. በፍጥነት አነበበ። 3. አጉተመተመ፥ ደገመ።
**አነብናቢ** ቅ (ስድብ) ምላሰኛ፥ ነገረኛ።
**ነበዘ**[1] ግ 1. መረዘ፥ አቀለመ፥ አመነቸከ። *ጸድፍ ልብሱን ነበዘው*። 2. ማስተዋል ወይም ማጤን ተሳነው፥ ፈዘዘ፥ ነፈዘ። 3. ጠቆረ፥ ተበላሸ፥ ማዲያት ያዘው። *ፊቱ ነበዘ።*
**ነባዛ** ቅ 1. ቀለሙ የተበላሸ፥ የመነቸከ፥ የቸከ (ልብስ)። 2. (ስድብ) ነፈዝ፥ ፈዛዛ። 3. ፊቱ የጠቋቆረ፥ ማዲያታም።
**ነበዘ**[2] ግ ቀማ፥ መነተፈ።
**ተነበዘ** ግ ተቀማ፥ ተመነተፈ።
**ነቢይ (ብ.ቁ.ነቢያት)** ስ ወደፊት ሊሆን፥ሊመጣ ወይም ሊደርስ የሚችለውን ነገር አስቀድሞ የሚናገር የእግዚአብሔር ሰው።
**ነባሪ** "ነበረ" ስር ተመ.
**ነባራዊ** ዝ.ከ.
**ነባር** ዝ.ከ.
**ነባዛ** "ነበዘ[1]" ስር ተመ.
**ነቤላ** ስ በበረሃ አካባቢ የሚገኝ አነስተኛ የእፅዋት አይነት።
**ነብሪድ** "ንቡረእድ" ን ተመ.
**ነብራራ** "ነበረረ" ስር "ነበረር" ን ተመ.
**ነብር** ስ 1. መልኩ ቢጫማ መደብ ይዞ እንደ ቀለበት ክብ የሆኑ ጥቋቁር ነጠብጣቦች ያሉበት፥ ረዥምም ሸንተና አጫጭር እግሮች ያሉት፥ በጢሻ በቋጥኝና በዋሻ ውስጥ የሚኖር ሃይለኛና ቁጡ የሆነ ስጋ በል አውሬ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)። 2. (ዘይ.) በጣም ቁጡ። *ባሏ ነብር ነው ትፈራዋለች።*
**ነብርማ** ቅ ዝጉርጉር፥ መልኩ ነብር የሚመስል።
**ነብሮ** ስ የነጭና የቀይ ድብልቅ የሆነና ከበሬ ጡንቻ ላይ የሚገኝ የስጋ አይነት።
**ነቦጨ** ግ ወድቆ ተሰበረ።
**ነተረ**[1] ግ 1. ብዙ በመቆየቱ በሰለ፥ ኮሰተረ (ጠላ፥ ጠጅ)። 2. ሆረጠ።
**ነተረ**[2] ግ ወጠረ፥ ነፋ፥ ቀበተተ (ሆድን)።
**ነተረከ** ግ ነዘነዘ፥ ጨቀጨቀ።
**ነትራካ** ቅ (ስድብ) ነዝናዛ፥ ጨቅጫቃ።
**ንትርክ** ስ ንዝንዝ፥ ጭቅጭቅ።
**ተነታረከ** ግ ተነዛነዘ፥ ተጨቃጨቀ።
**አነታረከ** ግ አነዛነዘ፥ አጨቃጨቀ።
**ነተበ** ግ ሳሳ፥ ተጎዳ፥ ማለቅ ጀመረ (ልብስ)።
**ነት** ስ ለምንጣፍ ወይም ለመተኛ የሚሆን የለፋ ወይም የለሰለሰ የከብት ቆዳ።
**ነት ይንካው** (ነገሩ) ይዋል ይደር፥ ይመከርበት፥ ይታሰብበት።
**-ነት** ቅፅል ወይም ስም በሆነ ቃል መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ረቂቅ ስምን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ፤ ለምሳሌ ኢትዮጵያዊነት፥ እናትነት፥ ደግነት፥...።
**ነትራካ** "ነተረከ" ስር ተመ.
**ነነዌ (ነይነይ)** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ከሁዳዴ ፆም መባቻ አስራ አራት ቀን ያህል ቀደም እየተባለ የሚፆም የሶስት ቀን የፆም ጊዜ።
**ነን** (አፍ. "አይደለንም") "ነው" ን ተመ.
**ነኝ** (አፍ. "አይደለሁም") "ነው" ን ተመ.
**ነኝ ባይ** ቅ እንዲህ ነኝ፥ እንዲህ ነበርኩ እያለ ራሱን የሚያኩራራ፤ ጉረኛ።
**ነከረ** ግ 1. ዘፈቀ፥ ከተተ። 2. ዘፈዘፈ፥ አራሰ። 3. አጠመቀ። 4. አጠቀሰ።
**ነክረው ያወጡት** (ዘይ.) ሞኛሞኝ፥ ቂላቂል።
**ነክርት(ንክርት)** ዝ.ከ.
**ንክር** ቅ 1. በውሃ እንዲረጥብ ወይም እንዲርስ የተደረገ። 2. (ዘይ.) ቂል፥ ሞኝ።
**ተነከረ** ግ 1. ተዘፈዘፈ፥ ውሃ ውስጥ ሆነ። 2. (ዘይ.) ተዘፈቀ፥ ተከተተ። *ጸዳ ውስጥ ተነከረ።* 3. ተጠመቀ።
**ነከሰ** ግ 1. በጥርሱ ያዘ፥ ወጋ፥ አጣበቀ። 2. በጥርሱ ቦጨቀ፥ ቦተረፈ። 3. ነደፈ፥ወጋ፥ ጠቅ አደረገ (እባብ)። 4. አጣብቆ ያዘ፥ አላንቀሳቅስ አለ (ሞተር)።
**ነክሶ ያዘ** 1. ጠመደ፥ ጠላ፥ ክፉኛ መርዞ ያዘ። 2. አልለቅም አለ፥ አጥብቆና አጠንክሮ ያዘ።
**ንክሻ** ስ በጥርስ መቦጨቅ፥ መውጋት፥ መዘንጠል።
**ተነከሰ** ግ ተቦጨቀ፥ ተዘነተረ፥ ተበላ። *ልጁ በውሻ ተነከሰ።*
**ተናከሰ** ግ1. በጥርሱ ነከሰ፥ ቦጨቀ፥ ቦተረፈ።2. ተጣላ፥ ተጠማመደ።
**ተናካሽ** ቅ የሚባላ፥ የሚነክስ (ለምሳሌ ውሻ)።
**አናከሰ** ግ 1. እርስ በእርስ አንዱ ሌላውን አጥብቆ እንዲይዝና በመደጋገፍ ጥንካሬ እንዲያገኝ አደረገ። *ካቡ(ግንቡ) ጠንካራ እንዲሆን ድንጋዮቹን እያናከሱ መካብ ያስፈልጋል።* 2. (ዘይ.) አጣላ፥ አናቆረ።
**ነከተ** ግ ተሰበረ፥ ደቀቀ።
**መንከት** ስ ከቁም ነገር የማይገባ፥ ደቃቃ፥ ውዳቂ ነገር።
**ነካታ** ቅ ደቃቃ፥ ሰባራ።

**ንካች** ዝ.ከ.

**አነከተ** ግ 1. ሰበረ፥ አደቀቀ:: 2. ደህና አድርጎ ተመገበ::

**እንክት አለ** ግ ነከተ፥ እንቅሽ አለ::

**እንክት አድርጎ በላ** ምንም ሳያስቀር ጠርጎ፥ ጨርሶ በላ::

**እንክትክት አለ** ስብርብር፥ ድቅቅ አለ::

**እንክትክት አደረገ** ስብርብር፥ ድቅቅ አደረገ::

**ነከነከ** ግ 1. እንደልቡ በብዛት ተመገበ:: 2. በብዛት ለረዥም ሰአት ዘነመ፥ ጣለ:: *ዝናሙ ሲነከንከው አደረ::*

***ነከነከ (ኖከኖከ)**

**ነክናካ (ኖክኗካ)** ቅ 1. ሰባራ በመሆኑ ድምፁ ጥራት የሌለው (ቃጭል፥ ደወል፥...):: 2. ሲናገር የሚነፋነፍ፥ አፍንጫው ችግር ያለበት በመሆኑ ትክክለኛ ድምፅ ለማውጣት የማይችል::

**ነካ** ግ 1. ዳሰሰ:: 2. ጎነጠ፥ ጎሸመ:: 3. ጎዳ፥ አሳመመ:: *ቅባት የበዛበት ምግብ በልቼ ሆዴን ነካኝ*: 4. ገጠበ፥ አቆሰለ:: *ጭነቱ የአህያውን ጀርባ ነካው*: 5. በደለ፥ ተተናኮለ:: *የማንን ወንድም ማን ይነካዋል*: 6. አሽሟጠጠ፥ ሸረደደ፥ሰደበ:: *በነገር ነካ*: 7. ተዳፈረ፥ ነቀፈ:: *የሰው ክብር አትንካ*:8 በግብረስጋ አወቀ፥ ተገናኘ:: *ያቺን ሴትዮ ከነካ ጀምሮ ልቡ በፍቅር ተይዟል*:: 9. አንድን ነገር በብዛት አደረገ፥ አከናወነ:: *አስከስታውን ነካው*:: 10. በከለ፥ አበላሸ:: *ልብሱን ጭቃ ነካው*::

**ያልነካ ይንካሽ አደረጉት** ሁሉም ደበደቡት፥ መቱት::

**-ነክ** -ቀመስ፥ -መሰል፥ -ጠቀስ:: *ሱፍ ነክ ልብስ እወዳለሁ*::

**ነክህን** በገበጣና በቅልቦሽ ጨዋታ ጊዜ አንድ ተጫዋች መጀመሪያ ከነካው ወይም ካነሳው ጠጠር ሌላ በሌላ ጠጠር እንዳይሄድ (እንዳይጫወት) በተቃራኒው ወይም በተጋጣሚው አንደበት የሚባል የመከልከያ ቃል::

**ንክ** ቅ 1. እንከን ያለበት፥ ሰባራ (እቃ):: 2. በከባድ ጭነት ምክንያት ጀርባው የተገጠበ፥ የቆሰለ (አህያ፥ በቅሎ፥ ፈረስ):: 3. የአእምሮ በሽታ ያለበት፤ ቀውስ፤ ወፈፌ::

**ንክች አላደርገውም** ፈፅሞ አልነካውም፥ አልሞክረውም::

**ንክች አድርገኝ** መምታት ቀርቶ በጣትህ ዳሰስ ወይም ነካ ብታደርገኝ ጉድህ ይፈላል ለማለት በጠብ ጊዜ ለጠበኛ የሚሰጥ የማስጠንቀቂያ ቃል::

**ንክኪ(ንክክ፥ ንክኪት)** ስ 1. አካላዊ ግንኙነት ወይም መነካካት (የአንዱ ነገር ከሌላው ጋር):: 2. ጥል፥ ፀብ:: *ንክኪ ናቸው*:: 3. ወዳጅነት፥ ትውውቅ (የግብረስጋ ):: 4. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ) በፆም ቀን ከስጋ ወይም ከቅቤ ጋር ተነካክቶ የተገኘ እቃ ወይም ምግብ::

**ነካካ** ግ 1. ደባበሰ፥ ዳሰስ ዳሰስ አደረገ:: 2 ተነኮሰ:: *በነገር ይነካካኛል*::

**የነካካው (የነካው)** 1. በመጠኑ አልፎ አልፎ ወጥ ያለበት፥ ወጥ ያራሰው (እንጀራ):: 2. ወፈፍ የሚያደርገው (ሰው)::

**ተነካ** ግ 1. ወፈፈ፥ ቀወሰ፥ ተለከፈ:: *ጤነኛ አይደለም ተነክቷል*:: 2. ተጎዳ:: *ስሜቱ በሃዘን ተነካ*::

**ተነካካ** ግ 1. እጅ አረፈበት፥ በእጅ ተዳሰሰ:: 2. ተበከለ:: *የፆሙ እቃ በስጋ ተነካካ*: 3. ተዋወቀ (በግብረስጋ):: 4 ተቃቃረ፥ ተቀያየመ፥ ተጣላ:: 5. ተፋሰሰ፥ በካከነ፥ ተላላሰ:: *ዱቄት ተነካካ*: 6. ተጎነተለ:: *እሳትና ድሃ ሲነካኩት አይወድም*::

**አነካካ** ግ 1. አንዱን አካል ከሌላው ጋር አገጣጠመ፥ አገናኘ:: 2. አቀያየመ፥ አጣላ፥ አጋጨ:: 3. የፍስኩ ምግብ (ስጋና ቅቤ) ለፆም ከሚሆነው ምግብ ወይም እቃ ጋር እንዲገናኝ አደረገ፥ በካከለ:: 4. አብቃቃ፥ በመጠኑ ተጠቀመ:: *በቂ ወጥ ስለሌለ እያነካካ በላ*::

**አነካኪ** ቅ ነገረኛ፥ ከሰው ጋር የሚያቀያይም፥ የሚያጣላ::

**አናካ** ግ አነካካ::

**አስነካ** ግ 1. በመድሃኒት አሳመመ፥ ጉዳት ላይ ጣለ:: *ሰውየውን መድሃኒት አስነካው*: 2. አንድን ድርጊት በደንብ አከናወነ፥ ሰራ:: *ዘፈኑን አስነካው*::

**ነካታ** "ነከተ" ስር ተመ.

**ነክ** "ነካ" ስር ተመ.

**ነክናካ** "*ነከነከ" ስር ተመ.

**ነኮረ** ግ ተቆራረሰ፥ ተፈረፈረ፥ እንኩሮ ሆነ::

**አነኮረ** ግ 1. ለጠላ ጠመቃ ዝግጅት እንዲሆን ተቆልቶም ሆነ ሳይቆላ የተፈጨን የገብስ ወይም የበቆሎ፥... ዱቄት እንደ በሶ ከውሃ ጋር ካሸ በሂላ በሰማ ምጣድ ላይ አድርጎ እስኪበስል ድረስ እያገላበጠ አመሰ:: 2. ከምጣዱ ላይ ሳይቆራረስ በደህና መውጣት የሚኖርበት እንጀራ ወይም ዳቦ ከጥንቃቄ ወይም ከሙያ ማነስ የተነሳ እየተቆራረሰ እንዲወጣ አደረገ:: 3. መነሳት የሌለበትን ሃሳብ በማንሳት ነገር አበላሸ::

**አንኳራ** ቅ ነገር የሚያበላሽ፥ የሚዘባርቅ::

**እንኩሮ** ስ 1. በውሃ ተበስብሶ ምጣድ ላይ እየተገላበጠ እንዲበስል የተደረገና ለጠላ የሚሆን ዱቄት:: 2. ከምጣድ ላይ በደህና ሁኔታ መውጣት የነበረበት የእንጀራ ወይም የዳቦ ቁርስራሽ፥ ስብርባሪ:: 3. (ዘይ.) ቂላቂል፥

አነጋገረ ጅል፥ ዘባራቂ፥ ነገረ ዘንቀል።

**ነኮተ** ግ ደቀቀ፥ መሸከ፥ ተሰባበረ።

**ነኳታ** ቅ ደቃቃ፥ ሰባራ።

**አነኮተ** ግ 1. አደቀቀ፥ አመሸከ። 2. እንኩቶ አዘጋጀ።

**እንኩቶ** ስ 1. አረኞች ከብት በሚጠብቁበት አካባቢ ተሰብስበው በአንድነት የሚበሉት ከነአገዳው ወይም ከነብሩ በእሳት ተለብልቦ የበሰለ የአተር ወይም የባቄላ ወይም የገብስ፥... እህል። ቅ 2. (ዘይ.) የማይረባ፥ ምንም ሊፈይድ የማይችል።

***ነወረ**

**ነውር** ቅ 1. በህብረተሰቡ ባህልና እምነት መሰረት እንደ መጥፎ ነገር የሚታይ፥ የሚቆጠር (ድርጊት፥ ምግባር፥...)። ስ 2. ነውር። *ነውርህን ሊታሳይ።*

**ነውር ነው** 1. ፀያፍ ፥ መጥፎ ነው። 2. ተገቢ አይደለም፥ ጥፋት ነው።

**ነውር ጌጡ** ነውር የሆነ ነገር ሲሰራ የማያፍር፥ ይሉኝ አይል(ሰው)።

**ነውረኛ** ቅ መጥፎ ፥ አፀያፊ ምግባር ያለው፤ ባለጌ።

**አነወረ** ግ አጣጣለ፥ አንቋሸሸ፥ ነቀፈ፥ ነውረኛ አደረገ።

**አስነወረ** ግ 1. ነውረኛ አደረገ። 2. አማገጠ፥ አባለገ፥ ደፈረ (ሴትን በግብረ ስጋ)። 3. የሚያስከፋ፥ የሚያስቀይም ሆነ።

**አስነዋሪ** ቅ አፀያፊ፥ አሳፋሪ።

**ነወር(ኖር)** ሰዎች ተቀምጠው ወደ አሉበት ቦታ በመቅረብና ሰላምታ በመስጠት ላይ ላለ ሰው፥ ተቀማጮቹ ብድግ ብለው "ይቀመጡልን" ለማለት ለሰውየው የሚያቀርቡት የአክብሮት መግለጫ ቃል።

**ነወር አለ** ወደአጠገቡ በመምጣት ላይ ያለን ሰው ከመቀመጫው ተነስቶ በአክብሮት ተቀበለ፤ ይቀመጡ ብሎ ጋበዘ።

***ነወጠ**

**ነውጥ** ስ 1. ሁከት፥ ብጥብጥ፥ ሽብር። 2. ርደት፥ ንቅናቄ (የመሬት ነውጥ)።

**ነውጠኛ** ቅ 1. ሁከት ፈጣሪ፥ ረብሸኛ። 2. አሸባሪ።

**ተናወጠ** ግ 1. ተነቃነቀ፥ ራደ። 2. ታወከ፥ ተበጠበጠ፥ ተሸበረ።

**አናወጠ** ግ 1. አራደ፥ አነቃነቀ፥ አንቀጠቀጠ። 2. አወከ፥ በጠበጠ፥ አሸበረ።

**ነዋሪ** "ኗሪ" ን ተመ.

**ነው** (አፍ. **አይደለም**) ግ 1. ምንነትን ወይም ማንነትን፥ መጠንን፥ አይነትን፥ ግብርን፥ ሁኔታን፥... ለመግለፅ ከሚነገሩ ቃላት ጋር እየተጎዳኘ የሚነገር የአሁን ጊዜ የመሆን ግስ። *ኢትዮጵያዊ ነው/ረዥም ነው/ቀይ ነው/ደግ ነው/ጤናማ ነው።* 2. በተወሰነ ስፍራ ወይም ሁኔታ ላይ መሆንን ወይም መገኘትን ለማመልከት ወይም ለማወቅ ከተለያዩ ቃላት ጋር እየተጎዳኘ የሚነገር ቃል። *ሳፈር ላይ ነው/ስብሰባ ላይ ነው።* (በየመደቡ ሲዘረዘር፥– 1ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር " ነኝ"፤ ብዙ ቁጥር "ነን"። 2ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር፥ ተባእታይ ፆታ "ነህ"፤ አንስታይ ፆታ "ነሽ"፤ ብዙ ቁጥር "ናችሁ"። የአክብሮት "ነዎት"። 3ኛ መደብ ነጠላ ቁጥር አንስታይ ፆታ "ናት" (ነች)፤ ብዙ ቁጥር ወይም የአክብሮት "ናቸው")።

**ነውረኛ** "***ነወረ**" ስር ተመ.

**ነውር** ዝ.ከ.

**ነውጠኛ** "***ነወጠ**" ስር ተመ.

**ነውጥ** ዝ.ከ.

**ነዎት** (አፍ. **አይደሉም**) "**ነው**" ን ተመ.

**ነዘረ**[1] ግ 1. በጣት ሲነካኩት ወይም ሲገርፉት ከፍ ያለ ሙዚቃዊ ድምፅ ሰጠ (የበገና ወይም የክራር ጅማት)። 2. ሰውነትን የንዝረት ስሜት ተሰማ። 3. ጠዘጠዘ፥ እየደጋገመ ወጋ (የቁስል ህመም)።

**ንዝረት** ስ ከኤሌክትሪክ ሽቦ ጋር በሚደረግ ያልታሰበ መነካካት ወይም እንደ ክርን ያሉ ገላዎች በሚመቱበት ጊዜ የሚሰማ ሰውነትን የሚወር ድንገተኛና ጊዜያዊ የህመም ስሜት።

**አነዘረ** ግ በመርገብገብ ሙዚቃዊ ድምፅ እንዲፈጠር የበገናን ወይም የክራርን ጅማት በጣቱ ገረፈ፥ መታ።

**ነዘረ**[2] ግ ለመምታት በሰው ወይም በእንስሳ ላይ በትር ወይም ሌላ ጎጂ ነገር አሳረፈ፥ ጣለ።

**ነዘነዘ** ግ 1. ጨቀጨቀ፥ ነተረከ። 2. ደጋግሞ በመጠየቅ፥ በመለመን አሰለቸ፥ አስመረረ። 3. ጠዘጠዘ፥ ነዘረ፥ አመመ(ቁስል)።

**ነዝናዛ** ቅ ጨቅጫቃ፥ አንዴ ነገር ከጀመረ በቶሎ የማይለቅ ፤ ችኮ ።

**ንዝንዝ** ስ ጭቅጭቅ፥ ንትርክ።

**ንዝንዘኛ** ቅ ተጨቃጫቂ፥ ተነታራኪ ።

**ተነዛነዘ** ግ ተጨቃጨቀ፥ ተነታረከ።

**ተነዛናኝ** ቅ ተጨቃጫቂ፥ ተነታራኪ።

**አነዛነዘ** ግ አጨቃጨቀ፥ አነታረከ።

**አነዛናኝ** ቅ አጨቃጫቂ፥ አነታራኪ።

***ነዘዘ**

**ንዛኽ** ስ ትንታ፤ ከሰውነት ጋር ባለመስማማቱ ወይም በሌላ ምክንያት ከተበላና ከተጠጣ በሂላ

ጥቂት ባፍንጫ በኩል በመምጣት ችግር የሚያስከትል ምግብ ወይም መጠጥ።

**አነዘዘ** ግ ተዘቅዝቆ በመተኛት ወይም በሌላ ምክንያት የተበላውና የተጠጣው ባፍንጫ ወጣ።

**ነዛ** ግ 1. ረጨ፥ ፈነጠቀ። 2. የተወሰነን የእህል መጠን በሰማ ምጣድ ላይ በተን አደረገ (ለመቁላት)። 3. አጠፋ፥ ጨረሰ፥ አባከነ (ገንዘብን)። 4. አዛመተ፥ አሰራጨ፥ አዳረሰ (ለምሳሌ ወሬን)። 5. ስምን በከንቱ አነሳ፥ አጠፋ። *ስሜን እየዞረ ነዛው።*

**ንዛት** ስ ምጣድ ላይ በአንድ ጊዜ ለመቆላት የሚችል የተወሰነ የእህል መጠን (ለምሳሌ አንድ ወይም ሁለት እፍኝ ጥሬ)።

**ነዝናዛ** "ነዘነዘ" ስር ተመ.

**ነይ** ግ በሁለተኛ መደብ፥ በነጠላ ቁጥር፥ በአንስታይ ፆታ ጊዜ የሚያገለግል የ"መጣ" ትእዛዝ አንቀፅ። *ላንቺ ቶሎ ነይ።*

**ነይነይ** "ነነዌ" ን ተመ.

**ነደለ** ግ በሳ፥ ሸነቆረ።

**መንደልት** ስ 1. የጆሮ መብሻ። 2. ድጅኖ።

**መንደልቶ** ስ ሰፊ ወይም ትልቅ የጆሮ ሎቲ።

**ነዳላ** ቅ ብስ፥ ሽንቁር፥ ቀዳዳ።

**ተነደለ** ግ ተበሳ፥ ተሸነቆረ፥ ተቀደደ።

**ተነዳደለ** ግ ተበሳሳ፥ ተሸነቋቆረ።

**ነደደ**[1] ግ 1. ተያያዘ፥ ተቃጠለ (እሳት)። 2. ተቃጥሎ አመድ ሆነ። 3. በጣም ሞቀ፥ በሙቀት ሃይል ተሰቃየ።

**ነዲድ** ስ በመቃጠል ላይ ያለ ነገር። (ለምሳሌ እንጨት)።

**ነዳጅ** ስ ሞተርን ለማንቀሳቀስ የሚያገለግል በጋዝ ወይም በቤንዚን መልክ የሚገኝ የሃይል ምንጭ።

**ነድ** ስ የእሳት ነበልባል፥ የእሳት ላንቃ።

**ንዳድ** ስ 1.በጣም ሃይለኛ ሙቀት፥ ቃጠሎ፥ እሳት። 2.ተኩሳት ያለበት ወባ።

**ማንደጃ** ስ 1. እሳትን በቶሎ ለማቀጣጠል የሚረዳ እንደሳር፥ ወረቀት ያለ ተቀጣጣይ ነገር። 2. እሳትን ጎንበስ ብሎ በአፍ እፍ እያሉ በማቀጣጠል ፈንታ ራቅ ብሎ ትንፋሽን በውስጡ ለማሳለፍና በእሳቱ ወላፈን ሳይጎዱ እሳቱን ለማቀጣጠል የሚረዳ፥ ለዚሁ ተብሎ የሚዘጋጅ የሸንበቆ ቁራጭ። 3. እሳት የሚነድበት ቦታ፥ እቃ ወይም እሳቱ የሚቀጣጠልበት ቦታ።

**ምድጃ** ስ 1. ምግብ ለማብሰል እሳት የሚነድበት ቦታ ወይም እሳቱ የሚቀጣጠልበት እቃ። 2. በጋዝ ወይም በኤሌክትሪክ አማካይነት እሳት ለመፍጠር የሚያስችልና ለምግብ ማዘጋጃነት የሚያገለግል እቃ።

**ነደደ**[2] ግ 1. ተበሳጨ፥ በገነ፥ በሸቀ። 2. ተሰቃየ፥ ተጠመደ (በፍቅር)።

**ንዴት** ስ ብስጭት፥ ብግነት፥ ብሽቀት።

**ንዴተኛ** ቅ ብስጩ፥ ቁጡ።

**ተናደደ** ግ ተቆጣ፥ ተበሳጨ፥ በገነ፥ በሸቀ።

**ተናዳጅ** ቅ ብስጩ።

**አናደደ** ግ አስቆጣ፥ አበሳጨ፥ አበገነ፥ አበሸቀ።

**አናዳጅ** ቅ አብሻቂ ፥ አናዳጅ።

**ነደፈ**[1] ግ በደጋን ላይ የተወጠረ ጅማትን በቅል አንገት እየሳበ በማንዘር ለፈትል የሚዘጋጀውን ጥጥ አፍታታ፥ ንድፍ እንዲሆን አደረገ።

**ንድፍ** ስ ከፍሬው ተለይቶ፥ በደጋን ተነድፎና እንደቁልል ደመና በስሱ ተከምሮ የሚገኝ፥ ለፈትል ወይም ለእንዝርት የተዘጋጀ ጥጥ።

**ንድፍ ይመስላል** በጣም ነጭ ነው።

**ነደፈ**[2] ግ በወረቀት ላይ ቀየሰ፤ ፕላን ሰራ፥ ሳለ፥ በገረ።

**ንድፍ** ስ ቢጋር፥ ቅያስ፥ ፕላን።

**ነደፈ**[3] ግ 1. ነከሰ፥ በመርዝ ወጋ (ለምሳሌ እባብ)። 2. ወጋ (በቀስት)። 3. አመመ፥ አሰቃየ (የመጠዝጠዝ፥ የመውጋት፥ የራስ ምታት ስሜት)። 4(ዘይ.)ወጋ፥ ጠቅ አደረገ (በነገር) ።

**ተነደፈ** ግ ተለከፈ፥ ተጠመደ፥ ተመረዘ፥ ተያዘ(በመጥፎ ነገር)።

**ተናደፈ** ግ ወጋ፥ ጠቅ አደረገ።

**ተናዳፊ** ቅ 1. መርዘኛና ተናካሽ የሆነ። 2. (ዘይ.) ተሳዳቢ፥ አሽሙረኛ፥ በነገር ሰውን የሚያስቀይም።

**ነዲድ** "ነደደ[1]" ስር ተመ.

**ነዳ** ግ 1. ወደ አስፈላጊው ቦታ ወሰደ (ለምሳሌ እንስሳትን)። 2. አሽከረከረ፥ ሾፌረ (ለምሳሌ መኪናን)። 3. (ዘይ.) በብዛት አስቀመጠ (ተቅማጥ)።

**መናጆ** ስ 1. ብቻውን በመሆኑ እየደነበረ በጉዞ ላይ ችግር ለሚፈጥር አዋኪ ከብት፥ እንደአጃቢ ሆኖ አብሮ እንዲሄድ የሚደረግ ገራም ከብት። 2. ከሌላው ጋር አብሮ ወይም ሌላውን አጅቦ የሚሄድ፤ አካሂያጅ (ሰው)።

**መንጃ ፈቃድ** ስ በማሽከርከር ሙያ ለሰለጠነ ሰው የሚሰጥ የሙያ ብቃት ማስረጃ።

**ነጅ(ነጂ)** ስ 1. እረኛ፤ ወዲያና ወዲህ የሚሄዱ ከብቶችን የሚከተል፥ የሚጠብቅ። 2. ሾፌር፤ አሽከርካሪ።

**ተነዳ** ግ 1. ተወሰደ፥ እንዲሄድ ተደረገ(ከብት)። 2. (ዘይ.) በሌላ ሰው ሃሳብ ተመራ።

**ነዳላ** "ነደለ" ስር ተመ.

**ነዳይ**(ብ.ቁ.**ነዳያን**) ስ ተመፅዋች፥ ድሃ።

**ነዳጅ** "**ነደደ**[1]"ስር ተመ

**ነድ**[1] ዝ.ከ.

**ነድ**[2] (**ነድ ቀለም**) ስ ፍም የሚመስል የቀይ ቀለም አይነት።

**ነድ**[3] ስ እሳት የሚመስል ቀይ ዶቃ።

**ነዶ** ስ ከነብርኡ (ከነአገዳው) እየታጨደና ሁለት ሁለት ወይም ሶስት ሶስት ጭብጥ በአንድነት እየተደረገ የታሰረ እንደገብስ፥ ስንዴ፥... ያለ የእህል ሰብል።

**ነጅ**(**ነጂ**) "**ነዳ**" ስር ተመ.

**ነገ** "**ነጋ**" ስር ተመ.

**ነገለ** ግ ከስሩ ተነቀለ፥ ተመነገለ።

**ነገረ** ግ በአእምሮው የያዘውን ወይም ያሰበውን ለሌላው ገለፀ፥ አሰማ፥ አሳወቀ።

**ነገረለት** 1.መልእክት አደረሰለት። 2. መሰከረለት ፥ በምስክርነት ረዳው (ረቺ፡ አሸናፊ እንዲሆን)።

**ነገረበት** 1. አወራበት፡ ለሌላ አሰማበት። 2. መሰከረበት፥ ተረቺ ወይም ተሸናፊ አደረገው።

**ነገረው** 1. አስረዳው። 2. ሰደበው፡ አዋረደው። *ልክ ልኩን ነገረው።*

**ነግሬሃለሁ** የቁጣ፥ የዛቻ፡ የማስጠንቀቂያ ሃሳብ መግለጫ ቃል። *ነግሬሃለሁ ከፊቴ ሂድ።*

**ነገረ ሰሪ** ቅ አሳባቂ፥ ሸውከኛ፡ አዋሻኪ።

**ነገረ ሰይጣን** ቅ ክፉ አሳቢ፡ ተንኮለኛ።

**ነገረ ስራ** ስ ሁኔታ፡ አኳኋን። *ነገረ ስራው አላማረኝም።*

**ነገረ በላ** ቅ 1. ነገር የሚያመነሽክ፡ የሚያብሰለስል። 2. ነገር ወዳድ፡ ነገረኛ። 3. ሙግት አዋቂ።

**ነገረ ዘርቅ** ስ ቁምነገር የሌለው ሧልት፡ ፌዝ፡ ቀልድ።

**ነገረፈጅ** ስ ጠበቃ፡ ተሟጋች፡ አቡካቶ።

**ነገር** ስ 1. ድርጊት፡ ስራ፡ ተግባር። *አይ የሰው ነገር!* 2. ሁኔታ፡ አኳኋን። *ነገሩ አላማረኝም።* 3 ጉዳይ። *ያ ነገር ከምን ደረሰ?* 4. ምክንያት፡ ጉዳይ። *ያለ አንድ ነገር ድንገት አገር ለቆ አይሄድም ነበር።* 5. ሙግት፡ ክርክር። *ፍርድ ቤት ነገር አለብኝ።* 6. ጠብ፡ ጭቅጭቅ፡ ንትርክ። *ነገር አያጣውም።* 7. ወሬ፡ ዜና። *የሰማሁት ነገር አለ።* 8. በስም ያልተጠቀሰ እቃን ወይም ጉዳይን እየተካ የሚነገር ቃል። *አንድ ነገር እገዛልሃለሁ።*

**በነገር ጎሸመ** ሌላውን ሰው ሊያስቀይም ወይም ሊያስቆጣ የሚችል ነገር በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ወይም በአግቦ ተናገረ።

**በነገር ጠለፈ/አጠመደ** 1. በንግግሩ፡ በምክሩ፡...ሌላውን አሳሳተ፡ ስህተት ላይ ጣለ። 2. አንዱ የተናገረውን አጣሞ በመተርጎም ሌላ አቅጣጫ እንዲይዝ አደረገ፡ ወነጀለ።

**ነገሩ በሰለ** በሚገባ ተብላላ፡ ለፍፃሜ ተቃረበ።

**ነገር ለኮሰ** ጥል እንዲፈጠር አደረገ፥ ጠብ ቀሰቀሰ።

**ነገር ሰራ** አሳበቀ፥ አዋሸከ፡ አጣላ።

**ነገር ቆሰቆሰ/ጫረ** ጠብ ጫረ፥ ነገር አነሳሳ።

**ነገር ቋጠረ** 1. ዶለተ፥ አሴረ፡ ክፉ ነገር አሰበ። 2. ክፉ ምክር ጠነሰሰ።

**ነገር በሆዱ ይዟል** ቂም ይዟል፥ ተቀይሟል።

**ነገር ተወለደ** ያልታሰበ ችግር ተፈጠረ።

**ነገር ነገሩን ይዞታል** ከሞላ ጎደል ስለ ጉዳዩ ያውቃል፡ ስለ ሁኔታው በመጠኑ ተገንዝቧል፥ ለመሆን ወይም ለመምሰል ሞክሯል።

**ነገር አለሙን ትቶታል** ለማንኛውም ጉዳይ ግዴለሽ ሆኗል።

**ነገር አመላለሰ** አሳበቀ፡ ያንዱን ነገር ለሌላው ነገረ።

**ነገር አረገዘ** ቂም ያዘ።

**ነገር አስከረው** በነገር ብስጭትና ንዴት ምክንያት ራሱን መቆጣጠር ተሳነው፡ እንደሰከረ ሰው ሆነ።

**ነገር አቡኪ** ነገር የሚያባብስ ፡ የሚያጣላ፡ ነገር ወዲያና ወዲህ በማመላለስ ሰዎችን የሚያጋጭ።

**ነገር አታባዳ** (ነውር) ያንዱን ለሌላው እየነገርክ ሰው አታጣላ ፡ አታፋጅ።

**ነገር አወጣ** ምስጢር አወጣ፡ ተናገረ።

**ነገር አወጣ አወረደ** አሰላሰለ።

**ነገር አዞረ** በቀጥታ የተነገረውን ሃሳብ በሌላ ተረጎመ፡ ወደ አልታሰበበት አቅጣጫ ለወጠ፥ ጠመዘዘ።

**ነገር አጥባቂ** ቅ ማንኛውም ጉዳይ በጥንቃቄ የሚይዝ፡ በቀላሉ የማይተው።

**ነገር ገመደ/ሸረበ/ጎነጎነ/ፈተለ** 1. አሴረ፥ ዶለተ። 2. አንድን ነገር ወይም ጉዳይ በቀና መንፈስ በማየት ፈንታ ልዩ ልዩ ትርጉም በመስጠት ቀላል የነበረው ከባድ፥ ቀና የነበረው የተወሳሰበና አስቸጋሪ እንዲሆን አደረገ።

**ነገር ጎተተ** 1. ያልታሰበ ነገር(ችግር) ውስጥ ገባ፡ ነገር አመጣ። 2. ነገር ቶሎ አልቆርጥ አለ።

**ነገር ፈለገ** ነገር ጫረ።

**ነገርን ነገር ያነሳዋል** ስለ አንድ ነገር ሲወራ ወይም ሲወሳ ሌላው ነገር ትዝ ይላል።

**ነገር ሸራቢ** ቅ አድመኛ፥ ሴረኛ፥ ነገር ጠምዛዥ።

**ነገር ቀማሚ** ቅ ነገር አዋቂ፥ አሳማሪ፥ ምክር አዋቂ።

**ነገር አሸታች** ቅ ጠብ ፈላጊ፥ ጥል ወደ አለበት የሚሳብ።

**ነገር ወዳድ** ቅ ጠብ ወዳጅ፥ ነገረኛ።

**ነገር የበላ** ቅ 1. ነገር አዋቂ፥ አስተዋይ፥ አመዛዛኝ፥ ብዙ የሚያውቅ። 2. ነገረኛ።

**[ነገር] ግን** መና. የመጀመሪያውን ሃሳብ ከሚቀጥለው ጋር ለማወዳደር ወይም በተቃራኒው አንፃር ለመግለፅ የሚያገለግል። *ስራቸው አድካሚ ነው፤ ነገር ግን ክፍያቸው ዝቀተኛ ነው /እሱ ይወዳታል፤ ነገር ግን እሷ ትጠላዋለች/የሚልህን አድምጥ፤ ነገር ግን አትመነው።*

**ነገር ጠምዛዥ** ቅ በቀና መንፈስ ግልፅና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ለሚቀርበው ሃሳብ ሁሉ ተቃራኒ የሆነ ትርጉም የሚሰጥ፥ ጠማማ፥ ተንኮለኛ።

**በነገራችን ላይ** በጭውውት ጊዜ ሌላ ጉዳይ በጣልቃ አስገብቶ ለመናገር ሲያስፈልግ እንደ ይቅርታ መጠየቂያ በማድረግ ተናጋሪው ለአድማጭ የሚያሰማው ቃል።

**የነገር መንገድ** የነገር ስልት፥ የነገር አያያዝ።

**የነገር አባት** ስ ባልና ሚስት በሚጋቡበት ጊዜ ከእያንዳንዳቸው በኩል የሚቀርብና በውለታው ላይ የሚገኝ፥ አለመግባባት በሚፈጠርበት ጊዜ ለቆመለት ወገን የሚከራከር ሰው።

**የነገር ስም** ስ (ሰዋ.) ከንግግር ክፍሎች ውስጥ ረቂቅ የሆኑ ስሞች፥ (ለምሳሌ ነፃነት፥ ብርሃን፥...) የሚጠሩበት የስም አይነት።

**የነገር ቋት** ስ ወሬኛ፥ ነገረኛ።

**ነገረተኛ** ሙግት፥ ክርክር ያለበት ሰው።

**ነገረኛ** ቅ 1. ጠብ ጫሪ፥ ተንኮለኛ። 2. ምላሰኛ።

**ንግ̈ር(ንግ̈ርት)** ስ አንድ ድርጊት (ከመፈፀሙ በፊት) ወደፊት እንደሚፈፀም በቅድሚያ የተነገረ ሃሳብ፤ ትንቢት።

**ንግ̈ረኛ(ንግ̈ርተኛ)** ወደፊት ስለሚሆነው ነገር አስቀድሞ የተነገረለት፥ የተወራለት፥ እንዲህ እንዲህ ይሆናል የተባለለት (ሰው)።

**ንግግር** ስ 1 አንድ ተናጋሪ ለአድማጭ በቃል የሚያቀርበው ሃሳብ፥ መልእክት፥ አስተያየት፥...። 2. በሰዎች መካከል የሚደረግ። የቃል ጭውውት፥ የሃሳብ ልውውጥ። 3. ጭቅጭቅ፥ ንትርክ። *ያ ጉዳይ በቶሎ የማይፈፀም ከሆነ ከንግግር እንዳያደርሰን እሰጋለሁ።*

**ንግግር አያውቅም** 1. ሃሳቡን በሚገባ የመግለፅ ችሎታ የለውም። 2. ቃላት ሳይመርጥ አፉ እንዳመጣለት ስለሚናገር ነገር ያበላሻል።

**ንግግር አደረገ** ስ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ላይ ስለ አንድ ጉዳይ በቃል ወይም በፅሁፍ ሃሳብ፥ መግለጫ፥ ማስረጃ፥... አቀረበ፥ ሰጠ።

**የንግግር ቋንቋ** ስ 1. ያደባባይ ያልሆነ፥ በንግግር ላይ ብቻ የሚያገለግል ቃል።2. ገና በፅሁፍ ላይ ያልዋለ ቋንቋ።

**ተነገረ** ግ ተባለ፤ መልእክት፥ ሃሳብ ተላለፈ።

**ተነገረው** ተረዳ፥ ሰማ። *ያባቱ ሞት ተነገረው።*

**የተነገረለት** እውቅ፥ የታወቀ።

**ትንግርት** ስ ጉድ፥ ድንቅ፤ ተአምር።

**ትንግርተኛ** ቅ ተአምረኛ።

**ተነጋገረ** ግ 1. ተወያየ፥ ሃሳብ ለሃሳብ ተለዋወጠ። 2. ተጫዋወተ፥ አወራ። 3. ተዋዋለ። *ቤቴን እንዲያድስልኝ ከመሃንዲስ ጋር ተነጋግሬያለሁ።* 4. ተጣላ፥ ተጨቃጨቀ። *ክፉና ደግ ተነጋገሩ።* 5. ታረቀ። *ተጣርፈው የነበሩት ተነጋገሩ።*

**ተናገረ** ግ 1.ሃሳቡን ገለፀ፥ አሰማ። 2. አወራ፥ ለፈለፈ። 3. አሳበቀ። 4. ተቆጣ፥ አስቀየመ፥ አስከፋ።

**ተናጋሪ** ቅ 1. ንግግር አዋቂ፥ ጥሩ የንግግር ችሎታ ያለው። ስ 2. ንግግር አድራጊ። 3. (ዘይ.) ምላሰኛ፥ ለፍላፊ፥ በንግግሩ ሰውን የሚያስቀይም፤ ተሳዳቢ።

**አነጋገረ** ግ 1. አጫዋወተ፥ አወራ። 2. ጠየቀ፥ ሃሳብ ተለዋወጠ። *ስለህመሙ ሃኪም አነጋግሯል።* 3. በቋንቋ የማይግባቡ ሰዎች በእሱ አስተርጓሚነት ሃሳብ እንዲለዋወጡ፥ እንዲግባቡ አደረገ። 4 አገናኘ፥ አስማማ፤ አዋዋለ። *ጉዳይህን በቶሎ ሊፈፅምልህ የሚችል ጠበቃ ፈልጌ አነጋግርሃለሁ።* 5. አነታረከ፥ አጨቃጨቀ። *እኔ ካንተ ጋር ምን አነጋገረኝ ያደረግከውን ለሚመለከተው አሳውቃለሁ።*

**አነጋጋሪ** ቅ 1. አጠያያቂ፥ የሚያወያይ (ነገር፥ ሃሳብ)። ስ 2. አጫዋች፥ ጓደኛ።3. አስተርጓሚ።

**አናገረ** ግ 1. ጠየቀ፥ አወያየ። 2. አስቀባጠረ፥ አስለፈለፈ።

**አናጋሪ** ቅ 1. አስቀባጣሪ፥ አስለፍላፊ። 2. ክፉ ተናግሮ የሚያናግር፥ ተንኮለኛ፥ አሳሳች። *ተናግሮ አናጋሪን ያዝልን።*

**አስነገረ** ግ 1. አሳወጀ። 2. ንግርት ጠየቀ። 3. አስጠነቆለ። 4. (ቤ.ክህ.) የተማሪዎችን ቅኔ እየሰማ አረመ፥ አስተካከለ፥ አስተማረ። ፣

**ነገሰ** ግ 1. ዘውድ በመጫን የሃገር መሪ ሆነ፥ ዙፋን ላይ ተቀመጠ። 2. (ታቦት) በአመት በአሉ

ቀን ወደ ውጪ ወጥቶ ቤተክርስቲያኑን ዞሮ ገባ:: 3. አየለ፥ ገነነ::

**መንግስት** (ብ.ቁ.**መንግሥታት**) ስ 1. የአንድ አገር ህዝብና የግዛት ስርአት:: 2. የአንድ አገር ህዝብና ግዛት፣ መስተዳድር::

**መንግስት ግልበጣ** ስ አንድን መንግስት፥ መስተዳድር በሃይል ከስልጣን ማስወገድ፣ መፈንቅለ መንግስት፣ ኩዴታ::

**መንግስተ ሰማይ(መንግስተ ሰማያት)** ስ (ሃይ.) ከሞት በሂላ ፃድቃን (ደገኞች) የሚኖሩባት ናት ተብሎ የሚታመንባት ሰማያዊት ቦታ::

**ነገስት** "**ንጉስ**" ን ተመ.

**ነጋሢ** ቅ 1. ነጋሽ፥የነገሰ፥ የሚነግስ:: ስ 2. ንጉስ ወይም የንጉስ ልጅ::

**ንጉስ** (ብ.ቁ. **ነገስት፥ ነገስታት**) ስ 1. በዘውዳዊ አስተዳደር ዙፋን ላይ የተቀመጠ የሃገር መሪ:: 2.በአንድ ቡድን ውስጥ ዋነኛ መሪ:: *አንበሳ የአራዊት ንጉስ ነው::* 3. እንደ ሰንጠረዥ፥ ዳማ፥ ካርታ ባሉ መጫወቻዎች ውስጥ ከመጫወቻዎቹ ጠጠሮች ወይም ካርታዎች የአንዱ መጠሪያ::

**ንግስት** (ብ.ቁ. **ንግስታት**) ስ 1 በዘውዳዊ አስተዳደር ዙፋን ላይ የተቀመጠች የሃገር መሪ:: 2. የንጉስ ሚስት:: 3. በሰንጠረዥ መጫወቻና በካርታ ውስጥ የአንደኛው መጫወቻ መጠሪያ:: 4.የንብ አውራ::

**ንጉስነገስት** ስ ለእርሱ የሚገብሩ፥ ትእዛዙን የሚቀበሉና በእርሱ ግዛት ስር በንጉስነት ማእረግ ላሉ ንጉሶች የበላይ የሆነ፥ የንጉሶች ንጉስ::

**ንጉሳዊ**(ብ.ቁ.**ንጉሳውያን**) ቅ የንጉስ::

**ንግስ** ስ ታቦት የሚወጣበት ክብረበአል::

**መናገሻ ከተማ** ስ 1. የአንድ አገር መሪ መኖሪያና የአገሪቱ ዋና ከተማ:: 2. የንጉሱ የንግስና ስርአት የሚካሄድበትና ንጉሱ የሚኖርበት ከተማ::

**አነገሰ** ግ 1. የታቦት በአል በሚከበርበት ቦታ ተገኝቶ የበአሉ ተካፋይ ሆነ:: 2. አጋነነ:: 3. አኩራራ፥ አተበተ፥ ትእቢተኛ እንዲሆንና አጉል አስተሳሰብ እንዲያድርበት ተገቢ ባልሆነ መስመር መራ፥ አሳደገ፥...::

**አንጋሽ** ስ 1. የንጉስ የንግስና ስነስርአት በሚፈፀምበት ጊዜ ንጉሱን ቀብቶ የሚያነግስና ስነስርአቱን የሚመራ ካህን ወይም ጳጳስ::2. የታቦት ክብረ በአል በሚደረግበት ቦታ ተገኝቶ የበአሉ ተሳታፊ የሆነ ህዝብ:: 3. አጋናኝ:: *ወሬ አንጋሽ:*

**አነጋገሰ** ግ አሞጋገሰ፥ አሞካሸ፥ አዳነቀ::

**ነገነገ** ግ ከመረ፥ ደረደረ፥ ቆለለ::

***ነገነገ**[1]

**አነገነገ** ግ ወፈር ባለና አስፈሪ በሆነ ድምፅ ጮሁ፥ የጩሀት፥ የጉምርምታ ድምፅ አሰማ (የነብር፥ የአንበሳ፥...)::

***ነገነገ**[2]

**አነገነገ** ግ ተነቃነቀ::

**ነገደ** ግ 1. የንግድ ስራ ሰራ፥ አካሄደ:: 2. በመደብር ውስጥ ሆኖ ወይም ገበያ ወጥቶ ሸጠ፥ ሸቀጠ::

**መነገጃ** ስ ለንግድ ስራ የሚያገለግል ማንቀሳቀሻ ገንዘብ::

**ነጋዴ** ስ በንግድ ስራ የሚተዳደር ሰው::

**ንግድ** ስ ትርፍ ለማግኘት ሲባል ሸቀጦችን የመግዛትና የመሸጥ፥ አገልግሎት የመስጠት፥ የማምረት ወይም ሸቀጥን በሸቀጥ የመለወጥ ስራ::

**ንግድ ምክር ቤት** ስ የአንድን አገር የንግድ እንቅስቃሴ ለማበረታት፥ እንቅፋቶችን ለማስወገድና አመቺ ሁኔታዎች ለመፍጠር፥ በንግድ ስራ ላይ በተሰማሩ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች የሚቋቋም ማህበር::

**የንግድ ልውውጥ** ስ በአገሮች መካከል የሚካሄድ የተለያዩ ምርቶችን የመግዛትና የመሸጥ ተግባር::

***ነገደ**

**እንግዳ** ስ 1. ያልዋለ፥ ያላደረ ወይም ያልሰነበተ፥ ከሌላ አካባቢ፥ አገር፥ ቤት፥... የመጣ ሰው:: ቅ 2. ባይተዋር፥ ባእድ:: 3. አዲስ የመጣ ወይም ለአካባቢው አዲስ የሆነ::

**እንግዳ መቀበያ** ስ 1. የእንግዳ ማረፊያ ወይም መቆያ ክፍል፥ ቤት፥ ቦታ:: 2. ለእንግዳ መቀበያ የሚሆን ወይም የሚያገለግል (የክት ልብስ፥ ገንዘብ)፥...)::

**እንግዳ ተቀባይ** ቅ እንግዳ ወዳድ፥ ተንከባካቢ፥ አስተናጋጅ (በመጋበዝ፥ በማጫወት፥...)::

**እንግዳ ነገር** ስ ቀደም ብሎ ያልተሰማ፥ ያልታሰበ፥ ያልተጠረጠረ ድንገተኛ ነገር::

**እንግዳ ደራሽ** ስ ሳይታሰብ ድንገት የመጣ እንግዳ::

**እንግዳ ጎርብጥ** ስ እንደ ምንጣፍ የሚያገለግል ያልተለፋ ደረቅ የከብት ቆዳ::

**ተስተናገደ** ግ 1. በእንግድነት ተጋበዘ፥ መስተንግዶ ተደረገለት:: 2. የሚፈልገው ጉዳይ እንዲፈፀምለት ተደረገ::

**መስተንግዶ** ስ 1. ተጠርቶ ወይም ሳይጠራ በእንግድነት ለመጣ ሰው የሚደረግ ግብዣ:: 2. እንግዳ አቀባበል፣ የእንግዳ አቀባበል ስነስርአት::

**አስተናገደ**[1] ግ 1. በእንግድነት ተቀብሎ ጋበዘ:: 2. አስተናበረ፥ ባለጉዳይን በመቀበል አስፈላጊውን ስራ አከናወነ::

**አስተናጋጅ** ቅ 1. እንግዳ የሚቀበል፥

የሚጋብዝ። ስ 2. አስተናባሪ።

**ነገድ** ስ በባህል፥ በኢኮኖሚና በአካባቢ ደዙታ አንድነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ያለው፣ ከጎሳ ይልቅ መጠኑ ሰፊ የሆነ ማህበረ ሰብ።

**ነጉላ** "*ነጎለ" ስር ተመ.

**ነጋ** ግ 1. ሌሊቱ አልቆ ብርሃን ተተካ፥ ወገግ አለ፥ ጎህ ቀደደ። 2. አለፈ፥ ወጣ። *ክረምቱ ሲነጋ እንመጣለን።*

**ነገ(ነግ)** ስ 1. ማግስት፥ ከዛሬ ቀጥሎ ያለው ቀን።

**ነገ ዛሬ አለ** አንድን ድርጊት በጊዜው አልፈፀም አለ፥ አዘገየ፥ ቀጠሮ አራዘመ።

**ነግ በኔ አለ** ነገሩ በእኔም ላይ ሊደርስ ይችላል ብሎ አሰበ።

**ከነገ ነገ አለ** አዘገየ፥ ቀን አልቆርጥ አለ፥ ጊዜ አጠፋ።

**በነጋታው (በበነጋው)** በማግስቱ፥ በሚቀጥለው፥ በሁለተኛው ቀን።

**ከነገ በስቲያ** ከነገ ቀጥሎ ያለው ቀን።

**ከነገ ወዲያ** ዝ.ከ.

**ነጋ ጠባ** ዘወትር፥ ሁልጊዜ።

**ነግህ** ስ ጧት፥ ማለዳ።

**ንጋት** ዝ.ከ.

**ነጋጋ** ግ ንጋት ተቃረበ፥ ጨለማው እየለቀቀ ሄደ።

**አነጋ** ግ 1. አንድ ቦታ ሆኖ አሳለፈ(ሌሊትን፥ ክረምትን)። 2. እንቅልፍ ሳይወስደው አደረ፥ ሳይተኛ ቀረ።

***ነጋ**

**ንግ** ቅ ሊወልቅ፥ ሊላቀቅ የደረሰ፥ እንከን ያጋጠመው፥ መዛባት የደረሰበት (የአጥንት መጋጠሚያ ወይም የማንኛውም አካል መገጣጠሚያ)።

**ተናጋ** ግ መጀመሪያ ከነበረው ስራቱ (አፈጣጠሩ) ተፋለሰ፥ ተነቃነቀ፥ ተናወጠ።

**አናጋ** ግ አናወጠ፥ አነቃነቀ።

**ነጋሪት** ስ እንደ ዋርካ፥ ዋንዛ፥...ካሉ የዛፍ ግንድ ቁራጭ ተፈልፍሎ የሚሰራ ጎኑ ሰፊ፥ ቁመተ አጭር የሆነና በአዋጅ፥ በዘመቻ፥...ጊዜ ይጎሰም የነበረ የከበሮ አይነት (ስእሉን የሙዚቃ መሳሪያ ስር ተመ.)።

**ነጋሪት ጋዜጣ** ስ የመንግስት አዋጆች የሚወጡበት ጋዜጣ።

**ነጋሲ** "ነገሰ" ስር ተመ.

**ነጋዴ** "ነገደ" ስር ተመ.

**ነጋድራስ** ስ 1. በመንግስት ይሾም የነበረ የቀድሞ ጊዜ የነጋዴዎች ተቆጣጣሪ፥ አለቃ። 2. ከንግድ ዘርፍ የሚገኘውን የመንግስት ግብር ይሰበስብ የነበረ ሹም።

**ነጋጋ** "ነጋ" ስር ተመ.

**ነግ** "ነጋ" ስር "ነገ" ን ተመ.

**ነግህ** ዝ.ከ.

***ነጎለ**

**ነጉላ** ቅ ሞኝ፥ ጅል።

**ነጎል** ስ ንፍጥ።

**አነጎለ** ግ (ንፍጥን) አፈረጠ፥ አወጣ፣ ተናፈጠ።

**ነጎረ** ግ በእሳት ቀልጦና ውሃ ተጨምሮበት ከቆሻሻው እንዲለይ ተደረገ (ቅቤ)።

**ንጉር** ቅ እንዲቀልጥ ተደርጎና ውሃ ተጨምሮበት ከቆሻሻ የፀዳ (ቅቤ)።

**ንጉር ቅቤ** ስ ከቆሻሻ የፀዳና የተነጠረ ቅቤ።

**አነጎረ** ግ ቅቤን በእሳት አቅልጦና ውሃ ጨምሮበት በማሰንበት ቆሻሻው ከውሃው ጋር እንዲወገድ አደረገ።

***ነጎተ**

**እንጎቻ** ስ መጠኑ አነስተኛ እንዲሆን ተደርጎ የሚጋገር እንጀራ።

**ተነጎተ** ግ እንጎቻ ተጋገረ።

**አነጎተ** ግ እንጎቻ ጋገረ።

**አስነጎተ** ግ እንጎቻ አስጋገረ።

**ነጎደ**[1] ግ ሄደ፥ ተጓዘ፥ እልም አለ።

**ነጎዴ(ነጎድ)** ስ 1. አንድ ላይ ግር ብሎ የሚበር የወፍ አይነት፣ መቁ። 2. ከጦርነት በታ እየሸሸ የሚመለስ ብዛት ያለው ጀሌ ጦር።

**አነጎደ** ግ አስኬደ፥ በብዛት አካናወነ፥ አጣደፈ (ስራን)።

**ነጎደ**[2] ግ ተመታ።

**አነጎደ** ግ በሃይል መታ።

**ነጎዴ** "ነጎደ[1]" ስር ተመ.

**ነጎድጓድ** "*ጎደጎደ" ስር ተመ.

**ነኻ** ግ 1. ኻ፥ ዱ አለ፥ ጮሀ (ጅራፍ፥ ፍንዳታ ፥...)። 2. ኻ፥ዱ የሚል ድምፅ በመፍጠር ተሰበረ።

**አነኻ** ግ 1. አጮሀ፥ አፈነዳ። 2. ሰበረ፥ ሲሰብር ኻ፥ ዱ የሚል ድምፅ አሰማ።

**ነጠለ** ግ 1. ለየ፥ ለየብቻ አደረገ። 2. ዘረጋ። *የታጠፈውን ነጥለው።*

**ነጠላ** ስ 1. ከድርና ማግ የሚሰራ፥ እንደ ጋቢ እጥፍ ያልሆነ ሸማ። 2. እጥፍ፣ ድርብ፥ መንታ ያልሆነ ነገር። ቅ 3. ከከኑ እጥፍ ያልሆነ (ዶሮ)። 4. (ዘይ.) ጥላቢስ፥ ከውካዋ።

**ነጠላ ሰረዝ** ስ በዝርዝር የሚፃፉ ነገሮችን ለመለያየት የሚያገለግል የስርአተ ነጥብ አይነት፤ ምልክቱም "፥" ወይም "፣" ነው (ለምሳሌ ጤፍ፥ ስንዴ፥ ገብስ፥...)።

**ነጠላ ቁጥር** (ሰዋ.) አንድ ብቻውን የሚገኝ ነገር ወይም አካል ብዙነት ካለው ነገር ወይም አካል ተለይቶ የሚጠራበት የቅርፅ ስም። ለምሳሌ "የበጎች" ነጠላ ቁጥር "በግ" የሚለው የስም ቅርፅ ነው።

**ነጠላ አረፍተ ነገር** ስ (ሰዋ.) አንድ ባለቤትና አንድ አንቀፅ ብቻ የሚገኝበት አረፍተ ነገር። ለምሳሌ "ልጁ አድጓል" የሚለው ነጠላ አረፍተ ነገር ነው።

**ነጠላ ጫማ** ስ ሽፍን ያልሆነና ተረከዝ የሌለው፥ ብዙውን ጊዜ ለቤት ውስጥ የሚያገለግል የጫማ አይነት።

**ንጣይ** ቅ ነጠላ የሆነ፥ ብቻውን ያለ።

**ንጥል** ዝ.ከ.

**ተነጠለ**[1] ግ 1. ተለየ፥ ተከፈለ፥ ተለይቶ ለብቻ ሆነ። 2. ተዘረጋ።

**ተነጠለ**[2] ግ ተለያየ።

**ተናጣላ** ቅ ብቸኛ፥ ብቻውን የሆነ።

**ተናጣላ ሆነ** ግ 1. ብቸኛ ሆነ። 2. ከስራ ተለየ፥ ራቀ። 3. ሳሳ፥ አልፎ አልፎ ብቻ ሆነ (ቡቃያ፥ ፀጉር፥...)።

**በተናጠል** ተው.ግ. ለየብቻ።

**አነጣጠለ** ግ አለያየ።

**ነጠረ**[1] ግ 1. ጠራ፥ ንፁህ ሆነ፥ የሚፈለገው ነገር ከማይፈለገው ተለይቶ እንዲወጣ ተደረገ፥ በእሳት ቀልጦ ተጣራ (ቅቤ፥ ብረት፥...)። 2. ትክክለኛው ነገር ታወቀ፥ ተረጋገጠ። *እውነቱ ነጥሮ ወጣ*።

**ነጥሮ ወጣ** ችግርን፥ መከራን ተቋቁሞ አለፈ፥ ታግሎ አሸነፈ።

**ንጣሪ** ቅ የቅቤ አር፥ ዝቃጭ።

**ንጥር** ቅ የጠራ፥ ከቆሻሻ ወይም ከማይፈልግ ነገር የተለየ (ቅቤ፥ ማር፥...)።

**አንጣሪ** ቅ ከብር፥ ከወርቅ፥... የተለያዩ ጌጣጌጦችን የሚሰራ ባለሙያ።

**አንጥረኛ** ዝ.ከ.

**ነጠረ**[2] ግ መሬት ነክቶ ወደላይ ዘለለ፥ ናረ፥ ጓነ (ለምሳሌ ኳስ)።

**ንጥር ንጥር አለ** ግ ናር ናር አለ፤ የቁጣ አረማመድ ተራመደ።

***ነጠረ**

**ተነጣጠረ** ግ ከዳኛ ፊት ቀርቦ ከባላጋራው ጋር ተከራከረ፥ ተሟገተ።

**ተነጣጣሪ** ቅ ክርክር፥ ሙግት ያለበት፥ ባለጉዳይ።

**አነጣጠረ** ግ 1. አሟገተ፥ አከራከረ፤ የከሳሽንና የተከሳሽን ማስረጃዎች አነፃፀረ፥ መረመረ፥ አመዛዘነ። 2. አለመ፥ አዘገበ፥ ኢላማ አስተካከለ።

**አነጣጣሪ** ቅ አስተካክሎ ኢላማውን መምታት የሚችል ፤ ተኳሽ።

**ነጠረቀ** ግ በሃይል መታ።

***ነጠሰ**

**እንጥስታ(ንጥሻ)** ስ በጉንፋን ወይም እንደበርበሬ ባሉና የሚሰነፍጥ ሽታ ባላቸው ነገሮች ምክንያት ከውሃ አዘል አየር ጋር ከአፍንጫ ውስጥ በከፍተኛ ሃይል ተገፍቶ የሚወጣ ድምፅ።

**እንጥስ አለ** ግ አነጠሰ።

**አነጠሰ** ግ በጉንፋን፥ አፍንጫን በሚሰረስር ወይም በሚሰነፍጥ ሽታ ምክንያት ውሃ አዘል አየር ወይም እስትንፋስ ከአፍንጫው ድንገት በሃይል አስወጣ፥ የእንጥስታ ድምፅ አሰማ።

**አስነጠሰ** ግ 1. አነጠሰ። 2. ለማነጥስ ምክንያት ሆነ።

**ነጠቀ** ግ 1. ቀማ፥ ወሰደ። 2. በብርጭቆ አገመ (ትንሽ ውሃና ጥጥ ከብርጭቆ ውስጥ አድርጎና ጥጡን በእሳት ለኩሶ ብርጭቆውን ወዲያውኑ የህመም ስሜት ባለበት አካል ላይ በመድፋትና ቆየት ብሎም ብርጭቆውን መንጭቆ በማንሳት)።

**ነጣቂ** ቅ ቀማኛ።

**ንጥቂያ** ስ ቅሚያ፥ ዝርፊያ።

**ነጠቅ ነጠቅ አለ** ግ ፈጠን ፈጠን አለ (በአካሄድ፥ በአነጋገር)።

**ተነጠቀ** ግ 1. ወደ ሰማይ ወጣ፥ አረገ ። *ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን*። 2. ተሳበ፥ ተመሰጠ።

**ተናጠቀ** ግ 1. ነጠቀ። 2. ተሻማ።

**አናጠቀ** ግ አሻማ።

**ነጠበ** ግ 1. ጠብ አለ፤ ወደቀ። 2. ተሳተ፥ ተገደፈ፤ አመለጠ (ነገር ወይም ቃል ከአንደበት)።

**ነጥብ** ስ 1. አንድን ቃል ከሌላው ቃል ለመለየት በቃላት መካከል የሚደረግ የቀለም ጠብታ ምልክት (፡) ። 2. ፍሬ ነገር። *ነጥብ ነጥቡን ብቻ ንገረን።*

**ነጠብጣብ** ስ 1. በቅደም ተከተል በተራ የተቀመጠ የቀለም ጠብታ ምልክት (....)። 2. የፈሳሽ ጠብታዎች ወይም አነስተኛ ካፊያ።

**ተናጠበ** ግ የጀመረውን ሳይጨርስ በመካከል እንዲያቋርጥ ሆነ።

**ተንጠባጠበ** ግ 1. መዝነብ ጀመረ፥ ዝናቡ

ጠብ ጠብ አለ። 2. በየቦታው ወደቀ፥ ተዝረከረከ።

**አነጠበ** ግ ነጥብ አደረገ፣ ሰራ፥ ፃፈ።

**አናጠበ** ግ በጣልቃ ገብቶ አቋረጠ፥ አደናቀፈ (ስራን፥ ነገርን)።

**አንጠባጠበ** ግ 1. መዝነብ ጀመረ። 2. በየቦታው ጣለ፥ አዝረከረከ።

**እንጥብጣቢ** ቅ 1. የፈሳሽ ጠብታዎች፣ ጠፈጠፍ። 2. ተዝረክርኮ ወይም ወዳድቆ የቀረ።

***ነጠበ**

**ተንጠበጠበ** ግ 1. ተንቀጠቀጠ፥ ተንዘፈዘፈ (በብርድ ወይም በህመም)። 2. ተሽቆጠቆጠ፥ ጠብ እርግፍ አለ።

**አንጠበጠበ** ግ አንቀጠቀጠ፥ አንዘፈዘፈ።

**ነጠነጠ**

**አነጠነጠ** ግ 1. ሰውነቱ ዳበረ፥ ወፈረ፥ ተመቸው። 2. ጠገበ፥ አረጠረጠ፥ አዘጠዘጠ።

***ነጠፈ**

**ምንጣፍ** ስ በላዩ ላይ ለመቀመጥ ወይም ለመተኛት ወይም ቤትን ለማስዋብ የሚዘረጋ ቁርበት ወይም ጀንዲ ወይም ስጋጃ፥...።

**ንጣፍ** ስ 1. ምንጣፍ። 2. የመንገድን ወይም የግቢን አቧራና ጭቃ ለመሸፈን መሬት ላይ የሚደረግ የጠፍጣፋ ድንጋይ ወይም የሸክላ፣... ልባስ። 3. መንግስት ከግለሰብ ለሚወስደው ቦታ በምትክነት የሚሰጠው ሌላ ቦታ።

**ተነጠፈ** ግ 1. ተዘረጋ ፡ ተስተካከለ (ምንጣፍ፡ አልጋ፥...)። 2. ተረበረበ፡ ተደረደረ። *መንገዱ በድንጋይ ተነጠፈ*። 3. በቁሙ ወደቀ፡ ተጋደመ፡ ተዘረረ።

**አነጠፈ** ግ 1. ዘረጋ፡ አስተካከለ (ምንጣፍን ፥አልጋን፥...)። 2. አለበሰ፣ ሸፈነ (በጣውላ ወይም በሸክላ ወይም በድንጋይ፥... ወለልን፥ መሬትን)። 3.ጣለ፥ ዘረረ (በመምታት)።

**አንጣፊ** ስ 1. በቤተ መንግስት የእልፍኝ አሽከሮች ሃላፊ የነበረ ሹም። 2. በቤተክርስቲያን ውስጥ ስጋጃ ምንጣፎችን የሚያፀዳና የሚያነጥፍ እንዲሁም ወለሉን የሚጠርግና የሚወለውል ሰራተኛ።

**ነጠፈ** ግ ደረቀ፥ መስጠት አቆመ።

**ነጠፈች** ግ ወተት መስጠት አቋረጠች፥ ደረቀች (ለምሳሌ ላም)።

**ነጣ** ግ 1. ነጭ ሆነ። 2. ፀዳ፥ ጠራ፥ ንፁህ ሆነ።

**ነጭ** (ብ.ቁ.**ነጫጭ**) ቅ 1. ወተት ወይም ንድፍ የመሰለ። ስ 2. ፈረንጅ።3. ወተት፥ ንድፍ፥... የሚመስል ቀለም።

**በነጩ ይዞታል** በቶሎ የሚያባራ አይደለም፤ ቀስ እያለ ነው የሚዘንመው (ዝናም)።

**ነጭ ሃር** ስ ቀለሙ ነጭ የሆነ የሃር ልብስ አይነት።

**ነጭ ለባሽ** ስ 1. መተዳደሪያ መሬት ከመንግስት ተሰጥቶት፥ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ወታደራዊ አገልግሎት ይሰጥ የነበረ የገበሬ ወታደር። 2. የሲቪል ልብስ የሚለብስና በምስጢር የስለላ፥ የወንጀል ክትትል ስራ የሚያካሂድ፥ ፖሊስ የህዝብ ደህንነት ሰው።

**ነጭ መጣፍጥ** ስ ነጭ አዝሙድ።

**ነጭ ሽብር** ስ በኮሚኒስት ስርአተ ማህበር ውስጥ የስርአቱ አራማጆች፥ ተቃዋሚዎቻቸው የሚፈፅሙባቸውን ጥቃት የሚጠሩበት ቃል ወይም ስም።

**ነጭ ሽንኩርት** ስ ፍሬው ነጭ ሆኖ እንደቀይ ሽንኩርት በመሬት ውስጥ የሚፋፋና የሚያኮርት፥ ሃይለኛ ሽታና ጣእም ያለውና አብዛኛውን ጊዜ ለምግብ ማጣፈጫነት የሚውል የተክል አይነት (ስእሉን ሽንኩርት ስር ተመ.)።

**ነጭ አዝሙድ** ስ ፍሬው ነጭ የሆነ የቅመም አይነት።

**ነጭ(ነጩ) ዝንጀሮ** ስ በጥቂቱ ቡናማ ቀለም የጣለበት ሆኖ አመድማ መልክ ያለው፥ መቀመጫው መላጣ የሆነና በቆላ አካባቢ በቁጥቋጦ ውስጥ የሚኖር፥ በኢትዮጵያና በሱማሊያ ውስጥ ብቻ የሚገኝ የዝንጀሮ አይነት።

**ነጭ ደመና** ስ የውሃ ነጠብጣብ ይዘቱ በጣም ዝቅተኛ የሆነና ጥጥ መስሉ የሚታይ የደመና አይነት።

**ነጭ ጤፍ** ስ ፍሬው ነጭ የሆነ የጤፍ አይነት።

**ነጫጭባ** ቅ (ስድብ) ሰውነቱ ወዘና የሌለው፥ አመዳም (ሰው)።

**ነጭሎ** ስ በደጋና በወይና ደጋ የሚበቅል ቅጠሉ ነጭ የሆነ የቁጥቋጦ አይነት።

**ንጣት** ስ ነጭነት። *ንጣቱ ወተት ይመስላል*።

**ነጣቂ** "**ነጠቀ**" ስር ተመ.

**ነጥር(ልጥር)** ስ የክብደት መለኪያ(ብዙውን ጊዜ እንደ ማር፥ ቅቤ፥ ወርቅ፥... ለመሳሰሉ) አንድ ነጥር አስራ ሁለት ወቄት ያህል ነው።

**ነጥብ** "**ነጠበ**" ስር ተመ.

**ነጨ** ግ 1. ቦጨቀ። *ማጭድ ስለሌለው በእጁ ሳር ነጭቶ ይዞ መጣ።* 2. ዘነተረ (ስጋን በጥርስ)። 3. ጋጠ፥ በላ (ከብት ሣርን)። 4. ፈተገ፥ መለጠ፥ ላጠ (ፊትን በሻካራ ነገር በመፈግፈግ)። 5. ገረፈ፥ ሸነቆጠ (በአለንጋ፥ በአርጩሜ)። 6. ቀምቶ፥ አታልሎ፥ በቁማር አሸንፎ፥... ወሰደ (ገንዘብን)።

**ተነጨ** ግ ተነቀለ፥ ተጎለሰሰ(ፀጉር)። 2- (ገንዘቡ) ተበላ፥ ተወሰደ (በቁማር፥ በቀማኛ፥...) ።

**አናጨ** ግ አበሳጨ፥ አናከሰ፥ አጨቃጨቀ::
**ነጨሬ(ነጨር)** ቅ አመለ ነጭናጫ፥ ከሰው የማይስማማ::
***ነጨነጨ**
**ነጭናጫ (ነጨነጭ)** ቅ አመለቢስ፥ ጨቅጫቃ፥ ብስጩ::
**ንጭንጭ አለ** ግ ተነጫነጨ::
**ተነጫነጨ** ግ ተበሳጨ::
**አነጫነጨ** ግ አበሳጨ፥ አመል ነሳ::
**ነጫጭባ "ነጣ"** ስር ተመ.
**ነጩ ዝንጀሮ "ነጣ"** ስር **"ነጭ ዝንጀሮ"** ን ተመ.
**ነጭ "ነጣ"** ስር ተመ.
**ነጭሎ** ዝ.ከ.
***ነፀረ**
**ንፅፅር** ስ አንድን ነገር ወይም ሁኔታ ከሌላው ጋር የማስተያየት፥ የማወዳደር፥ የማመዛዘን ድርጊት::
**አንፃር** ስ ትይዩ፥ አኳያ፥ ፊትለፊት:: *ቤታችን አንፃር ለአንፃር ነው::*
**ከ _ አንፃር ከ _ አኳያ::** *ነገሩን ከሚሰጠው ጥቅም አንፃር መመልከት ይበጅ ይሆናል::*
**ተነፃፀረ** ግ 1. ተስተያየ፥ ተመሳከረ:: 2. ተወዳደረ::
**አነፃፀረ** ግ 1. አስተያየ፥ አመሳከረ:: 2. አወዳደረ::
**ነፀብራቅ "*ፀበረቀ"** ስር ተመ.
**ነፃ** ቅ 1. ወንጀል፥ ሃጢአት፥... የሌለበት:: 2. እዳ፥ ብድር የሌለበት:: 3. ግዴታ፥ ሃላፊነት፥...የሌለበት:: 4. የሌላ ያልሆነ ወይም በሌላ ወገን ያልተያዘ (ለምሳሌ መሬት):: 5. ከጭቆና፥ ከባርነት፥ ከተገዥነት የተላቀቀ:: 6. እንደፈለገው መሆን የሚችል፥ ቁጥጥር የሌለበት:: 7. ያለ ክፍያ፥ በብላሽ የሆነ:: *ነፃ አገልግሎት የሚሰጥ::*
**ነፃ ወጣ** 1. ወንጀል ሳይገኝበት ቀረ፥ ከቅጣት ዳነ:: 2. ከእዳ፥ ከተገዥነት፥... ተላቀቀ:: 3. ራሱን ቻለ፥ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር በቃ፥ እንዳሻው ለመሆን ቻለ::
**ነፃ አውጪ** ቅ ህዝቡን (ወገኖቹን) ከጭቆና፥ ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ለማላቀቅ ትግል የሚያካሂድ (ሃይል፥ ሰራዊት፥...)::
**ነፃ ትምህርት** ስ ትምህርቱን ለመከታተል አስፈላጊ የሚሆኑትን ነገሮች ተማሪው ያለክፍያ (በነፃ) የሚያገኝበት የትምህርት (የመማር) እድል፤ ስኮላርሽፕ::
**ነፃ ወደብ** ስ የሌላ አገር ሸቀጦችን ያለ ቀረጥ አሳርፎ ተመልሶ የሚወጣበት ወደብ::
**ነፃነት** ስ 1. አርነት፤ የምንም ነገር ጥገኛ አለመሆን:: 2. ሌላውን ሳይነኩ የፈለጉትን ነገር የመስራት፥ የመናገር፥ የመፃፍ፥...መብት:: 3. በባእድ መንግስት ወይም በሌላ ሰው ቁጥጥር ስር አለመሆን:: 4. ራስን በራስ የማስተዳደር ፥ የመምራት ስልጣን፤ መብት::
**ነፃ** ግ ንፁህ ሆነ::
**ንፁህ** ቅ 1. የፀዳ፥ የጠራ:: 2. ወንጀል፥ ሃጢአት የሌለበት:: 3. ቅን፤ ተንኮል፥ ምቀኝነት የሌለው:: 4. ከሌላ ጋር ያልተደባለቀ፥ ያልተበረዘ:: *ንፁህ ወርቅ::*
**ንፁህ ደም ፈሰሰ** የሰራው በደል ሳይኖር እንደበደለኛ ደሙ እንዲፈስ ተደረገ::
**ንፅህና** ስ 1. ንፁህ ሆኖ መገኘት:: 2. ከሃጢአት፥ ከወንጀል ነፃ መሆን::
**ነፃነት "ነፃ"** ስር ተመ.
**ነፈለለ** ግ ነሆለለ፥ ቄለ፥ ጀለ::
**ነፈለል(ንፍላላ)** ቅ ነሁላላ፥ ቂል፥ ጅል::
**ተነፋለለ** ግተነሃለለ፥ ቄለ፥ ተጃጃለ(ሲናገር)::
**አነፋለለ** ግ አነሃለለ፥ አቄለ፥ አጃጃለ::
**ነፈረ** ግ 1. በጣም ሞቀ፥ ፈላ፥ ተፍለቀለቀ፥ እንደ እሳት የሚያቃጥል ሆነ (ውሃ):: 2. በጣም በሰለ፥ ሞከከ (ንፍሮ):: 3. ብዙ ቦታ ላይ ቆሳሰለ፥ ሰውነቱ በቁስል ተወረረ::
**ንፍር ውሃ** ስ በጣም የሞቀ፥ የፈላ ውሃ::
**ንፍሮ** ስ ተቀቅሎ በጣም የበሰለ ወይም የሞከከ እንደ ባቄላ፥ አተር፥ ስንዴ ያለ የጥራጥሬ እህል አይነት፤ ምግብ::
**ተናፈረ** ግ በነገር ተቋሰለ፥ ተባሰለ::
**አነፈረ** ግ 1. ንፍሮ ቀቀለ:: 2. በጣም አቃጠለ:: *ሻዩ ምላሴን አነፈረው::*
**ነፈረቀ** ግ 1. በጣም አለቀሰ፥ ተንሰቀሰቀ:: 2. ቁስሉ ፈነዳ፥ መገለ፥ እገር ፈሰሰ::
**ነፈረቅ (ንፍራቃ፥ ንፍርቅ)** ቅ አልቃሻ::
**ተነፋረቀ** ግ 1. በጣም አለቀሰ፥ ማልቀሱን አላቆም አለ:: 2. በጣም ቆሳሰለ፥ ቁስሉ በእኸና በመግል ተጨማለቀ::
**አነፋረቀ** ግ 1. አስለቀሰ:: 2. በቁስል አጨማለቀ፥ ቁስል በቁስል አደረገ::
**ነፈሰ** ግ 1. ነፋስ ተነሳ፥ ተንቀሳቀሰ፥ ሽው ሽው አለ:: 2. ተሰራጨ፥ ተዛመተ፥ ተነዛ (ወሬ):: 3. (ዘይ.) በጊዜያዊ ፍቅር ከነፈ::
**ነፈሰበት** 1. በተገቢው መንገድ ሳይከደን በመቅረቱ ተበላሸ (ለምሳሌ ጠላ፥ እንጀራ):: 2. ወቅቱ፥ ጊዜው አለፈበት፥ ተሰለቸ:: *የነፈሰበት ወሬ::*
**ነፋስ(ንፋስ)** ስ 1. በሃይል የሚንቀሳቀስ፥

የሚከንፍ አየር። 2. (ዘይ.) ሀ. ፈጣን፥ ሯጭ። ለ. ከውካዋ፥ እረፍተቢስ።

**ነፋስ መታው** 1. በእሸት ደረጃ ላይ ያለው ሰብል በሚገባ ከመጎምራቱና ከመብሰሉ በፊት ተስማሚነት የሌለው ነፋስ ስለገረፈው ፍሬው ሳሳ፥ ቀጨጨ። 2. አየር እንዲያገኝ፥ እንዲነፍስበት ተደረገ።

**ነፋስ ተቀበለ** ከመኖሪያ ቤቱ ወይም ከአካባቢው ራቅ ብሎ በመሄድ ተንሸራሸረ፥ ተዝናና።

**ነፋስ እንዳይወስደው** እንዳይሰራጭ፥ እንዳይዛመት(ወሬ)።

**ነፋስ ገባቸው** ተቀያየሙ፥ ፍቅራቸው ተቋረጠ፥ ተለያዩ።

**ነፋስ ያልነካው ወሬ** ብዙ ሰው ያልሰማው አዲስ ወሬ።

**ነፋሻ** ቅ 1. ተስማሚ የሆነ ነፋስ ያለበት (ቦታ)። 2. ነፋስ የሚበዛበት (ቦታ)።

**ንፋሽ** ስ ከደሀናው እህል ተለይቶ እንዲወጣ የተደረገ ብጣሪ፥ ግርድ፥ እሰር።

**ተናፈሰ** ግ 1. የታመቀው፥ የታሸገው ነገር (እቃ፥ ልብስ፥...) ተከፍቶ ወይም ተነጣጥሎ አየር እንዲያገኘው ተደረገ። 2. ነፋስ ተቀበለ፥ ተዝናና፥ ተዘዋወረ፥ ተንሸራሸረ። 3. ተሰራጨ፥ ተነዛ (ወሬው)። 4. ተፀዳዳ፤ አይነምድርን፥ ሽንትን ለማስወገድ ወደ መፀዳጃ ቤት ገባ ወይም ገለል ወዳለ ቦታ ሄደ።

**መናፈሻ** ስ 1. ለነፋስ መቀበያ የተሰራ ሰገነት። 2. ነፋሻ አየር፥ አትክልትና ለምለም ሳር ያለበት፥ በከተማ አካባቢ ለመዝናኛነት የተከለለ ቦታ፥ መስክ።

**አነፈሰ** ግ እህልን በሰፌድ አበጠረ፥ ከቆሻሻ ለየ።

**አናፈሰ** ግ 1. አዲስ አየር እንዲያገኘው አደረገ። 2. አዝናና፥ አንሸራሸረ። 3. ነዛ፥ አሰራጨ (ወሬን)።

**አናፋሽ (ወሬ አናፋሽ)** ቅ ወሬኛ፥ ወሬ የሚያዛምት።

**ነፈነፈ** ግ 1. በብዛት ተመገበ፥ ጠጣ። *ምግቡንም ሆነ መጠጡን እስኪሰለቸኝ ነፈነፍኩት*። 2. ነረተ፥ መታ፥ ደበደበ። *በቦቅስ ነፈነፈው።*

***ነፈነፈ**[1]

**ነፍናፋ** ቅ ሲናገር አፍንጫውን የሚይዘው፤ ከንኳና።

**ተነፋነፈ** ግ 1. አፍንጫው እንደልብ አየር የማያስተላልፍ በመሆኑ ሲናገር ድምፁ ጥራት የሌለው ሆነ። 2. ብልሽት ስላለው ድምፁ ጥራት የሌለው ሆነ (ለምሳሌ ሬዲዮ፥ የሙዚቃ መሳሪያ)። 3. አጉተመተመ፥ የቅሬታ፥ የብሶት፥... ንግግር ለገዛ ራሱ ተናገረ፤ አለቃቀሰ።

***ነፈነፈ**[2]

**አነፈነፈ** ግ አሸተተ፥አፈነፈነ።

**አነፍናፊ** ቅ አሳዳጅ፤ ፈልጎ የሚያገኝ (ወሬን፥ ሌባን፥ የተደበቀ ነገርን፥...)።

**ነፈዝ** ቅ ፈዛዛ፥ ነሁላላ፥ ቂላቂል።

**ነፈገ** ግ 1. ከለከለ፥ ነሳ። 2. ሰሰተ፥ ተንቀበቀበ።

**ንፉግ** ቅ (ስድብ) ስስታም፥ ቅቅታም።

**ንፍገት** ስ ስስት፥ ቅቅት።

**ንፍጊያ** ዝ.ከ.

**ተነፈገ** ግ ተከለከለ፥ እንዳያገኝ ተደረገ።

***ነፈጠ**

**ንፍጥ** ስ 1. በጉንፋን ህመም ምክንያት የሚፈጠርና በአፍንጫ ቀዳዳዎች ውስጥ የሚወጣ ዝልግልግ ነጭ ፈሳሽ። 2. (ስድብ) የማይረባ ሰው።

**ንፍጣም** ቅ 1. ንፍጥ ከአፍንጫው የማይጠፋ (ሰው)። 2. (ዘይ.፥ስድብ) የማይረባ፥ ጅላጅል (ሰው)።

**ተናፈጠ** ግ ንፍጡን ከአፍንጫው ጠረገ፥ አፀዳ።

**አናፈጠ** ግ 1. የሌላውን ንፍጥ ከአፍንጫው ጠረገለት (ለምሳሌ የህፃንን)። 2. አፍንጫን መታ።*በቦቅስ አናፈጠው ።* 3. ደበደበ።

**ነፈፈ** ግ ጅለ፥ ሞኛሞኝ ሆነ።

**መነፍ** ቅ ጅል፥ ሞኛሞኝ።

**ነፋፋ(ነፎ)** ዝ.ከ.

**ነፋ**[1] ግ 1. ቀበተተ፥ ወጠረ (ሆድን)። 2. በአየር ሞላ (ኳስን፥ ጎማን፥...)። 3. ትንፋሽን በሙዚቃ መሳሪያ ውስጥ በማሳለፍ ሙዚቃዊ ድምፅ እንዲፈጠር አደረገ። *ዋሽንት ነፋ*። 4. በብዛት አወራ፥ በየቦታው ወሬን አሰራጨ። 5. አንድን ድርጊት ከመጠን ባለፈ ሁኔታ አከናወነ። 6. ቡፍ አለ፥ ተቀበተተ። *እርሾ ስላለበት ዳቦው በጣም ነፋ።*

**ንፋው** ቅ (ስድብ) ውሸታም፥ ወሬኛ።

**ተነፋ** ግ 1. አበጠ፥ ተቀበተተ (የተጎዳ ገላ)። 2. (ዘይ.) በቁጣ ወይም በኩርፊያ ተከመረ፥ አበጠ፥ ተነረተ።

**ነፋ**[2] ግ ጥሩውን ከቆሻሻ በወንፊት ለየ፥ አጠራ። *ዱቄት ነፋ።*

**ንፈት(ንፌት)** ስ እህል ወይም ዱቄት በሚነፋበት ጊዜ በመጨረሻ ከወንፊቱ ላይ የሚቀረው እሰር፥ ቆሻሻ።

**ነፋስ "ነፈሰ"** ስር ተመ.

**ነፋሻ** ዝ.ከ.

**ነፍሳሳ "ነፈለለ"** ስር ተመ.

**ነፍራቃ "ነፈረቀ"** ስር **"ነፈረቅ"** ን ተመ.

**ነፍሳት** ስ 1. የ"**ነፍስ**" ብዙ ቁጥር:: 2. እንደትሳትል፥ በረሮ፥... ያሉ ጥቃቅን ፍጥረታት::

**ነፍስ (ብ.ቁ.ነፍሳት)** ስ ስጋ ለባሽ ለሆነ ፍጡር ሁሉ እንደ አንቀሳቃሽ ሞተር የምትቆጠር፥ ከፅንስት እስከ እለተ ሞት ስጋን ተዋህዳ የምትቆይና በሞት ጊዜ ከስጋ የምትለይ ረቂቅ ህላዌ ፤ ህይወት:: *ነፍስ የተለየው ስጋ በድን ነው፤ ህይወት የለውም::*

**ለነፍሱ አይሳሳም** ደፋር ነው፥ አይፈራም፥ አደጋ ፈርቶ ወደሂላ አይልም::

**ለነፍሱ/ለእግዚአብሄር ያደረ** ደግ፤ የፅድቅ ስራ የሚሰራ::

**በነፍሱ ደረሰ** 1. የታመመው፤...ሳይሞት ደረሰ፥ በህይወት አገኘው:: 2. ለእርዳታ ደረሰ (በችግር ወይም በአሳሳቢ ሁኔታ ላይ ላለ):: 3. እቃው፥ ጉዳዩ፥... ሊያልቅ ትንሽ ሲቀረው ደረሰበት::

**በነፍስ ተይዟል** በጣም ታሟል::

**በነፍስ ደረሰ** ለችግር በቶሎ ደረሰ፥ ተገኘ::

**ነፍሱ ተመለሰ** 1. ራሱን አወቀ፤ ዳነ (በህመም ወይም በሌላ ምክንያት ራሱን ስቶ የነበረ):: 2. በረታ፥ ሃይል አገኘ::

**ነፍሱ ወጣ(ወጣች)** 1. በጣም ደነገጠ:: 2. ነፍሱ ተለየችው፥ ሞተ::

**ነፍሱ ጥላው ሄደች** በጣም ደነገጠ::

**ነፍሱን ሳተ** 1. በድን ሆነ፥ ደነዘዘ:: 2. ማንነቱን ዘነጋ፥ እንደ እብድ ሆነ::

**ነፍሱን ሸጠ** በነፍሱ ፈረደ፥ ቆረጠ (የሚያጋጥመውን አደጋ ለመጋፈጥ)::

**ነፍሱን አወቀ** ህመሙ ተሻለው፥ ሰውነቱን ተቆጣጠረ::

**ነፍሱ እስኪወጣ** ከመጠን በላይ፥ በሃይል:: *ነፍሱ እስኪወጣ ይወዳታል*::

**ነፍሱን አጥቶ** ከመጠን በላይ፥ በሃይል፥ በጣም፥ በትጋት:: *ነፍሱን አጥቶ ነው የሚሰራው::*

**ነፍስ ሆነ** በጣም ተወደደ::

**ነፍስ አሳለፈ** ሰው ገደለ::

**ነፍስ አወቀ** አደገ፥ አእምሮው በሰለ (ህፃን የነበረው)::

**ነፍስ አዋለ** በአምባጓሮ መካከል ገብቶ እንዳይገዳደሉ ጠበኞቹን ገላገለ፥ ጠቡን አበረደ::

**ነፍስ የለውም** 1. አይረባም፥ ሙትቻ ነው:: 2. ቀዥቃዣ፥ ከውካዋ ነው:: 3. በጣም ይዋከባል፥ይጣደፋል፥ ይሯሯጣል (በስራ ጉዳይ)::

**ነፍስ ዘራ** ተሻለው፥ አንሰራራ::

**ነፍስና ስጋው ተለያየ** 1. በጣም ደነገጠ:: 2. ሞተ::

**የነፍስ ዋጋ ያድርግለት** (ምር.) ላደረገው ወይም ለተደረገው መልካም ስራ ብድሩን በሰማይ ቤት እግዚአብሄር ይክፈለው::

**ነፍሰቢስ** ቅ 1. ድንጉጥ:: 2. ችኩል፥ ቀዥቃዣ:: 3. ደፋር::

**ነፍሰ ገዳይ** ቅ 1. የሰው ነፍስ ያጠፋ፥ ሰው የገደለ:: 2. ጨካኝ፤ አረመኔ::

**ነፍሰጡር** ቅ እርጉዝ፥ ሽል በሆዷ የያዘች (ሴት)::

**[የ]ነፍስ አባት** ስ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) የንስሃ አባት፤ በማስተማር፤ በመምከር፥... ያንድን ክርስቲያን መንፈሳዊ ህይወት የሚጠብቅ ቄስ ወይም መነኩሴ::

**ነፍስ ያለው** ቅ 1. አዋቂ፤ ልጅ ያልሆነ፥ ትልቅ(ሰው):: 2. ጥሩ፥ ጠቃሚ:: *ላሁን ገና ነፍስ ያለው እቃ ገዛሁ::*

**ነፍስ ጥኑ** ቅ 1. ቢቀጠቅጡት፥ ቢወጉት ቶሎ የማይደክም ወይም የማይሞት:: 2. ጠንካራ፥ መከራ ቻይ::

**የነፍስ ልጅ** ስ የንስሃ ልጅ::

**የነፍስ ወከፍ** እያንዳንዱ ሰው በየግል ያለው፥ የሚይዘው፥ የሚያገኘው:: *የነፍስ ወከፍ ገቢ/የነፍስ ወከፍ መሳሪያ::*

**ነፍናፋ "ነፈነፈ[1]"** ስር ተመ.

**ነፍጥ** ስ ጠመንጃ::

**ነፍጠኛ** ስ ባለነፍጥ፥ የቀድሞ ጊዜ ወታደር::

**ነፎ "ነፈፈ"** ስር ተመ.

**ኑ[1]** የ"**ነ**" ፊደል ካእብ ዘር::

**ኑ[2]** ግ በሁለተኛ መደብ፥ በብዙ ቁጥር ጊዜ የሚያገለግል የ "መጣ" ትእዛዝ አንቀፅ (እናንተ "ኑ" እንጂ "ምጡ" ወዲህ የሚል አነጋገር በቋንቋው ውስጥ ያልተለመደ ነው)::

**ኑሮ "ኖረ"** ስር ተመ.

**ኑስ "ንኡስ"** ን ተመ.

**ኑዛዜ "ናዘዘ"** ስር ተመ.

**ኑግ** ስ ፍሬው ጥቁር ሆኖ መጠኑ ተልባ የሚያህል፤ አገዳው መጭ የሚመስል የቅባት እህል አይነት::

**ኑፋቄ** ስ (ሃይ.) ጥርጣሬ፤ ክህደት፤ መናፍቅነት::

**ኒ** የ"**ነ**" ፊደል ሳልስ ዘር::

**ኒሻን(ሊሻን)** ስ ከብር ወይም ከወርቅ፥... የሚሰራና በደረት ላይ የሚደረግ፤ ለሃገር፥ ለወገን፥... አኩሪ ስራ ለሰራ ሰው በሽልማት መልክ የሚሰጥ የክብር ወይም የታላቅ ስራ

ምልክት።

**ኒካ** ስ የእስልምና ሃይማኖት የጋብቻ ውል ስርአት።

**ኒካ አሰረ** ተፈጣጠመ፥ የጋብቻ ውል ተዋዋለ።

**ኒኬል** ስ መልኩ ግራጫ የሆነ ጠንካራ የማእድን አይነት።

**ኒያላ** ስ መልኩ በጠቅላላ ግራጫ ሆኖ ትንሽ ቀላ የሚል፥ ከአይኖቹ በታች፥ በአንገቱና በደረቱ ላይ ነጫጭ ሽንትሮች ያሉበት፥ አጋዘን የሚመስልና ቀንዶቹ ጠመዝማዛ የሆኑ ፥ በኢትዮጵያብቻ የሚገኝ የዱር እንስሳ (ስእሉን የዱር እንስሳ ስር ተመ.)።

**ና**[1] የ"ነ"ፊደል ራብእ ዘር።

**ና**[2] ግ መደቡ ሁለተኛ፥ ቁጥሩ ነጠላ፥ ፆታው ተባእታይ የሆነን የግስ ባለቤት የሚመለከት የ "መጣ" ትእዛዝ አንቀፅ ("ና" እንጂ "ምጣ" አይባልም)።

**-ና**[1] **(እና)** መፃ. ቃልን ከቃል ጋር ለማቆራኘት ወይም ለማጣመር የሚያገለግል መስተፃምራዊ ቃል። *ምግብና መጠጥ።*

**ና**[2] ስምን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ (ለምሳሌ ጥብቅ ጥብቅና ፥ ድርቅ ድርቅና፥ ቅልጥፍ ቅልጥፍና)።

**ናላ** ስ አንጎል፥ አእምሮ።

**ናላው ዞረ** 1. አእምሮው ተቃወሰ። 2. ተበሳጨ፥ ተናደደ።

**ናሙና** ስ ብዛት ካለው ነገር ውስጥ ለአይነት ያህል ተመርጦ የሚቀርበው ክፍል። *ከተገኙት ማእድናት ውስጥ ለናሙና ያህል ላንዳንድ ይዘን መጣን።*

**ናረ** ግ 1. ጓነ፥ ነጠረ። 2. ተወደደ፥ ዋጋ ጨመረ።

**ንረት** ስ ውድነት። *የዋጋ ንረት ያመጣው ቀውስ።*

**ናር ናር አለ** ቆጣ ቆጣ አለ፡ ሃይለ ቃል ተናገረ።

**ናረት** "ነረተ[2]" ስር ተመ.

**ናርጅ (ናርድ)** ስ ከሆዱ ዘርጠጥ፥ ከላይና ከታች ጠበብ እንዲል ተደርጎ ከግንድ ቁራጭ ተጠርቦና ተፈልፍሎ የሚሰራ የቅቤ ማስቀመጫ።

**ናሰ** ግ ገነባ፥ ግንብ ሰራ።

**ናስ** ስ ግንብ።

**ናስ ቤት** ስ ግንብ ቤት።

**ናሴ**[1] **"ነሃሴ"** ን ተመ.

**ናስ**[2] **"ነሃስ"**ን ተመ.

**ናስ**[2] **"ናሰ"** ስር ተመ.

**ናስትሮ** ስ ያልተሸፈኑ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች አደጋ እንዳያደርሱ በመሸፈኛነት የሚያገለግል የፕላስተር አይነት።

**ናቀ** ግ 1. በዝቅተኛ ደረጃ ተመለከተ፥ እንደተራ ነገር ቆጠረ። 2. ጠላ፥ ተገቢውን ክብር፥ ዋጋ፥ ሳይሰጥ ቀረ።

**ናቂ** ቅ 1. አንኳሳሽ። 2. ኩሩ።

**ንቀት** ስ አንድን ነገር አቃሎና ዝቅ አድርጎ የማየት ሁኔታ፤ ለአንድ ነገር ተገቢውን ክብር፥ ቦታ፥ ደረጃ፥...አለመስጠት።

**ተናቀ** ግ 1. ተንኳሰሰ፥ በዝቅተኛ ደረጃ ታየ። 2. ተጠላ፥ ተገቢውን ቦታ፥ አስተያየት አጣ።

**አናናቀ** ግ አንኳሰሰ፥ አንቋሸሸ፥ አጥላላ።

**አስናቀ** ግ ከሌሎቹ ተሸሎ፥ ልቆ፥... በመገኘቱ ሌሎቹ እንዲናቁ አደረገ።

**ናበዘ** ግ ፈዘዘ፥ ንቃት ወይም ቅልጥፍና አጣ።

**ናባዛ** ቅ ፈዛዛ፥ ንቃት ወይም ቅልጥፍና የሌለው።

**ናት** (አፍ. **"አይደለችም"**)**"ነው"**ን ተመ.

**ናትራ(ናትራን)** ስ ነጭ የሸቱ ተክል፥ አሪቲ።

**ናቸው** (አፍ. **"አይደሉም"**)**"ነው"**ን ተመ.

**ናችሁ** (አፍ. **"አይደላችሁም"**)ዝ.ከ.

**ናና (ናእናእ)** ስ በቅመም መልክ ከሻይ ውስጥ የሚጨመር፥ ጣፋጭ መአዛና ጣእም ያለው አነስተኛ የተክል አይነት።

**ናኘ** ግ 1. በብዛትና በስፋት ሰጠ፥ አደለ፥ ነዛ። 2. አዘዘ፥ እንደፈለገው አደረገ። *ባላዋቂ ቤት እንግዳ ናኘበት።*

**ተናኘ** ግ ተሰራጨ፥ ተነዛ፥ ተዘራ። *በሽታው ተናኘ።*

**ናወዘ(ናወተ)** ግ ተንከራተተ፥ ዋተተ፥ ተንገላታ።

**አናወዘ(አናወተ)** ግ 1. አንከራተተ፥ አዋተተ፥ አባከነ። 2. አንገለጀጀ፥ አንገላታ (እንቅልፍ)።

**ናዘረ** ግ ሻፈደ፥ ዛዘነ፥ በወሲብ ፍላጎት ተቅበጠበጠ።

**ናዘዘ** ግ 1. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ስልጣነ ክህነት ያለው ካህን በማንኛውም አይነት የስርአተ ፀሎት መጨረሻ ላይ የማሳረጊያ ፀሎት አድርሶና እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ እንበል ብሎ ከጨረሰ በሂላ እግዚአብሄር ይፍታህ በማለት ምእመናኑን አሰናበተ። 2. አረጋጋ፥ አፅናና።

**ኑዛዜ (ንዝ)** ስ አንድ ሰው ከመሞቱ በፊት ሃብቱን ለወራሾቹ ያከፋፈለበት ሰነድ ወይም በሽማግሌ ፊት የተናገረው ውርሱን የሚመለከት ቃል።

**ኑዛዜው ፈሰሰ** የኑዛዜው ቃል ተነገረ፥ ተሰማ፥ ሰነዱ ተነበበ።

**የኑዛዜ ወረቀት/ ሰነድ** ስ የኑዛዜ ቃል

የተፃፈበት ወረቀት፥ ሰነድ።

**ተናዘዘ** ግ 1. ከመሞቱ በፊት ንብረቱን በሚመለከት ኑዛዜ አደረገ። 2. የሰራውን ሃጢአት ለካህን ነግሮ፥ ማድረግ የሚገባውን ነገር እንዲያደርግ ከካህኑ ትእዛዝና መመሪያ ተቀበለ፤ በካህኑ ፀሎትና ምክር ተፅናና፥ ተበረታታ። 3. (ዘይ.) ምስጢሩን ዘከዘከ፥ አወጣ።

**አናዘዘ** ግ 1. የአውራሽን የኑዛዜ ቃል ተቀበለ። 2. (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ካህን ፀሎት አድርጎ፥ እግዚአ መሃረነ ክርስቶስ ካለ በሂላ፥ እግዚአብሄር ይፍታህ በማለት ምእመናኑን አፅናና፥ አሰናበተ። 3. (ዘይ.) ምስጢር እንዲያወጣ አደረገ።

**ናዜራ** ስ ሽረሪት የምትመስል፥ መርዛማና ተናዳፊ የሆነች አነስተኛ የነፍሳት አይነት።

**ናዝራዊ** ስ 1. የናዝሬቱ ወይም የናዝሬት ሰው (ኢየሱስ)። 2. መናኝ፥ ባህታዊ።

**ናደ** ግ አፈረሰ፥ ገነባረ፥ ጣለ (ግንብን፥ ክምርን፥ ገደልን፥...)።

**ናዳ(ናደት)** ስ ከተራራ ላይ ተፈንቅሎና ተንከባሎ ወደታች የሚወርድ ድንጋይ፥ የተራራ ቅራፊ።

**ተናደ** ግ ፈረሰ፥ብትንትኑ ወጣ።

**ናጠ** ግ 1. ቅቤን ከረጋ ወተት ውስጥ ለይቶ ለማውጣት፥ መጀመሪያ ወተቱን እንደ ገንቦ፡ እንስራ፥... ባለ እቃ ውስጥ አድርጎና ከድኖ እቃውን ወዲያና ወዲህ በመግፋት ወይም በመወዝወዝ ወተቱ እንዲንቦጫቦጭና ቅቤው እንዲለይ አደረገ። 2. አወዛወዘ፥ ነቀነቀ፥ አንገላታ።

**ተናጠ** ግ 1. ተወዘወዘ። 2. ተኩራራ፥ ተጀነነ።

**ናጠጠ** ግ 1. ፈነጨ፥ ዘለለ፥ ቀበጠ። 2. እጅግ በለፀገ፥ ከበረ። 3. ተንቀባረረ፥ ተኩራራ።

**ናጩርት(ናጩርቲያም)** ቅ ነጭናጫ፥ ጠባየ መጥፎ።

**ናጫ** ስ እንደ ሳማ የሚኮሰኩስና የሚያቃጥል ጭገር ያለው፥ ልጡ ለጠንካራ ገመድ መስሪያ የሚሆን የእፅዋት አይነት።

**ናፈለ(አናፈለ)** ግ በሃይል አመመ፥ አስጨነቀ፥ ትንፋሽ ከለከለ። *ጉንፋን ይዞ ያናፍለኛል።*

**ናፈረ(አናፈረ)** ግ በቀንዱና በእግሩ መሬት ጫረ፥ ጎደፈረ (ጠብ ወይም ውጊያ የፈለገ በሬ)።

**ናፈቀ** ግ ተለይቶት የሰነበተውን ወይም የቆየውን ሰው ወይም ሌላ ነገር እንደገና ለማየት፥ ለማግኘት ፈለገ፥ ጓጓ፤ ተመኘ።

**ናፋቂ** ቅ ሆደ ቡቡ፥ ከዘመድ ተለይቶ መቆየት የማይችል (ሰው)።

**ናፍቆት** ስ ተለይተውት የቆዩትን ሰው፥ አገር እንደገና የማየት፥ የማግኘት ፍላጎት፥ ጉጉት።

**ተናፈቀ** ግ በናፍቆት ስሜት ትዝ አለ፥ ታወሰ፥ ተፈለገ።

**ተናፋቂ** ቅ ከአጠገብ በመራቁ ወይም በቅርብ ባለመገኘቱ በናፍቆት ስሜትና በጉጉት የሚፈለግ፤ ተወዳጅ።

**ናፍታ(ናፍጣ)** ስ ከባድ መኪናን፥ ሞተርን ለማንቀሳቀስ ወይም ለማገዶነት የሚያገለግል ነዳጅ።

**ኔ** የ"ነ" ፊደል ሃምስ ዘር።

**ኔፕቲዩን** ስ ከፀሃይ በጣም ርቆ የሚገኝ ስምንተኛው ፕላኔት። በተጨማሪ "**ፕላኔትን**" ተመ.

**ን** የ"ነ" ፊደል ሳድስ ዘር።

**-ን** 1.በስም መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ተሳቢነትን የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ ካሳ ልጁን መከረ፥ ስራን ማክበር የሚገባ ነው)። 2.በግስ መድረሻ ላይ እየተቀጠለ የአንደኛ መደብ፥ የብዙ ቁጥር ተሳቢነትን የሚያመለክት ምእላድ (ለምሳሌ በሰአቱ ሄድን፥ለነፃነት ተጋደልን)። 3.በቃል መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ተውሳከ ግስን ለመመስረት የሚያገለግል ምእላድ(ለምሳሌ እለቱን ይገባል)። 4.(ብዙውን ጊዜ በፅሁፍ የሚገኝ) በግስ መድረሻ ላይ እየተቀጠለ ጥያቄን ለማቅረብ የሚያገለግል ምእላድ (ለምሳሌ ሰአቱ ደርሷልን?)።

**ንሃስ** "**ነሃስ**" ን ተመ.

**ንረት** "**ናረ**" ስር ተመ.

**ንስሃ(ንስሃ)** ስ (ሃይ.) 1. ቅጣት ፥ መቀጮ። 2. ፀፀት፥ የሰሩትን ሃጢአት አስታውሶ እግዚአብሄርን ይቅርታ የመጠየቂያ፥ ምህረት የመለመኛ መንገድ።

**ንስሃ ነው** ያስቀጣል፥ ያስኮንናል። *ሰው መግደል ንስሃ ነው።*

**ንስሃ አለብኝ** የሰራሁት ሃጢአት ስላለ ቅጣት፥ ኩነኔ አለብኝ።

**ንስሃ ገባ** 1. ከክፉ ስራ ወደ መልካም ስራ ተመለሰ፥ በሰራው ሃጢአት ተፀፅቶ የእግዚአብሄርን ምህረትና ይቅርታ ጠየቀ (በመፆም፥ በመፀለይ፥...)። 2. መቀጫ፥ ቅጣት ውስጥ ገባ (ሃይማኖት የሚያወግዘውን መጥፎ ተግባር በመፈፀሙ)።

**የንስሃ ልጅ** ስ የካህን የመንፈስ ልጅ፥ መንፈሳዊ ህይወትን በሚመለከት አንድ የተወሰነ ካህን በቋሚነት የሚያስተምረው፥ የሚመክረው፥...ምእመን።

**የንስሃ አባት** ስ የምእመናን የመንፈስ አባት፥ አበ ነፍስ፤ የነፍስ አባት (ሃይማኖቱ በሚያዘው መሰረት በማስተማር፥ በመምከር የሚጠብቃቸው የተወሰኑ ምእመናን ወይም የመንፈስ ልጆች

ያሉት ካህን)።

**ንሳ** "*ነሳ" ስር ተመ.

**ንስር** ስ ትልቅ የአሞራ አይነት (ስእሉን አሞራ ስር ተመ.)።

**ንሺ**[1] **(ንሺቴ)** በአንድ ነገር አለመስማማትን ወይም ተቃውሞን ለመግለፅ የሚያገለግል ቃል (የአነጋገር ፈሊጥ)። አረ ንሺ፥ ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል።

**ንሺ**[2] **(ንሽ)** ስ ዘር ለማብቀል በቂ የሆነና በእርሻ መሬት ውስጥ የሚገኝ የዝናም ርጥበት።

**ንሺ ሆነ** ዝናም በመጣሉ እርሻው ዘር ለማብቀል የሚያስችል ርጥበት አገኘ።

**ንቀት** "ናቀ" ስር ተመ.

**ንቁ** "ነቃ" ስር ተመ.

**ንቃሪ** "*ነቀረ" ስር "**እንቃሪ**"ን ተመ.

**ንቃሽ**[1] "ነቀሰ[1]" ስር ተመ.

**ንቃሽ**[2] "ነቀሰ[3]" ስር ተመ.

**ንቃተህሊና** "ነቃ[1]" ስር ተመ.

**ንቃቃታም** "ነቃ[2]" ስር ተመ.

**ንቃቃት** ዝ.ከ.

**ንቃት** "ነቃ[1]" ስር ተመ.

**ንቃይ(ንቅል)** "ነቀለ" ስር ተመ.

**ንቅሳት** "ነቀሰ[1]" ስር ተመ.

**ንቅስ** ዝ.ከ.


**ንቅናቄ** "ነቀነቀ" ስር ተመ.

**ንቡረእድ (ነብሪድ)** ስ በአክሱም ፅዮንና በአዲስ አለም ደብረፅዮን አብያተክርስቲያን ላይ ለሚሾሙ የካህናት አለቆች የሚሰጥ የማእረግ ስም።

**ንባብ** "ነበበ" ስር ተመ.

**ንባብ ቤት** ዝ.ከ.

**ንብ** ስ 1. ተናዳፊ የሆነች፥ አራት ክንፎች ያሏት፥ አበቦችን እየቀሰመች ማር የምትሰራ አነስተኛ የነፍሳት አይነት። 2. (ዘይ.) ትጉህ፥ ታታሪ፥ ባለሙያ።



ንብ 1ኛ ፍቺ

**ንባስል (ንብአስል)** ስ መጠኑ ከጦስኝ ጋር የሚቀራረብ፥ መልኩ ነጣ ያለና ጥሩ መአዛ ያለው፥ ለቀፎ ማጠኛነት የሚያገለግል የእፅዋት አይነት።

**ንበበል** ስ የቀይና የአረንጓዴ ዥንጉርጉር መልክ ያለው፥ መንቆሩ ረዘም ብሎ ሹል የሆነና እንደ ንብ፥ ቢራቢሮ፥...ያሉትን እየጠለፈ የሚበላ የወፍ አይነት (ስእሉን ወፍ ስር ተመ.)።

**የንብ አውራ (ንግስት)** ስ የንብ ሰራዊት አለቃ።

**የንብ እንጀራ** ስ ንቦች በቀፎ ውስጥ የሚያዘጋጁት የእንጀራ ቅርፅ ያለው ወፍራም የማር ግግር።

**የንብ እጭ** ስ ገና ክንፍ ያላወጣና በትልነት ደረጃ ላይ ያለ የንብ እንቁላል ፍልፍል።

**ንብረት** ስ 1. እንደ ቦታ፥ ቤት፥... ያለ የማይንቀሳቀስ ሃብት ወይም ጥሪት። 2. በአጠቃላይ የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ሃብት።

**ንብርብር (ንብብር)** "*ነበረበረ" ስር ተመ.

**ንብዝ** "ነበዘ" ስር ተመ.

**ንትርክ** "ነተረከ" ስር ተመ.

**ንኡስ (ኑስ)** ቅ አነስ ያለ፥ አነስተኛ የሆነ።

**ንኡስ ሃረግ** ስ ባለቤትና ማሰሪያ አንቀፅ የሌለው ጥምር ቃል (ለምሳሌ በዛፍ ላይ፥ከምድር በታች፥በክፉ ዘመን፥... )።

**ንኡስ አንቀፅ** ስ የንኡስ አንቀፅ አይነቶች አምስት ሲሆኑ እነሱም "መፈለግ፥ ፈልጎ፥ ፈላጊ፥ አፈላለግ፥ ፍለጋ" ያሉት የግስ እርባታ ቅርፆች ናቸው። ስማቸውም በቅደም ተከተል:- አርእስት፥ በዝ፥ ግሳዊ ቅፅል፥ ሳቢዘርና ጥሬዘር በመባል የሚታወቁት የግስ እርባታ ቅርፆች መጠሪያ።

**ንኡስ ከበርቴ** ስ በሶሻሊዝም ፍልስፍና አመለካከት መለስተኛ ገበሬዎችን፥ ነጋዴዎችን፥ ባለሙያዎችን፥... የሚያካትት የህብረተሰብ ክፍል።

**ንካች** "ነከተ" ስር ተመ.

**ንክ** "ነካ" ስር ተመ.

**ንክር** "ነከረ" ስር ተመ.

**ንክሻ** "ነከሰ" ስር ተመ.

**ንክች** "ነካ" ስር ተመ.

**ንክኪ** ዝ.ከ.

**ንክኪት (ንክክ)** ዝ.ከ.

**ንዋይ** ስ ገንዘብ፥ ሃብት።

**ንዋየ ቅድሳት** ስ እንደ አልባሳት፥ ፃህል፥ ፅዋ፥...ያሉ በአብያተ ክርስቲያናት ውስጥ

የሚገኙ የተቀደሱ እቃዎች።

**ንዛት** “ነዛ” ስር ተመ.

**ንዛዥ** “*ነዘዘ” ስር ተመ.

**ንዝ** “ናዘዘ” ስር “ኑዛዜ” ን ተመ.

**ንዝህላል** “እንዝህላል” ን ተመ.

**ንዝረት** “ነዘረ[1]” ስር ተመ.

**ንዝንዘኛ** “ነዘነዘ” ስር ተመ.

**ንዝንዝ** ዝ.ከ.

**ንዳድ[1]** “ነደደ[1]“ ስር ተመ.

**ንዳድ[2]** ስ የሚያተኩስ፥ የሚያንቀጠቅጥና የሚያቃዥ የወባ በሽታ።

**ንዳዳም** ቅ ንዳድ ወይም ወባ ያለበት።

**ንዴተኛ** “ነደደ[2]“ ስር ተመ.

**ንዴት** ዝ.ከ.

**ንድፈሃሳብ** ስ የተለያዩ ነገሮችንና ክስተቶችን በማገናዘብ ስርአት ባለውና በተጠቃለለ መልክ የሚገልፅ ወይም የሚያብራራ በተግባር ያልተተረጎመ እውቀት።

**ንድፍ[1]** “ነደፈ[1]“ ስር ተመ.

**ንድፍ[2]** “ነደፈ[2]“ ስር ተመ.

**ንድፍት** ስ በቆላማ አገር ውስጥ የሚገኝ የጋማ ከብቶችን የሚያጠቃ የበሽታ አይነት።

**ንጉር** “ነጎረ” ስር ተመ.

**ንጉር ቅቤ** ዝ.ከ.

**ንጉሳዊ** “ነገሰ” ስር ተመ.

**ንጉስ** ዝ.ከ.

**ንጋት** “ነጋ” ስር ተመ.

**ንግ** “*ነጋ” ስር ተመ.

**ንግረኛ (ንግርተኛ)** “ነገረ” ስር ተመ.

**ንግ̈ር(ንግ̈ርት)** ዝ.ከ.

**ንግስ** “ነገሰ” ስር ተመ.

**ንግስት** ዝ.ከ.

**ንግድ** “ነገደ” ስር ተመ.

**ንግግር** “ነገረ” ስር ተመ.

**ንጣሪ** “ነጠረ[1]” ስር ተመ.

**ንጣት** “ነጣ” ስር ተመ.

**ንጣይ** “ነጠለ” ስር ተመ.

**ንጣፍ** “*ነጠፈ” ስር ተመ.

**ንጥል** “ነጠለ” ስር ተመ.

**ንጥር** “ነጠረ[1]” ስር ተመ.

**ንጥሻ** “*ነጠሰ” ስር “እንጥስታ” ን ተመ.

**ንጥቂያ** “ነጠቀ” ስር ተመ.

**ንፁህ** “ነፃ̈” ስር ተመ.

**ንፅህና** ዝ.ከ.

**ንፅፅር** “*ነፀረ” ስር ተመ.

**ንፉግ** “ነፈገ” ስር ተመ.

**ንፊፊት** “ንፍፊት”ን ተመ.

**ንፋስ** “ነፈሰ” ስር “ነፋስ”ን ተመ.

**ንፋሽ** “ነፈሰ” ስር ተመ.

**ንፋው** “ነፋ[1]” ስር ተመ.

**ንፌት(ንፊት)** “ነፋ[2]” ስር ተመ.

**ንፍር ውሃ** “ነፈረ”ስር ተመ.

**ንፍርቅ** "ነፈረቀ" ስር "ነፈረቅ" ን ተመ.

**ንፍሮ** “ነፈረ” ስር ተመ.

**ንፍቅ [ቄስ፥ ዲያቆን]** ቅ (ኢ.ኦ.ተ.ቤ.) ረዳት፤ የቅዳሴ ስነስርአት በሚካሄድበት ጊዜ በዋናነት ተሰይሞ ስርአቱን ከሚያከናውነው ቄስ ወይም ዲያቆን በተጨማሪ በእለቱ ስርአት ላይ የሁለተኛነቱን ቦታ ይዞ የሚቀድስ ዲያቆን ወይም ቄስ።

**ንፍቅ እግር** ስ እንደጋማ ከብት ድፍን ሳይሆን እንደ ላም፥ በግ፥ ፍየል፥...ስንጥቃት ያለው ሰኮና።

**ንፍገት** “ነፈገ” ስር ተመ.

**ንፍጊያ** ዝ.ከ.

**ንፍጣም** “*ነፈጠ”ስር ተመ.

**ንፍጥ** ዝ.ከ.

**ንፍፊት(ንፊፊት)** ስ 1. ፍርንትት፤ የበጀድና የጭን መጋጠሚያ፥ ጉያ። 2. በእግር ወይም በእጅ ጣት ላይ በሚያጋጥም ህመም ምክንያት በፍርንትት ወይም በብብት ውስጥ የሚሰማ የህመም ስሜት።

**ኖ** የ"ነ" ፊደል ሳብእ ዘር።

**ኖረ** ግ 1. ቆየ፥ ተቀመጠ። *ዘጠና ዓመት በህይወት ኖረ።* 2. አለ፥ ተገኘ። *እቃው እቤት ከኖረ ዛሬውኑ ልትወስደው ትችላለህ።*

**መኖሪያ** ቅ 1. የአንድ ነገር ቋሚ አድራሻ፥ መቀመጫ፥መገኛ፥ ማደሪያ (ቤት፥ ሰፈር፥አገር)። 2. መተዳደሪያ፤ የአመት ልብስ፥ የእለት ጉርስ ለማግኘት የሚሰማሩበት የተግባር አይነት።

**የመኖሪያ ፈቃድ** ስ አንድ ሰው በባእድ አገር ሲኖር በዚያ አገር ውስጥ ለመኖር የሚያስችለውና በሚመለከተው የመንግስት አካል የሚሰጥ ፈቃድ።

**ነዋሪ (ኗሪ)** ቅ 1. የቆየ፥ ተቀማጭ። *ሰውየው እዚህ ቦታ ነዋሪ ነበሩ።* 2. ቋሚነት፥ ዘላቂነት ያለው።

**ኑሮ** ስ 1. አንድ ሰው በእድሜ ዘመኑ

የሚያሳልፈው ህይወት:: 2. ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች የሚገኙበት ሁኔታ:: 3.አኗኗር::

**ኑሮ ኑሮዬ አለ** ለቤቱ፥ ለቤተሰቡ፥ ለትዳሩ በማሰብ ጣረ፥ ጋረ፥ አጥብቆ ሰራ::

**አኖረ** ግ 1.አስቀመጠ:: 2. አቆየ፥ አከረመ:: 3. ረዳ፥ አስተዳደረ:: *የሚያኖረኝ ልጌቴ ነው::*

**አኗኗር** ስ የኑሮ ሁኔታ::

**ኖራ** ስ ከተቃጠለ በሃ ድንጋይ የሚገኝና ለግንባታ ስራ የሚያገለግል ነጭ ንጥረ ነገር::

**ኖር** "**ነወር**"ን ተመ.

**-ኖሮ** ተው.ግ. ትንቢታዊ ሃሳፊ ጊዜን የሚገልፅ ቃል:: *ብትመጣ ኖሮ በአሉን አብረን እናከብር ነበር::*

***ኖቀኖቀ**

**አኖቀኖቀ** ግ አጉተመተመ፥ አጉረመረመ::

**አኖቅናቂ** ቅ አጉረምራሚ፥ ነጭናጫ::

**ኖታ** ስ የተለያዩ የሙዚቃ ድምፀ ቃናዎችን ለመግለፅ የሚያስችል የሙዚቃ ዜማ ምልክት::

**ኖት** ስ ህጋዊነት ያለው የወረቀት ገንዘብ::

**ኖክናካ** "***ነክነከ**" ስር "**ነክናካ**" ን ተመ.

**ኗ** የ"**ነ**" ፊደል ፍንፅቅ ዘር::

**ኗሪ** "**ኖረ**" ስር "**ነዋሪ**"ን ተመ.